ከጥያቄዎች ቃርሚያ

ባለፉት በርካታ ዓመታት ወደ እኔ ለተላኩ ጥያቄዎች የሰጠኋቸው መልሶች።

ክፍል አንድ

ዘላለም መንግሥቱ

ከጥያቄዎች ቃርሚያ

ባለፉት በርካታ ዓመታት ወደ እኔ ለተላኩ ጥያቄዎች የሰጠኋቸው መልሶች።

ከዘላለም መንግሥቱ

ከጥያቄዎች ቃርሚያ

ባለፉት በርካታ ዓመታት ወደ እኔ ለተላኩ ጥያቄዎች የሰጠኋቸው መልሶች።

ዘላለም መንግሥቱ (© ፪ሺህ፲፬ ዓመተ ምሕረት)

ይህን መጽሐፍ ባለቤትነቱን ሳይወስዱና ለሽያጭ ሳያውሉ ጸሐፊውን በማሳወቅ ማባዛትም ማሰራጨትም ይፈቀዳል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. (1962) የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ካሳተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

የሽፋን ዲዛይን፥ ዘመን ግራፊክስ።

* * * * *

Gleanings from Queries

My Answers to the questions sent to me in the last several years.

Zelalem Mengistu (© 2021)

This work can be reproduced and disseminated by only notifying the author, without claiming ownership, and so long as it is not for profit.

All Scripture quotations are from the 1962 edition of the Amharic Bible published by the Bible Society of Ethiopia.

Cover: Zemen Graphics

መድረክ ዕዝራ
ለጌታ ቃል እና ለቃሉ ጌታ ታማኝ በመሆን
ezra forum
being true to the Word of God and the God of the Word

ከነጥያቄዎቻቸው ጌታን ታምነው ለሚከተሉና
የብዙዎችን ጥያቄ ለመመለስ ከልብ ለሚጥሩ ሁሉ
ማሰቢያ እንድትሆን የተበረከተች።

ማውጫ

መግቢያ (7)

1. ኃጢአት በምናችን ውስጥ ይኖራል? (8)
2. ሕፃናት መጠመቅ አለባቸውን? (9)
3. ማርያም ለዘላለም ድንግል ናትን? የኢየሱስ ወንድሞች የተባሉት እነማን ናቸው? (12)
4. ኤልሳዕ ያሳወራቸው ምናቸውን ነው? አሌፍ፥ ቤት፥ ጋሜል፥ ዳሌጥ ምን ናቸው? (15)
5. ስለ Joel Osteen የጻፍከው ስም ማጉደፍ አይደለም? (16)
6. ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት መጠበቅ አለብን? (17)
7. ኢየሱስ አምላክ ነው? እኔ አምላክ ነኝ ብሎ ነበር? (19)
8. ማርያም እመቤት ናት እንዴት አይባልም? (21)
9. የዘፍጥረት 6 የእግዚአብሔር ልጆች እነማን ናቸው? (24)
10. ኔፊሊም እነማን ናቸው? (29)
11. መላእክትን መጥራትና መላክ ይቻላል ወይ? (31)
12. ክርስቲያን የማይሳተፍበት የንግድ ዘርፍ አለ ወይ? (33)
13. መልከ ጼዴቅ ማን ነው? (35)
14. ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ነው? (39)
15. ሴቶች ሽማግሌ መሆን ይችላሉ? የሴቶች የመድረክ አገልግሎትስ እንዴት ይታያል? (45)
16. ሴት በመውለድ ትድናለች ሲባል ምን ማለት ነው? (49)
17. ተአምር ምንድነው? እዚህም እዚያም የሚሰሙ ተአምራት እውነት ናቸው? (50)
18. በአዲስ ኪዳን አሥራት መስጠት ግዴታ ነው? (51)
19. በቅዱሳን ስም ዝክር ማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? (54)
20. ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት ከማርያም አልወሰደም ወይ? (55)

21. ደም መስጠት ወይም መቀበል እና የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው? (57)

22. 'ሜጀር ዋን' አዲስ ማዕረግና ከፍተኛ መንፈሳዊ ሥልጣን ነው? (60)

23. ሙስሊሞች፥ 'ኢየሱስ እኔን አምልኩኝ ያለበትን ቦታ አሳዩን' ለሚሉት ጥያቄ ምን መልስ አለህ? (62)

24. በኤደን ገነት ውስጥ ዛፍ ተክሎ አትብሉ ለምን አላቸው? የዛፏ መኖር ለምን አስፈለገ? (64)

25. ሽማግሌዎች በማን ይመረጡ/ይሾሙ? ኤጲስ ቆጶስ ምንድር ነው? (67)

26. እግዚአብሔር በአዳምና ሔዋን ለምን ጨከነ? (69)

27. ብዙ ሚስት ማግባት የተከለከለ ነው? ለምን? (70)

28. የኤፌ. 4 አምስቱ ቢሮዎች ምንድር ናቸው? (73)

29. እግዚአብሔር በቀለኛ አምላክ ነው? (76)

30. እግዚአብሔር ተጸጸተ ሲል ምን ማለት ነው? ይጸጸታል? (77)

31. እግዚአብሔር ይፈትናል? (80)

32. የአልኮል መጠጥ መጠጣት ፈጽሞ የተከለከለ ነው? (82)

33. የሰው ሁለንተና ምንድር ነው? ሰው ነፍስ ያለው በሥጋ ውስጥ የሚያድር መንፈስ ነው? (91)

34. የእሳት ጥምቀት ምንድር ነው? (92)

35. ደኅንነት ይጠፋል ወይ? (94)

36. 'ወልድም ቢሆን አያውቅም' ብሎአልና ጌታ የሚመጣባትን ቀኒቱን አያውቅም ነበር? (99)

37. ግለ ወሲብ ኃጢአት ነውን? (101)

38. ክርስቲያን እራሱን ቢያጠፋ ምን ይሆናል? (103)

39. መንፈስ ቅዱስን መስደብ ምንና እንዴት ነው? (107)

40. እውነተኛ ትንቢት እና እውነተኛ ነቢያት ዛሬ አሉ? (109)

መግቢያ



አዲስ ክርስቲያን በነበርኩባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ብዙ ጥያቄዎችን እጠይቅ ነበር። አንዳንዶቹ ጥያቄዎች በጣም ቀላል ቢሆኑም በጊዜው ለኔ ቀላል አልነበሩም። ጌታን እንደተቀበልኩ ብዙም ሳልቆይ ነበር ወደ አሥመራ ዩኒቨርሲቲ የሄድሁት። ጊዜው የስደት ስለሆነ ክርስቲያናዊ መጻሕፍት ማግኘት ቀላል አይደለም። ብዙ ሳልቆይ በርካታ የነፍስ ቀለብ የሆኑኝ መጻሕፍት ካገኘሁባቸው የመጀመሪያው መጋቢዬ መጋቢ አብርሃም ዮሴፍ ቤተሰብ ጋር ቤተሰብ ሆንን። ከብዙ መጻሕፍት መካከል፥ 'ሁለተኛዋ አረንጓዴው ጓደኛዬ' ያልኳት አንዷ የቢሊ ግሬሃም My Answer የተሰኘች መጽሐፍ ነበረች።

ያኔ በጣም የተገለገልኩባቸው ሁለት አረንጓዴ መጽሐፎች ነበሩ። ሌላኛው ሦስተኛው አረንጓዴ ጓደኛዬ ያልኩት የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ሲሆን ይህቺ ሁለተኛዋ የጥያቄዎችና መልሶች መጽሐፍ ናት። አንደኛዋ አረንጓዴው ጓደኛዬ ጥንት የ3ኛ ክፍል የንባብ መጽሐፋችን ናት፤ ከፊደሏ በሌላ የማትለወጥ። ሁለተኛዋ አረንጓዴ ብዙ የልብና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄዎች መልሶች ከምችት መጽሐፍ ናት።

ብዙም አልቆየም፤ ሌሎች ከኔ ይልቅ አዲስ የሆኑ ክርስቲያኖች እና ክርስቲያን ያልሆኑ ስለ ክርስትና ሕይወት ማወቅ የሚፈልጉ ወጣቶች ጥያቄዎች ያቀርቡልኝ ነበር። የማውቀውን ያህል አካፍላቸው ነበር። አንዳንዴ ጥያቄያቸውን እንደ ቤት ሥራ ወስጄ የማማክራት ይህች አረንጓዴ መጽሐፍ ነበረች። ጥያቄዎች አልተቋረጡም። አንዳንዶቹ አጫጭር መልሶች ናቸው። አንዳንዶቹ መካከለኛ መጠን ያላቸው ናቸው። አንዱ ኋላ ራሱን የቻለ መጽሐፍ የተጻፈበት በ2012 የቅርብ ጓደኛዬ የቀረበለትና መልስ ፈልጎ የወረወረብኝ ጥያቄ ነው። ያ መጽሐፍ እንዝፈን ወይስ እንዘምር? የተሰኘው ነው።

ከተጠየቅኋቸው ጥያቄዎች ብዙዎቹ የግል ናቸውና በግል ነው የምመልስላቸው። አንዳንዶቹ ግን፥ በተለይም ከማኅበራዊ ሚድያ ስፋት በኋላ፥ በግል ብመልስላቸውም፥ ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄ የሚኖራቸው ስለሚኖሩ ያንን ጥያቄ ስማቸውን ሳልጠቅስ በማኅበራዊ ሚድያ እንደማስቀምጠው ነግሬ የምለጥፈው ነው። እዚህ የቀረቡት ብዙዎቹ በዚህ መልክ የተመለሱት ጥያቄዎች ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተመለሱት የጥያቄዎች መልሶች የየትኛዋንም ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋም የሚመለከት ሳይሆን እኔ በቃሉ ጥናት የተረዳሁት መረዳት ነው። ከቃሉ የመነጬና ከቃሉ ያልተጣረሰ እንዲሆን በተቻለኝ መጠን በጸሎትም በጥናትም ተደግፌ ነው መልሶቹን ለጠያቂዎች ያቀረብኩት። መልካም ንባብ።

ዘላለም መንግሥቱ (2021 / 2014)

1. ኃጢአት በምናችን ውስጥ ይኖራል?

'ህጢያት የሚኖረው በምናችን ውስጥ ነው? በስጋችን (body) ወይስ በልባችን? . . . የአመፅና የክፉ ሀሳብ ምንጭ ልባችን (አእምሮአችን) በመሆኑ መነሻውም ሆነ መገኛው እሱ ነው ብዬ አስባለሁ:: ስጋችን (body) ደግሞ መልካሙን ሀሳባችንን የምንፈፅምበት እንዲሁም ደግሞ ክፉ ሀሳባችንን የምንፈፅምበት ግኡዝ አካል ነው:: ያ ማለት ስጋችን ያለ አእምሮአችንን በራሱ ክፉም ሆነ መልካም ማድረግ አይችልም:: ስለዚህ በልባችን ያሰብነውን መፈፀሚያ በመሆኑ የህጢያት ተጠያቂ የሚሆነው ልባችን አንጂ ስጋችን አይደለም:: ስጋችን ያለ ነፍሳችን (አእምሮአችን) ንቁ ያልሆነ ምንም የማያውቅ በድን ነው:: ጌታ እንኳን ስጋችንን የሚቀጣው ከእኛ ጋር በተጣመረ ጊዜ እንጂ ነፍሳች ከስጋችን ከተለየች በኋላ በድኑን አይቀጣም ምክንያቱም በድን ስሜት የለውም:: ዘሌ ሀሳቤን አገኘኸው? (ሰ. ሳ.)

ስ. ሳ.፤ አሳብህን በደንብ አላገኘሁትምም አግኝቼዋለሁም። ጥያቄህ 'ህጢያት የሚኖረው በምናችን ውስጥ ነው? በስጋችን (body) ወይስ በልባችን?' ነው። ከገጽህም እንደተረዳሁት በቂ መረዳት አለህና ለማነጋገር የጠየቅከው መስሎኛል።

በሕይወት በሥጋ እስከኖርን ድረስ ኃጢአት በሁለንተናችን ሊኖር ይችላል። ቅድስናም እንዲሁ። 1ቆሮ. 6፥19-20 ወይስ *ሥጋችሁ* ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በ*ሥጋችሁ* እግዚአብሔርን አክብሩ። ይላል። ደግሞም 1ተሰ. 5፥23 የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ *መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም* ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ። ይላል። *ሥጋችን፥ መንፈሳችን፥ ነፍሳችን* ነቀፋም ቅድስናም ሊኖርባቸው ይችላል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ በተለይ አዲስ ኪዳን፥ *ሥጋ* ሲል ከአጥንትና ጅማት፥ ከደምና ሌሎች ብልቶቻችን ያለፈ ነገርን መናገሩ ነው። ለምሳሌ፥ ገላ. 5፥17 *ሥጋ* በመንፈስ ላይ መንፈስም በ*ሥጋ* ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። ሲል ወይም ኤፌ. 2፥3 በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የ*ሥጋችንን*ና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በ*ሥጋችን* ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ሲል ብልቶችን ሳይሆን *ሥጋዊ* አስተሳሰብን ነው።

ጥያቄህን ሰሞኑን እንደ አዲስ እየተናፈሰ ካለው አሮጌ ስሕተት ጋር ላቆራኘው። 'ሰው መንፈስ ነው' የሚሉ አንዳንዶች በተለይ ይህችን በጥያቄህ ያቀረብካትን ነጥብ የኃጢአት የፈቃድ ወረቀት አድርገው ሊጠቀሙባት ይሞክራሉ። *ሥጋችን* አይረክስም እና ኃጢአት ብናደርግም እውነተኛ ማንነታችንን (ማለትም፥ እንደ እነርሱ ትርጉም መንፈሳችንን) አይነካምና አንረክስም ይላሉ። ነገር ግን ይህንን ለማድረግ ሲጋብዙና ሲጋበዙ፥ *ሥጋቸው* ኃጢአት እንዲያደርግ ምንጫቸው የረከሰ መሆናቸውን ከስር፥ ከውስጥ፥ ከምንጭ የሆነ መበላሸታቸውን ይመሰክራል። ማር. 7፥20-23 ይህን ያሳያል፤ ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ መግደል፥

ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና፤ ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውን ያረክሰዋል።

አየህ? ከሰው ልብ የሚወጣ ብሎ ይጀምርና ሰውን ያረክሰዋል ብሎ ይጨርሳል። ስለዚህ ኃጢአት የሚኖረው በምናችን ነው ሲባል ምንጩንም መድረሻውንም መንካት ተገቢ ነው።

ስለዚህ ኃጢአት በምናችን ውስጥ ይኖራል? ቅድስናስ በምናችን ውስጥ ይኖራል? መልሱ ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የማያቋርጥ የመሰጠት ሂደቶች ናቸው። ኃጢአት በሁለንተናችን ሊሰለጥን ይችላል፤ መንፈስ ቅዱስም ሁለንተናችንን ሊገዛውና ሊቆጣጠረው ይችላል። ፈቃዱ በእጃችን አለ።

* * * * *

2. ሕፃናት መጠመቅ አለባቸውን?

> ሕፃናት መጠመቅ አለባቸውን? ሌላው ደግሞ በአሁኑ ሰዓት የህፃናት ጥምቀት እንደየ ቸርቹ ይለያያል። አንዳንዶች የህፃናት ጥምቀትን ሲደግፉ አንዳንዶቹ ደግሞ አይደግፉም። አንተስ በየትኛው ትስማማለህ?? ም. ኃ.።

ም. ኃ.፥ ይህ የመስማማት እና ያለመስማማት ወይም የመደገፍና ያለመደገፍ ጉዳይ አይደለም። ቃሉ የሚለው ይህንን ነው፤ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ማር. 16፥16። ጥምቀት ደግሞ እምነትን ይከተላል፤ ሐዋ. 2፥41። የጥምቀት ምልክትነቱ ከክርስቶስ ጋር መሞትንና መቀበርንና መነሣትን በይፋ መመስከር ነው፤ ሮሜ. 6፥3-5። በዮሐንስ ጥምቀትም ሰዎች ንስሐ እየገቡ፥ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ሲጠመቁ ነው የተጻፈው፤ ማቴ. 3፥6። የ40 እና የ80 ቀን ሕጻናት ይህንን ሊለማመዱ፥ ከቶም አይችሉም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሕጻናት በ40 እና 80 ቀን ሲጠመቁ ከቶም አልታየም። እኔ የምስማማው ሳይሆን ቃሉ ስለሚያስተምር የምቀበለው ቃሉን ሰምቶ አምኖ መጠመቅን ነው።

ቀጣይ፤ ይህ ጥያቄ በፌስቡክ ገጼ የተጠየቀ ነበርና በቀጣይ ጥያቄዎች እየቀረቡም ተመልሶ ነበር፤ አንድ ጣያቂ አጥብቆ በዚህ ጉዳይ ያቀረበው ሙግትና ምላሽ ይህ ነው፤

> ህጻናት ተጠምቀዋል የሚል በአዲስ ኪዳን መረጃ የለም ከማለትህ በፊት ህጻናት አለመጠመቃቸውን የሚያስረዳ መረጃ ይኖርህ ይሆን ጋሽ ዘላለም። ከአራት በላይ የቤቱ ሰዎች ተጠመቁ ከሚለው ቃል ተነስተ ቢያንስ ከአራቱ ቤት አንዱ ህጻን ይኖረዋል። ቤተሰብ ሲጠመቅ ህጻናት መቅረታቸውን በምክንያት አስረዳኝ። አንድ

ነገር ቀጥታ አልተጠቀሰም ማለት ጠንካራ ሙግት የለውም ማለት አይደለም። በዚህ ላይ የቤተክርስቲያንም ታሪክ ችላ የሚባልበት አንዳች ምክንያት የለም።

ከላይ የጻፍኩት ቃሉ በግልጽ የሚያስተምረውን ሲሆን አንተ የምትለው ግን ግምት ነው። "ቢያንስ ከአራቱ ቤት አንዱ ህጻን ይኖረዋል።" ለመኖሩ ከግምትህ ውጪ ምን አስረጅ አለህ? እኔ ሕጻናት አለመኖራቸውን ላስረዳህ እንደማልችል አንተም መኖራቸውን ልታስረዳኝ አትችልም። ሰዎች በተጠመቁባቸው ስፍራዎች ሁሉ ቃሉ መሰበኩና ቃሉን መቀበላቸው የሚያሳየን ነገር ቃል ከእምነት፥ እምነትም ከጥምቀት መቅደሙን ነው።

እንግዲህ ሂዱ አህዛብን ሁሉ አጥምቁ በሚለው ታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ህጻናት አለመጠቃለላቸውን ማሳየት የሚቻል አይመስለኝም። ሁሉ ማለት ሁሉ ነውና። ከዚህ በመነሳት የህጻናት ተለይቶ መጠቀሱ ምን አስፈለገ? የቤተሰብ ጥምቀት ህጻናትን ላለማጠቃለሉ ምን መረጃ አለ? በአምስቱም የቤተሰብ መጠመቅ በተገለጠባቸው ጥቅሶች ውስጥ በእያንዳንዳቸው ውስጥ ህጻናት አሉ ብል ልክ አልሆንም ይሆናል። ነገር ግን አንተም ደግሞ በአምስቱም ጥቅስ ህጻን የለም ብለህ ብትል ገማች መሆንህ አልቀረም። አሁን ጉዳዮ ጥሩ የተሻለው ግምት የቱ ነው የሚለው ነው። ቢያንስ ከአምስቱ በአንዱ ህጻን ይኖራል የሚለው የተሻለ ግምት ነው። መቼም በአምስቱም ጥቅስ ህጻን የለም ከሚለው ሻል ያለ ግምት ነው። ወንድ የበላይ በሆነበት ባህል የአባወራው ውሳኔ በልጆቹ ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ነውና። ስለዚህ ህጻናት አልተጠመቁም ለሚለው አሁንም ቢሆን መረጃ የለም።

ሕፃናት አሉም የሉምም ግምት መሆኑን ከላይ ተናግሬአለሁ። ግን በግልጽ የተጻፈው እያለ ወደ ግምት (ወደተሻለና ወዳልተሻለ ግምት) ለምን እንሄዳለን? ሕፃናት ተጠምቀዋል ብለህ እርግጠኛ የምትሆንባቸውን አምስቱንም ምንባቦች አቅርባቸው። እና ሕፃናት መኖራቸውን ለማረጋገጥ የቻልክባቸውን ነጥቦች አስፍርልን። ከግምት የላቀ እምነት ያሳደረብህን እውነት አያይዝልን።

አህዛብን ሁሉ የሚለው እኮ ህጻናትን ማጠቃለሉ ጥያቄ አይነሳበትም አልኩ እኮ። ኤክሰብሽን አለው እንዴ የጾታ እና የእድሜ ሁሉም ውስጥ? ወንድ አባ ወራ በቤተሰብ ውስጥ በሚወስንበት ባህል ለምን ህጻናት ለብቻቸው ተጠመቁ ብሎ መጥቀስ አስፈለገ?

ስለ ታላቁ ተልእኮ ያነሣኸውን ልመልስልህ። ማቴ. 28፥19-20 የሚለው ይህንን ነው፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ዋናው ግስ 'አድርጓቸው' የሚለው ነው። እያጠመቃችሁ፥ እያስተማራችሁ፥ አድርጓቸው። ምን አድርጓቸው? ደቀ መዛሙርት። ምን

እያደረጋችሁ? እያጠመቃችሁ፥ እያስተማራችሁ። ለ40 ቀን እና ለ80 ቀን ሕፃን ይህ እንዴት እንደሚደረግ አላውቅም።

ከላይ በመልሱ ውስጥ ሐዋ. 2፥41 ላይ ያለውን ቃል ብናስተውል ይህንን እውነት እናገኛለን። ያ ስፍራ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጥምቀት ነው። ያ ጊዜ የበዓል ጊዜ ነው፤ በዓለ ኀምሳ ነው። አይሁድ በኢየሩሳሌም ተገኝተው ከሚያከብሯቸው 3 ታላላቅ በዓላት አንዱ ነው። እዚያ በዓል ላይ ግምት ነው ካላልን በቀር ሕጻናት የሉም ማለት አንችልም። ቃሉ የሚለው ታዲያ፥ “ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤” ነው። ቃሉን የተቀበሉት ቃሉን የሰሙትና ከላይ በቁጥር 37፥ “ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት፡- ወንድሞች ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉአቸው።” የተባለላቸው ናቸው። የ40 እና የ80 ቀናት ሕፃናት ቃል ሰምተው መቀበል፥ ልባቸው መነካት፥ ውሳኔ መወሰን እንደማይችሉ ግልጽ ነው።

ይህ አሠራር በቀጣዮቹ ጥምቀቶችም የተከተለ ነው። ቤተ ሰብ ከተጠመቀ ከቤተ ሰቡ ውስጥ ቃሉን ሰምተው ኃጢአተኝነታቸው ገብቷቸው፥ የአዳኙ አስፈልጎት ገብቷቸው፥ ኃጢአታቸውን ተናዝዘው የተጠመቁ ለመሆናቸው የቀደሙቱ ትልሞች ያሳዩናል። ስለ ቤተሰብ ጥምቀት ግምትነት የሌለው ማስረዳት እንድታስረዳኝ እየጠበቅሁ ቃልና እምነት ጥምቀትን እንደሚቀድም ጥቂት ጥቅሶች ልጨምር።

ሐዋ. 8፥12 ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ፥ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ።

ሐዋ. 9፥18 (ጳውሎስ) ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ ከዓይኑ ወደቀ፥ ያን ጊዜም ደግሞ አየ፤ ተነሥቶም ተጠመቀ።

ሐዋ. 18፥8 የምኵራብ አለቃ ቀርስጶስም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ፥ ከቆሮንቶስ ሰዎችም ብዙ በሰሙ ጊዜ አምነው ተጠመቁ።

ሐዋ. 19፥5 ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ፤

ጥምቀት እምነትን ይከተላል ያልኩት ይህንን ነው። ቀጥሎ ከቆላ. 2፥11-12 በብሉይ ኪዳን ግዝረት የቃል ኪዳኑ መታወቂያ ምልክት እንደሆነና በአዲስ ኪዳን ይህ ግርዘት በጥምቀት መለወጡን በማመልከት ጠያቂው መከራከሪያ አቅርቧል።

ቆላ. 2፥11-12 *የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ፥ በክርስቶስ መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ። በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥ በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።* ይላል። ማናቸውም ክፍለ ምንባብ ከዐውድ ተገንጥሎ መታየት እንደሌለበት ይህም እንደዚያ መደረግ የለበትም። ይህ ክፍል ስለ ሕጻናት ጥምቀት ከቶም አይናገርም፤ ጥምቀትም ግዝረትን እንደተካ ምንም ፍንጭም አይሰጥም።

ይህ የቆላስይስ ክፍለ ምንባብ ስለ ሕጻናት ጥምቀት የሚናገር ቢሆን በግልጽ ስለ ጉዳዩ ከመናገር ባሻገር፥ ‘ሕጻን’ ወይም ‘ሕጻናት’ የሚለው ቃል በብዛት በውስጡ ይገኝ

ነበር። ነገር ግን፥ 'ሕጻን' ወይም 'ሕጻናት' የሚለው ቃል ጭራሹኑም በመልእክቱ ውስጥ አይገኝም። ስለዚህ ግርዘትን ጥምቀት ተካው ማለት ወደ ቃሉ ውስጥ እንዲገባ የተደረገ የሰው ትምህርት ነው። ከሆነ ሴቶችም በብሉይ ኪዳን ይገረዙ ነበር ማለት ነው? ወይም ሴቶች መጠመቅ የለባቸውም ማለት ነው? ሕጻናት ይጠመቁ የሚለው አመክንዮ የተሳሳተ ነው።

* * * * *

3. ማርያም ለዘላለም ድንግል ናትን?

> የኢየሱስ ወንድሞች የተባሉት በእውን ወንድሞቹ ካልሆኑ እነማን ናቸው? ስለ ማርያም ዘላለማዊ ድንጋሌ ከሚጠቀሱት ሁለት ክፍሎች አንዱ መኃ. 4፥12 ነው። ከሕዝቅኤል የሚጠቀሰው ደካማ ነው። ይህንን ልታብራራልኝ ትችላለህ? አመሰግናለሁ። (Y. A.)

(Y. A.) ጥያቄዎቹን ከኋቱም ክፍለ ምንባቦች አያስተያየሁ ለመመለስ እሞክራለሁ። የኢየሱስ ወንድሞች የተባሉት በእውን ወንድሞቹ ካልሆኑ እነማን ናቸው? ማርያም ድንግል ሆና ለዘላለም እንደምትኖር የሚያስተምሩ ሰዎችን ብንጠይቅ ደቀ መዛሙርቱና ሐዋርያቱ ወይም ዘመዶቹና ሌላም እንደሆኑ ይነግሩናል። በካቶሊክ ትውፊት እነዚህ ወንድሞች የአጎትና አክስት ልጆች ሲሆኑ በኦርቶዶክስ ደግሞ የዮሴፍ የቀድሞ ልጆች ናቸው። ለእንዲህ ያለው የቅርብ ዝምድና (ማለትም፥ የአጎትና አክስት ልጅ ወይም የእኅትና ወንድም ልጅ በአዲስ ኪዳን ἀνεψιός (አኔፕሲዮስ) የሚል ቃል እያለ ἀδελφός (አዴልፎስ) እና ἀδελφή (አዴልፌ) የሚል ቃል መጠቀማቸው የማንነት ገላጭ ነው።

እርግጥም መጽሐፍ ቅዱስ ወንድሞች የሚለውን ቃል በሰፊው የሥጋ ላልሆኑ ሥጋዊ ዝምድናዎች እና መንፈሳዊ ወንድሞችም ይገለገልበታል። ለምሳሌ፥ ዘጸ. 2፥11፤ አሞ. 1፥9፤ ሐዋ. 1፥15፤ 3፥22፤ 17፥14፤ 18፥18፤ 1ቆሮ. 16፥12። እነዚህ የሥጋ ወንድሞች አይደሉም ግን ወንድሞች ተሰኝተዋል። በወንጌላት ውስጥ የምናገኘው የኢየሱስ ወንድሞች አገላለጥ ከእነዚህ የተለዩ መሆናቸውን በግልጽ ያሳያል። ግን የኛዎቹና የዘመናችን ሰዎች ዘመዶቹ እንደሆኑ የሚነግሩንን እነዚያ ያኔና እዚያ የነበሩት፥ የሚያውቋቸው ሰዎች ዘመዶቹ መሆናቸው ጠፋቸውና ወንድሞቹና እኅቶቹ ብለው በስም እየጠቀሱ፥ ወላጆቻቸውንም በስም እየጠቀሱ ለምን ተናገሩ? ለምን?

ማርያም ማርያም ራሷ የምትናገረው ሌላው ስለ እርሷ ከሚናገረው ይበልጥ ተአማኒ መሆኑ እሙን ነው። እርሷ ስለ ራሷ ከተናገረችው በላይ ሰዎች ያልተጻፈ እየጨመሩ አመለኮቷት። እነዚህም ወንድሞቼ ስለተባሉቱ እኛ የመሰለንን እና የምንገምተውን ከምንናገር ያዩአቸውና የሰሙአቸው፥ አብረዋቸው የኖሩና በስም ያወቁአቸው የሚሉትን መቀበል አይቀልለንም? ማን ያርዳ? የቀበረ፤ ማን ይናገር? የነበረ ማለት እኮ ይህ ነው። በግምት ዮሴፍ ቀድሞ ሚስት ሳትኖረው አትቀርም፤ ወይም እንዳለችው አድርገን እንጻፍ ተብሎ መቼ እንደተፈጠረ እንኳ ማስረጃ የማይቀርብለትን ትውፊት ትምህርት አድርጎ ማስተማር ስሕተት ነው። በተለይም ትምህርቱ ከደኅንነት ጋር የሚቃረን ሲሆን የሐሰት ትምህርት ነው።

ስለዘላለማዊ ድንግልናዋ (ዘላለማዊ ድንግልና ሲሉ ከመውለዷ በፊት ስትወልድ እና ከወለደች በኋላ ነው) በጣሙን ተደጋግመው ከሚጠቀሱት ጥቅሶች ሁለቱን እንመልከት።

የመጀመሪያው መኃ. 4፥12 ያለው እኅቴ ሙሽራ የተቈለፈ ገነት፥ የተዘጋ ምንጭ የታተመም ፈሳሽ ናት የሚል ቃል ነው። ጥቅስ ከዕውዱ ተገንጥሎ መውጣት የለበትም። መኃልየ መኃልይ ሰሎሞን ከጻፋቸው ከሺህ የሚበልጡ መዝሙሮች አንዱ ነው። የፍቅርን ምንነት ለመግለጥ አካላዊ ውበትንና ወሲባዊ ቋንቋን በሰፊው ስለሚጠቀም እንደ ቅዱስ መጽሐፍ እንኳ መወሰዱ ከብሉይ ኪዳን ቀኖና ጀምሮ የሚከብዳቸው በታሪክ ውስጥ አልጠፉም። ክብደቱን ለማቅለልም መጽሐፉን መንፈሳዊ ብቻ በማድረግ የእግዚአብሔርና የእስራኤል ፍቅር ወይም የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ፍቅር መገለጫ አድርገው የሚያስተምሩ ብዙ ናቸው። እነሆ፥ አሁን ደግሞ ማርያም ሆና ቀርባለች።

መዝሙሩ ግን የሰሎሞንና የሱላማጢስ ፍቅር የተገለጠበት ቅኔ ነው እንጂ ስለማርያም ከቶም የሚናገር አለመሆኑን እንይ። በመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ደንብ አንድ ምንባብ ግልጽ ከሆነና ስሜት የሚሰጥ ከሆነ ሌላ ስሜት ልንፈልግለት አይገባም። ምሳሌ ካልሆነም ምሳሌ አድርገንና ግልጹን አወሳስበን ምስጢር አድርገን የምስጢሩ መፍትሔ ልንፈልግለት የተገባ አይደለም። ምክንያቱም፥ ቀድሞውኑም ምስጢር አልነበረማ!

በሰሎሞን ዘመን ከተጻፈ ከክርስቶስ ልደትና ከወንጌሉ ታሪክ 900 ዓመታት በላይ ቀድሞ የተጻፈ ነው። መኃልዩ የሆነና እየሆነ ያለ ነገርን እየገለጠ እንጂ የተጻፈው እንደ ትንቢት አለመሆኑ ግልጽ ነው። ይህች ገነት ተቆልፋ፥ ተዘግታ፥ ታትማ የቀረች አለመሆኗን ደግሞ መኃልዩን ስናነብብ እንረዳለን። ራሷም ወዳጇን፥ በዚያው ምዕራፍ ቁጥር 16፥ የሰሜን ነፋስ ሆይ፥ ተነሥ፥ የደቡብም ነፋስ ና በገነቴ ላይ ንፈስ፥ ሽቱውም ይፍሰስ ውዴ ወደ ገነቱ ይግባ፥ መልካሙንም ፍሬ ይብላ ብላ የለም? በ6፥2 ደግሞ፥ ውዴ በገነቱ መንጋውን ያሰማራ ዘንድ አበባውንም ይሰበስብ ዘንድ ወደ ሽቱ መደብ

ወደ ገነቱ ወረደ የሚል እናነብባለን። ወዳጇ ወደ ገነቱ ገብቷል። የተቆለፈ ገነት ለሁሉ የተከፈቱ ያለመሆን ምሳሌ እንጂ ለአንዱ የታሸጉ መሆን አይደለም። ይህች ሴት በውዷ ፍቅር ስትነደፍ ትታያለች፤ ወዳጇን ቀምሳዋለችና ጣፋጭ እንደሆነ ትመሰክራለች። ይህ ወዳጇ ወዳጇ ብቻ ሳይሆን ባልንጀራዋም ነው (5፥16)። ማርያም ከሆነች ይህ ወዳጅና ባልንጀራ ማን ነው? እግዚአብሔር ሊሰኝ ይሆን? ይህ ማርያምን ያለቅጥ ከፍ ማድረግ ነው ወይስ እግዚአብሔርን ዝቅ ማድረግ ነው?

ይህች ወዳጇ 'ውዴ' እያለ የሚጠራት ሴት ማርያም ከሆነች እርሷ 'ወዳጄ' እያለች የምትጠራው ሰው ማን ሊሆን ነው? 'ከልጅሽ ከወዳጅሽ ይቅርታን ለምኚልን' እንደሚሉት ልጇ ነው እንዳይባል ይህ ክፍል ስለ ልጅ ሳይሆን ስለ ተቃራኒ ጾታ ወዳጅ ነው የሚናገረው። ሌላ ማንም እንዳይሆን ሁለቱ ገጸ ባሕርያት በግልጽ ተጽፈዋል። ለሰሎሞንም ሌላ ትርጉም እንፈልግለት ብንል ደግሞ የማንወጣው የተሳሳተ አፈታት ውስጥ እንገባለን።

ሌላው ጥቅስ ማርያም የሕዝቅኤል የተዘጋው በር መሆኗ ነው። ቃሉ በሕዝ. 44፥2 የተጻፈው ነው። እንዲህ ይላል፥ እግዚአብሔርም፡- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል። ይህ ሕዝቅኤል በራእዩ ያየው ቤተ መቅደስ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ጥቅስ ነቅሎ ወይም ፈንቅሎ በማውጣት ግዙፍ አስተምህሮ መገንባት አይቻልም። በውዳሴ ማርያም ጸሎተ ረቡዕም ቁ. 7-8 ይኸው እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፤ "ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለ እርሷ መሰከረ ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ የተዘጋች ደጀ ምሥራቅ አየሁ አለ። ከኃያላን ጌታ በቀር ወደ እርሷ ገብቶ የወጣ የለም። ቅድስት ሆይ ለምኚልን። ኖኅትም ደጅም መድኃኒታችንን የወለደች ድንግል ናት፤ እርሱን ከወለደች በኋላ እንደቀድሞው በድንግልና ኖራለችና።"[1] ለማግነን ነው 'ድንቅ በሆነ ታላቅ ቁልፍ' የተሰኘው እንጂ በሕዝቅኤል ውስጥ ይህ ሐረግ የለም።

ወደ ጥቅሱ ስንመለስ፥ ይህ በር እውን የማርያም ድንግልና ነውን? ይህም ድምዳሜ ከዐውዱ የወጣ ጥቅስ መሆኑን ከዚያው ምዕራፍ ሳንወጣ እንረዳለን። ለምሳሌ ቀጥሎ ባለው ጥቅስ፥ አለቃው ግን እርሱ በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላ ዘንድ ይቀመጥበታል በበሩ ደጀ ሰላም መንገድ ይገባል በዚያም መንገድ ይወጣል ተብሎአል። አለቃው ማን ነው? ለምንስ ይቀመጥበታል? ደግሞ የሰሜኑ በር አለ ወደ መቅደሱም የሚገቡ አሉ። እውን ይህ የምሥራቁ በር የማርያም ድንግልና ከሆነ የሰሜኑ በርስ? ጠቅላላው መቅደስ ደግሞስ? የምሥራቁ በር አፈ ማኅጸኗ ነው ከተባለ

---

[1] ውዳሴ ማርያም የዕለተ ረቡዕ ንባብ፥ ቁጥር 7-8።

መቅደሱ ማኅጸኗ መሆን አለበት። ማኅጸን አንድ ብቻ በር እንዳለው የታወቀ ሲሆን ሌሎች እንዴትና በምን በኩል ገቡ?

ይህ ምላሽ በከፊል ከዕዝራ #16 የተወሰደ ነው። ሙሉውን መጣጥፍ ለማግኘት http://books.good-amharic-books.com/ezra15.pdf ይጫኑ።

* * * * *

4. ኤልሳዕ ያሳወራቸው ምናቸውን ነው? አሌፍ፥ ቤት፥ ጋሜል፥ ዳሌጥ ምን ናቸው?

የጌታ ፀጋና ሰላም ይትረፍረፍልህ ወንድሜ ዘሌ! ዛሬም ጥያቄ አለኝ?? 2ነገ6:14-23 ባለው ምንባብ ውስጥ የሶርያን ወታደሮች"እውር አደረጋቸው" ብሎ ደግሞ ቁ19 ላይ "የምትሹትን ሰው አሳያችሁ ዘንድ ተከተሉኝ"እንዳላቸው እናያለን ታዲያ እነዚህ ሰዎች አይነ ስጋቸው ነው ወይስ ማስተዋላቸውን(አይነ ልቦናቸውን) ዕውር ያደረገው?? ተከተሉትም ስለሚል ማለት ነው?? መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ የምናገኛቸው ለምሳሌ ሰቆቃው ኤርሚያስ ላይ ፡ አሌፍ፡ ቤት፡ ጋሜል፡ዳሌጥ .....ምንድናቸው ዘሌ??ተባረክልኝ! (ም. ዓ.)

ሰላም (ም. ዓ.)፤
1. ኤልሳዕ ያሳወራቸው ዕውርነት የዓይን ዕውርነት ነው። በብሉይ ኪዳን ቋንቋ ዕውር ለሚለው ቃል የተለያዩ ቃላት ቢኖሩም ይህ እዚህ የተጠቀሰው ቃል በሌላ አንድ ቦታ ብቻ ተጠቅሶአል፤ በዘፍ. 19፥11 በቤቱ ደጃፍ የነበሩትንም ሰዎች ከታናሻቸው ጀምሮ እስከ ታላቃቸው ድረስ አሳወሩአቸው፤ ደጃፉንም ለማግኘት ሲፈልጉ ደከሙ። ተብሎ ተጠቅሶአል። እዚያ የሎጥን ቤት የከበቡት ሰዶማውያን ዓይኖች ታውረው እንደነበረ የእነዚህም ታውሮ ነበር ማለት ነው። ቃሉም አገባቡም ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ የሥጋ ዓይን መታወር ነው። መከተልን በተመለከተ ለመከተል እኮ ማየት የለብህም። በመሪ እንደተከተሉ ይመስለኛል።

2. አሌፍ፥ ቤት፥ ጋሜል፥ ዳሌጥ አበገደ (አቡጊዳ) እንደ ማለት ነው። የዕብራይስጥ ፊደላት ናቸው። እነዚህ ፊደላት በተጠቀሱባቸው ምንባቦች (የግጥም ጽሑፎች ናቸው) የመጀመሪያው ቃል የሚጀምረው በዚያ ፊደል ነው። በጥቅሱ አንድ ወይ ሁለት ወይ ከዚያ በላይም መስመሮች ወይም ስንኞች ቢኖሩ የስንኞቹ የመጀመሪያ ፊደል ያ ፊደል ነው። ለዚህ ነው እነዚህ ፊደላት የተጠቀሱባቸው ምእራፎች ቁጥር ወይ 22 ወይ የ22 ብዜቶች የሆኑት። ለምሳሌ፥ መዝ. 119 176 ነው እያንዳንዱ ፊደል 8 ጥቅሶች (176/22) ነው። ሰቆ. 1 እና 2 እንዲሁም 4 እና 5 እያንዳንዳቸው 22 ጥቅሶች ሲኖሯቸው፥ ሰቆ 3 66 ይዟል።

ለምሳሌ፥ መዝ. 119፥ ፤-8 (አሌፍ) እና ፱-16 (ቤት) ምን እንደሚመስሉ ተመልከት። ዕብራይስጥ ከቀኝ ወደ ግራ ስለሚነበብ በስተቀኝ የመጀመሪያዎቹን ፊደላት አንድ መሆን ተመልከት።

መዝ. 119፥፤-8 አሌፍ

1 אַ֭שְׁרֵי תְמִֽימֵי־דָ֑רֶךְ הַֽ֝הֹלְכִ֗ים בְּתֹ֣ורַת יְהוָֽה׃
2 אַֽשְׁרֵ֗י נֹצְרֵ֣י עֵ֭דֹתָיו בְּכָל־לֵ֥ב יִדְרְשֽׁוּהוּ׃
3 אַ֭ף לֹא־פָעֲל֣וּ עַוְלָ֑ה בִּדְרָכָ֥יו הָלָֽכוּ׃
4 אַ֭תָּה צִוִּ֥יתָה פִקֻּדֶ֗יךָ לִשְׁמֹ֥ר מְאֹֽד׃
5 אַ֭חֲלַי יִכֹּ֣נוּ דְרָכָ֑י לִשְׁמֹ֥ר חֻקֶּֽיךָ׃
6 אָ֥ז לֹא־אֵבֹ֑ושׁ בְּ֝הַבִּיטִ֗י אֶל־כָּל־מִצְוֹתֶֽיךָ׃
7 א֭וֹדְךָ בְּיֹ֣שֶׁר לֵבָ֑ב בְּ֝לָמְדִ֗י מִשְׁפְּטֵ֥י צִדְקֶֽךָ׃
8 אֶת־חֻקֶּ֥יךָ אֶשְׁמֹ֑ר אַל־תַּעַזְבֵ֥נִי עַד־מְאֹֽד׃

መዝ. 119፥፱-16 ቤት

9 בַּמֶּ֣ה יְזַכֶּה־נַּ֭עַר אֶת־אָרְח֑וֹ לִ֝שְׁמֹ֗ר כִּדְבָרֶֽךָ׃
10 בְּכָל־לִבִּ֥י דְרַשְׁתִּ֑יךָ אַֽל־תַּ֝שְׁגֵּ֗נִי מִמִּצְוֹתֶֽיךָ׃
11 בְּ֭לִבִּי צָפַ֣נְתִּי אִמְרָתֶ֑ךָ לְ֝מַ֗עַן לֹ֣א אֶֽחֱטָא־לָֽךְ׃
12 בָּר֥וּךְ אַתָּ֥ה יְהוָ֗ה לַמְּדֵ֥נִי חֻקֶּֽיךָ׃
13 בִּשְׂפָתַ֥י סִפַּ֑רְתִּי כֹּ֝֗ל מִשְׁפְּטֵי־פִֽיךָ׃
14 בְּדֶ֖רֶךְ עֵדְוֺתֶ֥יךָ שַׂ֗שְׂתִּי כְּעַ֣ל כָּל־הֽוֹן׃
15 בְּפִקֻּדֶ֥יךָ אָשִׂ֑יחָה וְ֝אַבִּ֗יטָה אֹרְחֹתֶֽיךָ׃
16 בְּחֻקֹּתֶ֥יךָ אֶֽשְׁתַּעֲשָׁ֑ע לֹ֖א אֶשְׁכַּ֣ח דְּבָרֶֽךָ׃

* * * * *

5. ስለ Joel Osteen የጻፍከው ስም ማጉደፍ አይደለም?

በአንድ ስፍራ ስትጠቅስ ጌታን በመመስከር ፈንታ በተደጋጋሚ ፥ 'አላውቅም' ማለቱን ጽፈሃል። ይህ ስም ማጉደፍ አይደለም? Y. T.

ሰላም Y. T. ስም ማጉደፍ ማለት ምን መሆኑን እንዴት እንደተረዳሽ ባውቅ መልካም ነበር። በኔ መረዳት ያላለውን ነገር 'ብሏል' ብዬ ቢሆን እውነትም ስም ማጉደፍ ነው። አንድ ሰው ያለውን ነገር ብሏል ማለት ስም ማጉደፍ አይደለም። በሐሰት መመስከር ተግባሬ አይደለም። የጻፍኩት የሰማሁትንና ያየሁትን ነበር። መጣጥፉን ስጽፍ ሳለሁ

በቀጥታ እየሰማሁት ሳይሆን ያየሁትንና የሰማሁትን በማስታወስ ነበረና ስሕተት እንዳልጻፍኩ ባውቅም ምናልባት የተጋነነ ነገር ጽፌ ከሆነ ብዬ ይህንን መልስ ስጽፍልሽ እንደገና ቃለ መጠይቁን ተመልክቼው ነበር፤ አልተሳሳትኩም። እንዲያውም 'አላውቅም' የሚለውን ቃል የደጋገመው ከጻፍኩት በበለጠ ቁጥር ነው። ምናልባት ማየቱና መስማቱ ከኔ ይልቅ መልስ ሊሆን እንደሚችል አምናለሁና በስፍራው ተመልከቺው። የYouTube ቁራጩን ለማግኘት ይህን የዩቲዩብ ቁራጭ ተመልከቺ፤ http://www.youtube.com/watch?v=pKF_QgNezBY።

ዋናው ነጥብ አስረግጠን ስለምናውቀው ነገር እንኳን እንደ አገልጋይ፥ እንደ አንድ አማኝም ግልጥ በሆነው ነገር ላይ መንተባተብ የለብንም። በመጠይቁ ላይ ጠያቂው ያቀረበለት ግልጽ ጥያቄ ነው፤ አይሁድ፥ እስላም አይድኑም ነው የምትለው ክርስቶስ ከሌላቸው? ነው ጥያቄው። ቃሉ የሚመልሰው ደግሞ፥ *ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም። የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ* ነው፤ 1ዮሐ. 5፥12። ኢየሱስ እኔ መንገዱ ነኝ በኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ካለ (ዮሐ. 14፥6) ለምን ያንን አንደግምም? እኛ ምስክሮች ነን እንጂ ማሻሻያ አንቀጽ ጸሐፊዎች አይደለንም።

1ጴጥ. 3፥15 በግልጽ፥ *ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን* ይለናል። ይህንን ጌታ በልባችን መቀደስ እና በአፋችንም መመስከር አለብን። የዋህነት እርግጠኛ አለመሆን አይደለም። ፍርሃትም ስደትን ወይም መነቀፍን ፈርቶ የሚያውቁትን መደበቅ አይደለም። ምስክር ደግሞ ያየውን፥ የሰማውን፥ የዳሰሰውን ይናገራል። ይህ ሰው በዚያ መድረክ ላይ እውነትን አለመናገሩ ወይ እውነቱን ስላላወቀ ነው ወይም እውነትን መንገር ስላልፈለገ ወይም ስለፈራ ነው። ይህ ደግሞ መልካም ምሳሌነት የለውም። ያ አጋጣሚ ደጋግመው የሚያገኙት አይደለም። ዘመኑን መዋጀት ጥበብ ነው።

* * * * *

6. ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት መጠበቅ አለብን?

እኛ ክርስቲያኖች የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት መጠበቅና መታዘዝ ይኖርብናል ወይ? ኤ. ወ/ማ

ሰላም Y. T. በቅድሚያ የሁለቱን ኪዳናት ልዩነት ጠንቅቆ መረዳት ተገቢ ነው። ኪዳን ማለት ቃል ኪዳን ወይም የፈቃድ ስምምነት ነው። ብሉይ ኪዳን ወይም አሮጌው ኪዳን እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ኪዳን ነው። ብሉይ ኪዳን በምንለው ዘመንና መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ከተለያዩ ሰዎች ጋር የገባው ኪዳናት አሉ፤

ለምሳሌ፥ ከኖኅ፥ ከአብርሃም፥ ከዳዊት ወዘተ። ዋናውና ትልቁ ቃል ኪዳን እስራኤልን በሙሉ ያቀፈው ከሕዝቡ ጋር በሲና የገባው ኪዳን ነው፤ ዘጸ. 34፥10 (10-17)፤ ዘዳ. 5፥2፤ ዘጸ. 34፥28፤ ዘሌ. 26፥44። ይህ ከእስራኤል ጋር የተገባው ኪዳን ትልቁና ሕዝቡን በሙሉ ያካተተው ኪዳን ነው። የዚህ ኪዳን ምልክቶቹ፥ መገለጫዎቹ ወይም መታሰቢያዎቹም፥ ጽላት፤ ዘዳ. 4፥13፤ ሰንበት፥ ዘጸ. 31፥16፤ መስዋዕቶች፥ ዘሌ. 2፥13፤ 24፥8፤ ታቦት፥ ዘኁ. 14፥44፤ ክህነት፥ ዘኁ. 25፥12-13፤ መሐላ፥ ዘዳ. ዘዳ. 4፥23፤ 29፥12-13፤ እርሱን ብቻ ማምለክ፥ ኢያ. 23፥16፤ ወዘተ፥ ናቸው። በተጨማሪ 2ነገ. 17፥35-38፤ ነህ. 1፥5፤ ሐዋ. 3፥25፤ ሮሜ 7፥8፤ 9፥4 ተመልከቱ።

ይህ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባው ኪዳን በብሉይ ኪዳን ዘመን በሙሉና ክርስቶስ በመስቀል ላይ እስከሞተበት ድረስም የጸና ኪዳን ነው። ይህ ኪዳን 'ብሉይ ኪዳን' ተሰኝቶ ከወንጌላቱ በፊት ያሉት 39 መጻሕፍት የተካተቱበት፥ ከዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ሚልክያስ (በአይሁድ ቅደም ተከተል ደግሞ ከዘፍጥረት እስከ 2ኛ ዜና) ያሉት መጽሐፎች በሙሉ የተጠሩበት መጠሪያ ነው። ይህ 'ብሉይ ኪዳን' እና 'ፊተኛው ኪዳን' ተብሎአል፤ 2ቆሮ፣ 3፥14፤ ዕብ. 8፥6-10፤ 9፥15-18። ይህ ኪዳን ከአንድ ወገን ወይም ሕዝብ ብቻ ጋር የተገባ ነው። የእስራኤል ልጆች ግን ይህን ኪዳን ደጋግመው አፍርሰው ነበር፤ 1ነገ. 19፥10-14፤ 2ነገ. 17፥15፤ መዝ. 78፥10፤ ኢሳ. 24፥5፤ ኤር. 11፥10። ገና በብሉይ ዘመን የአዲስ ኪዳን ተስፋ ተሰጥቶ ነበር፤ ኤር. 31፥31-33፤ ሮሜ 11፥27፤ ዕብ. 8፥6-10፤ 10፥15-16። ይህ ማለት ያ የመጀመሪያው ኪዳን ሊመጣ ያለውን ሌላ ቋሚ፥ ዘላቂ አዲስ ኪዳን አመልካች ሆኖአል ማለት ነው።

አዲሱ ኪዳን ደግሞ በክርስቶስ ደም የተመሰረተው ኪዳን ነው፤ ማቴ. 26፥28፤ ማር. 14፥24፤ ሉቃ. 22፥20፤ 1ቆሮ. 11፥25። ይህ ኪዳን 'አዲስ ኪዳን' እና 'የተሻለው ኪዳን' ተብሎአል፤ 2ቆሮ. 3፥6፤ ዕብ. 7፥22፤ 12፥24። አሮጌው ኪዳን በተለይ ለእስራኤል ብቻ የተሰጠው ሲሆን አዲሱ ኪዳን ሰዎችን ሁሉ የሚያድነው ጸጋ የተገለጠበትና ወደዚህ ኪዳን ወደው የሚገቡትን ሁሉ የሚያቅፍ ኪዳን ነው። ይህ አዲስ ኪዳንም የታተመው ወይም የጸናው እንደ አሮጌው ኪዳን በደም ሲሆን ደሙም በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ነው። የወንጌሉ ታሪክ የሚገኘው አዲስ ኪዳን በሚባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይሁን እንጂ አዲሱ ኪዳን እስከ መስቀሉ ድረስ ገና አልቆመም። ኪዳኑ ከቆመ በኋላ ግን በመስቀሉ ላይ የሆነውን ለተቀበሉ ሁሉ የጸና ነው።

ከመስቀሉ ወዲህ መዳን ሕግጋትን በመጠበቅ ሳይሆን ሕግን ፈጽሞ የጠበቀውንና የፈጸመውን፥ ንጹህ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ 'እነሆ፥ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ' የተባለውን ክርስቶስን በማመን ነው። እንግዲህ፥ ብሉይ ኪዳንን መጠበቅና መታዘዝ ስለሚለው ጉዳይ ስንመጣ የብሉይ ኪዳን ሕግ የተሰጠው ለክርስቲያኖች ሳይሆን ለእስራኤል ነገድ ነው። ሕግጋቱ ማኅበራዊና መንግሥታዊ፥ የክህነትንና የመንጻትን፥ እንዲሁም ግብረ ገባዊ ትእዛዛትን ያጠቃልላሉ። ግብረ ገባዊ ከሆኑት ትእዛዛት ጥቂቱ ድንበርንና ዘመናትን ሁሉ የሚያካልሉ ናቸው። ለምሳሌ፥ አለመግደል፥ አለማመንዘር፥ ወዘተ። የተቀሩቱ ግን የመስዋዕት፥ የክህነት፥ የአበላል፥ የአለባበስ፥ የበዓላት፥ ወዘተ ሕግጋት ሆነው ያንን ሕዝብ ብቻ የሚመለከቱ ናቸውና

ክርስቲያኖች የሚጠብቋቸው አይደሉም። አይሁድም ራሳቸው እንኳ በአሁኑ ዘመን ሊጠብቋቸው አይችሉአቸውም፤ ምክንያቱም፥ አብዛኞቹ ሕግጋት የሚፈጸሙበት የመቅደስና የክህነት ሥርዓቶች የሉም። መቅደሱ ራሱም ስለሌለ ተፈጻሚ መሆን የሚችሉበት ማዕከል የለም።

አሠርቱ ትእዛዛት የብሉይ ኪዳን ሕግጋት ቁንጮና ድምድማት ናቸው ማለት ይቻላል። ልዩ የሚያደርጋቸውም በራሱ በእግዚአብሔር የተጻፉ መሆናቸው ነው። ከግብረ ገባዊ ሕግጋት፥ በተለይም ከአሠርቱ ትእዛዛት ውስጥ ዘጠኙ በወንጌላት ውስጥ በጌታ ትምህርቶች ተደግመዋል፤ ከሰንበት በቀር። ስለዚህ ግብረ ገባዊ ወይም ድንበርና ዘመን ዘለል የሆኑት ትእዛዛት በጌታ ተደግመዋል። ሕግ አዋቂው ሰው ሊፈትነው ከሁሉ ፊተኛ ወይም ታላቅ ስለሆነችው ትእዛዝ ጌታን በጠየቀው ጊዜ የመለሰለት አጭርና አጠቃላይ መልስ እግዚአብሔርን መውደድና ባልንጀራን እንደ ራስ መውደድ የሚለው ነው፤ ማቴ 22፥35-40። ጳውሎስ በገላ. 6፥2 የክርስቶስ ሕግ የሚለው ይህንን ነው። እግዚአብሔርን ከወደድን እና ባልንጀራችንን ከወደድን ከኛ የሚፈለገውን ሁሉ ፈጸምን ማለት ነው። ሌላውን የምናደርገውን ሁሉ የምናደርገው እግዚአብሔርን ስለምንወድድና ባልንጀራችንን ስለምንወድድ ነው። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሞተበት ጊዜ ለብሉይ ኪዳን ሕግ ፍጻሜ ሆነ። ስለዚህ፥ ዛሬ የብሉይ ኪዳን ሕግ እንደ ሕግ በክርስቲያኖች ላይ የጸና አይደለም። ደኅንነት በጸጋ በሆነ እምነት እንጂ በሥራ አይደለምና ሕግን በመጠበቅ ደኅንነትን መቀዳጀት ከመስቀሉ ወዲህ ቀርቶአል። ሮሜ 10፥4 እንደሚለው፥ *የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ ነውና።*

* * * * *

7. ኢየሱስ አምላክ ነው? እኔ አምላክ ነኝ ብሎ ነበር?

ኢየሱስ አምላክ ነውን? ኢየሱስ እኔ አምላክ ነኝ ብሎ ነበርን? ጣ. አ

ሰላም ጣ. አ. በዮሐ. 1፥1-2 *በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።* ይላል። ከዚህ ክፍል የምንገነዘበው ቃል እግዚአብሔር መሆኑን እና ይህም ቃል በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደነበረ ሲሆን በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 14 *ይህ ቃል ሥጋ መሆኑ* ተጽፎአል። ይህ ሥጋ የሆነው ቃል ኢየሱስ መሆኑም ተብራርቶአል። በነጥቦች የሚሠሩ ስዕሎችን አይተን እናውቃለን፤ በመጀመሪያ የምናየው ነጥቦች ብቻ ነው፤ ቁጥሮችን ተከትለን ነጥቦቹን ስናገናኝ ግን ስዕሉ ፍጥጥ ብሎ ይታያል። ስለ ክስቶስ የሚናገሩትን እነዚህን ነጥቦች ስናገናኝ የምናገኘው እውነት፥ አዎን፥ ኢየሱስ አምላክ ነው፤ እርሱ እግዚአብሔር ወልድ ነው የሚል ነው።

ኢየሱስ፥ 'እኔ አምላክ ነኝ' ብሎ በቀጥታ መናገሩ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። ይህ አቀራረብ ኢየሱስ፥ 'አምላክ ነኝ' አላለምና አምላክ አይደለም ለማስኘት ግን ጉልበት የሌለው አቀራረብ ነው። ኢየሱስ፥ 'እኔ አምላክ አይደለሁም' ብሎ አልተናገረምና አምላክ ነው ማለት ነው በሚል አጭር አጸፋ መመለስም ይቻላል። እንደ ጥያቄው አቀራረብ ማለቴ ነው። ይሁን እንጂ የኢየሱስ አምላክነት በወንጌላት ውስጥ በገሃድ ይታያል። በዮሐ. 8፥59 አይሁድ ኢየሱስን ሊወግሩት ድንጋይ ማንሣታቸው ተጽፎአል። ለአይሁድ መውገር የሞት ቅጣትን መቅጣት ነው። (በሐዋ. 8 እስጢፋኖስን እንደወገሩት። እስጢፋኖስን የወገሩት ኢየሱስን በመስበኩ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን በአብ ቀኝ ቆሞ አየሁ በማለቱ ነው። ይህ በቀኝ መቆም ኢየሱስንና አብን ማስተካከል ወይም ኢየሱስን እግዚአብሔር እንደሆነ መግለጥ ነው።) አይሁድ ኢየሱስን ለመውገር ድንጋይ ያነሡት ኢየሱስ፥ *አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ* ስላላቸው ነበር (ቁጥር 58)። ይህ ዘላለማዊነቱን መናገሩ ሲሆን ዘላለማዊነት የመለኮት ባህርይ ብቻ ነው።

ሌላ ሁለተኛ ኢየሱስን ለመውገር ድንጋይ የተነሣበት ጊዜም ነበረ። በዮሐ. 10፥33 *አይሁድም፥ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት።* የሚል ቃል አለ። ጥቂት ጥቅሶችን ወደላይ ከፍ ብለን ስንመለከት አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ እንዳነሡና ይህን ያደረጉትም፥ 'እኔና አብ አንድ ነን' በማለቱ እንደሆነ እናነብባለን። ኢየሱስ የተናገረው ንግግር ለአይሁድ አሻሚና አደናጋሪ አልነበረም። ምን ማለቱ መሆኑን አልጠየቁትም፤ እርሱም አላስተባበለም።

ቤተ ክርስቲያን በሐዋ. 20፥28 በገዛ ደሙ የዋጃት የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ተብላለች። የገዛ ደሙ የተባለው የተዋጀችበት ደም የእግዚአብሔር ደም ነው ማለት ነው። ይህ ከሆነ የፈሰሰው ደም የኢየሱስ ነውና ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው። ይህ የደም መፍሰስ ነው ኢየሱስ አምላክ ሳለ ሰው የሆነበት ምክንያት። ደም እንዲኖረው ሰው መሆን አስፈለገው። የብዙዎች ኃጢአት ለአንዴና ለመጨረሻ የሚወገድበት ሥርዓት ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ መስዋዕትን ከፍቅር የተነሣ አዘጋጀ። ደም ይፈስስ ዘንድ አምላክ ሰው መሆን ኖረበት፤ ደግሞም ምንም ኃጢአት የሌለበት መሆን ተገባው፤ እንዲያው ሰው ብቻ ከሆነ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና ንጹህ መሆን ባልቻለም ነበር። ደግሞም ለራሱ ኃጢአት ብቻ ነው የሚሞተው እንጂ ሌላውን መወከል አይችልም። ስለዚህ ሰው ብቻ ሳይሆን ሰው የሆነ አምላክ መሆን አለበት፤ ይኸውም በምትክነት የሚሰሰዋው ቁጥር ስፍር ለሌለው ኃጢአትና እጅግ ብዙ ለሆኑ ኃጢአተኞች በመሆኑ ነው።

ኢየሱስ እግዚአብሔር የመሆኑ ወይም የአምላክነቱ ሌላ አስረጅ የሚሆነው አምላክ ብቻ ሊያደርጋቸው የተገቡ ነገሮችን ማድረጉ ነው። ተአምራትን ማለቴ አይደለም። ይህ ተአምራትን ማድረግ የአምላክ ችሎታ ቢሆንም እግዚአብሔር በሰዎች አማካይነትም ተአምራትን በማድረጉ እዚህ አልጠቅሰውም። ነገር ግን፥ እንደ ኃጢአትን ይቅር ማለት፥ (ማቴ. 9፥2-5፤ ሉቃ. 7፥48)፤ ጌታ ተሰኝቶ ስግደትን መቀበል፥ (ማቴ. 14፥33፤ ሉቃ. 24፥52፤ ዮሐ. 20፥28፤ ራእ. 19፥10፤) የአምላክ ብቻ

ሥልጣን ነው። እነዚህን ካደረገ ኢየሱስ አምላክ ነው። አንድ ሰው ስለ ራሱ ሳይለፍፍ በጎ እያደረገ ቢዞርና ሰዎች ያንን ሰው፥ 'በጎ አድራጊ' ቢሉት አልተሳሳቱም፤ ያንን ነዋ! ሌላ ሰው ደግሞ፥ ይህም ስለ ራሱ ሳያውጅ፥ እየበደለና እየገደለ ቢዞርና ሰዎች ያንን ሰው፥ 'በደለኛ ወይም ነፍሰ ገዳይ' ቢሉት አልተሳሳቱም። ሰዎች ኢየሱስን አምላክ ወይም ጌታ ቢሉት ሰምተውና አይተው ነው። በሌሎችም ስፍራዎች በግልጽ አምላክ ተሰኝቶአል፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1።

ኢየሱስ አምላክ ካልሆነ ራሱን ከአብ ጋር አንድ ያደረገ ሐሰተኛ ነውና እንደ መልካም ሰው ወይም እንደ ነቢይ መታየት የለበትም። እንደ እንደ ይሖዋ ምስክሮች፥ 'ቃልም አምላክ ነበር' ብሎ በግርጌ ማስታወሻ፥ 'እንደ አምላክ ያለ፤ የመለኮትነት ባሕርይ የተላበሰ' ብሎ መተርጎም ማጣመም ነው። እንደ አምላክ ያለ ከተባለ አይደለም ማለት ነው። ወይም እንደ ኢስላም፥ 'ኢየሱስ ነቢይ ብቻ ናቸው እንጂ ሌላም አይደሉም' ማለት ሙሉውን እውቀት ጥሎ እውነትን ለመሸሽ ራስን መሸንገል ነው። ይህን አመለካከት በተመለከተ C.S. Lewis የተባለው እንግሊዛዊ ምሑር *Mere Christianity* በተባለ መጽሐፉ ውስጥ ገጽ 54-56 ስለ ኢየሱስ እንዲህ ያለውን ጠቅሼ ልጨርስ፤ ትርጉም የራሴ ነው።

ልከላከል የምፈልገው አንድ ነገር አንዳንድ ሰዎች ስለ ኢየሱስ፥ 'ኢየሱስን እንደ ታላቅ የሞራል መምህር አድርጌ እቀበላለሁ፤ አምላክነቱን ግን አልቀበልም' የሚሉትን ነው። ይህ ማለት የሌለብን አንድ ነገር ነው። እንዲያው ሰው ብቻ የሆነ ሰው ኢየሱስ የተናገራቸውን ነገሮች ከተናገረ ታላቅ የሞራል መምህር ሊሆን አይችልም። ይህ ሰው ወይ ዕብድ ነው፤ 'እኔ የተቀቀለ እንቁላል ነኝ' እንደሚል ያለ ዕብድ፤ ያለዚያ ከሲዖል የመጣ ሰይጣን ነው። ምርጫህን መምረጥ አለብህ። ይህ ሰው ወይ የእግዚአብሔር ልጅ የነበረና የሆነ ነው፤ ወይም ዕብድ፥ ወይም ከዚያ የከፋ ነው። ከፈለግክ ዘግተህ ዝም ልታሰኘው፥ ምራቅህን ጢቅ ልትልበት፥ እንደ ዲያብሎስ ቆጥረህ ልገድለው ትችላለህ፤ ወይም ከእግሩ ስር ወድቀህ ጌታ እና እግዚአብሔር ልትለው ትችላለህ። ነገር ግን፥ ታላቅ የሞራል መምህር ወደሚል የንቀት ንግግር አንምጣ። ይህንን ለምርጫችን አላቀረበልንም፤ ይህ አሳቡም አልነበረም።

* * * * *

8. ማርያም እመቤት ናት እንዴት አይባልም?

ስለ ፓስተር ዳዊትና ምሕረተ አብ ዲቪዲ የጻፍከውን አነበብኩ። እንዴት ደደብ ብትሆን ነው ቅድስት ማርያም እመቤት መባልዋን የምትቃወመው። በ2ኛ ዮሐንስ የተጻፈችው ሴት እግዝእት ስትባልስ ምን ትላለህ? እግዝእት ማለት የጌታ ተቃራኒ [ተነጻጻሪ ለማለት ነው] ሆኖ የተጻፈ ቃል ነው። . . . ስለዚህ እግዝእት ለማንም የተከበረች ሴት መጠሪያ ሊሆን ይችላል። እንዴት ጠባብ ጭንቅላት ያለህ መሆኑንና ፕሮቴስታንቲዝን የሞኞች ሃይማኖት መሆኑን ማወቅ

እፈልጋለሁ። ያዛ ታቦቱን ሲነካ ምን ሆነ? ታቦት ቀድሞ እግዚአብሔር የተገለጠበት ሲሆን ማርያም ደግሞ በሥጋ የተገለጠባት ናት። ከሁለቱ ማናቸው ይበልጣል? ደግሞስ፥ በአይሁድ ልማድ ዘመዶችን ወንድምና እኅት እንደሚሉ አታውቅም? ሎጥንና አብርሃምን ተመልከት። ጅል ከሆነው ጽሑፍህ ያነበብኩት ሌላው ነገር መለኮት አይወለድም፤ ስለዚህ ማርያም እመ አምላክ (Theotokos በኒቅያ ጉባኤ የተቀበሉት ቃል) አትባልም ያልከው ነገር ነው። ስለዚህ አብም አብ አይባልም ልትል ነዋ! ተጨማሪ የስነ መለኮት መጻሕፍት ልታነብብ ሞክር። የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳትህ የጅል ዓይነት መረዳት ነው። እግዚአብሔር ወደፊት እውነትን እንድታውቅ ይርዳህ። ዘመነ ማቴዎስ።

ውድ ዘመነ፥ ምንም እንኳ ኢሜልህ የስድብ ርችት ቢበዛበትም ለመመለስና ለመነጋገር ፈቃደኛ ነኝ። በ2ኛ ዮሐንስ የተጻፈችው ሴት ማርያም ናት ማለትህ አይመስለኝም። ይህን ማለትህ ከሆነ ስለ ልጆችዋ የተነገረውንም ተቀብለሃል ማለት ነውና ማርያም ናት የምትል አይመስለኝም። ነጥብህ ያቺ ሴት እመቤት ከተባለች ለምን ማርያምስ አትባልም? የሚል ነው።

እርግጥ ነው ለዚያቺ ሴት መልእክቱ ሲጻፍ በግዕዝ፥ 'ለኅሪት ወለእግዝእት' ተብላለች። ይህ ሲነበብ ሰምተህ ሊሆን ይችላል፤ አንብበህም ይሆናል። በአማርኛም ቃሉ እመቤት ነው የሚለው። በአጠራሩ ከሄድን ማርያምም እመቤት ልትባል ትችላለች። ነገር ግን ይህ እመቤት እና እመቤታችን የተለያዩ መሆናቸውን ሳንረሳ ነው። ያወሳሁት ጉዳይም ስለ ማርያም የተነገረ የአጠራር ሳይሆን ለማርያም የሚደረግ የአምልኮት ጉዳይ ነው። ይህ ይሁን እንጂ በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ያልተጻፈውን ቃልና ማዕረግ መጻፍ የኛ ድርሻ አይደለም።

ማርያም ለመጨረሻ ጊዜ የተጠቀሰችው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ሲሆን እዚያም 'እመቤታችን' አልተባለችም። *እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር* ነው የተባለው፤ ሐዋ. 1፥ 14። እግዝእት ማለት በአማርኛው በ2ዮሐንስ የተጻፈው እመቤት ነው። እንደ ዘመናችን 'ጌቶች' እና 'እሜቴ' የአክብሮት አጠራር እንጂ እግዚአብሔርን እንደምንጠራበት ያለውን ጌትነትን ለማቀዳጀት አይደለም። እንዳመለከትከው ጌታ የሚለው ቃል በጽርዕ ኩሪዮስ እመቤት ደግሞ ኩሪያ ነው። ለተባዕት ጌታ፥ ለአንስት እመቤት እንደምንለው ነው። እግዚእ፥ እግዝእት ማለት ያው ነው። ግን ጌታን እግዚእነ ወይም ጌታችን እንደምንል ሌላ ማንንም እንደዚያ እንደማንል ሁሉ ሌላ ሴትን በአክብሮት እግዝእት ልንል እንችላለን (ዮሐንስ እንዳለው) እንጂ ማንንም 'እግዝእትነ' አንልም። ደግሞም እንዲዚያ የሚል ቃል ግን በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቀጣዮቹ ዘመናት በተጻፉ ጽሑፎች ኖረው አያውቁም። እመቤታችን የሚለው ማዕረግ እጅግ ቆይቶ በሰዎች ተምጦ የተወለደ ቃል ነው። እመቤት ስትል በአክብሮት መጥራትህ ሲሆን እመቤቴ ስትል ግን እመቤቲቱን ባንተ ላይ ባለ ሥልጣን አድርገህ መቀበልህ ነው።

አንዳንድ ትላልቅ የስነ መለኮት ቃላትን በጥያቄና አስተያየትህ ውስጥ ስለወረወርክ የስነ መለኮት አጥኚ እንደሆንክ እገምታለሁ። ቃሉን መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ካጠናኸውና ከቃሉ ብቻ ጋር ካነጻጸርከው የስነ መለኮትህ ምንጩ የተሳሳተ መሆኑን አታጣውም። ምናልባት ራስህም እንደምታውቀው አማካዩ የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ምእመን ከኢየሱስ ይበልጥ ስለ ማርያም ነው የሚያውቀው። ራሴም ለብዙ ዓመታት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስሄድ መጽሐፍ ቅዱስን ከመሳምና መሳለም በቀር አልተነበበልኝም፤ እንዳነብብም አልተበረታታሁም። ማንም ቄስና ዲያቆን ስለ መዳንና በክርስቶስ ስላለው ነፃነት አልነገረኝም። ከሰማይ በታች ሰዎች ሊድኑበት ስላለው አንድና ብቸኛ ድንቅ ስም አልተነገረኝም። ያ ስም ኢየሱስ ነው፤ *መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።* ሐዋ. 4፥12። ይህ ኢየሱስ ዘላለማዊ አምላክ ነው።

ማርያም የኢየሱስ እናት ናት፤ ኢየሱስን ሰው ሆኖ የተወለደው አምላክ ነው። ሰው የሆነውም በዓላማና ለአንድ ግብ ነው፤ ያም ጴጥሮስ በ1ጴጥ. 2፥24 *ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤* እንዳለ ኃጢአታችንን በመስቀል ሊሸከም የኃጢአታችን ስርየት የሆነበትን ደሙን ሊያፈስስ ነው። እንጂ ኢየሱስ መለኮቱ ዘላለማዊ ነው። አምላክ አይወለድም፤ ሳይወለድም ነበረና። እኔ ተወልጃለሁ፤ አንተ ተወልደሃል። ከልደታችን በፊት አልኖርንም። እግዚአብሔር ሁሌም አለ። ኢየሱስ በቤተ ልሔም ከመወለዱ ቀድሞም ነበረ።

የኢ. ኦ. ቤ/ክ አስተምህሮ የኢየሱስ ማንነት ተዋሕዶ መሆኑና በዚህ መዋሐድ ስብዕናው በመለኮቱ እንደተዋጠ ነው። ስለዚህ ነው የእግዚአብሔር እናት (እመ አምላክ) የምትሰኘው። በነገራችን ላይ፥ ይህንን የTheotokos ትምህርት ያቆመው አንተ እንዳልከው የኒቅያ ጉባኤ ሳይሆን የኤፌሶን (431 ዓ. ም.) ጉባኤ ነው። እንደ ወንጌላዊ አማኝ ስለ ኢየሱስ የምረዳው ኢየሱስ አንድ አካል አንድ ባህርይ ሳይሆን አንድ አካል ሁለት ባህርይ እንደሆነ ነው። ነጥቡም፥ ማርያም ኢየሱስን ወልዳለች፤ የወለደችውም ለኃጢአታችን ስርየት በመስቀል ላይ ይሞትልንና ደሙን ያፈስስልን ዘንድ፥ ሞትንና በሞት ላይ ሥልጣን ያለውንም ይሽርልን ዘንድ በሥጋና ደም ሊካፈል ነው፤ *እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ።* ዕብ. 2፥14-15።

ስለ ታቦቱና ስለ ማርያም አመሳስለሃል። ይህ በስነ ማርያም (Mariology) መደበኛ የሆነ ትምህርት ነው። አንድ መጽሐፍ ማርያምንን ከ99 የብሉይ ኪዳን ምስሎች (የያዕቆብ መሰላል፥ የሙሴ በትር፥ የአሮን በትር፥ የሰሎሞን መቅደስ፥ ወዘተ፥) ጋር በማነጻጸር ይተነትናል። አንድ ሁለቱን በዕዝራ ቁ. 14 እና 15) ውስጥ በቅርበት እንድናይ ተንትኛለሁ። ይህ ዓይነት የማመሳሰል አመነዛዘርና ትምህርት ውኃ አያነሣም። ለምሳሌ፥ የሙሴ በትር ከሆነች ሙሴ ማን ሊሆን ነው? የሙሴ በትር የዋጠቻቸው እባቦችስ ምን ሊሆኑ ነው? ወዘተ። ወደ ታቦቱ ስመለስ፥ እግዚአብሔር

በታቦቱ ውስጥ አልነበረም። ስለዚህ ታቦቱ ቅድመ አካላዊ ምስል (theophany) ነው ማለት አትችልም። ግን ብለሃል፡፡ በጥንቃቄ ስናነብብ፤ ታቦቱ የእግዚአብሔር በመካከላቸው መገኘት ምሳሌ ምልክት እንጂ ታቦቱም እግዚአብሔር አልነበረም፤ ታቦቱም ውስጥ እግዚአብሔር አልነበረም። ታቦቱ በግራር እንጨት ተሠርቶ በወርቅ የተለበጠ ሳጥን ሲሆን በውስጡ የነበሩት የአሮን በትር፥ አሠርቱ ቃላት የተጻፉበት ጽላቶች እና አንድ ማድጋ ሙሉ መና ናቸው። ያዛ የተቀሰፈው ሕጋዊ ያልሆነ፥ እንደ ሕጉ ያልሆነ ነገርን በማድረጉ ነው። እንደተረዳሁህ አተረጓጎምህ ከላይ ወዳልኩት አሳብ ሄዶ ያዛ ታቦቱን ስለነካ ከተቀሰፈ ማርያምን የነካ የከፋ ቅጣት ይደርስበታል የሚል ነው። ነፍሷ ከአምላኳ ጋር ናት እንጂ በምድር የለችምና ማርያምን ማንም ሊነካ አይችልም። ትምህርተ ማርያምን የተቃወመ ቅጣት ይደርስበታል ማለትህ ከሆነም ይህ ብዙዎች ቀሳውስት እንደሚያስፈራሩት ያለ ማስፈራራት ነው። ማርያም በመጀመሪያው የጌታ ተአምር ስትጠቀስ፥ የኢየሱስ እናት ተብላ ነው፤ ዮሐ. 2፥3። ለመጨረሻ ጊዜ በተጠቀሰችበት ስፍራም የኢየሱስ እናት ተብላ ነው፤ ሐዋ. 1፥14። የአምላክ እናት፥ የእግዚአብሔር እናት የሚል ምልክቱም አልተጻፈም። ይህ ማለት ኢየሱስ አምላክ መሆኑን አለመናገር ሳይሆን መለኮት ዘላለማዊ ሲሆን ሥጋ መልበሱ ከማርያም መወለዱ መሆኑን መግለጥ ነው።

በመጨረሻ ስለ አብርሃምና ስለ ሎጥ ያነሣኸው ግልጽ ባታደርገውም በጽሑፌ ውስጥ የጠቀስኩትን የኢየሱስ ወንድሞች የሚለውን አሳብ ለማውሳት እንደሆነ እገምታለሁ። ከሆነ በስፍራው (በዕዝራ ቁጥር 15፥ ከገጽ 4-9) በሰፊው የጻፍኩት ስለሆነ እዚህ መድገም አስፈላጊ መስሎ አልታየኝም። ያንን ክፍል ደግመህ እይና ጥያቄህን ወይም ነጥብህን ገልጠህ እንደገና ላክልኝ። ከዚህ በፊት ልኬልህ ስለማላውቅ ከሌላ ስፍራ ተልኮልህ ያነበብክ ይመስለኛል።

በመጨረሻ፥ ውድ ዘመነ፥ ኢየሱስን በግልህ እወቀው እልሃለሁ። ጥቂት ጊዜ ለራስህ ለይና ለአንድ ወይ ለሁለት ሳምንታት ምንም ነገር ሳይሆን ወንጌላቱን ብቻ በጸሎት ታግዘህ አንብብ። ኢየሱስን ወደ ልብህ ጋብዘው። አስደናቂ የሕይወት ጉዞ ይሆንልሃል። እውነትም ኢየሱስ ወደ ልባችን ሲገባ ድንቅ ሕይወት ነው። ብዙ በረከት ይሁንልህ።

* * * * *

9. የዘፍጥረት 6 የእግዚአብሔር ልጆች እነማን ናቸው?

በዘፍጥረት 6፡1-4 የተጻፉት የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች እና የሰዎች ሴቶች ልጆች እነማን ናቸው? የወደቁ መላእክት ናቸው ብለው ስላስተማሩኝና ጠቅላላውን መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤ ስጨርስ ደግሞ ይህንን የሚመስል ነገር ስላላገኘሁ ግር አለኝ። መላእክትና ሰዎች መጋባት ይችላሉ ወይ? (ሳ. ጎ)

ውድ ሳ. ጎ. በዘፍ. 6፡1-4 የተጻፉት ሰዎች የአዳም ዘር የሆኑ ሰዎች ናቸው። እነዚህን በተመለከተ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ፍጡራን መላእክት ናቸው ይላሉ። አይደለም።

በመጀመሪያ የተጻፈበትን የዘፍጥረትን ጽሑፍ ስናጤን ግለ ሰቦች ከተጻፉበት ከምዕራፍ 5 ወጣ ያለና ሰፊውን ስዕል የሚያሳይ ነው። ዘፍ. 6 ጠቅላላውን የሰው ልጆች ሁኔታ የሚያሳይና በቀጣዩ ምዕራፍ የሚታየውን የጥፋት ውኃ ቅጣት የሚሆነውን የጥፋት መንስዔ የሚያሳይ ነው። ጠቅላላው መልክ ይህ ሲሆን ሰዎች በጥፋት የመዝቀጣቸውን ሁኔታ ለማሳየት የተጻፈ ነው። የእግዚአብሔር ልጆች בְנֵי־הָאֱלֹהִים (ብኔይ ኻኤሎሂይም) የሚለውን ቃል የእግዚአብሔር መላእክት በማለት የእስክንድርያው የሰባ ሊቃናት የጽርዕ ትርጉም በመተርጎሙ እነዚህ ሰዎች እንደ መላእክት መስተዋል የጀመሩት ከዚያኔ ጀምሮ ነው። ይሁን እንጂ בְנֵי־הָאֱלֹהִים (ብኔይ ኻኤሎሂይም) እና בְּנוֹת הָאָדָם (ብኖውት ኻአዳም) የሰውን ማንነት፥ ሰው ሰው መሆኑን፥ኣዳም ልጅ መሆኑን የእግዚአብሔርም ፍጡር መሆኑን የሚያሳይ ይመስላል እንጂ ሁለት የተለያዩ ፍጡራን መጋባታቸውን አያሳይም። ጥቂት ነጥቦችን እንይ፤

1ኛ፥ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ ሁሉ እንደ ወገኑ ተፈጠረና ይዋለዳል እንጂ አንድ ፍጡር ከወገኑ ውጪ ካለ ፍጡር ጋር ሊዋለድ አልተፈጠረም። ይህንን ማድረግም አይችልም። አንድ ፍጡር ከሌላ ፍጡር ጋር ሊዳቀል አይችልም። በሣይንስ ልብ ወለድ ካልሆነ በቀር በግ ከአሞራ ወይም ግመል ከአነር ጋር ሊዋለዱ አይችሉም። ሰውም ከመላእክት ጋር መዋለድ አይችልም። መላእክት መናፍስት እንጂ አካላውያን ፍጡራን አይደሉም። ለራሳቸውም አካልን መፍጠር አይችሉም። ከቻሉ ፍጡር ሳይሆን ፈጣሪ ሆኑ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር በቀር መላእክትን ጨምሮ ማንም ፍጡር የመፍጠር ችሎታ የለውም። በአካላዊ መልክ ሊገለጡ ቢችሉም በተፈጥሮአቸው መናፍስት ናቸው፤ ዕብ. 1፥7፥14።

2ኛ፥ ጌታ መላእክት እንደማያገቡና እንደማይጋቡ በግልጽ ተናግሮአል፤ ማቴ. 22፥30፤ ማር. 12፥25፤ ሉቃ. 20፥34። መላእክት እንኳን ከሰዎች ጋር፥ ከመላእክት ጋርም እንደሚጋቡ ሆነው አልተፈጠሩም። ወሲባዊ ፍጡራን ስላይደሉ አይበዙም፥ አይባዙምም። ይህ ለሰው የተሰጠ ትእዛዝ ነው። የመላእክት አፈጣጠራቸውና የፍጥረታቸው ዓላማ የተለየ ነው። መላእክት ስለማይዋለዱ፥ ካመጹ በኋላ ፍርዳቸው የየግል ነው እንጂ የአንዱ ለሌላው የተላለፈ አይደለም። የሰው ግን እንዲህ አይደለም። አዳም ሲወድቅ የሰው ልጅ ሁሉ በአዳም ውስጥ ነበረና ወደቀ። በአዳም ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ እንደሆነ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ያመኑ ሁሉ መዳንን ይወርሳሉ። መላእክት እንዲህ ያለ ውድቀትና ደኅንነት አያገኛቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ የመላእክትና የሰው ዲቃላ ስለሆኑ ሰዎች ከቶም አይናገርም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቅጣትም ሆነ ደኅንነት ሰዎችንና መላእክትን የተመለከተ እንጂ የሰዎችና መላእክት ዲቃሎችን ፍርድም ሆነ ደኅንነት ከቶም አይናገርም።

3ኛ፥ ከዚህ ከዘፍ. 6፥1-4 ትክክለኛ ያልሆነ አተረጓጎም በቀር በሌላ በየትም መላእክትና ሰዎች ግብረ ተራክቦ ሲያደርጉ ከቶም አልተጻፈም። በዘፍ. 19፥1-5 የተጠቀሱት የሰዶም ሰዎች መላእክቱን ሊገናኙ መፈለጋቸውን እንደ ማጣቀሻ የሚያቀርቡ ሰዎች ተሳስተዋል። የሰዶም ሰዎች ኃጢአት ግብረ ሰዶም፥ ወይም ሰዶማዊነት ነው። የሰዶም ሰዎች የሎጥ እንግዶች ሰዎች እንጂ መላእክት መሆናቸውን አያውቁም። ቁጥር 5 የሚለን፥ *በዚህ ሌሊት ወደ ቤትህ የገቡት* <u>*ሰዎች*</u> *ወዴት ናቸው? እናውቃቸው ዘንድ ወደ እኛ አውጣቸው ነው።* በቁጥር 8 ላይ እንደምናገኘው ሎጥም፥ *በእነዚህ* <u>*ሰዎች*</u> *ብቻ ምንም አታድርጉ ነው ያለው።* ሰዎቹ ከሰው ፍጥረታዊ ባህርይ ውጪ ከሰዎች ጋር ለመባለግ እንጂ ሴቶችን ለመድረስ አልነበረም ጥረት ያደረጉት። እንዲያው ሆነ ቢባልና ሰይጣን ያኔ ይህን ካደረገ፥ ማለትም፥ ከሴቶች ጋር ወሲብ መፈጸምና ልጅ መውለድ ከቻለ ከዚያ በኋላስ ለምን አላደረገም? ዛሬስ ከማድረግ ምን ሊያግደው ይችላል? የማይችለው ወይም ያላደረገው ሊያደርግ ስለማይችል ነው።

4ኛ፥ ሰይጣን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ አልተጠራም። በኢዮ. 1፥6፤ 2፥1፤ ሰይጣን ኢዮብን በከሰሰበት ስፍራ እንዲሁም በ38፥7 መላእክት እንደ እግዚአብሔር ልጆች እንደተጠቀሱ ይታያል። ሆኖም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ስፍራዎች የሰይጣን አጠቃቀስ እንደ ሰይጣን (ጠላት) እንጂ እንደ እግዚአብሔር ልጆች አይደለም። በዘፍ. 6 የምናገኛቸው የእግዚአብሔር ልጆች አጋንንት ከሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው መጠራት አይችሉም። እንደ ቅዱሳን መላእክት የባህርያቸው ባልሆነ ተግባርም አይሰማሩም። አጋንንትም ቢሆኑ በዚህ እኩይ ሥራ ይሰማራሉ ማለት ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ከቶም የማያደርጉት መሆኑን ለማጉላት ነው።

5ኛ፥ በዘፍ. 6፥3 እንደምናየው ፍርዱ (የመቶ ሀያው ዓመት ገደብ) የታወጀው በሰዎች ላይ መሆኑን የጥፋት ውኃ ያረጋግጣል። ቅጣቱ በሰዎች ላይ መሆኑ ጥፋቱ የሰዎች መሆኑን ያረጋግጣል። በዘፍ. 3 ሰይጣን ሰውን ባሳተበት ጥፋት ሰው ስለሳተ ቢቀጣም ሰይጣን ግን አሳች በመሆኑ ፍርዱን አግኝቶአል። እዚህ ግን ስለ ሰይጣን የተነገረ ቅጣት አይታይምና ስዕሉ ውስጥ የለም። የጥፋት ውኃ በሰይጣን ላይ የመጣ ቅጣት አይደለም።

ዘፍ. 6፥5-7 *እግዚአብሔርም* <u>*የሰው*</u> *ክፋት በምድር ላይ እንደ በዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም* <u>*ሰውን*</u> *በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ። እግዚአብሔርም፦ የፈጠርሁትን* <u>*ሰው*</u> *ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥* <u>*ከሰው*</u> *እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ።*

6ኛ፥ ኔፊሊም הַנְּפִלִים (ኻነፊሊይም) የመላእክትና ሰዎች ቅይጦች አይደሉም። ጤነኞች፥ የዳበሩ፥ ግዙፎች ማለት ነው። ትርጉሙ በሰያፍ አካላዊ ግዝፈትን ብቻ ሳይሆን ጨቋኝነትንም ሳያመለክት አይቀርም። ቀጥተኛ ትርጉሙ ግን የዳበረ ሰውነት ወይም አካላዊ ግዝፈት ነው። ከፍጥረት ጀምሮ እስከ ጥፋት ውኃ ድረስ በእግዚአብሔር እጅ የተሠሩት የፍጹማን ፍጡራን አዳምና ሔዋን ጤናማ ፍጥረትና

እንደ ዘመናችን ያልተበከለ ምድር ሰዎች እንዲዳብሩና እንዲገዝፉ አስችሎአቸዋል። ይህ የግዙፋን መኖር ከጥፋት ውኃ በኋላም እንኳ አላቆመም። ይህንን የሚያረጋግጥልን ከዚህ በኋላ ብዙ ብዙ ዘመናት ቆይቶ አይሁድ ከግብጽ ወደ ተስፋዋ ምድር ሲገቡም፥ ከጥፋት ውኃ ብዙ ብዙ በኋላም፥ ከኖኅ ዝርያ ውስጥም እነዚህ ኔፊሊም የተባሉ ግዙፎች በምድር ላይ ነበሩ። የተስፋይቱን ምድር ሰልለው የመጡት ሰዎች በዘኍ. 13፥33 ስላዩአቸው ሰዎች ሲናገሩ፥ *በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ የዔናቅን ልጆች፥ አየን እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ።* እነዚህ የመላእክት ልጆች አይደሉም።

በእነዚህ ምክንያቶች በዘፍ. 6፥1-4 የተጠቀሱት ሰዎች ሰዎች እንጂ መላእክት አይደሉም።

. . . . .

በቀጣይ ከዚህ ጥያቄ ጋር ተያያዥ የሆነ ማጣቀሻ ቀርቦ ነበር። ያም በይሁዳ መልእክት ላይ ከጻፍኩት ጋር ተያያዥነት አለው። ወንድም ሰሎሞን በለጠ በገጹ ላይ በጻፈው አሳብ ላይ የሰጠሁት መልስ ነው። ሰሎሞን በይሁዳ ቁ. 6 የተጠቀሱትና በዘፍ. 6፥1-4 የተጻፉት ተመሳሳይ መሆናቸውን እና የወደቁ መላእክት ከሰው ሴቶች ጋር ግብረ ሥጋ በመፈጸም ሰዎችን (የመላእክትና ሰዎች ቅይጦች) መውለዳቸውን በመጥቀስ ጽፎአል። ከይሁዳ መልእክት ጋር የተያያዘው ምላሽ ይህ ነው።

ውድ ሰሎሞን፥ ስለአስተያየትህ ምስጋና እሰነዝራለሁ። ጽሑፍህም ማለፊያ ነው። ነገር ግን ትርጓሜው መላእክትን፥ በተለይም፥ የወደቁ አጋንንትን ወደ ሰውነት የሚያመጣና ግብረ ሥጋ የሚያስፈጽም መሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያሳጣዋል ብዬ አምናለሁ። የእኔ ቀለል ያለ ሐቲት በይሁ. 6-7 ያለው ነው። የዘፍ. 6፥1-4 አሳብ ለመፍታት አሻሚ መሆኑን አስምረህበታል። ሁለቱንም ጥቅሶች ላስቀምጣቸው።

ዘፍ. 6፥1-4 እንዲህም ሆነ ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ። እግዚአብሔርም፦ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና፤ ዘመኖቹም መቶ ሀያ ዓመት ይሆናሉ አለ። በእነዚያ ወራት ኔፊሊም በምድር ላይ ነበሩ፤ ደግሞም ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤ እነርሱም በዱሮ ዘመን ስማቸው የታወቀ ኃያላን ሆኑ።

ይሁዳ 6-7 መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል። እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።

እኔ ስለ ይሁዳ ሳትት የጻፍኩትን የመጀመሪያውን አንቀጽ እዚህ ልድገመው። "ቀጥሎ ይሁዳ ስለ ሐሰተኞች ምሳሌ አድርጎ ምስክር የጠራው ስፍራቸውን የለቀቁ መላእክትን ነው። የይሁዳ መልእክት በግልጽ የማናገኛቸውን ነገሮች በማውሳት የታወቀ አጭር መጽሐፍ ነው። አንዱ ስፍራ ይህ ነው። ይህ ጥቅስ ስፍራቸውን ለቅቀው በእስራት ስለሚገኙ መላእክት ይናገራል። በጣም ግልጽ አይደለም። ይህ መኖሪያን መተው እና አለቅነትን አለመጠበቅ በዘፍ. 6 ካለው የእግዚአብሔር ልጆች እና የሰው ሴቶች ጋር የተደረገው የዝሙት ኃጢአት እንደሆነ ይገምታሉ። ቁጥር 6 ከቁጥር 7 ጋር ስለሚያያዝም ያ ሳይሆን አይቀርም ይላሉ። መላእክት ሊያገቡና ሊጋቡ ስለማይችሉ ያ ሊሆን አይችልም። ይህ ከሆነና ያንን ኃጢአት ያደረጉት ታስረዋል ቢባል ያልታሰሩት ያንን ከማድረግ የሚከለክላቸው የለምና ሰውና ኢጋንንት እየተጋቡና እየተዋለዱ ሊኖሩ በቻሉም ነበር። ቃሉም መኖሪያቸውን መተዋቸውን እንጂ መልአክነታቸው ትተው ሰውነትን መላበሳቸውን አይናገርም። . . . ቀጥሎ ይሁዳ ስለ ሐሰተኞች ምሳሌ አድርጎ ምስክርና የቅጣት ምሳሌ የጠራው ሰዶምና ገሞራን ነው። 'እንደ እነርሱ' ሲል በቁ. 6 እንደተጻፉት እንደ መላእክቱ ማለቱ አይደለም። መላእክቱ መኖሪያቸውን መተዋቸውን እንጂ መልአክነታቸው ትተው ሰውነትን መላበሳቸውን አለመሆኑን ባለፈው አይተናል። እዚህ፥ 'እንደ እነርሱ' ሲል እንደራሳቸው እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች ማለቱ ነው።"

የእግዚአብሔር ልጆች ማለት መላእክት ናቸው ብለው ከሚያስተምሩት ጠቅሰሃል። የአንተም መረዳት እንደዚያ ነው። መላእክት ከሰዎች ጋር ሊገናኙ ወይም ሰዎች ከመላእክት ጋር ሊገናኙ እንደሚችሉም ወደ ሎጥ ቤት የመጡትን ሁለቱን መላእክት በመጥቀስ አስረድተሃል። የሰዶም ሰዎችም ሆኑ ሎጥ እነዚያን እንደ መላእክት አለመረዳታቸው ግን ግልጽ ነው። አብርሃምንም ጨምሮ ሎጥም የሰዶም ሰዎችም ሰዎችን ነው ያዩት። ሰዶማውያኑ ሊደርሱባቸና ሊያውቋቸው ወደ ሎጥ ቤት የመጡትም ሰዎችን እንጂ መላእክትን አይደለም።

በጽሑፍህ በገጽ 12 ያልከው እነዚህ መላእክት በሰው ክልል ከተከሰቱ በኋላ የግብረ ሥጋ ግንኙነትም ሆነ ልጅ ማስወለድ እንደሚችሉ ብቃት ያላቸው መሆኑን ነው። እዚያው ገጽ መኖሪያቸውን መኖሪያ አካል ማለትህ ወደ ይሁዳ መተላለፊያ ሆኖአል። መኖሪያን መተው ከመልአክ አካልነት ወደ ሰው፥ ማለትም፥ ከሴቶች ጋር ግብረ ሥጋ ሊያደርግና ሊወልድ ወደሚችል አካልነት ገብቶ ዝሙት የማድረግ መተላለፍ መሆኑንም በገጽ 13 ላይ ቀጥለህ አብራርተሃል። እነዚህ መላእክት መኖሪያቸውን መተዋቸው 'ወደ ሰብአዊ ፍጡር የመኖሪያ ከበብ' (አካልነት??) መምጣታቸው መሆኑን ጽፈሃል። እነዚህ ይህን ያደረጉ መላእክት ከሌሎቹ ተለይተው ታስረው መቆየታቸው ከዚያ በኋላ እንዲህ ያለው ግንኙነት እንዳልቀጠለና ኔፊሊም የተባሉት የመላእክትና የሰዎች ድብልቅ የሆኑ ሰዎች መወለድ ማቆማቸውን የሚያስተምሩ አሉ።

እንዲህ ያለው ትምህርት ለመረዳት አዳጋች በሆኑ ክፍለ ምንባቦች ለማስረዳት ቀላል የሚያስደርጉ አሳቦችን በመሳግ ግልጽ ለማድረግ መሞከር ነው። ስሕተቱ ለማስረዳት ቀላል የሚያስደርጉት ማብራሪያዎች ግምታውያን መሆናቸው ነው። መላእክት ተባእት ናቸው ወይስ አንስት? ወይስ ጾታቢስ? ብለን ስንጠይቅ መላእክት እንደማያገቡና

እንደማይወልዱ ስለ ትንሣኤ አካል በሚናገርበት ጊዜ በማቴ. 22፥30 እና ማር. 12፥25 ጌታ በግልጽ ተናግሮአል። እርግጥ ነው መላእክት ለሰዎች ለመገለጥ አካልን ለጊዜው ሲቀዳጁ እንደ ሰው (ወንድ) ይገለጡ እንጂ መላእክት መናፍስት ናቸው። ሥጋ አይደሉም። አይወልዱም፤ አይበዙም፤ አይባዙም፤ አይሞቱም፤ አይነሡም።

ኔፊሊም ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩና በጥፋት ውኃ ዘመን የጠፉ ብቻ ሳይሆኑ ከጥፋት ውኃ በኋላም ነበሩ። ዘኁ. 13፥33 ይህንን ሲገልጥ እንዲህ ይላል፤ በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ የዔናቅን ልጆች፥ አየን፤ እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ። በተጻፈበት ቋንቋ נְפִל (ንፊይል) ግዙፍ፥ ኃያል፥ በጣም ትልቅ (በቀጥታ ዛፍ ጣይ) ማለት ነው። በጥንት ዘመን እንደዚያ ያሉ ሰዎች ነበሩ። ሰውነታቸውም ዕድሜያቸውም እንደ ዛፍ ነበር የጥንት ሰዎች፤ በተለይ ከጥፋት ውኃ በፊት። 900 በላይ ዓመት ከተኖረ ሜትር ከዘጠና ብቻ አይኮንም። በሁለቱም ጥቅሶች ውስጥ ያለው ኔፊሊም የሚለው ቃል ተመሳሳይ ነው። እና እንደገና የወደቁ መላእክት ከሰዎች ሴቶች ጋር ተገናኝተው እንደገና ወለዱ? ዘፍ. 6ን እንደዚያ የሚተረጉሙ ይህንንም እንደዚያ እንዲፈቱ የተገባ ነው። ግን አይደለም። ኔፊሊም የሰዎቹን ግዝፈት መናገሩ እንጂ የመላእክትና ሰዎች ቅይጥነታቸውን መናገሩ አይደለም። መላእክት መናፍስት ከሆኑና ራሳቸውን ወደ ‘ሰው ክበብ’ ማስገባት ከቻሉ ፈጣሪ ናቸው ያሰኛል። ግን አይደሉም። አንድ ሰው በራሱ ፈቃድ ራሱን ወደ ሌላ አካል ሊለውጥ ቢችል መለኮታዊ ችሎታን ተቀዳጀ ማለት አይደል?

ደግሞም እነዚያ የታሰሩትና የተጠበቁት ‘ወደ ሰው ክበብ’ መግባት ከቻሉ የቀሩትና ያልታሰሩት ለምን ወደዚያ ክበብ እየገቡ ቅይጦችን ማስወለድ አቆሙ? መቼም ጾታ የላቸውም እንጂ ተኮላሹ ማለት የሚቃጣቸው ሰዎች አይጠፉም። ቃልን ስንፈታ ስሜት እስከሰጠ ድረስ ሌላ ስሜት ልንፈልግለት የተገባ አይደለም። ስሜት ካልሰጠ ግን ተጠንቅቀንና ቃሉን ከቃሉ ጋር አስተያይተን ልንፈታው ይገባል።

* * * * *

10. ኔፊሊም እነማን ናቸው?

አንድ ጥያቄ ነበረኝ፤ በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ የዔናቅን ልጆች፥ አየን፤ እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ።” ዘኊልቁ 13፥33 ከጥፋት ውሃ በኋላ እንዴት ድጋሚ ልከሰቱ ቻሉ ኔፊሊሞች? በዚህ ዘመንም አሉ ማለት ነው? (አ. ዳ.)

ውድ አ. ዳ. ኔፊሊም አንድ ወገን ወይም የአንድ ኔፊሊም የሚባል ነገድ ሰዎች አይደሉም። ደግሞም በዘፍ. 6፥4 የተጻፈው፥ 'የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች ባገቡ ጊዜ ልጆችን ወለዱላቸው፤' የተባሉት ሰዎችም አይደሉም። የእግዚአብሔር ሰዎች እና የሰው ሴቶች ልጆች የተባሉትም፥ ከዚህ በፊት በተጠየቀ ጥያቄ እንደመለስኩት፥ የወደቁ መላእክትና የሰው ሴቶች ልጆች የሩካቤ ሥጋ ማድረግ ጉዳይ አይደለም። መላእክት (የወደቁትም ያልወደቁትም) መናፍስት ናቸው፤ በአካላዊ ቅርጽ ሊገለጡ ቢችሉም እንኳ አካል የላቸውም። ሥጋዊ አካል ስለሌላቸው ከሴቶች ጋር ሩካቤ ሥጋ መፈጸም አይችሉም። ደግሞም መላእክት ሊያገቡና ሊወልዱ እንደማይችሉ ጌታ በትንሣኤ አካል ስለምንገኝበት መንፈሳዊ አካል ሲናገር በግልጽ ተናግሮአል፤ በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ ኣያገቡም አይጋቡምም። ማቴ. 22፥30።

አንዳንድ ሰዎች እነዚህ የወደቁ ርኩሳት መናፍስት ናቸውና ያልተፈቀደላቸው ያደረጉና በቅጣት የሚገኙ ናቸው በማለት፣ ይሁ. 6፥ መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆአቸዋል። የሚለውን ይጠቅሳሉ። እነዚህ ከሰው ሴቶች ልጆች ጋር ግብረ ሥጋ የፈጸሙት ግዞተኞች የሆኑ መላእክት ናቸው ይላሉ። ይህ ክፍል ያንን እንድንል ፈቃድ አይሰጠንም። የራስን አለቅነት አለመጠበቅ እና ግብረ ሥጋ መፈጸም አንድ አይደሉም፤ የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

ስለ መላእክት DNA የምናውቀው ነገር ባይኖርም፥ ሲጀመርም፥ DNA እንዳላቸውና እንደሌላቸው ባናውቅም፥ ሰውና ሌሎች ፍጡራን መዳቀል እንደማይችሉ፥ ሰውና መላእክትም ሊዳቀሉ አይችሉም። እንዲህ ስለመሰለው ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኘው ፍንጭ የለም። እነዚያ ያንን ድርጊት ወይም ከሴቶች ጋር ማመንዘርን የፈጸሙት የወደቁት መላእክት ከሆኑ፥ ዛሬም የወደቁ መላእክት (አጋንንት ማለት ናቸው) ስላሉ፥ ዛሬም ያንን ያደርጋሉ፥ ወይም ቢያንስ በንድፈ አሳብ ደረጃ ያንን ማድረግ ይችላሉ ማለት ነው። ከሆነም ዛሬም የሁለቱን ዲቃላዎች መውለድ ይችላሉ ሊባል ነው። ዛሬም በየአገሩ የመላእክትና የሰዎች ቅይጦች ሊኖሩ ነው ማለት ነው። ግን ያንን መሳይ ነገር የለም። ኖረው ከነበሩ በጥፋት ውኃ ጠፍተው ነው እንዳይባል፤ ቃሉ ከጥፋት ውኃ በኋላም ተጠቅሶ ይገኛል። አንዴ ከጥፋት ውኃ በፊት፥ አንዴ ከጥፋት ውኃ በኋላ።

ወደ ኔፊሊም እና ወደ ቃሉ ትርጉም እንምጣ። ኔፊሊም እነማን ናቸው? ኔፊሊም נְפִל ንፊል ወይም נְפִיל ንፊይል፤ ግዙፍ ማለት ነው። ዛፍ የሚጥል ወይም ዛፍ ገንጣይ ማለትም ነው። እንደ ዛፍ ግዝፈት ያለ ግዝፈትን አመልካች ቃል ነው። ኔፊሊም ከጥፋት ውኃ በፊት የነበሩ ግዙፋን ሰዎች ናቸው፤ ዘፍ. 6፥4። ምድር ከተረገመች በኋላም የተፈጠረችበት ስነ ምሕዳር ገና እጅግ ያተበከለ፥ የሰውም ተክለ ሰብዕና ገና በብዙ ያልተጎዳ ነበረና የዚያ ዘመን ሰዎች በዕድሜም ብዙ መቶዎች ዓመታት ይኖሩ ነበርና በአካል የዳበሩ ግዙፋን የነበሩ ይመስላል። ኔፊሊም ማለት ያ ነው። ኔፊል ግዙፍ ማለት ነው። ኔፊሊም ግዙፋን ማለት ነው።

በኋላም እስራኤል ወደ ተስፋዋ አገር በሚሄዱበት ዘመን በአገሩ ላይ የነበሩ ግዙፋን ሰዎች ኔፊሊም ተብለዋል፤ ዘኍ. 13፥33። በዘፍ. 6፥4 የተጠቀሱት ኔፊሊም በጥቅሱ መጨረሻ ከተጻፉት፥ 'ኃያላን' ከተባሉት የተለዩ ናቸው። ከጥፋት ውኃ በኋላ የነዚህ ሰዎች መጠቀስ እነዚህ ግዙፋን ሰዎች ከጥፋት ውኃ በኋላ ከአንድ ኔፊሊም ከሚባል ነገድ ተርፈው ይኖሩ ነበር ማለት ሳይሆን ከጥፋት ውኃ በኋላም ኔፊሊም ወይም ግዙፋን ሰዎች ነበሩ ማለት ነው። ከጥፋት ውኃ የተረፉት ስምንት ሰዎች ብቻ መሆናቸውና ምድር እንደገና የተሞላችው ከሦስቱ የኖኅ ልጆች መሆኑን እናውቃለን፤ ይህ በግልጽ የተጻፈ ነው።

ጥቅሱ፥ በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ የዔናቅን ልጆች፥ አየን፤ እኛም በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ ደግሞም እኛ በዓይናቸው ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ። ይላል። ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ሲል አንድ ነገድ ወይም ወገን ያስመስለዋል። የግዙፋን ልጆች ወይም ዝርያዎች የሆኑትን ግዙፋን እንደማለት ነው። እነዚህ ግዙፋን ልዩ ወገን ሳይሆኑ የዔናቅ ልጆች ናቸው። ዔናቅ፥ עֲנָק ዓናቅ፤ (አናቂ ወይም የሚያንቅ ማለት ነው፤ የአንገት ሰንሰለት ጌጥ ማለትም ነው።) የአባቱ ስም አርባቅ የተባለ፥ ኬብሮን በተባለው ስፍራ ይኖሩ የነበሩት ራፋይም የተባሉት ቁመታቸው የረዘሙ ሰዎች ዔናቃውያን፥ የዔናቅ ልጆች አባት የሆነ ሰው ነው፤ ኢያ. 15፥13። ልጆቹ ሴሲ፥ አኪመንና ተላሚ ይባሉ ነበር፤ 15፥14።

የዔናቅ ልጆች ወይም ዔናቃውያን እስራኤል ወደ ተስፋዋ ምድር ከመግባታቸው በፊት ሰላዮችን ልከው ሳለ በምድሪቱ ካዩአቸው ግዙፋንና አስፈሪ ሰዎች መካከል ነበሩ፤ ዘኍ. 13፥22-33፤ ዘዳ. 1፥28፤ 2፥10-221፤ 9፥1-2። እስራኤል ወደ ተስፋዋ ምድር ከገቡ በኋላ ዔናቃውያንን መቱ፤ ኢያ. 11፥21-22። ይኖሩባት የነበረችው ኬብሮን ቀድሞም ለስለላ በሄዱ ጊዜ እንዝመትባቸው አንፍራቸው ያለው የካሌብ ርስት ሆና ተሰጠችው፤ ኢያ. 14፥12-15፤ 15፥13-14፤ መሳ. 1፥20።

ስለዚህ እነዚህ ኔፊሊም የዔናቅ ልጆች የሆኑ ዔናቃውያን ግዙፋን ሰዎች ናቸው።

* * * * *

11. መላእክትን መጥራትና መላክ ይቻላል ወይ?

ሰላም ዘሌ፥ አንድ ጥያቄ ነበረኝ ስለ መእክቶችና ስለ እነሱ ሥራ፤አሁን አሁን በብዛት ምንሰማው ቋንቋ ሆኖዋል። መላእክት መጥራት ይቻላል ወይ? እንደ ቡሽሪ የሚካኤል፥ የገብሬል ቀን ነውወደ ቤት፥ ወደ ቢሮ እልካለሁ፥ ሁሉን ነገር ያስተካክላሉ ይላሉ። ቸርች ውስጥም በካሜራ ተቀርጸው ይታያሉ እና የኔ ጥያቄ እንዴት ነው ይህ ነገር አንድ ዳግም የተወለደ ሰው መላእክት መጥራት ወይ መላክ ይችላል ወይ? አመሰግናለሁ። ማ.።

አጭሩና እቅጩ መልስ ፈጽሞ አይቻልም የሚል ነው።

በመጀመሪያ መላእክት ፍጡራን መሆናቸውን እንወቅ። መጠንቀቅ ያለብን አጋንንትም በፍጥረታቸው መላእክት መሆናቸውን ነው። ከመላእክት ሰይጣንን በዓመጽ ተከትለው የወደቁ አጋንንት ናቸው።

መልአክ የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን መልእክተኛ የተላከ ማለት ነው። የአዲስ ኪዳኑ መጠሪያቸውም ይህንን የተላኩ መሆንን የሚያሳይ ነው። የሚላኩ ይሁኑ እንጂ ሰዎች የሚልኳቸው ሳይሆኑ እግዚአብሔር የሚልካቸው ፍጡራን ናቸው። ስማቸው የሚያሳየውን ፍጥረታቸውን ሳይሆን ይህንን አገልግሎታቸውን ነው።

መላእክት ሥራቸው ብዙ ዓይነት ነው። በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ ውስጥ የደኅንነትም የቅጣትና የበቀልም ስፌ የሆነ ድርሻ ነበራቸው። ዘጸ. 12፥23፤ ማር. 13፥32፤ 1ቆሮ. 10፥10፤ 2ሳሙ 24፥16። በብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሱት በአብርሃም ታሪክ ነው። ከአብርሃም በኋላ ብዙ ጊዜ ደጋግመው ሲገለጡና የተለያዩ ሥራዎችን ሲፈጽሙ ይገኛሉ። ለጌዴዎን፥ ለሰምሶን ወላጆች፥ ለነቢያትም ለኤልያስ፥ ለዳንኤል፥ ለሌሎችም ተገልጠዋል። መላእክት በዚህ ዘመን አማኞችን ያገለግላሉ፤ ንስሃ በሚገባ ኃጢአተኛ ይደስታሉ፤ ዕብ. 1፥14፤ መዝ. 34፥7፤ እና 91፥11፤ ማቴ. 18፥10፤ ሐዋ. 5፥19፤ 8፥26፤ 10፥3፤ 12፥7፤ እና 27፥23። በሚመጣውም ዘመን የፍርድ አገልጋዮች ይሆናሉ፤ ማቴ 13፥39-39-49፤ 16፥27 እና 24፥31። በመጽሐፍ ቅዱስ በሱም የተጠቀሱ መላእክት ሁለት ብቻ ናቸው፤ እነርሱም፥ ሚካኤል እና ገብርኤል ናቸው። መላእክት የማይሞቱ ፍጡራን ናቸው። ሉቃ. 20፥36፤ ከሰብዓዊ ችሎታ በላይ የሆነ እውቀትና ኃይልም አላቸው። ማር. 13፥32፤ 2ተሰ 1፥7፤ መዝ. 103፥20። ሆኖም ሁሉን የሚያውቁ ሁሉን የሚችሉና በሁሉ ቦታ የሚገኙም ሳይሆኑ ውስኖች ናቸው። ሊመለኩም ከቶ አይገባም፤ ቆላ. 2፥18፤ ራእ. 19፥10።

መላእክት ከሰዎች ጋር ኖሮአቸው በሚያውቀው በመጽሐፍ ቅዱስ በተጻፉልን ታሪኮች ውስጥ ሰዎች መላእክትን ሲያነጋግሩ፥ መልእክትን ሲቀበሉ፥ መላእክት የታዘዙትን ሲፈጽሙ ሲመለከቱ ወይም የተነገራቸውን ሲያደርጉ እንጂ ሲያዝዙና ተግባር ሲያስፈጽሙ ከቶም አልተጻፈም። መላእክትን እግዚአብሔር ቅዱሳንን እንዲያገለግሉ እንዲልካቸው በቃሉ ተጽፎአል፤ በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤ መዝ. 91፥11። ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን? ዕብ. 1፥14። ቅዱሳንን ያገልግሉ እንጂ ቅዱሳንን ያገለግሉ ዘንድ የታዘዙት ከእግዚአብሔር ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድም ስፍራ ሰዎች መላእክትን በራሳቸው ወይም በእግዚአብሔር ስም ሲልኳቸው፥ ሥራ ሲያሰሯቸው፥ ሲያዝዟቸው አልተጻፈም። እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ ያላደረገውን አዲስ ነገር በኛ ዘመን ያደርጋል የሚሉ ሰዎች ሲነሡ እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስቲያኖች ማስተዋል አለብን። መላእክት ተገልጠው ያደረጉትን ባደረጉባቸው ቦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ልኳቸው እንጂ ሰዎች ጠርተዋቸው አልመጡም።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረው ይህ አሳብ ተገልብጦ ዛሬ ሰዎች መልአኬን እልካለሁ፤ ይህንን፥ ያንን ያደርጋል ሲሉ የሚደመጡ ሰዎች አሉ። መጠንቀቅና መጠበቅ ያለብን ሐሰተኞች ሰዎች የወደቁ መላእክትን ሊልኩ ስለሚችሉ ነው። መናፍስት ጠሪዎች መናፍስት ጠሪ የሚባሉት ጠሪ ስለሆኑ ነው። መናፍስቱ ከተጠሩና ተጠርተው ከመጡ ታዘዙ ማለት ነው። ርኩሳን መናፍስት የወደቁ መናፍስት ወይም መላእክት ናቸው። ለቅዱሳን በተሰጠ ስልጣንም ታዝዘው ከሰዎች ውስጥ ይወጣሉ፤ ማር. 6፥7፤ ሉቃ. 10፥17-20። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ስለሚያዝዟቸው መላእክት ሲናገር ስለ ወደቁ መላእክት ወይም መናፍስት ነው። እናዝዛለን የሚሉት ሰዎች የሚያዝዙት እነዚህን መላእክት ወይም መናፍስት ሳይሆን አይቀርም። ከሆነ እጅግ፣ እጅግ፥ እጅግ በጣም መጠንቀቅ ተገቢ ነው። እንግዲህ ሰዎች እነዚህን የወደቁ መላእክትን ላክን ወይም እንልካለን ሲሉ ወይም እውነትም ሲልኩ አንድም፥ ከቃሉ የወጣ ነገር እየፈጸሙ መሆናቸውን፥ ሁለትም፥ እነዚያ ለሰዎች ፈቃድ ታዛዥና ተገዢ የሆኑ መላእክት የሰዎች መጠቀሚያዎችና መገልገያ በመሆን ሰዎችን ለማስደነቅና ለማሳት የተላኩ መሆናቸውንም እንወቅ። ሰይጣን የብርሃን መልአክ ሊመስል ራሱን እንደሚለውጥም ተጽፎልናል፤ 2ቆሮ. 11፥14።

እኛ በክርስቶስ ያመንን ቅዱሳን ይህን መሳይ ነገር ሊያስፈራን አይገባም። በእርሱ ጥበቃ ውስጥ የምንገኝ መሆናችን እረፍታችን ነው። ሆኖም እንዲህ በመሰለ ድንቅ መታለልና መወሰድ የለብንም።

* * * * *

12. ክርስቲያን የማይሳተፍበት የንግድ ዘርፍ አለ ወይ?

ሰላም፥ በንግድ አለም ክርስቲያን የማይሳተፍበት የስራ ዘርፍ አለው ወይ ለምሳሌ አንድ አማኝ ራሱን ጠብቆ ስጋ፣ መሸጥ ጫት መነገድ ይችላል ወይ? B. T.

ውድ B. T. ፥ አዲስ ክርስቲያን ሳለሁ ይህን ጥያቄ እኔም ጠይቄ ነበር። ያኔ ጉዳዩ አጠያያቂም አልነበረም፤ ግን የሙያ ግብረ ገብነት ጉዳይ ላይ ነው ጥያቄው የተነሣው። በጊዜው ደግሞ አንድ መጽሐፍ እጄ ውስጥ ገባ። In His Steps ይባላል። ሙሉ ርእሱ፥ In His Steps: What Would Jesus Do? ይባላል፤ ኋላ በጣም የተለመደው፥ What Would Jesus Do? ወይም፥ WWJD የተባለው አጽሕሮተ ቃል የተገኘው ከዚያ ነው። መጽሐፉ መጀመሪያ የታተመው በ19ኛው ምእት ዓመት መጨረሻ ሆኖ በእጅግ ብዙ ቁጥር የታተመ ልብ ወለድ መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ሴራ መንደርደሪያ በከተማዋ (ከተማዋ ሬይመንድ ትባላለች) በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ የሆነው ማክስዌል የተባለ መጋቢ የቤተ ክርስቲያኒቱን ምእመናን አንድ ነገር ይጠይቃል፤ ያም፥ ‘ለአንድ ዓመት ሙሉ፥ ‘ኢየሱስ በኔ ቦታ ቢሆን ኖሮ ምን

ያደርግ ነበር?’ (WWJD) ሳንል ምንም ነገር እንዳናደርግ ቃል እንግባ።’ የሚል ነው። ሰዎቹም ያንን አደረጉ። በውጤቱ ታላቅ የሆነ መንፈሳዊ መነቃቃት ሆነ። ከተደረጉት ነገሮች መካከል የንግድ እንቅስቃሴን መልክ የቀየረ ጉዳይ ነው። ‘ኢየሱስ በኔ ቦታ ቢሆን፥ አልኮሆል ይሸጥ ነበር?’ ‘ኢየሱስ በእኔ ቦታ ቢሆን እንዲህ ያሉ መጽሔቶች ያትም ነበር?’ ወዘተ፥ የሚሉት ጥያቄዎች ብዙ ንግዶች እንዲዘግጉና ብዙዎችም በጽድቅ እንዲነግዱ አደረጋቸው። የመንፈሳዊው መነቃቃት መነሻ ይህ ነው። ነገሩ ልብ ወለድ ቢሆንም እውነታውም ከዚህ የራቀ አይደለም።

ጥያቄህ፥ ክርስቲያን የማይሳተፍበት የሥራ ዘርፍ መኖሩን ይመለከታል። ሥራ ሁሉ የጽድቅ መድረክ ነው ማለት አይደለም። ኃጢአት የሚከናወንባቸውና የሚተላለፍባቸው ሥራዎች መኖራቸው ገሃድ ነው። ያንተ ጥያቄ በተለይ፥ አንድ አማኝ ራሱን ጠብቆ ሲጋራ ወይም ጫት መሸጥ ይችላል ወይ የሚል ነው።

ከአንድ ክፍለ ምንባብ ልንደርደር፤ ትንቢተ ሐጌ 2፥11-14 እንዲህ ይላል፤

የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ካህናቱን ስለ ሕጉ ጠይቅ፤ አንድ ሰው የተቀደሰ ሥጋ በልብሱ ዘርፍ ቢይዝ፥ በዘርፉም እንጀራ ወይም ወጥ፥ ወይም የወይን ጠጅ፥ ወይም ዘይት፥ ወይም ማናቸውም መብል ቢነካ ያ የተነካው በውኑ ይቀደሳልን? ብለህ ካህናቱን ጠይቃቸው፤ ካህናቱም፦ አይሆንም ብለው መለሱ። ሐጌም፦ በሬሳ የረከሰ ሰው ከእነዚህ አንዱን ቢነካ ያ የተነካው በውኑ ይረክሳልን? አለ። ካህናቱም፦ አዎን ይረክሳል ብለው መለሱ። ሐጌም መልሶ እንዲህ አለ፦ ይህ ሕዝብና ይህ ወገን በፊቴ እንዲሁ ነው፥ ይላል እግዚአብሔር፤ የእጃቸውም ሥራ ሁሉ እንዲሁ ነው፤ በዚያም ያቀረቡት ነገር ርኩስ ነው።

በዚህ ክፍል የሐጌ ቃል ጽድቅና ቅድስና ሳይሆን ርኵሰት ግን በንክኪ ተላላፊ መሆኑን ነው። ርኵሰት የሚነካውን ሁሉ ያረክሳል። ኃጢአት ይቅርና በድርጊት፥ በንክኪና በማስተላለፍ፥ በአሳብና በኅሊናም ያረክሳል። አንድ ሰው ጫት አይቅምም። የማይቅምበት በቂ ምክንያት አለው። ያ ምክንያቱ ለራሱ አሳማኝ ምክንያት ነው። ሆኖም ያ ምክንያቱ ለሌሎች ቅድስና ምክንያት ካልሆነ በሁለት ሚዛን ጉዳዩን እየመዘነ ነው ማለት ነው። ለራሱ በአንድ ሚዛን፥ ለሌላው በሌላ ሚዛን። ሁለት ሚዛን ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው። ምሳ. 20፥10 እና 23። የዚህ አስጸያፊነት በሁለቱም በኩል ነው፤ ለሌላ ሲያደሉም፤ ለራስ ሲያደሉም። እንዲህ ያለ ሰው ለራሱ ሊደረግ የማይፈልገውን በሌላ ያደርጋል፤ ወይም በራሱ ሊደረግ የሚፈልገስን ነገር ለሌላ እንዳይደረግ ይፈልጋል። ይህ ደግሞ ወርቃማው ሕግ የተባለውን መጻረር ነው፤ ማቴ. 7፥12።

አንድ ሰው ባያመነዝርና ሴትኛ አዳሪዎችን አከራይ ቢሆን ንጽሕናው በምን መለኪያ ነው የሚለከካው? ለመሆኑ በሥጋው የሚያመነዝርና በልቡ የሚያመነዝር በጌታ ፊት ልይነት አላቸውን? አንድ ሰው ሲጋራ መሸጡ አዋጪ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ንግዶች አንዳንድ ቅመሞች ከሌሉባቸው ሙቀታቸውና እንቅስቃሴአቸው የተገታና የታገተ ነው። አንድ ሰው ጫት የማይቅም ከሆነና ሌሎች እንዲቅሙ የሚያበረታታ

ወይም የመቃማቸው ሰንሰለት አንድ ቀለበት ከሆነ የሂደቱ ተካፋይ ነው። በሕግ ፊት ወንጀለኛም የወንጀል ተባባሪም ወንጀለኞች ናቸው።

በልዝብ ክርስትና ሰርቆና አጭበርብሮ፥ ወይም ጫትና ትንባሆ ሸጦ አሥራት መስጠት የተለመደ ሊሆን ይችላል። የተለመደ ነው ማለት ግን በጽድቅ የሆነ ተግባር ነው ማለት አይደለም። አንድ ጊዜ ከአባቴ እርሻ አንድ ማሳ የሚያህል ቦታ ቆርሼ ጫት ተክዬበት ነበር። በቀጣዩ ዓመት ጌታን ተቀብዬ ክርስቲያን ሆንኩ። ይህ እርሻ ትክክል አለመሆኑን የነገረኝ ባይኖርም አውቄው ነበርና አንድ ቀን መቁረጫና መመንጠሪያ መሣሪያ ይዤ በተከልኩበት እጄ ከስሩ እየነቀልኩ እመሃል ላይ ከምሬ አቃጠልኩት። እንደ ሞኝ ተቆጥሬ ነበር። ‘አንተ ባትቅም ጥቅም የሚሰጥ፥ ገቢ የሚያመጣ ስለሆነ ሌላው ቢቅምስ? ለምን ነቃቅለህ መጣል አስፈለገህ?’ ተብዬ ነበር። ነገር ግን ሳላውቅ፥ ለካስ፥ ይህን ያዩና ይታዘቡ የነበሩ ሰዎች ነበሩ። ኋላ እነሱም ክርስቲያን ሲሆኑ ወጉ እንደዚያ ስለመሰላቸው በየተራ ነቅለው ማቃጠል ጀመሩ። እንዲያውም እንደ ደንብ ተወሰደ። ይህን የአካባቢው ክርስቲያኖች በኋላ ነው የነገሩኝ።

ክርስቲያን የማይሳተፍበት የሥራ ዘርፍ አለ ወይ? አዎን፤ አለ። ጌታ የማይከብርበት፤ ቅዱሳን የማይታነጹበት፤ ሰዎች በአካል፥ በአእምሮ፥ በስሜት፥ በሕሊና የሚጠቁበትና የሚጎድዱበት ማናቸውም የሥራ ዘርፍ ክርስቲያን ሊሳተፍበት የተገባ አይደለም። ጫትና ሲጋራም ከዚህ ምድብ ውስጥ ናቸው። ገንዘብ ስላስገኘ ብቻ አይነገድም። በጽድቅ ይነገዳል።

* * * * *

13. መልከ ጼዴቅ ማን ነው?

> መልከ ጼደቅ ማን ነው? የተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትርጉም ይሰጡታልና አንዳንዱም ከሌላው ጋር በጣም የተጋጨ ነው። ማን ነው ይህ ሰው?

በዘመናችን ሰዎች ማን እንደሆነ ይሉታል? ይህ ሰው የተጠቀሰባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፤ ዘፍ. 14፥18-20፤ መዝ. 110፥4፤ ዕብ. 5፥6-10፤ እና ዕብ. 7 በሙሉ ናቸው።

የመጀመሪያ አጠቃቀስ ስልትን (አንድ ገጸ ባህርይ ወይም ታሪክ በመጀመሪያ የተጠቀሰበትን ስፍራ) በመከተል ይህ ሰው ማን መሆኑን እንመልከት። ሌሎች ክፍሎች ስለዚህ ሰው ይናገራሉ፤ ግን ሌሎች ክፍሎች እንደሌሉ በመገመት ይህን ሰው መጀመሪያ በተጠቀሰበት ስፍራ ብንመለከተው ማን ስለመሆኑ ምን እናገኛለን?

ይህ ሰው ሁለት ነገሮች ነው፤ ንጉሥም ነው ካህንም ነው። <u>በንጉሥነቱ</u> የሳሌም ንጉሥ ነው። ሳሌም የሚለው ቃል በሌላ ስፍራ በመዝ. 76፥2 ተጠቅሶአል። በዮሐ. 3፥23ም ተጠቅሶአል ግን ሳሊም ያሰኘዋል ግሪኩ፤ ብዙ ትርጉሞችም ያንን ይከተላሉ። ሆኖም አካባቢው በዚያው በኢየሩሳሌም ነው። ሳሌም ኋላ ኢየሩሳሌም የተሠራችበት ስፍራ

ነው። ሳሌም ማለት ሰላም ማለት ሲሆን ኢየሩሳሌም የሰላም መንደር ወይም ከተማ ማለት ነው። በክህነቱ ደግሞ የልዑል እግዚአብሔር ካህን ተብሎአል። ጥንት ነገሥታት እንደ ነገሥታትም፥ እንደ ከፎል ወይም ሙሉ አማልክትም፥ እንደ ካህናትም ወይም ከነዚህ ከፊሉን አጣምረው በመያዝ ይመሩ ነበር። ይህ የተለመደ ነገር ነው።

ስሙ መልከ ጼዴቅ ነው። የጽድቅ ንጉሥ ማለት ነው። ይህ በዚያን ዘመንም ያልተለመደ ስም አይደለም። ለምሳሌ በኢያ. 10፥1-3 አዶኒጼዴቅ የተባለ በኢያሱ ዘመን የነበረ የኢየሩሳሌም ንጉሥ እናገኛለን። የስሙ ትርጉም የጽድቅ ጌታ ማለት ነው፤ ግን ኋላ ተሰቅለው ከተገደሉቱ 5 ነገሥታት አንዱ ሆነ።

ከዘፍ. 14፥17-18 እንደምንመለከተው ሁለቱ ነገሥታት የሰዶምና የሳሌም ነገሥታት ብቻ ሆነው ይታያሉ። ሁለቱም አብራምን ሊቀበሉ ወጥተዋል። ሁለቱም ከምርኮው ተቀብለዋል። መልከ ጼዴቅ አሥራት ሲቀበል ባላ ደግሞ በምርኮ የተወሰደበትን ተመልሶለት ተቀብለዋል። ባላ ሎጥ ይኖርበት የነበረው የሰዶም ንጉሥ ሲሆን መልከ ጼዴቅ ደግሞ አብርሃም ይኖርበት የነበረው አካባቢ ንጉሥ ይመስላል። ስለዚህ በመንግሥቱ ውስጥ ከሚኖረው አሥራት ተቀበለ። ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚህ በኋላ በቀጥታ ይህን ሰው ወይም ትውልዱን በተመለከተ የምናገኘው ነገር የለም። ይህ ሰው መጀመሪያ ከተጠቀሰበት ስፍራ ልናገኝ የምንችለው ይህንን ብቻ ነው።

ይህ መልከ ጼዴቅ የተጠቀሰባቸው ሌሎች ሁለት ቦታዎች አሉ። አንዱ መዝሙረ ዳዊት ሲሆን ሁለተኛው በአዲስ ኪዳን የሚገኘው የዕብራውያን መጽሐፍ ነው። በመዝሙረ ዳዊት የተጠቀሰው በመዝ. 110 ነው። ይህ መዝሙር መሢሐዊ ወይም ስለ መሢሑ የተነገረ ትንቢታዊ መዝሙር ነው። የመሢሑን ድርብ ሹመት፥ ንጉሥነቱንና ክህነቱን የሚናገር ነው። በዚህ በዳዊት ዘመን ካህናት አሉ፤ እነርሱም ከመጀመሪያም ሲያገለግሉ የኖሩት የሌዊ ልጆች ናቸው። ከሌላ ነገድ ካህን የሚሆን ወይም ሊሆን የሚችል ሰው የለም። እንዲህ የሚያደርግ ከኖረ ሌላ ሥርዓት፥ ሌላ መልከ ወይም ዓይነት፥ ሌላ ሁኔታ፥ ሌላ ደንብ መኖር አለበት። እንደ መልከ ጸዴቅ ሥርዓት የተባለው ይህ ነው።

አሁንም መዝ. 110 ይህን ከማለት ሌላ ብዙም አይፈታልንም። ግን ሌላ ሥርዓት መኖሩን፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ሌላ ካህን የሚነሣበት ሁኔታ መኖሩን ያመለክታል። እንዴ ሌላ ሥርዓት ካህን የሚሆን እንደሚመጣ ይተነብያል። በዓይነቱና በሥርዓቱ ሌላ የሆነ ክህነት እንደሚኖር ብቻ ሳይሆን ይህ ካህን ካህን ብቻ ሳይሆን ገዢ ወይም ንጉሥም እንደሚሆን ይናገራል።

መልከ ጼዴቅ ቀጥሎ የተጻፈበት ስፍራ የአዲስ ኪዳኑ የዕብራውያን መልእክት ነው። ዕብ. 5-7ን ከመመልከታችን በፊት በመጀመሪያ መልእክቱ ለማንና ለምን እንደተጻፈ ማስተዋል ያስፈልጋል። ይህ መልእክት እንደ እግዚአብሔር ቃልነቱ ለኛም ጭምር የተጻፈ ቢሆንም የመጀመሪያዎቹ ተቀባዮች እኛ ሳንሆን በተለይ የተጻፈላቸው ዕብራውያን ወይም አይሁድ ክርስቲያኖች ናቸው። እነዚህ አይሁድ ክርስቲያኖች ጌታን፥ መሢሁን ተቀብለው መከተል ከጀመሩ በኋላ በስደትና በሌሎችም ጫናዎች

ወደ ቀድሞ ሃይማኖታቸው ወደ ይሁዲነት፥ ወደ ብሉይ ኪዳንና ወደ ሥርዓቶቹ ሁሉ ጥበቃ እየተመለሱ ያሉ ሰዎች ሆነዋል።

እነዚህ ዕብራውያን በሦስት ቡድን ሊከፈሉ ይችላሉ። ሀ. በእምነት የጸኑ፤ ለ. የሚወላውሉ፥ የሚያመነቱና የሚያፈገፍጉ፤ ሐ. በቂ እውቀት ያገኙና ግን የካዱ ናቸው። በየትኛው ክፍል ስለ የትኛው እየተናገረ መሆኑ ይታያል፤ ይህንንም ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

የመልእክቱ ዋና ጭብጥ የክርስቶስ <u>መሻል እና በላጭነት</u> ነው። ለአይሁድ ንጽጽሩ እኛ በአዲስ ኪዳን ውስጥ፡ያለን ክርስቲያኖች ‘ብሉይ ኪዳን’ ከምንለው ኪዳን ጋር ነው። የበለጠ፥ የተሻለ፥ እና ይልቅ የሚሉት ቃላት ይህን ያሳዩናል። ለምሳሌ፥ ስሙ ከመላእክት ስም እርሱም ከመላእክት ሙበለጡ (ምዕ. 1)፥ ከሙሴ ክብር የሚበልጥ ክብር የተገባው መሆኑ (3፥3)፥ ተስፋው ከሕጉ መሻሉ (7፥18-19)፥ በኢየሱስ የሚሻል ኪዳን ዋስትና መኖሩ (7፥22)፤ በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ቃል የተሻለ አገልግሎት ማግኘቱ (8፥6)፥ ደሙ ከሌሎች ደሞች ይልቅ ኀሊናንም የሚያነጻ ነው (9፥14)፥ መስዋዕቱ ወይም መስዋዕትነቱ የሚበልጥ መሆኑ (9፥23) ተጽፈዋል። እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፤ 8፥6፤ 9፥15፤ 12፥24። (በተጨማሪ ቃሉ የተጻፈው በገላ. 3፥19-20 እና 1ጢሞ. 2፥5 ነው። ገላ ሕጉ ስለተጨመረበት ስለ መላእክት ሲናገር ጢሞቴዎስ ውስጥ ደግሞ ስለ ክርስቶስ ይናገራል)።

ዕብ. 5 ውስጥ ጸሐፊው ስለ መልከ ጼዴቅ ማብራራት ይጀምርና መልእክቱ የተጻፈላቸው ሰዎች ገና ያልበሰሉ መሆናቸውን በመውቀስ ስለ እድገት ይናገራል። “እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት” የሚለው ቃል ግብዓት እዚህ ነው። በምዕ. 6 ወቀሣውንና ማስጠንቀቂያውን ከተናገረ በኋላ መልከ ጼዴቃዊ ክህነቱን በማብራራት ወደ ምዕ. 7 ይሻገራል። በዚህ ክፍል ደጋግሞት በመጥቀሱም ማብራሪያውን መልከ ጼዴቅ መጀመሪያ ከተጠቀሰበት ከዘፍ. 14 በመውሰድ ይተነትናል።

በመግቢያው ላይ ይህ ሰው ማን እንደሚባል ግምቶችን በመውሰድ ጀምረን ነበር። ኃይለ ሥላሴ የሚሉት ራስታዎች ናቸው። ሴም የሚሉትም ይህን የአዳም ልጅ ዕድሜውን አስልተው በዚያን ዘመንም እንደነበረ በመቁጠር ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት ነው። ዋናዎቹ እጩዎች ኢየሱስ እና ማንነቱ በዝርዝር ያልታወቀ ንጉሥና ካህን የነበረ ሰው የሚሉት ናቸው። የኔ መረዳት ይህ ሰው ኢየሱስ ሳይሆን በአብርሃም ዘመን የነበረ ንጉሥና ካህን የሆነ ሰው ነው የሚል ነው። ይህ ከሆነ ክርስቶስ ነው ለሚያሰኙ ወይም ለሚያስመስሉ ነጥቦች ማብራሪያ ልስጥ።

በዚህ ክፍል መልከ ጼዴቅን ዘላለማዊ የሚያስመስሉ ነጥቦች በቁጥር 3 ላይ ይገኛሉ። አባትና እናት የሌለው፥ የትውልድ ቁጥር የሌለው፥ እና ለዘመኑ ጥንትና ለሕይወቱም ፍጻሜ የሌለው መሆኑ ናቸው። *ቃሉ፥ አባትና እናት የትውልድም ቍጥር የሉትም፥ ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል* ይላል።

ሀ. አባትና እናት የሉትም ሲል ያለ አባትና እናት የተገኘ መሆኑን ሳይሆን በስፍራው ወላጆቹ አለመጠቀሳቸውን ነው። ይህ ሰው የትውልድ ቁጥርም የለውም። የትውልድ

ቋጥር የትውልድ ሐረግ ነው። ኋላ በመጣው በሙሴ በተሰጠው ሕግ ካህን የሚሆን የአንድ ነገድ ወገን፥ ማለትም የሌ ልጅነት ነው። ለክህነት ከዚህ ነገድ መሆንና ትውልድን ማረጋገጥ ግዴታ ሆኖአል፤ (ለምሳሌ፥ በዕዝ. 2፥62-63 እና ነህ. 7፥61-65 ከዚህ ነገድ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያልቻሉ ከክህነት ታግደው ነበር)። መልከ ጼዴቅ ግን ያለ ትውልድ ሐረግም፥ ከሌዋዊ ክህነት አስቀድሞም ካህን ሆኖ ተገኝቶአል። ይህ ሰው ድንገት ብቅ ያለ ሰው ነው። የዘፍጥረት መጽሐፍ ደግሞ የትውልዶች መጽሐፍም ነው። እገሌ እገሌን ወለደ እያለ ከአዳም የጀመረ መጽሐፍም ነው። የአብርሃም ትውልድ ተጽፎ የዚህ ከአብርሃም የሚበልጠው ሰው ትውልድ ግን አልተጻፈም። አለመጻፉ የዘላለማዊነት ምሳሌ አድርጎታል።

ለ. የዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል የሚለውን ሐረግ በቀረቤታ እንይ። ዘላለማዊ የሚለው የአዲስ ኪዳን ቃል በብዙ ቦታዎች ዘላለም የተሰኘው ቃል (አዮኒዎስ) ሳይሆን ቀጣይ (ዲዬኔኬስ) የሚል ነው። የዚህ ሰው ክህነት ከዚያ በኋላ ሲቀጥል ግን አይታይም። ኋላ ሌላ ነገድ ነው ካህን የሆነው።

ሌላው፥ *በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል* በሚለው ውስጥ ያለው 'ተመስሎ' የሚል ቃል ነው። ይህ ሰው ክርስቶስ ነው ከተባለ ክርስቶስ በክርስቶስ ተመስሎ ማለት ይሆናልና ይጋጫል። የተመሰለው ደግሞ ማን ነው? የተመሰለው ክርስቶስ ሳይሆን መልከ ጼዴቅ ነው። እርሱ የተመሰለው ከሆነ የተመሰለበት ሌላ አለ ማለት ነው። ቅጅ ከኖረ ዋና ወይም ኮፒ ከኖረ ኦርጂናሌ እንደሚኖር ማለት ነው። መልከ ጼዴቅ ኮፒ ከሆነ ውዋናው ማን ነው? ይህ የጥላና የአካል ግንኙነት ዓይነት ነው። ጥላው አንዱ አካሉ ሌላው ነው። ጥላው ጥላውንም አካሉንም መሆን አይችልም። ስለዚህ መልከ ጼዴቅና ክርስቶስ አንድ አይደሉም። ደግሞም፥ በቁ. 15-16 ላይ 'ሌላ' *ሌላ ካህን በመልከ ጼዴቅ ምሳሌ ቢነሳ* ይላል። ይህ 'ሌላ' የሚል ቃል መልከ ጼዴቅ ሌላ፥ ክርስቶስም ሌላ መሆናቸውን ያሳያል።

የምንባቡ ዋና ነጥብ ኢየሱስ ካህን ለመሆን ሌዋዊ መሆን፥ ሊቀ ካህናት ለመሆን ደግሞ አሮናዊ መሆን አለበት። ከዚህ ውጪ በአይሁድ ሕግ ክህነትና ሊቀ ክህነት የለም። ክርስቶስ ከይሁዳ ነገድ ነው። ከይሁዳ ነገድ በመሆኑ ከነገሥታት ዘር ሆኖ ንጉሥ ነው። መልከ ጼዴቅም ንጉሥ ነበር። ጌታ ከሌዊ ነገድ ሳይሆን ደግሞ ካህንም ሆኖአል። መልከ ጼዴቅም ከራሱ ከሌዊ ቅድመ አያትም አሥራትን የተቀበለ ካህን ነው። መመሳሰላቸው ይታያል።

መልከ ጼዴቅ ክርስቶስ ቢሆን ኖሮ የዕብራውያን ጸሐፊ ወይም ዳዊት በመዝሙሩ ውስጥ፥ 'አንተ መልከ ጼዴቅ ነህና' ባሉ ነበር። ነገር ግን እነዚህ እንደ፥ ሌላ፥ ተመስሎ፥ ምሳሌ፥ የሚሉት ቃላት ሁለቱ አንድ ያለመሆናቸውንን ነገር ግን የሚመሳሰሉና የሚነጻጸሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ። መዝ. 110 እንደ በማለት ያነጻጽራል። ንጽጽሩ ሹመቱ መሆኑ ይስተዋላል።

ሌዋውያን ካህናትና አሮናውያን ሊቃነ ካህናት በሁሉ ውሱኖች ናቸው። ሌዋውያን አገልግሎት የሚጀምሩት በ30 ዓመት ሆኖ 50 ሲሆኑ ማገልገል ያቆማሉ (ዘሌ. 4)። ስለዚህ አገልግሎታቸው ቢበዛ 20 ዓመት ብቻ ነው። ሊቀ ካህናት ደግሞ እስኪሞት

ያገለግላል፤ ይሁን እንጂ ይሞታል። ለዘላለም እንዳያገለግል ሞት ያግደዋል፤ ዕብ. 7፥ 23። ደግሞም ፈጽሞ የማያነጹ ወይም አንጽተው የማይፈጽሙ መስዋዕቶች ሲያቀርቡ ይኖሩ ነበር። ክርስቶስ ግን ራሱን አንድ ጊዜ ብቻ ፈጽሞ አቀረበ። ደግሞም ለዘላለም የሚኖርና የማይሻር የማይለወጥ ክህነት ይዞአል። ይህ የሊቀ ካህናት አገልግሎት አሳብ ወደ ምዕ. 8ም የተሻገረ ነው። በምዕ. 8 ሊቀ ክህነቱን ብቻ ሳይሆን ኪዳኑንም በማነጻጸር አዲሱ ከአሮጌው መሻሉን ያሳያል።

የመልከ ጼዴቅ ክህነት በሕጉ ያልተዘጋጀ ብቻ ሳይሆን ከሕጉ በፊትም የነበረ ክህነት ነው። ካህን ለመሆን ዝርያውን ማቅረብ ያላስፈለገው ካህን ነው። ይህ አላገደውም። ደግሞም ካህንም ሆኖ ንጉሥም ነው። የሳሌም ንጉሥ። ሳሌም ኋላ ኢየሩሳሌም የተባለችው ናት፤ ሳሌም ማለት ሰላም ማለት ነውና የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ማለት ነው። ክርስቶስም የሰላም አለቃ ተብሎአል። መልከ ጼዴቅ ማለት የጽድቅ ንጉሥ ማለት ነው። ክርስቶስም በጽድቅ የሚፈርድ፥ ጻድቅ ፈራጅ ነው። መልከ ጼዴቅ የትውልድ ቁጥር የለውም፤ በድንገት ብቅ ብሎ በዚያው የጠፋ ነው። ወላጆች የሌሉት ሳይሆን ወላጆቹም ሆኑ ዘሩ ያልተጻፈ ነው። ይህ እንዲሆን እንዲጻፍ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው። በኋላ ይህንኑ መቼና ለምን እንደሚያነሣው ያውቅ ስለነበረ እንደዚያ ተቀንጭቦ ብቻ እንዲታይና የዘላለማዊ ክህነት ምሳሌ እንዲሆን ያደረገ ይመስላል።

ሲጠቃለል መልከ ጼዴቅ በአብርሃም ዘመን የነበረ፥ የኖረ፥ ሳሌም የምትባል ኢየሩሳሌምን የሆነች ከተማ/አገር ንጉሥ ነው። ከአብርሃም ይበልጣል። ሌዋዊነት የለውም። ይህ ሰው ንጉሥ ብቻ ሳይሆን ካህንም ነው። ክህነቱ በሰው የተሾመ ሳይሆን የማንነት ክህነት ነው፤ ከእግዚአብሔር ነው። ከሕጉ በፊት ነበረና በሕግ ሥርዓት ያልሆነ ካህን ነው። በዚህም የመሢሕ ምሳሌ ነው።

* * * * *

14. ልሳን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ነው?

ልሳኖች መናገር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ነው ወይ? ሙላትና ልሳን ጎፈርና ዘውድ ናቸው? (ኢ. አ.)

የዘመናዊው ጴንጤቆስጣዊ ልምምድ አንድ ዋናና ብቸኛ መታወቂያ ተደርጎ የሚወሰደው በልሳን መናገር በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ምልክት ተደርጎ መወሰዱ ነው። ብዙ ጊዜ ይህንን አሳብ ደጋግሞ ከመስማትና ከድግግሞሹና ከሰዎች ልምምዶች የተነሣ እንደ እውነት የተቀበሉ ብዙዎች ናቸው። እንደ ቃሉ አክባሪ ክርስቲያኖች መጠየቅ ያለብን፥ እኛን ሊመራን የተገባው የሰዎች ልምምድ ነው ወይስ ቃሉ የሚለው ትምህርት ነው ብለን መሆን አለበት። አንዳንድ ሰዎች ከልምምዳቸው በኋላ የቃሉን

እውነት ከተረዱ በኋላም እንኳ ሊታረሙ አይወድዱም። ልምምዳቸው ከቃሉ ስለሚበልጥባቸው።

1ቆሮ. 12፥30 ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ይላል። የዚህ ጥያቄ መልስ በጥያቄው ውስጥ የተቋጠረና ግልጽ ነው። እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች በሰዋሰው መልሳቸው ግልጽ የሆኑ rhetoric questions ይባላሉ። የጥያቄው መልስ ግልጽ ነው፤ ሁሉ በልሳኖች አይናገሩም። ሁሉም አይተረጉሙም። ቢያንስ የማይናገሩ መኖራቸው ግልጽ ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ወይም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ከሆነ ኤፌ. 5፥17-18 ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ ይላል። ይህ ለጥቂቶች ተመርጦ የተሰጠ ሳይሆን ጠቅላላ ትእዛዝ ነው። ቅዱሳን ሁሉ በመንፈስ እንዲሞሉ ወይም በእርሱ ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ የጌታ ፈቃድ ሲሆን ሁሉ በልሳኖች መናገራቸው ግን ብቸኛ ምልክቱ ተደርጎ መወሰዱ ስሕተት ነው።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በአዲስ ኪዳን ውስጥ አሥራ አራት ጊዜ ተጠቅሶአል። ከእነዚህ ከአሥራ አራቱ በስንቱ ውስጥ ልሳን እንዳለ ማየቱ ሙላትና በልሳን መናገር ምን ያህል የተቆራኙ እንደሆኑ ያስተምረናል። ሁሉንም በቅደም ተከተል እንያቸው። ከእነዚህ አሥራ አራት ክፍሎች አንዳንዶቹ ክስተቶችን (የሆኑ፥ የተፈጸሙ ድርጊቶችን) የሚያሳዩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከድርጊት ይልቅ ሁኔታን ያመለክታሉ።

1. ሉቃ. 1፥15 በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤ ይላል። ይህ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ለአባቱ ለዘካርያስ የተነገረው ነው። ይህ መቼ እንደተፈጸመ አናውቅም። ምናልባት ይህ የተፈጸመው ማርያም ኤልሳቤጥን በጎበኘቻትና እርስዋ ራስዋም በመንፈስ ቅዱስ በተሞላች ጊዜ ሳይሆን አይቀርም። ሙላት አለ፤ በልሳን መናገር ግን የለም።

2. ሉቃ. 1፥41 ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች፦ . . . ። ይህ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እናት ስለ ኤልሳቤጥ የተነገረ ነው። የጌታን እናት ማርያምን ሰላምታ ድምጽ በሰማች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሞላባት። በታላቅ ድምጽም ጮኻ ከቁ. 42-45 ያለውን ቃል ተናገረች። የተናገረችው በግልጽ ተጽፎልናልና በምታውቀው ቋንቋዋ ነው የተናገረችው። ሙላት አለ፤ በልሳን መናገር ግን የለም።

3. ሉቃ. 1፥67 አባቱ ዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ እንዲህም አለ፦ . . . ይህ በዚህ በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ የተነገረለት የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስ ነው። ዘካርያስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ትንቢት ተናገረ። የተናገረው ትንቢትም ከቁ. 68-79 ተጽፎአል። በዘካርያስ ሕይወትም ሙላት አለ፤ በልሳን መናገር ግን የለም።

4. ሉቃ. 4፥1 ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ ተመለሰ፥ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ፥ አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ። ይህ ስለ ጌታ የሚናገር ሲሆን ፍጹም መለኮት ሳለ ሥጋን በመልበሱ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሆኖ ስለመመላለሱ የሚያሳይ ነው። ጌታ በልሳን ስለመናገሩ አንዴም አልተጠቀሰም። ሙላት አለ፤ በልሳን መናገር ግን የለም።

5. ሐዋ. 2፥4 በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። እዚህ የምንመለከተው ጌታ እንደሰጠው የተስፋ ቃል፥ መንፈስ ቅዱስ በይፋ ሲወርድ ነው። የተስፋው ቃል በሉቃ. 3፥16፤ 24፥ 49፤ ሐዋ. 1፥8 የተነገረው ነው። በተጨማሪም በኢዩ. 2፥28-29 የተነገረው ትንቢት ከፊል ፍጻሜም ነው። በዚህ ክፍል በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለ፤ በልሳኖች መናገርም አለ። የተነገረው ልሳን ግን ልሳን ነው። ልሳን ማለት መላስ ማለት ሆኖ ቋንቋ ማለት ነው። ስለ ልሳኑ ወይም ስለ ቋንቋው ሲያብራራ፥ ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር የሚሉትን አጡ። ተገርመውም ተደንቀውም እንዲህ አሉ፡- እነሆ፥ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን? ብሎ የቋንቋዎቹን ብዛት ከዘረዘረ በኋላ፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን። ይላል። በልሳኖቻችን። እነዚህ ቋንቋዎች ወይም ልሳኖች በዓለ ኀምሳን ለማክበር በመጡት 15 ያህል የተጠቀሱ ሕዝቦች ቋንቋዎች ናቸው። የገዛ ቋንቋቸው የሚል ቃል ሁለቴ መጠቀሱ 120 የሚያህሉቱ የጌታ ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት የተናገሩባቸው ልሳናት በሰዎቹ ቋንቋ እንጂ የማይታወቅ ልሳን አለመሆኑን ያስረግጣል።

6. ሐዋ. 4፥8 በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ እንዲህ አላቸው፡- ይልና የተናገረውን ፍሬ ነገር ስናጤን ድውዩ የተፈወሰው በኢየሱስ ስም መሆኑንና ከዚህ ስም ውጪ ምንም መዳን አለመኖሩን ነው በድፍረት ሊያስረዳቸው ለመቱት ለካህናት አለቆች፥ ለሰዱቃውያንና ለመቅደስ አዛዥ የተናገረው። ቀደም ሲል ባየነው በሐዋ. 2 ታሪክ ውስጥ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉትና በልሳን ከተናገሩት መካከል እንደሚገኝ የሚታመን ነው። እዚህ በድጋሚ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ መባሉ የሚያሳየው ጉልህ እውነት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት የአንድ ጊዜ የማያዳግም ልምምድ ሳይሆን ተደጋጋሚና ቀጣይ ሂደት መሆኑን ነው። እዚህም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ሲኖር ልሳን ግን የለም።

7. ሐዋ. 4፥31 ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ። ይህ እነ ጴጥሮስ ተፈትተው ወደ ወገኖቻቸው መጥተው የሆነውን ነገር ከነገሩአቸው በኋላ የሆነው ነገር ነው። የተለየው ክስተት የተሰበሰቡበት ስፍራ መናወጥ ሲሆን የተሞሉት ሁሉም ናቸው። ከተሞሉ በኋላ የሆነው ደግሞ ቃሉን በግልጥ መናገራቸው ነው። ቃሉን በግልጥ የሚናገሩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች ናቸው። እዚህም ሙላት አለ ልሳን የለም።

8. ሐዋ. 6፥3-8 ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን። ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ። ከዚህ ክፍል የምናገኘው በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ መሆን አገልጋዮችን ለመምረጥ መስፈርት ሆኖ መቅረቡን ነው። የመንፈስ ሙላት እዚህ የተጠቀሰው ወይም መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸው እና የሞላበት የሚሉት ሐረጎች አጠቃቀስ እንደ አንዲት ጊዜ ክስተት ሆኖ ሳይሆን ነዋሪ ሁኔታን በሚያሳይ መልኩ ነው። ይህም በባህርይ የሚገለጥ ማንነት ነው። ክስተት አይደለም ስል እዚህ የሚታየው ዲያቆናቱ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ሳይሆን ቀድሞውኑ የተሞሉ መሆናቸው የታወቀ፥ የተመሰከረለት መሆኑ ተረጋግጦ ነው ሐዋርያቱ ጸልየው እጅ ጭነው የሾሙአቸው።

9. ሐዋ. 7፥55-56 መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፦ እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ። እነዚህ እስጢፋኖስ ከመሞቱ በፊት የተናገራቸው የመጨረሻ ቃላት ናቸው። ቀድሞም በሐሰት ተከስሶ ወደ ሸንጎ የቀረበ፥ ፊቱን እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ያዩት፥ እውነትን የመሰከረ፥ ጌታን አይቶ ያየውን የተናገረ ሰው ነው። ይህ እስጢፋኖስ ቀደም ሲል ባየነው የዲያቆናት ምርጫ ከተመረጡት አንዱ ነው።ልክ እንደዚያኛው እዚህም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለ፤ ልሳን ግን የለም።

10. ሐዋ. 9፥17 ሐናንያም ሄዶ ወደ ቤቱ ገባ፥ እጁንም ጭኖበት፦ ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ ጌታ፥ እርሱም በመጣህበት መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው፥ ደግሞ ታይ ዘንድና መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ አለ። ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ ከዓይኑ ወደቀ፥ ያን ጊዜም ደግሞ አየ፤ ተነሥቶም ተጠመቀ፥ መብልም በልቶ በረታ። ይህ ክፍል አሳዳጅ ስለነበረው ስለ ሳውል መለወጥ ከሚተርከው ውስጥ ሳውልና ሐናንያ የተገናኙበት ክፍል ነው። ጳውሎስ በዚህ ክፍል እንደተነገረው ተስፋ ታይ ዘንድ የተባለው እንደተፈጸመው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ የተባለውም ተፈጽሞአል። ሙላት አለ ልሳን ግን የለም፤ ወይም አልተጠቀሰም። ጳውሎስ በልሳኖች እንደሚናገር በሌላ ቦታ የጻፈ በመሆኑ እንደሚናገር የታወቀ ነው። በዚህ ግን አልተጻፈም።

11. ሐዋ. 11፥24 ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበረና። ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ። ይህ ስለ በርናባስ የሚናገር ምንባብ ክፍል ነው። ከዚህ የምንረዳው ቀደም ሲል ካየናቸው ቦታዎች በጥቂቱ ውስጥ እንደሆነው ቅጽበታዊ ክስተትን ወይም በርናባስ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞላ ሳይሆን በርናባስ መንፈስ ቅዱስ መልቶበት የሚኖርበት፥ መኖሪያው አድርጎት የተደላደለበት መሆኑን ነው። ሙላት አለ፤ ልሳን አልተነገረም።

12. ሐዋ. 13፥9 ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኵር ብሎ ሲመለከተው፡- . . . ይልና ጳውሎስ ጠንቋዩን ሲሞንን ሲገስጸው ያለው ቃል ተጽፎአል። ቀደም ሲል በሐዋ. 9፥17 ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበት ዘንድ ሐናንያ እንደተላከ አይተናል። እዚያ እንደተሞላ ከተጻፈ ይህ ዳግመኛ መሆኑ ነውና ሙላት የአንድ ጊዜ ልምምድ ብቻ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ከሐዋ. 4፥8 እና 31ም እንደምናጤነው ሙላት ተደጋጋሚ ልምምድ ነው እንጂ የአንድ ጊዜ መከሰት ብቻ አይደለም። እዚህ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ለጠንቋዩ ኤልማስ እንደተናገረው ሙላት አለ፤ ልሳን ግን የለም።

13. ሐዋ. 13፥52 በደቀ መዛሙርትም ደስታና መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው ይላል። ይህ ክፍል የሚናገረው መሞላት የጲስድያ በሆነው አንጾኪያ ከሆነው ድንቅ የወንጌል ስርጭት እና ከዚያም ጋር የተያያዘ ስደትን ተከትሎ የመጣ ደስታ ነው። እዚህም ሙላት አለ፤ ልሳን የለም።

14. የመጨረሻው ኤፌ. 5፥18 ነው። መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ ይላል። ይህ የአስተያየት ሳይሆን የትእዛዝ ቃል ነው። ያኔ የኤፌሶን አማኞች፥ ዛሬም እኛም አማኞች ሁሉ ልንከተለው የተገባ ትእዛዝ ነው። 'ይሙላባችሁ' የሚለው ግስ (πληροῦσθε) በተጻፈበት ቋንቋ ትእዛዝንና ቀጣይነትን የያዘ ግስ ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በወይን ጠጅ መስከር በመመሳሰል ሳይሆን በመነጻጸር ነው ጎን ለጎን የተጠቀሱት። ሙላት ከስካር ጋር አይመሳሰልም ይነጻጸራል እንጂ። ንጽጽሩም ቁጥጥሩ ነው። የሰከረ ሰው በመጠጡ ቁጥጥር ስር እንደሆነ በመንፈስ የተሞላ ክርስቲያንም መንፈስ ቅዱስ የተቆጣጠረው ሰው ነው። ከቁ. 15-20 ያለው አንቀጽና ከ21 ጀምሮ ያለውም አሳብ የተያያዘና መነጣጠል የሌለበት አንድ አሳብ ነው። መዝሙር፥ ዝማሬና መንፈሳዊ ቅኔ፥ ሁሌ እግዚአብሔርን ማመስገንና በክርስቶስ ፍርሃት አንዱ ለሌላው መገዛት ተያይዘው ነው የተገለጡት። በመንፈስ በመሞላት እነዚህ ባህርያት ይታያሉ። እዚህም ሙላት አለ ልሳን አልተነገረም።

ሲጠቃለል እስካሁን ካየናቸው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከተጠቀሰባቸው አሥራ አራት ጥቅሶች ውስጥ ልሳን የተጠቀሰው በአንዱ ብቻ ነው። ላለፉት በርካታ ዓመታት በመጋቢነት ሳገለግላት የቆየኋትን ቤተ ክርስቲያን መጋቢነት ከመቀበሌ በፊት ቀደም ሲልም ጀምሮ እየመገብኩ ብቆይም አሁን ግልጽ አደራ ልቀበል ስለሆነ ስለ እምነት አቋሜ እንድናገር ከተደረገ በኋላ ወደ ሁለት ሰዓት ያህል የፈጀ የጥያቄና መልስ ጊዜ ሆኖ ነበር። ይህ የሆነው በእሁድ አምልኮና በጠቅላላው ጉባኤ ፊት ነው። አንዱ ጥያቄ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና የልሳን ግንኙነት ነበር። የሙላትን ምንነትና የልሳንን ምንነት ትርጉም ከተናገርኩ በኋላ እነዚህን 14 ጥቅሶች በመጥቀስ ሙላትና ልሳን የተቆራኙት በአንዲት ጥቅስ ብቻ፤ ያውም ያም የማይታወቅ ሳይሆን የሚታወቅ ቋንቋ መሆኑን ስናገር ጠያቂው ወንድም፥ እንደ እግር ኳስ ግብ ቆጥሮት፥ 'እንደዚህማ 13 ለ 1 አይሆንም' ነበር ያለው። ይህ የቁጥርና የእስታቲስቲክስ ጉዳይ አለመሆኑ እውነት ነው። በመንፈስ መሞላት የሚለው ቃል በብዛት መጽጻፉና የተጻፈበት መልክ የሚያሳየው ምልከታም እጅግ ግልጽ ነው።

ይህ የጸጋ ስጦታ የለም ቆሞአል፤ ተቋርጦአል ብለው የሚያምኑ 'ተቋርጧሎች' ወይም cessationists አሉ። እኔ ሁሉም የጸጋ ስጦታዎች፥ ልሣኖችን ጨምሮ አልተቋረጡም እላለሁ። እንደ ሐዋ. 2 ያለ ልሳን ከኖረ ግልጽ ነው። ምንም ጥያቄ የለበትም። የማይታወቅ ልሳን ከኖረ ወይም በጉባኤ ከተነገረ ደግሞ በ1ቆሮ 14 መሠረት ወይ መተርጎም አለበት፤ ካልተተረጎመ አሁንም በ1ቆሮ. 14 መሠረት በጉባኤ መነገር የለበትም። ስጦታው እንዳለው የሚመስለው ሰው በግሉ ሊጸልይበትና ሊታነጽበት ይችላል፤ በጉባኤ አይደለም። ነገር ግን የልምምድና የኩረጃ ልሳኖች በእጅጉ ስሕተት ናቸው። እነዚህ የኩረጃ ልሳኖች ጉባኤን ብቻ ሳይሆን ተናጋሪውንም ጭምር የማያንጹ ብቻ ሳይሆኑ የሚረብሹ ናቸው። የማያንጽ ምንም ነገር በጉባኤ መደረግ የለበትም።

የዚህ የመልስ ጽሑፍ ዋናው አሳብ ከመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች ገጽ 42-45 የተወሰደ ነው። መጽሐፉን ከዚህ ሊንክ ማግኘትና በነጻ ማውረድ ይቻላል። ከhttp://www.good-amharic-books.com/library?id=107

. . . . .

ከዚህ ጋር ተቀራራቢ የሆነ በሌላ ጊዜ የቀረበልኝ ጥያቄም አለ፤ ይህኛውን ጥያቄና መልሱንም ጨምሬ ለማቅረብ ያስፈለገው የመጀመሪያውን ጥያቄ ከመለስኩ በኋላ በሁለት ቪድዮዎች ይህንን ጉዳይ በስፋት አስተምሬበት ነበርና፥ እነዚያ ሁለት ምንጮች እዚህም ለአንባቢዎች ተጨማሪ መልሶች

> ሰላም ላንተ ይሁን መምህር ዘላለም አንድ ጥያቄ አለኝ ልሳን አሚሞላው አንድ ሰው እንዴት ነው? ከቻልክ ግዜ ካለክ አስረዳኝ please በጌታ ገና አዲስ ተጠማቂ ነኝ (ሐ. በ)

ሰላም ሐ. በ.። በዚህ ጉዳይ ላይ በሁለት ቪድዮዎች በስፋት አስተምሬአለሁና ከታች ስላያያዝኩልሽ ተመልከቺያቸው። በአጭሩ ግን ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ ወይም መንፈስ ቅዱስ እንዲገዛቸው፥ እንዲቆጣጠራቸው እንጂ በልሳን እንዲሞሉ አልተጻፈም። በልሳን መሞላት የሚባል ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከቶም አይገኝም። ልሳን ከብዙ (ወደ ሃያ ከሚደርሱ) በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተዘረዘሩ የጸጋ ስጦታዎች መካከል አንዱ ነው። ሁሉ በልሳን አይናገሩም፤ 1ቆሮ. 12፥29-30። በጉባኤ ውስጥ በልሳኖች የመናገር አገልግሎት ምን መምሰል እንዳለበት በ1ቆሮ. 14 በሰፊ ዝርዝር ተጽፎ ይገኛል። ያንን ምዕራፍ በጥሞና አንብቢው።

በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ነዋሪ ምልክት ወይም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰውን የምናውቅበት ዋናው፥ አስምሪበት፥ ዋናው መለኪያ የመንፈስ ፍሬ በውስጣችን መታየቱ ነው። የመንፈስ ፍሬ በገላ. 5፥22 የተጻፈው ነው፤ እንዲህ ይላል፤ የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።

በተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተጻፈባቸው ቦታዎች በሙሉና በተሞሉት ላይ የሆኑትን ነገሮች ወይም መንፈስ ቅዱስን በተሞሉ ጊዜ የተከሰቱትን ነገሮች በሙሉ በነዚህ ሁለት ትምህርቶች ውስጥ በዝርዝር አስተምሬአቸዋለሁ። ቪድዮዎቹ እዚህ ይገኛሉ፤

የመንፈስ ቅዱስ ሙላትና በልሳን መናገር ግንኙነት አላቸውን?

https://www.youtube.com/watch?v=s07c4jE1wDw

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና በልሳን መናገር ግንኙነት አላቸውን?

https://www.youtube.com/watch?v=rLfSANxxvVY

* * * * *

15. ሴቶች ሽማግሌ መሆን ይችላሉ? የሴቶች የመድረክ አገልግሎትስ እንዴት ይታያል?

በቤተ ክርስቲያናችን ሴቶች እንዳያገለግሉ፥ በጸሎትም እንኳ እንዳያገለግሉ ከ1ጢሞ. 2፥9-14 ካለው ክፍል ትምህርት ተሰጥቶአል እስካሁን በማስተማር በጉባኤ ጸሎት እና በአንዳንድ ክፍሎች ማስተማርንም የምናገለግል እህቶች አለን። እና ምን ማድረግ አለብን? ሴቶች በቤተ ክርስቲያን አያገለግሉም? በአንዳንድ ቦታ ሽማግሌም በመሆኑ ሲያገለግሉ ይታያል፤ ሽማግሌ መሆን ይችላሉ? (እ. ደ)

የተለያዩ አብያተ እምነቶች የሴቶችን አገልግሎት በተመለከተ እያራሳቸው አቋመና በጽሑፍም የሰፈረ ደንብ አላቸው። በጥያቄው እንደገለጥሽው ሴቶችን ከምንም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጸሎትንና ምንም ዓይነት ትምህርትን ጨምሮ ሴት ስለሆኑ ብቻ ማገድ ርቀ መሄድ ይመስለኛል። ይህ ጉዳይ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ውስጥ የፈጠረው ውዝግብ ነበረ? በቤተ ክርስቲያኒቱ ደንብ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠና ቃሉን መሠረት ያደረገ መርህ ይገኛል? ይህ ውሳኔ ተጠንቶበትና ተሰልቶ የቀረበ ነው ወይስ በአንድ ቀን ብልጭ ባለ የትምህርት ጊዜ የተደነገገ ድንጋጌ ነው? ይህስ እንዲሆን የተፈጠሩ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ? እኒህና የመሳሰሉት ጥያቄዎች ሳይኖሩ ስለሆነ የተጠየቀው ሙሉው ስዕል የለኝም። ሆኖም በቃሉ አንጻር በማየት ይህንን ለማለት እፈልጋለሁ።

በዚህ ክፍል ጳውሎስ ይህን የጻፈው ለጢሞቴዎስ ሲሆን በዚህ ጊዜ ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እየመገበ የነበረ አገልጋይ ነው። ኤፌሶን የአሕዛብ ባህል የወረራት ከተማ ብትሆንም ቤተ ክርስቲያኗ የአሕዛብም የአይሁድም ቅይጥ ናት። አሕዛብነታቸውን ከአረማዊ ባሕል አንጻር፥ በተለይም በከተማዋ በድምቀት ትመለክ

ከነበረችው የአርጤምስ አምልኮ አንጻር ሊታይ ይችላል። አይሁዳዊው ዳራ ደግሞ ከብሉይ ኪዳን የሴቶች ሚና አንጻር ሊታይ ይችላል።

ከአሕዛብ አምልኮና ባህል የሚመጡ ሴቶች የልብስና የጠጉር ይዞታቸውንና አለባበሳቸውን በሙሉ ይዘው መጥተው፥ እዚያ የሚደረገውን ሁሉ በቅዱሳን ጉባኤ ሊለማመዱ ስለሚፈልጉ ይህ ችግር ይፈጥራል። ለዚህ ነው በ1ቆሮ. 11 ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለዚህ ጉዳይ የጻፈላቸው። ባህል ጥሩና መጥፎ እሴቶች ቢኖሩትም ሳይፈተሽና ከቃሉ አንጻር ሳይታይ ወደ ቅዱሳን ጉባኤ ገብቶ ወግ መሆን የለበትም። ቁ. 9-10 አለባበስን ስለሚናገር ይህ ከጨዋ አለባበስ አንጻር ጤናማ ትእዛዝና ምክር ነው። ይህ ግልጽ ነውና ማብራሪያ አያሻውም። 1ጴጥ. 3ም ከዚህ ይሄዳል። 1ቆሮ. 11፥3 የሴት ራስ ወንድ የሚለው በባህሉና በወጉም ውስጥ ጾታዊ ሚና የተጠበቀ መሆኑን ያስረዳል። 1ቆሮ. 14፥34-35ንም ተመልከቱ።

በአይሁዳዊ ዳራም ሴቶች ተገቢ ስፍራ አላቸው። ሰፊው ሚናቸው የሚስትነትና የእናትነት ሚና ነው። ይሁን እንጂ እንደ ዲቦራ የመሰሉ መሪዎች አልታጡም። ሴቶች ነቢያትም ነበሩ፤ ዲቦራ ራስዋ ነቢይትም ነበረች (መሳ. 4፥4)፤ የሙሴ እኅት ማርያም (ዘጸ. 15፥20)፤ ሕልዳና (2ዜና 34፥22)፤ የኢሳይያስ ሚስት (ኢሳ. 8፥3)። ሉቃ. 2፥36 ሐናን ይጠቅሳል፤ ይህ ከመስቀሉ በፊት ነውና ብሉይ ኪዳን መሆኑ ይታወስ።

ከዚህ ጋር የመጀመሪያውን የፍጥረት እቅድና የአዲሱን ኪዳን የሴቶች ስፍራም እናጢን። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር አንዱ የሌላው ገዢና ሌላው የአንዱ ተገዢ እንዲሆን ሳይሆን ሁለቱም እንዲገዙ ነው የፈጠራቸው፤ ዘፍ. 1። የሔዋን (የሴት) ፈቃድ ወደ አዳም (ወንድ) የሆነው ከውድቀት በኋላ ነው፤ ዘፍ. 3። አንድ ሰው የሌላ ሰው ገዢ የሆነውም ከውድቀት በኋላ ነው። ከውድቀት በኋላ ይህ የጸናው ሥርዓት ሆነ። ይህ መሪነትን፥ ገዢነትን፥ ራስነትን የተመለከተ ነው።

1ጢሞ. 2፥11-12 ሴት ብሎ በነጠላ ነው የሚናገረው። ሴት ሲል በቤት ነው ወይስ በጉባኤ? ይህ ወደ ቁ. 8 ሄደን እንድንንደረደር ያስገድደናል። ንጽጽሩ ከዚያ ጋር ነውና። ቁ. 8 እንግዲህ ወንዶች በስፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ እፈቅዳለሁ። ይላል። ስፍራ ሁሉ አደባባይና የመንገድ ማዕዘን ሁሉ አይደለም። የጸሎት ስፍራ ወይም ቅዱሳን የሚሰበሰቡበት ስፍራ ሁሉ እንጂ። ይህ ስለ ሴት ለሚናገረውም ዐውዱ ወይም ስፍራው ከሆነ የቅዱሳን ማኅበርን ይመለከታል። ሴት ሲል ነጠላ ቢሆንም የአንዳንዶች አንድምታ እንደሚገምተው ስለ አንዲት ሴት ብቻ መናገሩ አይደለም። እዚህ ሴት እና ወንድ የሚሉት የግሪክ ቃላት ባል እና ሚስት የሚል ትርጉምም ስላላቸው ይህንን አሳብ በቤተ ክርስቲያን ሳይሆን በቤት ውስጥ የሚነገር ትምህርትና ሥልጣን አድርገው የሚፈቱም አሉ። ሴት በቤት ውስጥ ለባሏ ካላስተማረች እና ካልሰለጠነችበት በቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ ነገር ልታደርግ አትችልም። ባሏ እዚያም አለና። መሰልጠን ባለ ሥልጣን መሆን ነው። ግን ማስተማር መሰልጠን ነው ወይ? እርግጥ ነው፤ ቅዱሳን በተሰበሰቡበት ቃሉ ነው የሚሰበከው እና የሚስተማረው። ቃሉ ደግሞ ባለ ሥልጣን ነው። ቃሉ ከሆነ ባለ ሥልጣኑ ሰውየው ወይም ሴቲቱ ቃሉ ቢያካፍሉ ባለ ሥልጣኑን መግለጣቸው እንጂ ሥልጣናቸውን መግለጣቸው አይደለም። ከሆነ ወንዱም የቃሉን ሳይሆን የራሱን

ወይም ሌላ ሥልጣንን ከገለጠ በዚያ ስፍራ ቆሞ ማስተማር ወይም መስበክ የለበትም።

ቁ. 11-12 በዝግታ ይላል። ዝግታ የሚለው ቃል ἡσυχία (ሄሱኪያ) ἡσύχιος (ሄሱኪዮስ) ቃል የሚለው አንስታዊ አቻ ነው። አለመናወጥ፥ አለመታወክ፥ መርጋት፥ መረጋጋት፥ በስፍራ መቀመጥ ማለት ነው። ዝግታው ከመምማር ጋር የተቆራኘ ቢሆንም እርጋታው ጭምትነትንም የሚያመለክት ነው። ቁ. 13-14 ላይ ይህ አሳብ ከመጀመሪያው ውድቀት ጋር መቆራኘቱ መለኮታዊ የሥልጣን ተዋረድን ግልጽ ያደርጋል። በዘፍ. 3 የሆነው የውድቀት ጅማሬ ከሴት ነው። የቅጣቱ ብያኔም ሴት በወንድ ላይ ከቶም እንዳትሰለጥን ነው። በዔድን ገነት ትእዛዙ በቀጥታ የተሰጠው ለአዳም ሲሆን በመጀመሪያ የተላለፈችው ግን ሔዋን ናት። ሆኖም የውድቀት ምልክትና ኃላፊ የሆነው አዳም ነው፤ ሮሜ 5፥12። ሴቲቱ ተታለለች፤ አዳም ግን ያደረገውን ሳያውቅ አይደለም ያደረገው። በቀላሉ የምትታለል ስሜታዊ ፍጡር መሆኗ መግዛትንና መሰልጠንን ነስቶ ፈቃዷን የባሏ አደረገው። ከውድቀት በፊት ይህ ሥርዓቱ ባይሆንም ከውድቀት በኋላ ግን ሆነ። ይህ የእግዚአብሔር ውሳኔ ስለሆነ መጠየቅ መብታችን ነው፤ መቀልበስ ግን አንችልም።

በክርስቶስ አካል ውስጥ የበላይና የበታች መሆን የለም። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። (ገላ 3፥28)። የጸጋ ስጦታ በጾታ ተከፍሎ አልተሰጠም። ስለዚህ ወንድ ወይም ሴት ነቢያት፤ ወይም አስተማሪ፥ ወይም የእርዳታ አገልጋዮች ሊኖሩ ይችላሉ። መግዛት ወይም ማስተዳደርም ከጸጋ ስጦታዎች ውስጥ እንደሚገኝ ግልጽ ነው፤ (ሮሜ. 12፥8፤ 1ቆሮ. 12፥28)። ሆኖም በጌታ እና በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ሴቶች መሪዎች አልተደረጉም። በአዲስ ኪዳንም የወንዶች የመሪነት ስፍራ እንደጸና ይገኛል። ይህ ሴቶችን ጭቁን የሚያደርግ አካሄድ አይደለም። ሴቶች ከወንዶች በፍጥረትም ይሁን በክብር፤ በጸጋም ሆነ በአገልግሎት ያነሱ ባይሆኑም የመሪነት ስፍራ ለሴቶች አልተሰጠም። ጌታ ሐዋርያቱን ሲመርጥ ከሴቶች አልመረጠም፤ አልሾመም። ደቀ መዛሙርቱ ነበሩ፤ ያገለግሉም ነበር፤ ጸጋም ነበራቸው።

ከዚህ የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ በጤናማ አሠራር ሴቶች ከመሪነት ኃላፊነት ርቀዋል። ዛሬም በብዙ አብያተ ክርስቲያናትና አብያተ እምነቶች ከመሪነት ኃላፊነቶች የራቁ ናቸው። በተለይ ከ1970ዎቹ feminist movement እና feminine theology (አንስታዊ ንቅናቄና ስነ መለኮት) በኋላ ሴቶች ይህን የመሪነት እርካብ ለመቆናጠጥ የራቀ ጽንፍ የያዘ እርምጃ ተራምደዋል። አንዳንዴ የበላይነት ሚና ለመጫወትም ጥረዋል። አዲስ ኪዳን የወንድ ወይም የሴት የበላይነት ሳይሆን የክርስቶስ የበላይነት ነው።

በቤተ ክርስቲያን ብቁ ወንዶች ባሉበት ወንዶች መሪ መሆን አለባቸው። ምንም ወንዶች የሌሉበት በሴቶች ብቻ የተመሠረተ ቤተ ክርስቲያን ቢኖርስ? ኖሮ ያውቃል። አንድ በቅርብ የማውቀው ወንድም በመካከለኛው ምሥራቅ ካገለገለባቸው ስፍራዎች

በአንዱ ለሥራ ከአገር በወጡ ሴቶች በተመሠረተች ቤተ ክርስቲያንን አገልግሎ ነበር። የሰጣቸው ጤናማ ትምህርት ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚመሩት ሴቶች መምራታቸውንና ማገልገላቸውን እንዲቀጥሉና ብቁ የሆኑ በሳል ክርስቲያን ወንዶች ሲደርሱ ለእነርሱ አመራሩን እንዲያስረክቡ ነበር። ወንዶች ሁሉ ወንዶች ስለሆኑ ብቻ መምራት ይችላሉ ማለት አይደለም። ሴቶች ሴቶች ስለሆኑ ብቻ መምራት አይችሉም ማለት አይደለም። በአንዳንድ አብያተ እምነት ሚዛናዊነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ሴቶች የሴቶችን አገልግሎቶች እንዲመሩና እንዲያስተዳድሩ፥ እንዲያስተምሩና እንዲያገለግሉ ያደርጋሉ። ይህም በጣም ጤናማ አሠራር ነው። አንቺም በጥያቄሽ እንዳነሳሽው በዚህ ረገድ በቂ ከማስተማር እስከ መሪነትና እረኝነት አገልግሎት ውስጥ ተሰማርተሽ አገልግለሻል።

ስለ ሴቶች ማስተማር ጳውሎስ ለቲቶ ሲጽፍ፥ በቲቶ 2፥3-5 እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ፥ የማያሙ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ፤ ቆነጃጅትም የእግዚአብሔር ቃል እንዳይሰደብ፥ ባሎቻቸውን የሚወዱ፥ ልጆቻቸውን የሚወዱ፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ ንጹሖች፥ በቤት የሚሠሩ፥ በጎዎች፥ ለባሎቻቸው የሚታዘዙ እንዲሆኑ ይምከሩአቸው። ብሎአል። በጎ የሆነውን ማስተማር መቻል ብቻ ሳይሆን ይጠበቅባቸዋል። አሮጊቶች ሲል ሽማግሌዎች የሚለው ቃል አንስታዊ አቻ ነው። በእድሜ የበለጠጉ ብስለት ያላቸው ሴቶች ናቸው። ቁጥር 5 መጨረሻ ይምከሩአቸው የሚለው ግስ ባለቤት አሮጊቶቹ ሲሆኑ ተሳቢዎቹ ወይም ተቀባዮቹ ደግሞ ቆነጃጅቱ ወይም ወጣቶቹ ሴቶች ናቸው። የምክሩ ዐውድ ሴቶች ለሴቶች ነው። ትምህርቱ ግን ከዚህ የሰፋ ይመስላል።

ሴቶች መሪዎች ሆነው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስላልታየ መሰልጠን ወይም መግዛት አልታየም። ስለዚህ ሴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብታስተምር ወይም ካስተማረች ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሥልጣን ስር ሆና ማስተማር አለባት። ይህ ማስተማር በነጠላ ወይም በጥቂት ቁጥር ፥ በግል ወይም በቡድን ሊሆን ይችላል።

የጌታ የመጀመሪያ የትንሣኤው ምስክሮች ሴቶች ነበሩ፤ ማቴ. 28፤ ማር. 16፤ ሉቃ. 24። ይህ ያዩትን የመናገር፥ የመመስከር አገልግሎት የመናገር አገልግሎት ነው። ከመጀመሪያዎቹ 120 የቤተ ክርስቲያን ጅማሬ እሆኑ ሰዎች መካከል ከሐዋርያት ጋር ሴቶችና የጌታ እናት በጸሎት ይተጉ ከነበሩት ጋር ተጠቅሰዋል፤ ሐዋ. 1፥12-14። ስለ አጵሎስ ሐዋ. 18፥24-26 ሲናገር፥ በወገኑም የእስክንድርያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጵሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ፤ እርሱም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ነበረ። እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበረ፥ የዮሐንስንም ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል ስለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክል ያስተምር ነበር። እርሱም በምኵራብ ገልጦ ይናገር ጀመር። ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፥ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት።ይላል። ይህንን አጵሎስን ያስተማሩት አቂላና ጵርስቅላ ናቸው። እነዚህ ባልና ሚስት ስማቸው በቁርኝት 5 ጊዜ ሲጻፍ እንደ ልማድ የወንዱ ሳይሆን የሴቷ ስም ነው ቀድሞ የተጻፈው። ምናልባት የማስተማርና የማገልገሉ ታላቁ ሸክም በእርሷ ስላረፈ ይሆን? አላውቅም። ግን ይህ

የግል ማስተማርና በግል ያስተማሩትን የብዙዎች በረከት ማድረግ አንዱ የማስተማር መንገድ ነው። ከመድረክ ባይሆንም የሴቲቱ ጉልህ ተሳትፎ በገሃድ ይታያል።

አንዳንድ ቤተ እምነቶች እንዲህ እንደነጽርስቅላ ያለውን እና የጢሞቴዎስ እናትና ሴት አያቱ ያስተማሩትን ማስተማር፥ በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አረጋውያን ሴቶች ሌሎች ሴቶችን ማስተማራቸውንም እንደ ሞዴል በመውሰድ በተግባር ያውሉታል። አንዳንዶች ደግሞ ምንም ገደብ ሳይኖር እንዲያገለግሉ ይፈቅዳሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ቀሳውስት እና መጋብያን በመሆን ሹመትንም እየተቀበሉ ይገኛሉ። የአጥቢያችሁን ጉዳይ በተመለከተ ነባር ነገር በአንድ ጊዜና በአንድ ትምህርት በግብታዊነት ከመገልበጥ ጠቅላላው የቃሉ ምክር ከበርካታ መሪዎችና አገልጋዮች አንጻር ታይቶ በጸሎት እንደ ቃሉ መተግበር ተገቢ ይመስለኛል።

ሴቶች እንደተሰጣቸው ጸጋና ስጦታ ከቤት እስከ ቡድኖችና ከዚያም ባለፈ በየእርከኑ ከጸሎት እስከ ማስተማርና መስበክ ሊያገለግሉ ይችላሉ። ከላይ የጠቀስኩት ዓይነት ወይም መሰል ወንዶች መሪዎች የሌሉበት አስገዳጅ ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር ግን ሊመሩ ወይም ሽማግሌ ሊሆኑ አይችሉም።

* * * * *

16. ሴት በመውለድ ትድናለች ሲባል ምን ማለት ነው?

1ጢሞ. 2፥15 ሴት በመውለድ ትድናለች ሲል ምን ማለቱ ነው? (እ. ደ)

ቃሉ የሚለው ይህንን ነው፤ ነገር ግን በእምነትና በፍቅር በቅድስናም ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ በመውለድ ትድናለች። ነው። ይህን ጥያቄ በአጥጋቢነት መመለስ እንደምችል እርግጠኛ አልሆንም። አንዳንድ ፍቺዎች ከዐውዱ ሲታይ ሴት በመግዛት ወይም በመሰልጠንና በማስተማር ሳይሆን በመውለድ፥ ማለትም በሚስትነትና በእናትነት መዳኗን በእምነት፥ በፍቅር፥ በቅድስና እንድትፈጽም መናገሩ ነው ይላል። ሌሎች ፍቺዎች ቃል በቃል በመውለድ ትድናለች ይላሉ። ይህ ደግሞ ድነትን በሥራ የሚገኝ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የወላዶች ብቻ ያደርገዋል።

ሌላው፥ የመልሱ አቅጣጫ ሰው ሁሉ ሴቶችም ጭምር የወደቁት በመጀመሪያዋ ሴት በሔዋን መተላለፍ እንደሆነ ሁሉ በዘፍ. 3፥15 በተሰጠው ተስፋ አማካይነት የእባቡን ራስ በሚቀጠቅጠው የሴቲቱ ዘር አማካይነት፤ በገላ. 4፥4 በተነገረው የተስፋው መፈጸም እንደተገለጠው ከሴት በተወለደው መሢሕ በኩል መዳን እንደሚገኝ መናገሩ ነው ይላሉ። ችግሩ ጳውሎስ ይህን እያለ ያለው መሢሑ ከተወለደ በኋላ እንጂ ገና ተስፋው ሳይፈጸም አይደለም። እንዲያም ሆኖ ለእኔ የሚመስለኝ ይህ ነው።

* * * * *

17. ተአምር ምንድነው? እዚህም እዚያም የሚሰሙት ተአምራት እውነት ናቸው?

dear zelalem. Happy new year. be ortodoks betekristian yemidereg teamir min yahil ewnet alew tilaleh be ahun seat letiwlid gera yemiyagaba fewse teamir begnam benesum yisemal what do think? (ና. መ.)

ሰላም ናቲ፥ ጥሩና ትልቅ ጥያቄ ነው። እርግጥ ነው ጌታ ተአምራት አድራጊ አምላክ ነው። የጎልውናው ወይም የማንነቱ አንድ ምስክርም ተአምር አድራጊነቱ ነው። ተፈጥሮ ተአምር ነው። አክሲጅን ተአምር ነው። አውራ ጣታችን ተአምር ነው። እኔና አንተ ተአምር ነን። እንዲያው ከምናየው ልነሣ ብዬ ነው።

ተአምር ማለት በተፈጥሮ አካሄድ የማይገኝና የማይለማመዱት፤ ዲበ አካላዊ ወይም ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነ ክስተት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በቀጥታ ወይም በአገልጋዮቹ ያደረጋቸው ነገሮች ተአምራት ናቸው። የሞተ ሲነሣ ተአምር ነው። ዕውር ሲበራ ተአምር ነው። ውኃ ከመፍሰስ ሲቆም ተአምር ነው። ሌሎችም።

የተአምራት ዓላማና ግብ ምንድርነው? ቢባል። እግዚአብሔር ለክብሩ የሚያደርገው፥ ሰዎችን ለመታደግና ለማዳን የሚያደርገው ነገር ነው። የሚከበረውም እርሱ ነው። እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ወይም ሌላ የሚታይና የሚሞገስበት ከሆነ ምንጩን መጠርጠር ተገቢ ነው።

ምንጩን የምለው ከእግዚአብሔር ሌላ ሰይጣንም ተአምራትን ማድረግ የሚችል ችሎታ ስላለው ነው። በፈርዖን ዘንድ የነበሩ ጠንቋዮች ተአምራት ሠርተዋል። በዘዳ. 13፥1 ሰዎች ያለ እግዚአብሔር ኃይል፥ በሌላ ኃይል ተአምራት ሊያደርጉ መቻላቸው ተጽፎአል። በማቴ. 24፥24 በመጨረሻው ዘመን በሰይጣን ኃይል የሚያምኑትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ የሚሞክሩ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ነቢያት እንደሚነሡ ተጽፎአል። በራእ. 19፥20 የአውሬው ነቢይ የሆነው ሐሰተኛው ነቢይ ተአምራትን ያደርጋል። እንዲህ ከሆነ ከጌታ ሌላ ተአምር ማድረግ የሚችል ኃይል አለ ማለት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም። በጌታ ስም ተአምራትን የሚያደርጉ ግን በእርሱ የማያምኑ ሰዎችም መኖራቸው ነው። ማቴ. 7፥22 ይህን ይነግረናል። እነዚህን ሰዎች ጌታ፥ “ከቶ አላወቅኋችሁም” ነው ያላቸው። ይህ ማለት ቀድሞ ያን ሁሉ ሲሠሩም ያልታወቁ ነበሩ ማለት ነው። ተአምራቱ በስሙ ተደርጓል ይህ እውነት ነው። ጌታም ስለ ስሙ ሲል ወይም ተአምራቱ በጊዜውና በቦታው አስፈልጎ ነበርና አድርጎአል።

ተአምራት በዘመናችንም አለ። ከላይ እንዳልኩት እግዚአብሔር እስከኖረ ድረስ ተአምራት አለ። እርሱ ደግሞ ሁሌም አለ። ከጸጋ ስጦታዎች አንዱ ተአምራትን ማድረግ ነው። በ1ቆሮ. 12 የተአምር ስጦታ የተባለው "ኃይል" የሚል ቃል ነው። የእግዚአብሔር ኃይል የተገለጠበት *ሥራ* ማለት ነው። ስለዚህ ተአምር ከተደረገ ሠሪው እግዚአብሔር እንጂ ሰው አለመሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።

በ1980ዎቹ መጨረሻ ከጻፍኩት መጽሐፍ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ ከገጽ 225 ጀምሮ ያለውን እንድታይ አያይዤ ልኬልሃለሁ። መጽሐፉን በሙሉው ማግኘት ከቻልክ፥ *መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች* ይባላል።

እንደጠቀስከው በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወይም በወንጌላውያን ቤተ ክርስቲያን ወይም በሌላ ቦታ ተአምር ከተደረገ ማን ነው እየታየ፥ እየጎላ ያለው? ሰዎች ወደ ማን እየቀረቡ ወይም እንዲጠጉ እየተደረገ ነው? የመዳናችን ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ያመለክታል ተአምሩ ወይስ ወደ ሌላ? ኃጢአተኞች ንስሐ ገብተው ወደ መዳን ይመጣሉ ወይስ በምልክቶቹ ተደሳስተው በነበሩበት የጠፋ ሕይወት ይቀጥላሉ? ተአምራቱ በክርስቶስ ስም ይደረጋል ወይስ በሌላ? (ለምሳሌ፥ በማርያም ወይም በሰዎችና በመላእክት?)

ይህን የምለው ተአምራት በራሱ እምነትን የሚወልድ ነገር ባለመሆኑ ነው። ጌታ ብዙ ተአምራት አድርጎአል። ግን ይህን ያዩ ሁሉ አላመኑበትም። ብዙ ተአምራት የተደረጉባቸው ከተሞች ብዙ ሰዎች ያመኑባቸው አልነበሩም።

እና በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ይደረጋሉ ያልካቸውን ተአምራት ምን መሆናቸውን፥ በማን ስም መደረጋቸውን፥ ዓላማና ግባቸው ምን መሆኑን፥ ወደ የት እና ወደ ማን ማመልከታቸውን፥ በመመዘን የሰዎቹንም እምነት፥ ትምህርትና የኑሮ ፍሬ በመመልከት ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ነው ወይስ አይደለም ብሎ መመለስ ይቻላል።

ተአምራቱ በጌታ ስምና *ሥ*ልጣን ካልተደረጉ ወይ በሰይጣን ኃይል የተደረጉ ናቸው። ወይም በማቴ. 7 እንደተጠቀሱት ሰዎች ባለ ሁኔታ የተፈጸመ ነው ማለት ነው።

* * * * *

18. በአዲስ ኪዳን አሥራት መስጠት ግዴታ ነው?

> የጌታ ፀጋ ይብዛልህ! በአዲስ ኪዳን አስራት መክፈል ግዴታ ነው ወይ! Some teacher saying that it is the law given to old covenant era! what is your understanding regarding to this idea? Thank you for kind response? your brother in Christ Jesus muluneh!

ሰላም ሙሉነህ፥ አሥራት መክፈል . . . ብለው የሚጠይቁ ሰዎችን ስሰማ ግፊታቸውን ማወቅ እፈልጋለሁ። ብዙ ጊዜ ይህን ጥያቄ የሚያቀርቡ ሰዎች ለመስጠት የሚጓጉ ሳይሆኑ ከመስጠት የሚሸሹ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ሲጠይቁ ለመስጠት ነው ወይስ ላለመስጠት? እቅጩን አሥራት ላይ ለማቆም ነው ወይስ ከዚያ ያነሰ ወይም ያለፈ ለመስጠት? አንዳንዶች ግን እውነቱን ማወቅ የሚሹ ናቸው። ይህኛውን እንደዚህኛው እወስዳለሁ። ግፊታችንን ማወቁ ይጠቅመናል።

ሁለት ጉልህ ቃላት ላይ ላተኩር። የመጀመሪያው ክፍያ የሚለው ሲሆን ሁለተኛው ግዴታ የሚለው ነው። አስራት ክፍያ አይደለም። መክፈል ለተደረገ አገልግሎት የሚደረግ ተመጣጣኝ የገንዘብ ወይም የሌላ ነገር እኩያ ልዋጭ ነገር ነው። ገበያ ሄደህ የበግ ግልገል ወስደህ 500 ብር ብትከፍል ወይም በወሩ መጨረሻ ለተጠቀምክበት ውኃ ወይም ስልክ 2ሺህ ብር ብትከፍል ለተቀበልከው ነገር የሰጠኸው ልዋጭ ነው። አሥራት በአዲስ ኪዳን ይቅርና በብሉይ ኪዳንም የኪዳኑ ሰዎች የመሆን አንድ መግለጫ እንጂ የተቀበሉት በጎነት ክፍያ አይደለም። ለምሳሌ ለምንሞቀው ፀሐይ ወይም ለምንተነፍሰው አየር አሥራት በምንም መልኩ ተመጣጣኝ ዋጋ አይደለም። አንድ ሳምባ ሙሉ አየር ዋጋው ስንት ነው? ማንስ ይገምተዋል?

ሁለተኛ ግዴታ ላልከው ከላይ እንዳልኩት በብሉይ ኪዳንም የኪዳን ትስስር ምልክት እንጂ ግዴታ አይደለም። ለዚህ ነው አሥራቱን ይከለክሉ፥ ይሰርቁ የነበረው። በአዲሱ ኪዳን ደግሞ ምንም ነገር በግዴታ አይደረግም። ግዴታ ከሆነ ፈቃድ የለበትም። እግዚአብሔር ደግሞ በፈቃዳችን ላይ የሚጫን ጨቋኝ አምላክ አይደለም።

ይህን ካልኩ በኋላ አሥራት ምን መሆኑን እንይ። አሥራት በብሉይ እና አዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፈ ቃል ነው። አሥራት (מַעֲשֵׂר ማዓሤር ወይም מַעֲשְׂרָה ማዓሥራህ፤ עָשַׂר ዓሣር፤ δεκάτη ዴካቴ፤ ἀποδεκατόω አፖዴካተኦ) ከአሥር አንድ፤ ከአሥር አንድ እጅ፥ አንድ አሥረኛ ማለት ነው፤ ዘፍ. 14፥20፤ ዕብ. 7፥1-9። አይሁድ የኪዳኑ ሰዎች እንደመሆናቸው ከእጃቸው ፍሬ ሁሉ አሥራትን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡ በሕጉ ታዝዘዋል፤ ዘሌ. 27፥30፤ ዘዳ. 14፥22-28፤ 2ዜና. 31፥5-6፤ ነህ. 10፥37-38፤ 13፥5-12፤ አይሁድ የሚሰጡት አሥራት ለሌዋውያን እንደ ርስት ሆኖ የሚቀርብ ነው፤ ዘኁ. 18፥21-24። ሌዋውያን ራሳቸውም ከሚቀበሉት አሥራት፥ የአሥራት አሥራት የማንሣት ቁርባን አድርገው ያቀርባሉ፤ ዘኁ. 18፥26-28። ለሌዋውያን ከሚሰጠው በተጨማሪ በሦስት ዓመት አንዴ ከሌዋዊው ጋር ለመጻተኛ፥ ለድሀ አደግና ለመበለት ይሰጣሉ፤ ዘዳ. 26፥12። ነገሥታትም አሥራት ይወስዳሉ፤ 1ሳሙ. 8፥15-17። አሥራትን ለእግዚአብሔር ቤት አለመስጠት እግዚአብሔርን መስረቅ ነው፤ ሚል. 3፥8-10።

አሥራት የሕጉ ትእዛዝ ብቻ ሳይሆን ከሕግም ይቀድማል፤ ዘፍ. 14፥20፤ ዕብ. 7፥1-9። በቀረቤታ ስናየው በብሉይ ኪዳን አይሁድ አሥራት ወይም አንድ አሥረኛ ብቻ ሳይሆን ከዚያ በጣም ያለፈ ነበር የሚሰጡት። ሕጉ አስሰጪ ነው፤ መስጠትን ያበረታታል። ኪዳኑ ደግሞ ሰጪ ነው። ቢታዘዙ በረከት ተቋጥሮበታልና። ያ በሕግ ዘመን ነው።

በአዲስ ኪዳን ሰዎች አሥራትንም ይሰጡ ነበር፤ ማቴ. 23፥23፤ ሉቃ. 11፥42፤ 18፥12። ሰዎች አሥራትን መስጠታቸውን ጌታ አላወገዘም። ይልቅስ ያወገዘው ከጥቃቅኑም አሥራት መስጠትን እየሰጡ ትልልቁን ነገር፥ ፍርድን፥ ምሕረትን፥ ታማኝነትን፥ እግዚአብሔርን መውደድን ስለሚተዉና በዚህ ስለሚተላለፉ ያንን ነው የወቀሰው። ሕጉ የተሰጣቸው አሥራት ከሰጡ ልጁ የተሰጠን ደግሞ ምንኛ ከዚያ በላይ መስጠት አይኖርብንም? ይሁን እንጂ፥ የአዲስ ኪዳን ስጦታ መሥዋዕት ሆኖ በደስታ፥ በፈቃድ፥ እና በልግሥና የሚሰጡት ስጦታ ነው፤ ሮሜ. 12፥8፤ 2ቆሮ. 9፥6-7፤ ፊል. 4፥18፥19። ግዴታ ከኖረ ሕግ ነው፤ እኛ ደግሞ ከሕግ በታች አይደለንም። ግዴታ ከኖረ ቅሬታም ይኖራል። ግዴታ ከሆነ እንደተጠየቀው ክፍያም ይመስላል፤ ከሆነ ደግሞ እጅ በጅ ልንል ነው፤ ዱቤ አይፈቀድም ውስጥ ልንገባ ነው።

በአዲስ ኪዳን እንደ መሥዋዕት አድርገን እንድናቀርብ የተነገሩን ነገሮች አሉ፤ 1ጴጥ. 2፥5 እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ። ይላል። እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች ሁላችንም ካህናት ነንና መሥዋዕት አቅራቢዎች ነን። የምናቀርባቸው መሥዋዕቶች እነዚህ ናቸው፤

1. ሰውነታችን፤ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። ሮሜ. 12፥1፤ 15፥15-16።

2. ምስጋናችን፤ እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰከሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት። ዕብ. 13፥15።

3. መልካም ማድረግና ለሌሎች ማካፈላችን፤ ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና። ዕብ. 13፥16።

4. ለወንጌል ሥራ የምንሰጠው ስጦታችን፥ ገንዘባችን፤ ነገር ግን ሁሉ አለኝ ይበዛልኝማል፤ የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚሆነውን ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቼአለሁ። ፊል. 4፥18።

5. ነፍሳችንም፤ ከላይ የተዘረዘሩት ሁላችንንም የሚመለከቱ ሲሆኑ ይህ ለሁሉም አይደለም፤ ሲጠየቅ ግን ለመሠዋት ማፈግፈግ የሌለብን መሥዋዕት ነው። በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። 2ጢሞ. 4፥6። ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና አገልግሎት ተጨምሬ ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ፥ ደስ ብሎኛል፤ ከሁላችሁም ጋር አብሬ ደስ ብሎኛል፤ ፊል. 2፥17።

ከላይ ካየናቸው መሥዋዕቶች አንጻር ሲታይ አሥራት ለጌታና ለቤቱ ሥራ የምንሰጠው በጣም ትንሹ ስጦታችን ነው። የመቄዶንያ ሰዎች ከብልጽግናቸው ሳይሆን ከድህነታቸው የሰጡት የመስጠትን በረከት ስለተለማመዱ ነው፤ 2ቆሮ. 8 እና 9።

መስጠት ደግሞ በረከት ብቻ ሳይሆን ብጽዕናም ነው፤ እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ፦ ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ። ሐዋ. 20፥35። በአዲስ በአዲስ ኪዳን አሥራት በግዴታ አይከፈልም፤ ክፍያም አይደለም፤ በውዴታና በፍቅር ግን ይሰጣል።

* * * * *

19. በቅዱሳን ስም ዝክር ማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው?

ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም። (ማቴ. 10፥41-42)

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ለምን ትዘክራላችሁ ሲባሉ ይህንን ቃል ጠቅሰው መጽሐፍ ቅዱስ ያዛል ይላሉ ይህ ምን ያክል እውነት ነው ወይም ይህ ስፍራ ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ማ. መ.

ማ. መ.፥ አንድን ጥቅስ ከስፍራው ነቅለን ማየት አይኖርብንም። ይህ ክፍለ ምንባብ ወደ ላይ ከፍ ብለን ጠቅላላ አሳቡን ስናጤን ስለ ስደት ነው የሚናገረው። በጌታ ስም የሚሰደዱትን ስለመቀበልና ስለመርዳት ነው የሚናገረው። ጠቅላላውን ማቴ. 10ን ማንበብ ካልቻልን አሳቡን ጨርሶ አናገኘውም። ምዕራፉ በ12ቱ ሐዋርያት መመረጥና መላክ ይጀምርና ተልእኳቸውን በቅደም ተከተል ያወሳል። ከዚያ የክርስቶስ ስለሆኑ ብቻ የሚደርስባቸውን ስደትና መከራ በመተንተን ይቀጥላል። በዚህ የስደት ዐውድ ውስጥ ነው ለደቀ መዝሙር በደቀ መዝሙር ስም ቀዝቃዛ ውኃ መስጠት የተነገረው። ለደቀ መዝሙር በደቀ መዝሙር ስም ቀዝቃዛ ውኃ መስጠት ማለት ደቀ መዝሙር በመሆኑ እንደ ማለት ነው እንጂ ለአንድ ደቀ መዝሙር በሌላ ደቀ መዝሙር ስም ውኃ ማጠጣት ወይም ዝክር ማድረግ አይደለም።

በአገራችን ልማዳዊ ሃይማኖት የሚዘክሩ ሰዎች መከራ የሚቀበሉ ስደተኞችን የጌታ ስለሆኑ፥ ነቢያት ስለሆኑ፥ ጻድቃን ስለሆኑ፥ ወይም ደቀ መዛሙርት ስለሆኑ መቀበላቸው ነው? በእውነት የጌታ የሆኑ ስደተኞችን የጌታ ሆነው መከራ ስለደረሰባቸው ተቀብለው የሚረዱ ከሆኑ ጌታንና የጌታ የሆኑትን የሚወድዱ ሰዎች የመሆናቸው ምስክር ነው። ለሥራቸውም ዋጋ አላቸው። ልክ ዕብ. 6፥10 እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና። እንደሚለው ማለት ነው። እንዲህም ሆኖ ይህ ሥራ ያድናቸዋል ማለትም አይደለም።

መዳን በጸጋ እንጂ በሥራ አይደለምና። ከተዳነ በኋላ የሚደረግ ሥራ ግን ዋጋ አለው። ከተዳነ በኋላ።

በጥያቄህ መሠረት በአገራችን የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ በጻድቃንና ነቢያት ስም የሚደገሰው ድግስና ዝክር ስደተኛ ክርስቲያኖችን መርዳት ነው ወይስ ወደሞቱ ጻድቃን፥ ነቢያት፥ ደቀ መዛሙርት የሚደረግ ተማጽኖ ነው? በግልጽ እንደሚታየው ተማጽኖ ነው። ወደሞቱ ጻድቃንና ደቀ መዛሙርት መለመንን መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፋል? ያስተምራል? አይደግፍም፤ አያስተምርም።

* * * * *

20. ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት ከማርያም አልወሰደም ወይ?

ሰላም ወንድም zelalem እባክህ እችን ነገር አስረዳን እየሱስ የውርስ ሀትያት original sin ከማርያም አልወሰደም ወይ? ወይስ ማርያም ትለያለች ? ካልወሰደ ሰው ነው ማለት ይቻላል ወይ? ደሞስ ካልወሰደ ልምን ትንሳኤ ልይ ስጋው ተለወጠ? Please our bible study is waiting to know the truth. we are christians/protestant/ so we want to know our beliefs may God bless you moreover thank you (ም. ኢ.)

ሰላም (ም. ኢ.) ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት ከኖረበት ኃጢአተኛ ነው ማለት ነው፤ ከሆነ እንኳን ሌላውን ራሱንም ለማዳን ባልቻለም ነበር። ቢበዛ ደግሞ ራሱን ብቻ ባዳነ ነበር።

ኢየሱስ በማርያም ማኅጸን ያደረው በልዩ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር (መንፈስ ቅዱስ ይጸልልሻል በተባለው) ነው። ኢየሱስ አስቀድሞ የነበረው ፈጣሪ መሆኑን አንዘንጋ። በማርያም ማኅጸን ሲያድር ሥጋ ሊሆን ነው። ማንም በማኅጸን ያለ ሕጻን የሚያድግበትን ምግብ ብቻ ከእናቱ ይወስዳል እንጂ ከእናቱ ደም እንኳን አይወስድም። ይህ ሰውን ብቻ ብንመለከት ነው። ሰው የሁለቱም የእናትም የአባትም ውጤት መሆኑን እናውቃለን። እንዲያም ሆኖ እንኳን በማኅጸን ያለ ሕጻን ደምንም ከእናቱ አይወስድም። ስለዚህ ነው የእናትና የልጅ ደም አንድ ዓይነት (የደም ዓይነት እና RH factor ማለቴ ነው) የማይሆነው። ስለዚህም ነው ደም ከእናት ወደ ልጅ ስለማይተላለፍ የኤድስ ሰለባ የሆኑ እናቶች ንጹሕ ልጅ የሚወልዱት።

ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት እንደሌለው ለማስረዳት የሚከብዳቸው ማርያምን ከኃጢአት ወይም ጥንተ አብሶ ነጻ ናት ብለው የሚያስተምሩት ስሕተት ይህንን ለመሸፈን ነው። ማርያም ከጥንተ አብሶ ነጻ መሆኗን ከቃሉ አናገኝም። ይህ የተፈጠረ የሰዎች ትምህርት ነው። ራሷ የኢየሱስ እናት ማርያም ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ

በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤ ብላለች፤ ሉቃ. 1፥47። በመድኃኒቷ ሐሴት ካደረገች መድኃኒት አስፈልጓት ነበር ማለት ነው። መድኃኒት ወይም አዳኝ ካስፈለጋት ኃጢአተኛ መሆኗም አይደል? በኦርቶዶክስና በካቶሊክ እምነት እንደሚባለው ማርያም ከሌሎች የሰው ልጆች ፍጥረት የተለየች አይደለችም። በሉቃ. 1፥28 ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። ነው የተባለላት እንጂ ከሴቶች መካከል የተለየሽ ነሽ አልተባለላትም። የተለየች ከሆነች እርሷ ኃጢአት የሌለባት መሥዋዕት ሆና ልታድነን ስትችል ኢየሱስ በሥጋ መምጣት ባላስፈለገውም ነበር።

ትንሣኤው ላይ ሥጋው ለምን ተለወጠ የሚለው ጥያቄ ግልጽ አይደለም። በመጽሀፍ ቅዱስ ከሞት የተነሡና ተመልሰው የሞቱ ሰዎች አሉ። እነዚህ የነበራቸው ሥጋ ወይም አካል ቀድሞ የነበራቸው ነው። የኢየሱስ የትንሣኤው አካል የትንሣኤ አካል ወይም መንፈሳዊ አካል ነው። ማንነቱ ተጠብቆ፥ ሰዎች ሲያዩት ታይቷቸው፥ ዳሰውት አውቀውታል። ይህ ዓይነት አካል እኛም ከትንሣኤ በኋላ የሚኖረንን የራሳችን መንፈሳዊ አካል ያንን የሚመስል ነው። በዚህ ለኃጢአት፥ ለተፈጥሮ ሕግጋትና ለሞት በሚሸነፍ ሥጋና ደም ለዘላለም ልንኖርና መንግሥቱን ልንወርስ አንችልም። ለዚያ መንግሥት የሚሆን አካል ያሻናል። ያም መንፈሳዊ አካል ነው፤ 1ቆሮ. 15ን በሙሉ ተመልከቱት።

አዳም በኃጢአት ሲወድቅ ሰው ሁሉ በእርሱ ውስጥ ነበረና ሰው ሁሉ ነው የወደቀው። ይህ ጥንተ አብሶ (original sin) የሚባለው ነው። ኢየሱስ የአዳም ፈጣሪ እንጂ በአዳም ውስጥ አልነበረምና ኢየሱስ የዚህ ኃጢአት ተካፋይና ተሳታፊ አይደለም። ጥንተ አብሶ የቀደመወን አዳም የተፈጠረበትን የጽድቅ አቋም ከውድቀት ወይም ከኃጢአት በኋላ እንዳጣው ባለ የወደቀ ሁኔታ መገኘት ማለት ነው። በኃጢአት ከእግዚአብሔር ክብር ጎድሎ መገኘት ነው፤ ሮሜ. 3፥9-23። ሁሉ ከኃጢአት በታች ሆነዋል፤ እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከሰናቸዋልና፤ ሮሜ 3፥9።

ጥንተ አብሶ በሰው ላይ መሠልጠኑን በእርግጥ የምናውቀው ሰው ሁሉ ሟች በመሆኑ ነው። ባይሆን ኖሮ እያንዳንዱ ፍጡር ልክ አዳም በመጀመሪያ በተገኘበት ሁኔታ ከነምርጫው ሊገኝ በተገባ ነበር። እያንዳንዱ ፍጡር በባዶ ገጽ ላይ አዲስ ታሪክ ባስጻፈ ነበር። ግን አይደለም። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። 1ቆሮ. 15፥22።

በማርያም ማኅጸን ያደረው በልዩ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር (መንፈስ ቅዱስ ይጸልልሻል በተባለው) መሆኑ ተጽፎአል እንጂ በዝርዝር ይህ ነገር እንዴት መሆኑ አልተጻፈም። ያልተጻፈውን ከተጻፈው ወጥተን ማብራራት አንችልም። መንፈስ ቅዱስ በላይዋ ያጠላው ወይም የጸለለው ምን መሆኑ፥ እንዴት መሆኑ፥ ዝርዝር ምክንያቱ ቢጻፍልን ብዙዎች ይወዱ ነበር። ግን አልተጻፈም። አለመጻፉ የራሳችንን እንግዳ ትምህርት

እንድንፈጥር ሊያደርገን የተገባ ግን አይደለም። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ኃጢአትን ያላወቀ፥ በእርሱም ኃጢአት የሌለ መሆኑን በደንብ ይገልጣል፤

እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው። 1ቆሮ. 5፥21።

እርሱም ኃጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፥ በእርሱም ኃጢአት የለም። 1ዮሐ. 3፥5

ይህ የኢየሱስን ማንነት የሚናገረው እውነት ግልጽ ነው። ስለ እኛ ኃጢአተኝነት የሚናገረውም ግልጽ ነው፤ ሮሜ 5 በጠቅላላው፥ በተለይም ከቁጥር 12-21፤ 1ቆሮ. 15፥21-22፤ የአዳም በመሆናችን ኃጢአተኞች መሆናችንን ይህንን ያስተምራል። መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት ወደ ዓለም የመጣበትን መንገድ ደጋግሞ ሲገልጥ ሔዋንን ሳይሆን አዳምን ነው የሚጠቅሰው። አንዳንድ ሊቃውንት ኢየሱስ ከወንድ ዘር ስላልተወለደ ነው ጥንተ አብሶ የሌለበት ይላሉ። እርግጥ ኢየሱስ ከሴት የተወለደው ተብሎአል፤ ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ ገላ. 4፥4። ይህ ከሴት ብቻ መወለድ ሴቲቱ ከወንድ ዘር የተወለደች እስከሆነች የሷ ዘር ከጥንተ አብሶ ነጻ የማድረግ ትምህርት የለውም። ቀደም ሲል እንዳልኩት በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ነገረ ማርያም፥ ማርያም ከጥንተ አብሶ የጸዳች ናት የሚለው ትምህርትና ይህንን ትምህርት ለመፍጠር የተጎዘጎዘው ጉዝጓዝ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የሌለው ፈጠራ ነው።

ኢየሱስ በሥጋ ሲመጣ የመጣበት ሥጋ ሁኔታ ያለ ኃጢአት ይሁን እንጂ (ኃጢአትን አይወቅ፤ በእርሱ ኃጢአት አይኑር እንጂ) ሰው ነው። የሴቲቱ ዘር የተሰኘውም ከዔድን ገነት ገና ሳይወጡም ቢህን ከወደቁ በኋላ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ሰው ሲሆን ከኃጢአት በቀር የሰውን ድካም ሁሉ ተጋርቷል። የሕማም ሰው ሆኗል፤ ደክሟል፤ አልቅሷል፤ ተሰቃይቷል፤ ሞቷል፤ ወዘተ። ስለዚህ የለበሰው ሥጋ ምናባዊና የኛን የማይመስል ነው ማለት አይደለም።

እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ፥ እርሱ ደግሞ በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፥ ይኸውም ዲያብሎስ ነው፥ በሕይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ሁሉ ነጻ እንዲያወጣ፥ በሥጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ። ዕብ. 2፥14-15።

* * * * *

21. ደም መስጠት ወይም መቀበል እና የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው?

ዘሌ ሁለት ጥያቂዎች በውስጤ ይመላለሳሉ። በቂ ሚላሽ የሠጠኝ ሠው እስካውን የለም። ጥያቂዎቹም እንደሚከተሉ ናቸዉ።

፩. ደም መስጠትም (blood donation) ሆነ መቀበል (blood transfusion) መጻፍ ቅዱሳዊ ነው ወይ?

፪. ማንኛውም ዓይነት የወሊድ መቆጣጠርያ መጠቀምስ? እነዚህ ጥያቂዎች በመጻፍ ቅዱስ አስደግፊህ እንደምታብራራልኝ በትህትና እጠይቃለው። ተ. ማ.

ተ. ማ. ሁለቱም ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍም ሆነ ቅዋሜ የሌለባቸው ከዘመናዊ እውቀት ጋር የተያያዙ የስነ ምግባር (ethics) ጉዳዮች ናቸው። የደም ልገሳም የወሊድ ቁጥጥርም የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጦች አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ሳይንሳዊ እውነቶችን ቢይዝም በመጀመሪያ ሳይንሳዊ እውቀት መማሪያ መጽሐፍ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ችግር ምንነትና የዚያም ችግር መፍትሔ አመልካች መጽሐፍ ነው። ችግሩ ኃጢአት፥ መፍትሔውም ኢየሱስ ነው።

1. ደም መለገስና መቀበል።

ስለ ደም በዘዳ. 12 ቁጥር 16፥ 23 እና 24 ደሙን ግን እንደ ውኃ በምድር ላይ አፍስሰው እንጂ አትብላው። . . . ነገር ግን ደሙ ነፍሱ ነውና፥ ነፍሱንም ከሥጋው ጋር መብላት አይገባህምና ደሙን እንዳትበላ ተጠንቀቅ። በምድር ላይ እንደ ውኃ አፍስሰው እንጂ አትብላው። ተብሎ ተጽፎአል። በዘሌ. 17፥11 ደግሞ የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት። ይላል።

በብሉይ ኪዳን ብዙና የተለያዩ መሥዋዕቶች ቢኖሩም ትልቁ የስርየት መንገድ የደም መሥዋዕት ነው። ደም ፈሰሰ ማለት ሕይወት ፈሰሰ ማለት ነው። ደም ሕይወት አለበት፤ ደም የሚያስተሰርየውም ከሕይወቱ መፍሰስ የተነሣ ነው። የኃጢአት ማስተስረዩ ዋና አሳብም የሕይወት ዋጋ መከፈሉ ነው። ኃጢአት ደመወዝ አለው፤ ደመወዙም ሞት ነው። የሞት ክፍያ ሞት ነው ማለት ዋጋውም ሕይወት ነው ማለት ነው።

ደም መስጠትንና መቀበልን የሚያወግዙ ሰዎች ዋና መከራከሪያ ነጥብ ደም ሕይወት ስላለበትና ሰዎች ደምን እንዳይበሉ የተነገረባቸው ከላይ ያየናቸውና እነሱን መሳይ ክፍሎች በመኖራቸው ነው። እጅግ ተለጥጠው የሚነገሩት እነዚህ ናቸው። መብላት ከተከለከለ በመርፌና በቀሰም መውሰድማ ከዚያም የባሰ ነው የሚል ነው። ከዚህም ተያይዞ የብልቶች ልዋጭ እና ተከላንም አብረው ያወግዛሉ። 'ያ የአካል ብልቱን የምቀበለው ሰው ምን ይሁን ምን አላውቅም። በትንሣኤ ቀንም ሌላ ሰው ሆኜ

አልነሣም።' የሚል ነው። በሳይንሱ ከሄድን፥ በሴል ደረጃ አንድ ሰው በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሴሎቹ በሙሉ በሌሎች ሴሎች ይቀየራሉና የነበረውን ራሱን አይደለም። ይህ ግን እውነተኛ ማንነቱን አይለውጠውም። በእውነቱ የበግ ሥጋ ብንበላ በግ እንደማንሆነው፥ የበግ ዓይን ቢተከልልንም በግ አንሆንም።

በአንጻሩ፥ የአንድ ሰው ኩላሊቶች ቢበላሹና የሌላ ሰው አንድ ጤናማ ኩላሊት ቢገባለት ያንን ሰው መሆን አይደለም። ያ ሰው ጤናማ ኩላሊት አግኝቶ በሰውነት ፈሳሾች መጥራት ከመመረዝ ቢተርፍ ስለ እግዚአብሔር ፍጥረትና ለሰው ልጆች ስለሰጠው ጥበብ በማመስገን የሚቀበሉም አሉ። ወደ ደም ልገሳና ቅበላ ስንመጣም ከዚህ የተለየ አይደለም። በደም ፍሰት ሊሞት የሚችል ሰው በተለገሰ ደም ቢተርፍ ይህን ሌላ ሰው መሆን የሚመስላቸው ያሉትን ያህል በምስጋና የሚቀበሉም አሉ።

በኔ መረዳት በብሉይ ኪዳን ደምን እንዳይበሉ ለእስራኤል ልጆች የተነገረውን ሕግ ከተባለውም አስፍተንና ለጥጠን ወደ አዲስ ኪዳን አማኞችና ወደ ሕክምና ሙያዊ እርዳታ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ስሕተት ነው። ያልተመረዘና ያልተበከለ እስከሆነ ድረስ ደምን መለገስም ሆነ መቀበል መድኃኒት ከመውሰድ የተለየ አይደለም። ሆኖም በእውቀትና በመረዳት፥ በኅሊና ዳኝነትም፥ 'የለም፤ አልፈልግም።' በሚሉ ላይ አላግባብ የሆነ ጫና መፍጠርም ተገቢ አይደለም እላለሁ።

2. የወሊድ መቆጣጠሪያ።

የወሊድ መቆጣጠሪያን በተመለከተም ከላይ እንዳልኩት መሳይ ነው። ይህም ጉዳይ የስነ ምግባር (ethics) እና ከዘመናዊ የሕክምና ሙያ ጋር የተቆራኘ ጉዳይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ልጆች ያሏቸው እና ጥቂት ብቻ ልጆች ያሏቸው ሰዎች አሉ። የወሊድ መከላከያ ተጠቅመው መሆኑን ግን አናውቅም። አልተጻፈልንም።

መጽሐፍ ቅዱስ የወሊድ መከላከያ ስለመኖሩ አያስተምርም። በዘፍ. 38 አውናን የሟች ወንድሙን ሚስት ካገባ በኋላ የሚወለደው ልጅ በወንድሙ እንደሚጠራና ለእርሱ እንደማይሆን ስላወቀ ከወንድሙ ሚስት ጋር ከተኛ በኋላ ዘሩን በእርሷ ውስጥ ሳይሆን በምድር ያፈስስ እንደነበር ተጽፏል። ይህንን በአውናን ስም አውናኒዝም (Onanism) ይሉታል። በቴክኒካዊ ስሙ Coitus interruptus ይባላል። ከኮንደም አጠቃቀም ጋር ተቀራራቢ ነው። አውናን የተቀሰፈው ማድረግ ያለበትን ቤተሰባዊ ኃላፊነት ስላልፈጸመ እንጂ በተለይ ይህን ስላደረገ አይደለም። ከዚህ ሌላ ከወሊድ ክልከላ ጋር የተቆራኘ ክፍል የለም።

በቤተ ክርስቲያን የወሊድ መከላከያ ነጻነትን የሚጠቀሙ የመኖራቸውን ያህል የሚያወግዙም አሉ። የሚያወግዙት ቃሉ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ብሎ በዘፍ. 1 እነ አዳምን፥ በዘፍ. 9 ደግሞ የኖኅን ልጆች ስላዘዘ መከልከል የለበትም ይላሉ። ደግሞም፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ስለሆኑ መቀበል እንጂ መከላከል የለብንም

ይላሉ። መከላከያን የሚደግፉ ደግሞ አቅምንና ኃላፊነትን በማገናዘብ የሚወስኑት ግላዊና ቤተሰባዊ ውሳኔ ነው።

ከላይ ስለ ደም ልገስናና መቀበል እንዳልኩት ይህም ጉዳይ በእውቀትና በመረዳት፥ በኅሊና ዳኝነትም፥ 'የለም፤ ከጥቂት በላይ መውለድ አልፈልግም።' በሚሉ ላይ፥ ወይም፥ 'አዎን፥ መውለድና መብዛትና መባዛት ታዝዣለሁና አትንኩኝ።' በሚሉም ላይ አላግባብ የሆነ ጫና መፍጠር ተገቢ አይደለም እላለሁ። የሚያበረታቱ ወይም የሚያወግዙ የመኖራቸውን ያህል፥ ሙሉ ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ለባለ ጉዳዮቹ መተውን የሚመርጡ ብዙዎች ናቸው። ሁለቱም ጉዳዮች በቃሉ ውስጥ በግልጽ የተደገፉም፥ የተከለከሉም አይደሉም።

* * * * *

22. 'ሜጀር ዋን' አዲስ ማዕረግና ከፍተኛ መንፈሳዊ ሥልጣን ነው?

> ሰላም ጋሽ ዘሌ፥ ሜጀር ዋን አዲሱ ማዕረግ ነው? ወይስ ከፍተኛው የእድገት እርከን ነው? የሰሞኑ ሰውዬ እንደዚያ ሲጠራ አንብቤ ነው። ው. ታ.

ሰላም ው. ታ. ይህንን ጥያቄ የሚመስል [ከዚህ በፊት] እስራኤል ዳንሳ ከነቢይነት ወደ ሐዋርያነት እንዲሻገር በተቀባ ጊዜ ይህንን ጥያቄ በሌላ ጠያቂ ተጠይቄ መልሼ ነበር። ከስር ስለዚህኛውም ጥቂት እላለሁ፤ ያ የያኔው መልስ በቀጥታ ይህ ነው፤

ስንታየሁ፤ ይህ እኮ ምንም ግራ አያጋባም። ጸጋና አገልግሎት ማዕረግና ሹመት አይደለም። በማዕረግ ከመቶ አለቃ ወደ ሻምበል፥ ወደ ሻለቃ፥ ወደ ወዘተ፥ ይታደጋል እንጂ ከነቢይ ወደ ሐዋርያ ማደግን ቃሉ አያስተምርም። ሐዋርያት ደግሞ አንድም ጌታ የሾማቸው አሥራ ሁለቱ ናቸው፤ ወይም በቃሉ ትርጉም ብንሄድ ወንጌል ወዳልደረሰበት ጠፍ አገር ሄደው ወንጌል የሚያበስሩ ናቸው። እነዚህ ሁለተኞቹ እንደ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን የሚላኩ እና አደራ ለተሰጡባት ቤተ ክርስቲያን መጥተው የሚዘግቡ ናቸው እንጂ በአንድ ሰው የወይራ ወይም የጉሎ ዘይት ተቀብተው የትም ጠፍ አገር ሳይሄዱ እንደ ዔሊ ዘማች እዚያው የሚከርሙ አይደሉም። ይህ እከከኝ ልከክህ ነው እንጂ ሌላ ምንም አይደለም።

የትናንት በስቲያው ነቢይ (ነቢይ አይደለም እንጂ) ትናንት በሞግዚቱ [በሀብታሙ ጳውሎስ] ሜጀር ነቢይ ተደረገ። ዛሬ ደግሞ ሐዋርያ ሆነ እንበልና፤ ነገ ምን ሊደረግ ይሆን? ከነገ ወዲያስ? እያደገ ስለመጣ ነገሩ ሹመት መሰለኝ። ሿሚውስ ምንድን ነው ማዕረጉ? አሁንም ቄስ? ወይስ ምን? ይህ ጉዳይ በቀደም እንደለጠፍኩት የሚሰለችና ቶሎ አርጅቶ የሚለወጥ ልምምድ ነው። ይህ ሹመት ልክ እንደ ዕቃ ዕቃ ጨዋታ ከሆነ

ከ'ነቢይ' ወደ 'ሐዋርያ' ማደግ ይቻላል፤ ከሜጀር ሐዋርያም ወደ ሱፐር አፖስል ማደግ ይቻላል። ግን የቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም።

. . . . .

ይህ ያኔ ነው። ወደ ዛሬው ጥያቄ ወደ ሜጀር ዋን ስንመጣም ይህ ማዕረግ በመጽሐፈ ቡሺሪ እና ሌሎችም የአፍሪቃ ሐሰተኛ ነቢያትና ጠንቋዮች እንደ ማዕረግ የሚውለበለብ ባንዲራ ነው እንጂ ከቶውኑም ማዕረግ አይደለም። እንዲህ ያለውን ማዕረግ እነ ጳውሎስ ስሙንም እንኳ ሳይሰሙት ኢዮብ ጪሮን የመሰለ የአገራችን ድራማ ተዋኝ መቀዳጀታቸው ድራማና ተውኔት ነው። በቃ ይኸው ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሐዋርያ ነበረ። የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ግን እርሱ ሐዋርያ እንዳልሆነ ወይም ከሌሎቹ እኩል እንዳልሆነ ሲናገሩ ብቻ፥ ከእነዚህ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በአንድ ነገር እንኳ እንደ ጎደልሁ ራሴን አልቆጥርም። 2ቆሮ. 11፥5 እና በመመካቴ ሞኝ ሆኜአለሁ፤ እናንተ ግድ አላችሁኝ፤ እናንተ እኔን ልታመሰግኑ ይገባ ነበርና። እኔ ምንም ባልሆን እንኳ፥ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በምንም አልጎድልምና። 2ቆሮ. 12፥11 ብሎ ጻፈ። ይህንን የጻፈውም ግድ ሆኖበት ነው። ሐዋርያ መሆኑን ካላወቁ የሰበከውን ወንጌልና በሥልጣን ያስተማረውን ትምህርት፥ የጻፈውንም መልእክት እንደ እግዚአብሔር ቃል ላይቀበሉት ነው።

ሜጀር ዋን ራሱን በራሱ የቀባው ቡሺሪ ለግሉ የሰጠው ማዕረግ ነው። ይህ አሳች አገራችን መጥቶ አዚሙን ረጭቶ ከሄደ በኋላ ነው አማኙ የአገራችን ሕዝብ ነሆለልና ሐሰተኞች የሚሸልቱት በግ እና የሚዘግኑት ቆሎ የሆነው። ሌሎችም ጥቂት የአፍሪቃ ሐሰተኛ ነቢያት የሚጠሩበት ማዕረግ ነው። በእውነቱ ይህ የስስታቸውንና የሥልጣን ጥማታቸውን ጥግ የሚያሳይ ነገር እንጂ ማዕረግም አይደለም።

ዱሮ ልጆች ሆነን ሌባና ፖሊስ ስንጫወት ሌባው ተይዞ መጣና ለፖሊሱ፥ 'ሻለቃ ይኸው ሌባውን እጅ ከፍንጅ' ብለን ስንሰጠው፥ ተናደደና፥ 'እንዴት ሻለቃ ትለኛለህ? መቶ አለቃ እኮ ነኝ!' ብሎ አምባረቀብን! ማዕረግ የተቀነሰበት ነው የመሰለው፤ ያኔ መቶ ነዋ ለኛ ትልቁ ቁጥር! ሺህ አትታወቅም።

ትልቁን ማንነት፥ የእግዚአብሔርን ልጅነት ያልተቀዳጁ ሰዎች የሚረኩ እየመሰላቸው በፈጠሩት ድሪቶ ተሽሞንሙነው ለመታየት መጣራቸው እንግዳ ነገር ሆኖ መታየት የለበትም። በተለይም በአሁኑ ወንጌላዊ ክርስትና በወሮ በሎች እየታገተ ባለበት ጊዜ ይህ አዲስ ሆኖ መታየት የለበትም። ጺጋ ስጦታ እንጂ የሚያድግ ማዕረግ አይደለም።

* * * * *

23. ሙስሊሞች፥ ‘ኢየሱስ እኔን አምልኩኝ ያለበትን ቦታ አሳዩን’ ለሚሉት ጥያቄ ምን መልስ አለህ?

ጋሽ ዘሌ ሙስልሞች ኢየሱስ እኔን አምልኩኝ የለበትን ቦታ አሳዩን ለምሉት ጥያቄ ምን መልስ አለህ? JD

ሰላም JD፤ ጥሩ ጥያቄ ነው። ችግሩ ግን፥ እነሱ የሚፈልጉትን ቃል ቀምረው፥ አስተካክለው ቀርጸው ያንን ቃል አምጡ ሲሉ ነው።

በመጀመሪያ እንደ መንደርደሪያ ማወቅ ያለብን ሙስሊሞች ስለ ኢየሱስ ያላቸው አመለካከት ፈጽሞ ከአዲስ ኪዳን የተለየ መሆኑን ነው። የቁርአኑ ኢሳ እና የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ የተለያዩ ናቸው። ዐረብኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ኢሳ አይሉትም፤ የሱዋ ነው የሚሉት። ያም አንድ ያለመሆኑን ለማሳወቅ ነው። ስለዚህ ከጅምሩ ኢየሱስና ኢሳ አንድ አለመሆናቸው ይሰመርበትና ኢየሱስ እኔን አምልኩኝ ያለበትን ቦታ አሳዩኝ ሲሉ መሠረታዊ የማንነት መዛባት መኖሩን በማሳየት መጀመር አለብን።

ሁለተኛ፥ ለሙስሊሞች ኢየሱስ (በነሱ ኢሳ) እንደ አዳም ብጤ ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ ኢየሱስ የሥላሴ ሁለተኛ አካልና ፍጹም ሰው፥ ፍጹም አምላክ የሆነ ነው። ሰው የሆነው በሥጋው ኃጢአታችንን ለመሸከምና በደሙ ስርየትን ሊሰጠን ነው። ሰው ሆኖም አምላክ ነው። ስለዚህ አምላክ እንደመሆኑ መጠን አምልኩኝ ቢልም ባይልም ሊመለክና ሊሰገድለት የተገባው ነው።

ሦስተኛ፥ ስለ ኢየሱስ ለማወቅ ትክክለኛው ምንጭ ደግሞ ከኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት በኋላ ወደ 700 ዓመታት ዘግይቶ የተጻፈ ሰነድ ሳይሆን ራሳቸው ደቀ መዛሙርቱ፥ ሐዋርያቱ የጻፉት ምስክርነት ነው። ሲጀመር ሙስሊሞችን መጠየቅ የተገባው ጥያቄ፥ የመጽሐፉ ሰዎች የተባልነውን የክርስቲያኖችን መጽሐፍ፥ አዲስ ኪዳንን ይቀበሉና አይቀበሉ እንደሆነ መጠየቅ ነው። እንቀበላለን ካሉ ስለ ኢየሱስ ጌትነት (ጌትነት ሲባል አምላክነት ነው) መነጋገር ይቻላል። ችግሩ እንቀበላለን ይሉና ግን ተበርዟን የናንተ መጽሐፍ የሚሉት ፈሊጥ ነው። የኢስላም ነቢይ ሙሐመድ የክርስቲያኖችን መጽሐፍ ተበርዟል አለማለቱን መግለጥ አስፈላጊ ነው። ደግሞም በሙሐመድ ዘመን የነበረው እና አሁን በእጃችን ያለው አዲስ ኪዳን ከቶም አንድ መሆኑን በብዙ ማረጋገጫ ሰነዶች ማረጋገጥ ተችሏል።

አራተኛ፥ ኢየሱስ፥ ‘እኔን አምልኩኝ’ ብሎ በቀጥታ የተናገረበትን ቦታ አሳዩን የሚሉ ሰዎች ዋና መነሻ፥ ‘ይህንን አላለምና አምላክ አይደለም’ የሚል ነው። ግን መስተዋል ያለበት ነጥብ፥ ሥጋ ለብሶ የመጣ ጌታ አምላክነቱን ለሰዎች ለማረጋገጥ፥ ‘አምላክ ነኝና እኔን አምልኩኝ’ እያለ በመዞር ማወጅ የለበትም። በቃሉና በሥራው ማንነቱን ገልጧል ወይስ አልገለጠም? ያላቸው ነገሮችና ያደረጋቸው ድርጊቶች አምላክ ብቻ ማድረግ

ወይም መሆን ያለበት ከሆነና እርሱ ያንን ያለውን ነገር ካልሆነ ፈጸሞ ሐሰተኛ እንጂ ሙስሊሞች እንደሚሉት ነቢይም አይደለም።

አምላክ መሆኑን አረጋጋጭ ነገሮች ከኖሩ፥ ‘እኔን አምልኩኝ’ ብሎ ባይናገርም ሊመለክ የተገባው ነው። እንዲህ ማለት አለበት ብለን ቃል ፈጥረን መጠየቅ ያለብን እኛ አይደለንም። አምላክ መሆኑን ደግሞ አረጋጋጭ እጅግ ብዙ ትምህርቶቹና ያደረጋቸው ተአምራት፥ እንዲሁም ከአምላክ በቀር ማንም ሰው ሊያአደርጋቸው የማይችላቸው ነገሮች መኖር ነው። እነዚህ በወንጌላቱ በሙላት ተዘርዝረዋል። በቃሉ ተፈጥሮን ማዘዙ፥ ኃጢአትን ይቅር ማለቱ እንደ አብነት ይታያሉ።

ማምለክን በተመለከተ፥ ማምለክና ማመን አንድ ናቸው አይደል? ደግሞም ማምለክና መስገድም አንድ ናቸው። እንደዚያ ከሆነ ኢየሱስ በእርሱ እንድናምን የተናገረባቸውን በርካታ ጥቅሶችና ሐዋርያቱም በእርሱ እንድናምን የተናገሩበትን፥ እንዲሁም የተሰገደለትን ክፍሎች እንመልከት፤ ጥቂቶቹ እነሆ፤

ማቴ. 18 በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መስጠም ይሻለው ነበር።

ዮሐ. 6፥47 እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።

ዮሐ. 7፥38 በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ።

ዮሐ. 12፥44 ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ፦ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤

ዮሐ. 12፥46 በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።

ዮሐ. 14፥1 ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።

ዮሐ. 3፥14-16 ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል። በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

ዮሐ. 6፥40 ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።

ዮሐ. 7፥39 ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።

ሐዋ. 10፥43 በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።

ሮሜ 10፥11 መጽሐፍ፡- በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም ይላልና።

መስገድ ወይም ስግደት ለሰላምታና አክብሮትም የሚደረግ ቢሆንም ለአምልኮም ነው። መስገድን በተመለከተም ኢየሱስ ሲሰገድለት ሰዎች ወይም መላእክት እንዳደረጉት፥ አታድርግ ብሎ አልተከላከለም። ለምሳሌ፥ ዮሐ. 9፥38-39 'እርሱም፡- ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም።' ይላል። ጌታም አትስገድ በማለት ፈንታ፥ 'የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ።' አለው። በተጨማሪ፥ ማቴ. 14፥33 በታንኳይቱም የነበሩት፡- በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት። ማቴ 28፥9 እነሆም፥ ኢየሱስ አገኛቸውና፡- ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። ሌሎችም ጥቅሶች አሉ።

ኢየሱስ የሆነውን ማንነቱን በእርግጥ ሆኖ ከሆነ ጌታ ነው ብለን ወድቀን እንሰግድለታለን እንጂ ነቢይ ነው ብለን አንሸነግልም። ካልሆነ ግን ነቢይ ሳይሆን ውሸታም ነውና ነቢይ መባልም የለበትም። ደኅንነታችን የተመሰረተው ጌትነቱን በመቀበልና በማወጅ ላይ ነው፤ ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሮሜ 10፥9።

ይህ አዲስ ሆኖ መታየት የለበትም። ጸጋ ስጦታ እንጂ የሚያድግ ማዕረግ አይደለም።

* * * * *

24. በኤደን ገነት ውስጥ ዛፍ ተክሎ አትብሉ ለምን አላቸው? የዛፏ መኖር ለምን አስፈለገ?

> እግዚአብሄር አዳምና ሄዋን እንደሚበሉና እንደሚወድቁ ካወቀ ወይም እያወቀ በኤደን ገነት ውስጥ ዛፍ ተክሎ አትብሉ ለምን አላቸው? የዛፏ መኖር ለምን አስፈለገ? (መ. መ)

መ. መ.፥ ይህ መሠረታዊ ጥያቄ ነው። እኔም ራሴ ገና አዲስ ክርስቲያን በነበርኩባቸው በርካታ ዓመታት (አሁንም፥ ሁሌም አዲስ ክርስቲያን ነኝ) ደጋግሜ ጠይቄአለሁ። የዚህን ጥያቄ መልስ አንኳር የወሰድኩት መጀመሪያ መጻፍ ሀ ስል ከጻፍኩት (በኛ 1985) አዲስ ሕይወት የሚባል የትመማ መጽሐፍ ነው።

በመጀመሪያ የጥያቄው መነሻ የሆነውን ጥቅሱን በመጻፍ ልጀምር፤

እግዚአብሔር አምላክም ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፥ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ፤ በገነትም መካከል የሕይወትን ዛፍ፥ መልካምንና ክፉን የሚያስታውቀውንም ዛፍ አበቀለ። ዘፍ. 2፥9። እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡- ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ ነገር ግን መልካምንና ክፉን

ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና። ዘፍ. 2፥16-17።

የዛፏ መኖር ለምን አስፈለገ ለሚለው ጥያቄ አጭሩ መልስ ትርጉም ላለው የፍቅር ግንኙነት ነው።

በተን አድርጎ ለመረዳት ደግሞ የግንኙነትን መስፈርት መረዳትን ይጠይቃል። ግንኙነት ሲባል የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ኅብረት አስፈልጎት ነበር ማለት አይደለም። እርሱ በዘላለማዊ ግንኙነትና ኅብረት ውስጥ የሚኖር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ሦስቱ አካል፥ አሐዱ አምላክ ነው። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን፥ ወይም እኔንና አንተን የፈጠረው እርሱ ኅብረት አስፈልጎት ሳይሆን እኛ ኅብረት ይኖረን ዘንድ ነው። ዮሐንስ ስለዚህ ኅብረት ሲጽፍ በ1ዮሐ. 1፥3 እንዲህ ይላል፤ *እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።*

ኅብረት ከእርሱ ጋር ይኖረው ዘንድ ሰውን መፍጠሩ ድንቅ የቸርነት ሥራው ነው። ሰውን መፍጠሩ ምንም ግዴታ ኖሮበት ሳይሆን እንዲያው የቸርነቱና የነጎነቱ ብዛት ብቻ ነው። መፍጠሩ ደግሞ እንዲያው እንደ እንስሳ ሁሉ በልቶና ጠጥቶ፥ ወልዶና አሳድጎ፥ ኖሮና ሞቶ ያለ መታሰቢያ እንዲቀር ሳይሆን ትልቁን ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ያደርግ ዘንድ ነው። ለዚህም ነው ከእንስሳት የለየውን የራሱን እስትንፋስ እፍ ያለበት። የእግዚአብሔር እስትንፋስ ሰውን ከሌሎች ምድራውያን ፍጡራን ሁሉ ለይቶ ዘላለዋሚ ያደርገዋል፤ እግዚአብሔር ራሱ ዘላለማዊ ነውና።

ለግንኙነት ወይም ለኅብረት ደግሞ ፍቅርና ፈቃድ የግድ ያስፈልጋል። ለእንስሳዊ ግንኙነት ይህ አያስፈልግም። ለዚህ ደመ ነፍስ ብቻውን በቂ ነው። ለሰውና ሰው፥ እንዲሁም ለሰውና እግዚአብሔር ግንኙነት ግን ፍቅርና ፈቃድ ያስፈልጋሉ። ፍቅር ከፈቃድ የሚመነጭ ሲሆን ፈቃድ ራሱ ግን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሕይወት ቀጥሎ የሰጠው ትልቅ ስጦታ ይመስለኛል።

የዛፉ (መልካምና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ) መኖር አስፈላጊነት እንግዲህ እዚህ ላይ ነው። ይህ ግንኙነት በፈቃድ ላይ የተመሰረተ ለመሆኑ ምስክር፥ መፈተኛ፥ ማረጋገጫ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ፈቅዶና ወድዶ ነው። በእርሱ በኩል ፈቃድ አለ፤ መውደድም አለ። አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዶአልና ነው ቃሉ የሚለን። በዚህ ኅብረት ውስጥ በአዳም በኩልም የፈቃድና የፍቅር ግንኙነት ሊኖር ግድ ነው። ወድዶ ፈቅዶ የሚገባበት ግንኙነት ነው፤ ካልፈለገ፥ ካልወደደና ካልፈቀደ ላይገባ መብት አለው። ፈቃድ አለውና። አዳምና ሔዋን በገነት ሲኖሩ ሙሉ ነጻነት ነበራቸው። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈለግና ለመፈጸም፥ ኃጢአትንም ሳይሠሩ ለመኖር ችሎታ ነበራቸው።

እግዚአብሔር ሲጀመር አዳምንም፥ ዓለምንም ላይፈጥር ይችል ነበር። ዓለምም ባትፈጠር፥ እኛም ባንፈጠር ብለን እናስብ። ይህ ጥያቄም አይኖርም ነበር። ሌላው አማራጭ ዓለምን ፈጥሮ መልካምና ክፉ የሌለበት ማድረግ ወይም ስትፈጠርም

መልካምና ክፉ የሚባል ነገር የሌለባት አድርጎ መፍጠር ነው። ይህ ደግሞ፥ ሁሉ ልክ የሚሆንበትና ትርጉም የሌለው እንስሳዊ ኑሮ እንደሚሆን መገመት አይሳነንም። ሌላው ምርጫ አዳምን መልካሙን ብቻ እንዲመርጥ አድርጎ መሥራት ነው። የዚህ ችግር ደግሞ ፈቃድ አልባነት ነው። አድርግ የተባለውን ያለ ምንም ምርጫ፥ ያለ ምንም ጥያቄ፥ አማራጭ ሳይኖር፥ ጥቅምና ጉዳት ሳይታወቅ፥ የግንኙነት ትርጉሙ ራሱም ሳይታወቅ፥ ልክ እንደ ሰው-ሠራሽ ሮቦት የተሠራበትን ተግባር ብቻ እንዲፈጽም፥ እንዲያደርግ ሆኖ ተሠራ ማለት ነው። ከሮቦት ጋር ግንኙነት መመሥረት አይቻልም። ሮቦት ነፍስና መንፈስ የለውም። ነፍስና መንፈስን መፍጠር የእግዚአብሔር ብቸኛ ሥልጣንና ችሎታ ነውና ሰው ነፍስን የመስራት ጥበብ ሊኖረውም አይችልም። የመጨረሻው አማራጭ በቃሉ ውስጥ የተጻፈውን አዳም መፍጠር ነው። ምርጫ ያለው፥ ፈቃድ ያለው፥ መታዘዝና አለመታዘዝ የሚችለውን፥ መውደድና አለመውደድ የሚችለውን አዳም መፍጠር። እግዚአብሔር ይህንን ነው ያደረገው። ማናችንም ከዚህኛው አማራጭ በፊት ያሉትን አማርጮች የምንፈልጋቸው አይመስለኝም።

ከአማራጮቹ ሁሉ እውነተኛ ኅብረትና ፍቅር ያለበት ግንኙነት ሊኖር የሚችለው በዚህ ፈቃድ ባለበት፥ ምርጫ ባለበት ግንኙነት ውስጥ ብቻ ነው። ምርጫ የመኖሩ አስፈላጊነት እግዚአብሔር የሚፈልገው በምርጫችን የምንግገዛለት ሲሆን ነው።

አዳምን ሲፈጥር ምንም ምርጫ ስለሌለው ሳይሆን ሙሉ የምርጫ ፈቃድ እያለው፥ ግን በፈቃደኝነት እንዲወድደው እግዚአብሔር ስለፈለገ በዔድን ገነት ውስጥ እንዳይበላ ያዘዘውን ዛፍ አኖረ። ይህም እግዚአብሔርን ታዝዞ በኅብረት እንዲኖር ወይም እግዚአብሔርን መታዘዙ በአዳም ፈቃድ ላይ እንዲመሠረት ስለወደደ ነው። አሳዛኙ ክስተት፥ አዳምና ሔዋን ለጥቂት ጊዜ (ምን ያህል መሆኑ አይታወቅም) እግዚአብሔርን ወደው ከተከተሉ በኋላ አለመታዘዝን መረጡ። እናም ውድቀት ሆነ። እዚህ ላይ፥ 'ሰይጣን ባያስታቸው ኖሮ አይወድቁም ነበር፤ በመጀመሪያ ሰይጣን ለምን ተፈጠረ?' ሊባል ይችላል። የዚህም መልስ ከላይ እንደተመለሰው ያለ ተመሳሳይ ነው። ሰይጣን ሲፈጠር ሰይጣን ሆኖ አልተፈጠረም፤ እርሱም እንደ ሰው ሁሉ ፈቃድ ያለው መልአክ ነበረ። እርሱም ፈቃዱን ተለማምዶ፥ አለመታዘዝን መርጦ የወደቀ ፍጡር ነው። ለአዳምና ሔዋን አለመታዘዝ ሳቢያው፥ ፈተናውን አቅራቢው ሰይጣን ሆነ እንጂ ውሳኔው የነ አዳም ነው። እምቢ ማለት ይችሉ ነበርና። ምርጫና ፈቃድ ነበራቸውና። ሰይጣን ባይፈትናቸውም ፈቃዳቸው አንድ ቀን ይጠይቃቸው ነበርና። የዛፉ (መልካምና ክፉን የሚያስታውቀው ዛፍ) መኖር አስፈላጊነት እንግዲህ ለዚህ ነው።

* * * * *

25. ሽማግሌዎች በማን ይመረጡ/ይሾሙ? ኤጲስ ቆጶስ ምንድር ነው?

ጥያቄ አለኝ? እንደ ቲቶ1:5-6 ባለው መሠረት ሽማግሌዎችን የምንመርጠው ምዕመኑ አይደለም ግን በአሁኑ ሰዓት ይህ እየሆነ ነው? ምን ትላለ?

2, ሌላው ቲቶ1:7፤1ጢሞ3:1-2፤ፊልጵ1:1 ላይ አማርኛው ኤጵስ ቆጳስ ይላል በእንግሊዘኛው Bishop ይላል ስለዝህ ትክክል ናቸው ማለት ነው Chatolicoch/ሌሎችም የምጠቀሙት Bishop ብለው??

ሰላም ጆ፥ ቲቶ ፩፥5-6 ስለ ሽማግሌዎች ምርጫ ሳይሆን ስለ ሹመት ነው የሚናገረው። ዛሬ ካለው ጋር ልታስተያይ የሞከርከው ግልጽ ባይሆንልኝም እንደተረዳሁት በመጋቢያን ወይም በባለ አንድ ሰው መሪዎች ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚደረገውን መጋቢው ሽማግሌዎችን ራሱ መርጦ ራሱ የሚሾምበትን አሠራር ከቲቶ ጋር ለማመሳሰል የወሰድከው መስሎኛል።

እንዳልኩት ይህ ክፍል ስለ ምርጫ አይናገርም። ስለ ሹመት እንጂ። መራጩ ቲቶ ስለመሆኑ የሚያመለክት ምንም ነገር አናገኝም። ቲቶ ደግሞ የአንዲት አጥቢያ መጋቢ ሳይሆን በየከተማው እየሄደ ሽማግሌዎችን ይሾም ዘንድ ከጳውሎስ አደራና ኃላፊነትን የተቀበለ ሰው ነው። ቁጥር 5 የሚለው ይህንን ነው፤ ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤ ቲቶ የተተወው በቀርጤስ ነው። ቀርጤስ ደሴት ናት። በየከተማው የተባለው በደሴቲቱና ምናልባት ከደሴቲቱ ውጪ ባሉት በሌሎችም ከተሞች ይሆናል።

ይህንን የቲቶን የሽማግሌዎች መሾም ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አንድ መጋቢ ሽማግሌዎችን መሾም ጋር ልናቆራኝ የተገባ አፈታት አይደለም። ሽማግሌዎችን የመረጡት መጋቢ ከኖረ መጋቢው፥ ወይም መጋቢውና ሽማግሌዎች በጥምረት፥ ወይም ጉባኤው፥ ወይም ሁሉም በአንድነት ሊሆኑ ይችላል።

ያኔ የተደረገውን አሁን ከሚደረገው ጋር ከማስተያየትህ የተረዳሁት አሁን እየተደረገ ያለውን ወይም ሽማግሌዎች በጉባኤ መመረጣቸውን የሚኮንን ይመስላል። እኔ መጋቢያዊ ወይም የአንድ መጋቢ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን የምደግፍ አይደለሁም። አንድ መጋቢ ብቻውን ሽማግሌዎችን የሚመርጥና የሚሾምና የሚሽር፥ እንዲሁም ለእነርሱ የሥራ ድልድልን የሚሰጥና የሚከለክል ሲሆን እርሱን የሚደግፉና እርሱን የሚመስሉ፥ በምንም መልክ እርሱን የማይገዳደሩና አደራረጉን የማይጠይቁ ሰዎችን ብቻ በዙሪያው የሚኮለኩል ሰው ቤተ ክርስቲያንን ሳይሆን የንግድ ድርጅትን ወይም ኩባንያን የሚመስል መሥሪያ ቤት መሪ ይሆናል። ይህንን በብዙ አጥቢያዎች ተመልክቻለሁ። እንዲህ ባለው አስተዳደር መጋቢው በመንፈሳዊ አገልግሎቱና በስነ መለኮታዊ እድገቱ ይቀጭጫል እንጂ አይለመልምም። ይልቁንም የመጋቢነት ሥራው

ላይ ማተኮሩን ትቶ በአስተዳደራዊ እና በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ይያዝና ይጠላለፋል። መንፈሳዊ ሳይሆን ሜካኒካዊ ብቻ የሆነ ሥራ መሥራትም ይጀምራል። ለራሱም፥ ለቤተ ክርስቲያንም የማይጠቅም ይሆናል።

በኔ መረዳት፥ ዛሬ በየከተማው እየሄደ ሽማግሌዎችን የሚሾም እንደ ቲቶ ያለ አሠራር የሚጠቀሙ ሲኖዶሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም፥ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን መምረጥ የመጋቢው፥ በአመራር ላይ ያሉ ሽማግሌዎች፥ እና የምእመናን ወይም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ድምር ኃላፊነት መሆን አለበት። የቀጣዩን ዘመን የሽማግሌዎች ቦርድ የሚመርጡት አካላት በሚመረጥበት ጊዜ የሚገኙት መጋቢው ወይም መጋቢዎች፥ ሽማግሌዎች እና ምእመናን ወይም አባላት ናቸው የሚል ነው። ምርጫው በአንድ ሰው መዳፍ ውስጥ የተጠቀለለ መሆን የለበትም ባይ ነኝ። አንድ ሰው ብቻውን የሚመራት ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ጤነኛ አይደለችም፤ አትሆንምም።

ሁለተኛውን ጥያቄ በተመለከተ በጠቀስካቸው በሦስቱም ጥቅሶች ያሉት ቃላት በአንዳንድ የእንግሊዝኛ ትርጉም bishop ቢሰኙም ጳውሎስ በጻፈበት ቋንቋ ልክ አማርኛው በወሰደበት መልኩ ኤጲስ ቆጶስ የሚል ነው።

ኤጲስ ቆጶስ ἐπίσκοπος ኤፒስኮፖስ፤ ኤፒ ከላይ፥ ስኮፖስ ማየት፥ መቃኘት ከላይ ሆኖ ማየት ወይም የሚያይ ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያንን በኅብረት የሚመሩ መሪዎች ከተጠሩባቸው የሹመት ወይም ኃላፊነት ስሞች አንዱ፤ ፊል. 1፥1። ኤጲስ ቆጶሳት ምን መምሰል እንደሚገባቸው በ1ጢሞ. 3፥1-7 እና ቲቶ 1፥7-9 ተጽፎአል። በሐዋ. 20፥28 ጳጳሳት የተሰኘው እና በ1ጴጥ. 2፥25 እረኛ የተሰኘው ቃል ቀድሞ በተጻፈበት ቋንቋ ኤጲስ ቆጶስ ነው። እንደ ግስ ደግሞ በ1ጴጥ. 5፥2 ጠብቁ የሚለው እና ዕብ. 12፥15-16 ተጠንቀቁ የሚሉት ግሶች ከኤጲስ ቆጶስ አንድ ናቸው።

ስለዚህ ኤጲስ ቆጶስ (ትክክለኛው አጣጣል ወይም አጻጻፍ ኤጲ ስቆጶስ መሆን ነበረበት) ትክክለኛው ቃል ነው። bishop እና overseer የሚለው የእንግሊዝኛው ትርጉምም ማለፊያ ነው። ቲቶ በቁጥር 5 ላይ ሽማግሌዎች ብሎ ቁጥር 7 ላይ ኤጲስ ቆጶስ ይላል። ቃላቱ የተለያዩ ቢሆኑም ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ተመሳሳይ ባለቤት ነውና ቃሉ ተለዋዋጭ መሆኑን ልብ በል።

ይህ ቢሾፕ ካቶሊኮችና ሌሎችም የሚጠቀሙበት ነው? ላልከው ሌሎች ስትል ግልጽ አይደለምና ካቶሊኮች ላልከው ብቻ ልመልስ። አይደለም። በታሪክ ውስጥ እንዲሁም በአሁኑ ዘመን የምናውቀው ካቶሊካዊ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በጳውሎስ ዘመን የነበረው አይደለም።

* * * * *

26. እግዚአብሔር በአዳምና ሔዋን ለምን ጨከነ?

አዳምና ሔዋን እንዴት ጥፋት ነው ያጠፉት፤ እኛ ስንቴ እያጠፋን ይምረን የል ወይ? ታዲያ እግዚአብሔር ለምን ጨከኖ እንዲህ ቀጣቸው? ለጥፋት የዳረጋቸው ሰይጣን ከሆነ ለምን እነርሱ ከበደል ነጻ አልሆኑም? ለምን ሌላ ዕድል ተነፈጉ? (M)

ሰላም M፤ አንዷት ስትል ቁጥሯንም ባይሆን መጠኗን ለማሳነስ የሞከርክ ይመስላል። ጨክኖ ስትልም እግዚአብሔርን እየከሰስክ ያለ ይመስላል። በመጀመሪያ ማየት የተጻፈውን ነገር ከራሳችን አመለካከት አንጻር ነው ማየትና መፍታት ያለብን ወይስ ከታሪኩ ግብአት አንጻር ነው መፍታት ያለብን የሚለው ነው። የዘፍጥረት ጸሐፊ (ሙሴ) ለኛ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚለዋወጥ አመለካከት ተጨንቆ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የገለጠለትን እውነት ነው የጻፈልን።

የአዳምንና ሔዋንን እና የእግዚአብሔርን ግንኙነት ስናጤን ተራ ሳይሆን ልዩ ነው። በእግዚአብሔር እጅ ተቀርጸውና ተሠርተው የወጡ ከእርሱ ጋር ኃጢአት የሌለበትን ግንኙነት የተላበሱ ሰዎች ናቸው። ምንም የጎደላቸው የሌለ ብቻ ሳይሆን ሁሉ ያላቸው ነበሩ። ሁሉን ታድለው ከአንድ ብቻ የታገዱ ነበሩ። ይህ ፈቃድ ያላቸው ፍጡራን እንደመሆናቸው መጠን ይህን ፈቃድ የተባለውን የማንነታቸውን መታወቂያ እንዲያሳዩት፥ እንዲለማመዱበት የተደረገ ድንበር ነው።

እነ አዳም እውቀት ያነሳቸው ሰዎች አልነበሩም። መንፈሳዊ ብስለትም የጎደላቸው አልነበሩም። ከእግዚአብሔር እጅ ተሠርተው የወጡ ትኩስ ፍጡራን መሆናቸውን አንዘንጋ። ይህን እንዳያደርጉ የተባሉትን ነገር ካደረጉ ወደው፥ ፈቅደው (ፈቃዳቸውን ተግብረው)፥ ትእዛዝን ጥሰው፥ መዘዙንና ቅጣቱን ተረድተው ነው ያደረጉት። ዘፍ. 3ን ስናጤን እባብ (ሰይጣን) አሳች ነውና ወደ ልባቸው ሊያስገባ ያሰበው ጥርጣሬ ሠርቶለታል። ግን ሔዋን ለእባብ የመለሰችው መልስ እግዚአብሔር ከተናገረው የተጨመረበት ቃል አለበት። ቀድሞውኑ በልቧ የሚጉላላ ነገር ነበረ ማለት ነው። በዚህ ሁለቱም ተመሳሳይ ነገር እያሰቡ ናቸው፤ ያም `እግዚአብሔር እኛ እንዳንሆን የሚፈልገው ነገር አለ` የሚል ነው። ይህ የልብ ዝንባሌን የሚያሳይ ነገር ነው። አብሮ የመሆንን እና ያለመሆንን፥ ፈቅዶ የመገዛትንና ያለመገዛትን፥ የመታዘዝንና ያለመታዘዝን ሁኔታ የሚያመለክት ነው። ቁጥር 6 ሴቲቱ ዛፉ ለመብላት ያማረ፥ ለዓይን የሚያስጎመጅ፥ ለጥበብ መልካም መሆኑን አየች ይለናል። ሰይጣን ያሳሰበው የዓይን መከፈትና (የሥጋ ዓይን አይደለም) እንደ እግዚአብሔር የመሆን ክፉና መልካሙን የማወቅ ጥሪም አለበት። ስለዚህ የነአዳም ኃጢአት አስቀድሞ ያልተነገራቸው ሳይሆን አውቀውና መዝነው፥ መርጠውና ወደው ያደረጉት በደል ነው።

እግዚአብሔር ደግሞ ቅዱስ ነው። ይቅር ባይ ነው። ጨካኝ አይደለም። ኃጢአትን ይቀጣል፤ ኃጢአተኛን ይግ ይምራል። ስለሆነም ነው በአካል ሳይሞቱ በሕይወት ያኖራቸውና ያ ሕይወት ለእኛም የተረፈው። በመንፈስ ግን ሙታን ሆነው ከእርሱ የተለዩ ሆኑ። ወደው ያደረጉት መሆኑ በግልጽ ቢታይም ይበልጥ የሚያጎላው ነገር

በሁለቱም ውስጥ የጸጸትና የንስሐ ነገር ያለመኖሩ ነው። አጠፋሁ፥ በደልኩ፥ አልታዘዝኩም ይቅር በለኝ ሳይሆን ሌላውን መክሰስን ነበር ጉዳዩ ብለው የተያያዙት። አዳም ሔዋንን፥ ሔዋን እባብን። ከተነገራቸው ግልጽ ትእዛዝ በመነሣት ራሳቸውን ተጠያቂ ግን አላደረጉም።

ሁለተኛ ዕድል ተሰጥቶአቸው ኖሮ ቢሆንስ? ምን እንደሚሆኑ መገመት ብቻ ነው የምንችለው። ሁለተኛ ዕድል ቢሰጣቸው ሁለተኛ እንደሚያጠፉም ጥርጥር የለበትም። ይህ የልብ ጉዳይ ነው። ልብ የማይታዘዝ ከሆነ በኋላ ነው እግር የሚሄደው፥ ዓይን የሚያየው፥ ጆሮ የሚሰማው፥ እጅ ዘርግቶ የሚቀጥፈው። አዳምንና ሔዋንን እንደ እንስሳ ፈቃድ የሌላቸው ደመ ነፍስ ብቻ አድርጎ ካልፈጠራቸው በቀር ፈቃዳቸውን መለማመዳቸው የማይቀር ነው። `እግዚአብሔር እኛ እንዳንሆን የሚፈልገው ነገር አለ` የሚለው የልብ ዝንባሌን እስካለ ድረስ ደግሞ ያደረጉት ነገር መልሰው የሚያደርጉት ነገር ነው።

የተሰጣቸውን ልዩ ስፍራና የግንኙነቱን ጥልቀት ስንመረምር ለቅጣታቸው አንድ ጥፋት በቂ ነው። በጣም የሚዋደዱ በትዳር የተሳሰሩ ባልና ሚስት ቢኖሩ ከሁለት አንዳቸው ቃላቸውን ሰብረው አንድ ጊዜ ብቻ ቢያመነዝሩ ያ ግንኙነት ምን ይሆናል? መተማመን የሚባለው ነገር ወደቀ ማለት ነው። ቀድሞ እንደነበረው ሆኖ መቀጠል አይቻልም። ምናልባት ይቅርታ ቢኖርም እንኳ ግንኙነቱ ተበላሽቷል። ያ ነገር እንዳልነበረበት ጊዜ መሆን ከቶም አይችልም። የግንኙነቱ ጥልቀት የታማኝነቱን ክብደት ይጨምረዋል።

* * * * *

27. ብዙ ሚስት ማግባት የተከለከለ ነው? ለምን?

በክርስቲያኖች ዘንድ ብዙ ሚስት ማግባት የተከለከለ ነው? አንድ ሚስት ብቻ አግቡ ተብሎስ ታዟል? (ጆ. ተ.) [ወደ አገሬ ሄጄ 4 ሚስቶች አገባለሁ ከሚል መንደርደሪያ የተነሣ ጥያቄ ነው።]

ይህን ጥያቄ ከሦስት አቅጣጫ እንመልከት። ጥያቄው የክርስቲያኖችን አቋም የሚመለከት ስለሆነ ሦስተኛው ሰፋ ይላል።

1) ከዓለም እስታቲስቲክስ ብንነሣ በዓለም በሙሉ እና በእያንዳንዱ አገር የወንድና የሴት ቁጥር በጣም ተቀራራቢ ሆኖ መሳ ለመሳ ወይም እኩል ነው። የ2012ን ጠቅላላ የዓለም ቁጥር ብናይ የጠቅላላው ሕዝብ የጾታ ልዩነት 1.01 ወንድ ለ 1 ሴት ማለት ነው፤ ልዩነቱ እጅግ ጠባብ ነው። በጥቂት አገሮች የአንዱ ጾታ በጥቂት የሚጨምር ቢሆንም ጠቅላላው አዝማሚያ ግን እኩል ናቸው የሚል ድምዳሜ ይሰጠናል። ኢትዮጵያን እንደ ናሙና ብንወስድ አጠቃላዩ ቁጥር 1.03 ለ 1 ነው። ስለዚህ ወንድ ሁሉ 4 የማግባት ዕድል ቢኖረውና ቢችል ብለን ብንገምት አንዱ 4 ሲያገባ ሦስቱ ያለ

ሚስት ይቀራሉ። ሁለቱ 2 ቢያገቡ እንኳ ሁለቱ ነጠላ ሆነው ይቀራሉ ማለት ነው። ከእስታቲስቲክስ አንጻር ይህ ትክክል አይደለም።

2) ወደ ባሕላዊ ኑሮ ከሄድን ብዝሐ ሚስት የተለመደባቸው ባሕሎች በዓለማችን በርካታ ናቸው። ምክንያቶቹ እንደየባሕሎቹ ይለያያሉ። አንዳንዳንዶቹ ባሕሎች ሃይማኖታዊ ባሕል ናቸው። አንዳንዶቹ ሃይማኖቶች ባሕላዊ ሃይማኖት ናቸው። እናም ቅይጥይጥ ያለ መልክ ይታይባቸዋል። ወደ መነሻው ስንሄድ ግን፥ ጦርነትና ምርኮ (በጦርነት ውስጥ የወንዶች መፈጀትና የሴቶች መበርከት የሚያመጣው የጾታ ቁጥር መዛባት)፥ የወንዶች እብሪትና የበላይነት፥ የወንዶች ከሌሎች ወንዶች ጎልቶ ወይም በልጦ የመታየት እንሰሳዊ ፍላጎት (በአራዊት ወንዶች የሚታይ ባህርይ)፥ እና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ። በአንጻሩ የብዝሐ ባል (አንዲት ሴት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ባሎች ጋር የምትኖርበት) ባሕል የሚንጸባረቅባቸው ጥቂት ባሕሎችም በጥቂት አገሮች ውስጥ ይገኛሉ። ይህ ባሕል ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አናያይዘውም።

3) ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስንመጣ ደግሞ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት ብቻ ማግባት እንዳለበት የመጀመሪያው አመልካች እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር አንድ አዳምና አራት ሔዋኖች አለመፍጠሩ ነው። ሔዋን የተፈጠረችበትን ታሪክ በሚናገረው ክፍል በዘፍ. 2፥18-25 እግዚአብሔር የሚመቸውን ረዳት እንጂ ረዳቶች አላለም። ደግሞም ሰው በሚስቱ ይጣበቃል አለ እንጂ በሚስቶቹ አላለም። በትእዛዙ ውስጥም የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ ሲል ነጠላ ነው እንጂ ብዙ አይደለም፤ ዘጸ. 20፥ 17።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ሚስቶች ያገቡ ሰዎች መኖራቸው የታወቀና በግልጽ የተጻፈ ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ሁሉ እውነት ቢሆንም በውስጡ የተጻፈውን ያደረጉት ሰዎች ሁሉ ትክክል ናቸው ማለት ግን አይደለም። በብሉይ ኪዳን ዘመን (ከክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ዘመን በፊት ማለት ነው) እንዲህ የመሰሉ ብዙ ሚስቶች ያገቡ ብዙ ሰዎች አሉ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሁለት ሚስቶች ያገባው ሰው ላሜሕ ነው፤ ዘፍ. 4፥19-23። ይህ ሰው የመልካም ምግባር ምሳሌ ከቶም ሊሆን አይችልም። ላሜህ ብዙ ያገባ ብቻ ሳይሆን ነፍሰ-ገዳይም ነበረ። ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን እንዲህ ያለው ሰው መጀመሩ ብዝሐ ጋብቻ ከተበላሸ ምንጭ እንደተጀመረ ይጠቁመናል። ዔሳውም እንዲሁ ከአንድ በላይ ሚስት አግብቶ ለወላጆቹ ልብ ኀዘን ሆኖ ነበር፤ ዘፍ. 26፥34-35። ያዕቆብ ፈልጎ አይደለም ሁለት ሚስቶች ያገባው፤ አማቱ አታለለውና አጋባው። ጌዴዎን ብዙ ሚስቶች ነበሩት፤ መሳ. 8፥30። ዳዊትም ወደ 8 ሚስቶች ነበሩት፤ 1ዜና. 3፥1-5፥ 13-16። አቢሳ ባያውቃትም ሚስቱ ነበረችና 9 ይሆናሉ፤ ቁባቶችም ነበሩት። የአኪን ስንት መሆናቸው ባይታወቅም ሚስቶች ነበሩት፤ 2ነገ. 24፥25። ሮብዓም 18 ሚስቶችና ቁባቶችም ነበሩት፤ 2ዜና. 11፥21። አብያ 14 ሚስቶች ነበሩት፤ 13፥21። ብዙ ሚስቶች በማግባት እጅግ የሚታወቀው ንጉሥ ሰሎሞን ነው። በ1ነገ. 11፥3 እንደምናነብበው ሰሎሞን 700 ሚስቶችና 300 ቁባቶች ነበሩት። እነዚህ ለበረከት በመሆን ፈንታ ወደ ጣኦት አምላኪነት ነበር ልቡን ያዘነበሉት።

ሰሎሞንም ሆነ ሌሎቹ ነገሥታት ያደረጉት ይህ ነገር በቀጥታ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመጣስ ነው። በሕጉ አስቀድሞ ንጉሥ ለራሱ ሦስት ነገሮች እንዳያበዛ በግልጽ

ታዞአል፤ እነዚህም ፈረሶች፥ ሚስቶች እና ወርቅና ብር ናቸው፤ ዘዳ. 17፥16-18። ሰሎሞን እነዚህን ሁሉንም በማድረግ የተላለፈ ሰው ነው። ስለዚህ ሁላቸውም፥ በተለይም ሰሎሞን፥ ብዙ ሚስት ለማግባት እንደ ምሳሌና እንደ ሞዴል መታየት የሌለበት ሰው ነው። የእነዚህን ባለ ብዙ ሚስቶች ሕይወት ስናጤን፥ ቢያንስ ንጉሦቹ ንጉሥ ሆነው፥ ሕግን ጥሰው፥ ማድረግ የሌለባቸውን ማድረጋቸውን ይህን ያሳያል። እንደ ሕጉ ተጠንቅቀው ሲሄዱ አናያቸውም። እነዚህና ሌሎችም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያቸው ብዙ ሚስቶች ያገቡ ሰዎች በማግባታቸው ደስተኛ ከመሆን ይልቅ በኑሮአቸው ችግር ሲሆን ነው የምናነብበው። ጣውንቶቹ ሲጣሉ፥ ልጆቻቸው ሲጣሉና ሲጋደሉም ይታያል።

ማግባት ያለባቸው አንዲት ሚስት ቢሆንም ሰዎች እንደዚህ እንደሚያደርጉ፥ ማለትም ከአንዲት ሚስት ያለፈ እንደሚወስዱ ስለሚያውቅ እግዚአብሔር በሁለት ሚስቶች መካከል አድልዎ እንዳይደረግ ደንግጎአል፤ ዘጸ. 21፥10-11፤ ዘዳ. 21፥15-17። ይህን ማድረጉ ይህ እንዲሆን መፍቀዱ ሳይሆን ይህ ቢሆን ወይም ይህ ከሆነ በኋላ ጭቆናና አድልዎ እንዳይሆን ለመከልከል ነው። ከዚህ ሌላም የዋርሳ ሕግ ደግሞ አለ፤ ይህ ባል ሲሞት የሚቹን ሚስት ወንድምየው እንዲያገባና ቤተ ሰቡን እንዲጠብቅ ዘርና ውርስ እንዳይጠፋ የሚፈቀድበት ሥርዓት ነው። ወንድምየው ሚስት ብትኖረውም እንኳ የማግባት ኃላፊነት አለበት፤ ዘዳ. 25።

እግዚአብሔርን በመፍራትና በመከተል የተመሰገኑቱ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ባለ አንድ ሚስቶች የነበሩ ናቸው። ኢዮብ አንዲት ሚስት ነበረችው። ይስሐቅ የአንዲት ሚስት ባል ነው። እንዲህ የመሰሉ በርካታ ሊጠቀሱ ይችላሉ። ደንቡ ግን አንድ መሆኑን ሚስቶች እና ሚስቶችህ ሳይሆን ሚስት እና ሚስትህ የሚሉት ጥቅሶች ያመለክታሉ፤ መዝ. 128፥3፤ ምሳ. 5፥18፤ 18፥22፤ 19፥14፤ መክ. 9፥9። ሕዝቅኤል አንዲት ሚስት ብቻ ነበረችው፤ ይህንን እንደ ምሳሌ አድርጎ ተጠቀመበት፤ ሕዝ. 24፥16-21። የእስራኤልና የእግዚአብሔር ግንኙነት ከብካቤና ጥበቃ፥ ፍቅርና ታማኝነት ባለበት በባልና በሚስት ግንኙነት ተመስሎአል፤ ኢሳ. 54፥6፤ ኤር. 3፥1፤ ሆሴ. 2። ይህ አሳብ ወደ አዲስ ኪዳን ይመራናል።

ከአዲስ ኪዳን ቀደም ባለው የአይሁድ ታሪክ ውስጥ ብዝሐ ሚስት የተናቀና የቀረ ይመስላል። በምርኮው ዘመን አይሁድ ወደ ልባቸው ሳይመለሱ አልቀሩም። በዚህ ዘመን በክርስቲያኖች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሮማውያንና በግሪካውያንም ዘንድ እንኳ በሕግ የተደነገገ ደንባቸው አንድ ባል አንዲት ሚስት ማግባት ነው። ከክርስትና ውጪ ያለው ባሕልም ወደ ትክክለኛው አስተሳሰብ እየመጣ የነበረ ይመስላል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ የምናገኘው ትምህርት በጥቅሉ አንድ ባል አንዲት ሚስትን እንዲያገባ ነው። ጌታ ክርስቶስ ባስተማረው ትምህርት ሚስቱን ፈትቶ ሌላ የሚያገባ ማመንዘሩ መሆኑን ገለጠ፤ ማር. 10፥1-12፤ ማቴ. 19፥1-12። በነዚህ ክፍሎች ዋናው ትምህርት ስለ ፍቺ ቢሆንም ቃሉን በነጠላ በመጠቀም (ሚስቱን በማለት) ነው የገለጠው። በአዲስ ኪዳን አንድ ባል አንዲት ሚስት እንዳለችው ወይም እንድትኖረው ብቻ ነው የተስተማረው፤ 1ቆሮ. 7። ልክ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርና እስራኤል በባልና ሚስት እንደተመሰሉት የባልና የሚስት ግንኙነትም በአዲስ ኪዳን የክርስቶስና የቤተ

ክርስቲያን ግንኙነት ምሳሌነትን ይዞ ተጽፎአል፤ ኤፌ. 5፤ ራእ. 19፥7፤ 21፥9-27። ክርስቶስ አንዲት አካል ብቻ ናት ያለችው።

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከብሉይ ኪዳን እምነት የመጡ አይሁድ ስለሆኑ ወይም ከአሕዛብ የመጡቱ ደግሞ ብዙ ማግባት ከለመዱ አሕዛብ የመጡ ስለሆኑ ይህ ነገር እንደ ችግር ሆኖ በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ሳይኖር አይቀርም። ግን ቀጣይ አለመሆኑ በግልጽ ይታያል። ቢያንስ መሪዎች የአንዲት ሚስት ባል መሆን እንዳለባቸው ተደንግጎአል፤ 1ጢሞ. 3፥2፤ ቲቶ 1፥6። በአዲስ ኪዳን ባል የሞተባቸውን ባልቴቶች በተመለከተ ጌታን ሊያገለግሉ ወስነው ካላገቡ በቀር ቤተ ሰቦቻቸውም፥ ቤተ ክርስቲያንም እንዲረዱአቸው ተነግሮአል፤ እነዚህ ሴቶች ወጣቶች ከሆኑ ደግሞ እንዲያገቡ ተብለዋል እንጂ እንደ ብሉይ ኪዳን ሕግ የባል ወንድም እንዲወስዳቸው አልተደነገገም፤ 1ቆሮ. 7፥8፤ 1ጢሞ. 5፥3-16፤ ያዕ. 1፥27።

ሲጠቃለል አንዲት ሔዋን ለአንድ አዳም እንደተፈጠረች የእግዚአብሔር አሳብ አንድ ባል አንዲት ሚስት ብቻ እንድትኖረው ነው።

* * * * *

28. የኤፌ. 4 አምስቱ ቢሮዎች ምንድር ናቸው?

ሰላም፤ የኤፌ. 4፥11 አምስቱ ቢሮዎች ቢሮዎች ናቸው ወይ?

ለዘመናችን ሐዋርያትና ነቢያት መቀፍቀፍ ዋና ጥቅስ የሆነው ኤፌ. 4፥11 ነው። The Five Fold Ministry ይሉታል። ጥቅሱ፥ እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤ ይላል። ከአምስቱ ሁለቱ ሐዋርያትና ነቢያት ተመርጠው ለምን ልዩ የክብር ስፍራ እንደተሰጣቸው ለእነርሱም ለራሳቸውም ግልጽ አይደለም።

የዚህ ትምህርት ዋና መንደርደሪያ የኋለኛው ዝናብ እየተባለ የሚጠራው በ1940ዎቹ መጨረሻ እና 1950ዎቹ በአሜሪካ የነበረው ጴንጤቆስጣዊ ንቅናቄ ነው። ኋላ በ1970ዎቹ ሦስተኛው ሞገድ የተባለው ንቅናቄ ቅርጽም ሰጠው። መንግሥታሁን (Kingdom Now) ወይም የግዛት ስነ መለኮት (Dominion Theology) ደግሞ አራገበው። ስለ ግዛት ስነ መለኮት በዕዝራ ቁ. 32 አካፍያለሁ። ስለ ሦስተኛው ሞገድ በመንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች በመጠኑ በስፋት ጽፌአለሁ።[2]

ሦስተኛው ሞገድ የሚባለው ንቅናቄ ከዚህ በፊት በ20ኛው ምዕት ዓመት መጀመሪያ በቶፒካውና በአዙሳ ጎዳናው ንቅናቄዎች አካባቢ ይታወቅ ከነበረው 'ሦስተኛው ልምምድ' ከሚባለው የተለየ ነው። በዚያን ጊዜ ሦስተኛው ልምምድ ይባል የነበረው

---

[2] መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች፤ ገጽ 225-226።

አንደኛው ደኅንነት ሁለተኛው ቅድስና ሲሆኑ ሦስተኛው ልምምድ የሚባለው የመንፈስ ቅዱስ 'ጥምቀት' ነው። በጴንጤቆስጣውያን ዘንድ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት በልሳን መናገር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሁለተኛ ቡራኬና ሦስተኛ ልምምድም ተደርጎ ቢስተማርም ቅድስና ጣልቃ የገባው በጊዜው የቅድስና ትምህርት ተስፋፍቶ ይሰበክብት የነበረ ዓቢይ ርዕስ በመሆኑ ነው።

ሦስተኛው ሞገድ ከ1970ዎቹ በኋላ የተጀመረና እስከ ዘመናችንም ድረስ ያለ ንቅናቄ ሲሆን ቃሉን መጀመሪያ የቀመረው ፒተር ዋግነር የተባለው የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ምሑር የነበረው ሰው ነው። ዋግነር በቦሊቪያ ሚሰዮናዊ ሆኖ ለ16 ዓመታት ያገለገለ በኋላም በፉለር የሥነ-መለኮት ሲሚናሪየም የቤተ ክርስቲያን ዕድገት አስተማሪ የሆነ ሰው ነው። እንደ ዋግነር አባባል የመጀመሪያው ሞገድ የበዓለ ኀምሳው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ካሪዝማዊ ንቅናቄ ሲሆን ሦስተኛው በዚህ ዘመን (በ1970ዎቹ) መንፈስ ቅዱስ እየሠራ ወይም ሊሰራ ያለው እንቅስቃሴ ነው። ይህን እርሱ የቀመረውን ንቅናቄ ሰዎች ካሪዝማዊ ወይም ጴንጤቆስጣዊ ብለው እንዲጠሩት ዋግነር አይፈልግም። ምክንያቱ የቃሉ ጥላቻ ሳይሆን በነዚህ ንቅናቄዎች ውስጥ የሚደረጉት መስመር ያለፉ ልምምዶች ብዙዎችን በማስደንገጥ አፍራሽነትያለው ስሜት በመፍጠራቸው ነው።[37] የዚህ ንቅናቄ ማዕከላዊ ጭብጥ ድንቅና ተአምራትን አጥብቆ መፈለግና እነዚህ ነገሮች ለወንጌል ስርጭት ያላቸው ሚና ጉልህ በመሆኑ እርሱ የሌለበት ወንጌል ጎዶሎ እንደሆነ እስከማሰብና ማስተማር መድረስ ነው።

John F. MacArthur *Charismatic Chaos* በተባለ መጽሐፉ ገጽ 130 ስለዚህ ንቅናቄ ሲጽፍ እንዲህ ብሎአል፤ "የሦስተኛው ሞገድ ተከታዮች ሐሴታዊ ልምምዶችን፣ ምስጢራዊ ክስተቶችን፣ ተአምራዊ ኃይሎችንና ተፈጥሮ አለፍ ምልክቶችን አጥብቀው ይከታተላሉ በአንጻሩም ለተለመዱት በመንፈሳዊ ሕይወት የማደጊያ መንገዶች ማለትም ለጸሎት፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ ለቃሉ ትምህርት፣ በመታዘዝ ለመጽናትና ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረትን ለማድረግ አነስተኛ ግምት ይሰጧቸዋል።"

ይህ ንቅናቄ በመሠረቱ ስሙ ብቻ ተለወጠ እንጂ በባህርዩ ከዘመናዊው ካሪዝማዊ ንቅናቄ በምንም የተለየ አይደለም። እንዲህ ያለውን ትምህርት በሚያስተምሩባቸው አብያተ ክርስቲያናት በነፃነት በማምለክ ስም እንግዳ ነገሮች በመንፈስ ቅዱስ ስም ደግሞ ሰው ሰራሽ ድርጊቶች መፈጸማቸው ይስተዋላል። የሚታዩ አካላዊና ቁሳዊ ድንቆች ተአምራትና ምልክቶች ካልኖሩበት ያ ክርስትና ክርስትና ነው ሊባል አይገባውም ይላሉ 3ኛ ሞገደኞች። ወንጌል ሲሰበክ ተአምር መኖር አለበት ተአምር ሲያዩ ነው ሰዎች በሚገባ የሚለውጡት በማለት ተአምራትና ምልክቶችን ለመውለድ እስኪያምጡ ይደርሳሉ። ይህ የመጨረሻው አሳብ በተለይ ጆን ዊምበር በተባለውና ከንቅናቄው መሪዎች አንዱ በሆነው ሰው በሰፊው ተዘክሯል። በሌላ አነጋገር 3ኛው ሞገድ የተአምራትና የምልክቶች ንቅናቄ ሊባልም ይችላል። . . .

Shaping Things to Comes በተባለ መጽሐፋቸው Alan Hirsch እና Michael Frost ገጽ 166-7 ይህንን አሳብ በጉልህ ጽፈውታል። ፒተር ዋግነር አዲሱ ሐዋርያዊ ተሐድሶ የተሰኘውን ቃል የቀመረና ይህን የዘመናችንን ሐዋርያትና ነቢያት በገፍ መፈጠር ያመነጨ ሰው ነው። እንደ ዋግነር እምነት ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያዊ አመራር ስር መሆን አለባት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሐዋርያት፥ ነቢያት፥ ወንጌልን ሰባኪዎች፥ እረኞችና አስተማሪዎች ቃላቱ በእንግሊዝኛ ሆነው በምኅጻረ ቃል APEPT በሚል መጠሪያ እየታወቁ ነው።

ወደ ነጥቡ ስንመጣ፥ አምስት እጥፍ አገልግሎት ወይም በአማርኛ ተናጋሪዎች ዘንድ በተለመደው አጠራር አምስቱ ቢሮዎች ቤተ ክርስቲያን በመጨረሻው ዘመን መመራት ያለባት የአመራር ዘዬ ወይም ስልት ነው ብለው የሚናገሩለት አሠራር ነው። ይህ ከመጽሐፉ የተወሰደው ነው። አንዳንዶች አምስቱንም በሚዛናዊነት ለማየትና ለማሳየት ቢሞክሩም ሁለቱ ሐዋርያትና ነቢያት) አፈትልከው ወጥተውባቸዋል። ሲጀመር ሐዋርያቱን እና ነቢያቱን በየእርከኑ የሚቀቡ፥ የሚያሳድጉ፥ የሚያማክሩ ሰዎች ኖረው ነበር። እየቆየ ግን በራሳቸው እጅ ራሳቸውን የሚቀቡት ሐዋርያትና ነቢያት እንደ እንጉዳይ እየፈሉ ማንም የማይመራው፥ ማንም ሃይ የማይለው ልቅ ንቅናቄ ሆነ። በእነዚህ ሁለት እና ሦስት ዓመታት በአህጉራችን እና በአገራችን የሚታየው ዓይነተኛ ምሳሌ ነው።

ኤፌ. 4፥11 በቅርብ ዐውዱ ሲታይ ከ4፥1-16 ያለውን የሚያቅፍ ስለ አካል የሚናገር ክፍል ነው። በዚህ ክፍል ስለተጠቀሱት ጸጋዎች እና ሰዎች ሲናገር አካሉን ስለማነጽ ነው የጻፈው። ጸጋዎች እና ሰዎች ስል ጸጋው በሌሎች ቦታዎችም ስለተጠቀሰ፥ ለምሳሌ፥ በኤፌ. 4 ነቢይ የተባለው በሮሜ 12 እና 1ቆሮ 12 ትንቢት ተብሎአል። ትንቢት ጸጋው፥ ነቢይ አገልጋዩ ነው። እነዚህ እዚህ የተጠቀሱት ሰዎች የአካሉ አገልጋዮች እንጂ የተለዩ ቅቡዓን መሪዎች መሆናቸውን ይህ ክፍል አያስተምርም። ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዲስ ኪዳን የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም፥ ለምሳሌ፥ ሽማግሌዎች፥ ጳጳሳት፥ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ዲያቆናት፥ ወዘተ እያለ ሲጠቅስ ከእነዚህ ቃላት ጋር አልቆለፈውም። በእርግጥ የመጀመሪያዎቹ በጌታ የተሾሙት ሐዋርያት የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሆናቸው የታወቀ ሲሆን በኤፌን መልእክት ውስጥ ጳውሎስ የሚናገረው ክርስቶስ ራሷ ስለሆነው እና እርሷ ደግሞ አካሉ ስለሆነችው ስለ ኩላዊት ቤተ ክርስቲያን ነው። በዚህ አካል ውስጥ ደግሞ የጸጋ ስጦታዎች ሳይበላለጡ ያገለግላሉ፤ ግባቸው አካሉን ማነጽ፤ ዓላማቸውን ጌታን ማክበር ነው።

ስደመድም፥ አምስቱ ቢሮዎች ቢሮዎች ናቸው ወይ? ለሚለው ጥያቄ፥ ሲጀመር፥ ቢሮ የሚል ቃልም አሳብም በክፍሉ ውስጥ አይገኝም። ስለዚህ አምስቱ ቢሮዎች የሚባለው ተቀባይነትን የተቀዳጀ ስሕተት ነው። እነዚህ አምስቱ በሌሎች ክፍለ ምንባቦች ውስጥ ከተጠቀሱት ጋር የጸጋ ስጦታዎች እና የጸጋ ስጦታዎን የተቀበሉ አገልጋዮች ናቸው። በአካሉ ውስጥ ነቢይ (ትንቢት የሚናገር) ከሚገዛ (ከሚያስተዳድር) ወይም ሐዋርያ (ወንጌል ሰብኮ ቤተ ክርስቲያን ሊተክል የተላከ) ከሚሰጥ (በገንዘቡ ከሚያገለግል)

የተለየ እንጂ የሚበልጥ አይደለም። ዓይን ከጆሮ የተለየ እንጂ የበለጠ እንዳልሆነ አስተማሪም ከሌጲስ ቆጶስ የተለየ እንጂ የበለጠ ባለ ቢሮ አይደለም።

ደግሞም ጳውሎስ ጌታ እነዚህን ሰዎች ሰጠ እንጂ ሾመ አላለም። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች ባለ ቢሮ ሹመኞች አይደሉም። ለምሳሌ፥ በላይ ሽፈራውን ዳዊት ሞላልኝ ነቢይ አድርጎ ሲቀባው፥ 'በነቢያት ቢሮ . . . ነቢይ አድርገን ይህንን ቅባት በላዩ ላይ እናፈስሰዋለን' ሲል የነቢያት ቢሮ ያለ ይመስላል፤ አዲስ ኪዳን ግን እንዲህ ያለ ነገር አያስተምርም። በብሉይ ኪዳን የነቢያት ልጆች የሚባል ነበረ፤ በአዲስ ኪዳን ግን የነቢያት ልጆችም፥ የነቢያት ቢሮም የሚባሉ ነገሮች የሉም። አምስቱ ቢሮዎችም የነ ፒተር ዋግነር፥ ጆን ዊምበር፥ ማይክል ፍሮስት፥ ወዘተ ቀመሮች ናቸው እንጂ የሐዋርያው ጳውሎስ ወይም የሐዋርያው ዮሐንስ ትምህርቶች አይደሉም።

* * * * *

29. እግዚአብሔር በቀለኛ አምላክ ነው?

> ዓይን ስለ ዓይን፥ ጥርስ ስለ ጥርስ በሚለው ሕግ መሠረት እግዚአብሔር ተበቃይና በቀለኛ አምላክ ነው፤ በተለይ በብሉይ ኪዳን ሲታይ። ስለዚህ የመበቀል ትእዛዝ ምን ትላለህ?

. . .

እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነውና በብሉይና በአዲስ ኪዳን አልተለወጠም። አልተሻሻለም ወይም ራሱን አላሻሻለም። በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ቁጡም፥ ለቁጣ የዘገየም፤ ታጋሽም፥ ኃጢአትን የሚቀጣም፤ መሐሪና በደልን ይቅር የሚል፤ ተበቃይም፥ ባለ ብዙ ቸርነትና ፍቅርም የሆነ አምላክ ነው። ብሉይና አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ማንነት ያልለወጠው መሆኑን ብቻ አውስቼ ስለ ባህርያቱ የተዘረዘረ ስነ መለኮታዊ ትንታኔ መስጠት ልተውና ወደ ጥያቄው ልግባ።

የእግዚአብሔር ትእዛዛትና ሕግጋት በአንድ ወቅት ለኖረ ሕዝብ የተሰጡ ቢሆኑም ዘላለማዊ ክብደትን የተላበሱ ናቸው። ይህ ትእዛዝ በቀልን የሚያሳስብና የሚያነሣሳ ነው ከመሰኘት ይልቅ ለቅጣት ምላሽ ድንበርን የሚወስን ነው። ዘጸ. 21፤ ዘሌ. 24፤ ዘዳ. 19 ምዕራፎቹን በሙሉ አንብቡ። ተበቃይ ሰው ከተበደለው በደልና ከደረሰበት ግፍ በላይ ማስከፈል ነዋ የሚፈልገው።

ይህን የሚመስሉ ለቁጥር የበዙ ምሳሌዎች ቢኖሩም አንድ ምሳሌ ልስጥ፤ በ1994 አሜሪካ ውስጥ አንዲት ሴት ከመክዶናልድስ ካፌ ቡና ገዝታ ስትሄድ ከገዛ እጇ ፈሰሰባትና ኩባንያውን ከሰሰች። የቡናው ዋጋ 49 ሳንቲም ነው። ስለተቃጠለችበት ያወጣችው ለሕክምና ሰማይ ጠቀስ ዋጋ ስለሚጠየቅና ከልክ በላይ ሕክምናም ተደርጎ ወደ 10 ሺህ ያህል ነው። ኩባንያው የተቀጣውና የከፈለው ግን 2ሚልዮን 8መቶ

60ሺህ ዶላር ነው። ይህ ፍትሕ ነው? ወይስ ከበደል በላይ የበቀልና ካሳ ጥያቄ ነው? ይህን ምሳሌ ያመጣሁት የዓይን በዓይን ፋንታን መንፈስ ለማስረዳት ነው። ከላይ እንዳልኩት ይህ ሕግ ድንበርን የሚወስን ነው። ይህ ድንበር ባይኖር አንድ ዓይን የጠፋበት ሁለት ሊያጠፋ ይችላል። ወይም አንድ ጥርስ የተሰበረበት መንጋጭላ ሊያወልቅ ይችላል። ድንበር ከኖረ ግን ከልኩ አይታለፍም።

በቀል ቅጣት ወይም የቅጣት ምላሽ ነው። በተለይ በአዲስ ኪዳን ቋንቋ የጥፋት ቅጣት ነው። ሆኖም በአዲስ ኪዳን በግልጽ እንደተጻፈው በቀል የክርስቲያኖች ድርሻና ምላሽ አይደለም። ሮሜ 12፥19 በቀል የእግዚአብሔር መሆኑን ከብሉይ ኪዳን በመጥቀስ ያስተምራል። ቃሉ የተወሰደው ከዘዳ. 32፥35 ነው። ቀድሞም ኋላም በቀል የሰው ሳይሆን ፍትሕን የተሞላው የቀጪው የእግዚአብሔር መሆኑ ፍርድንና ፍትሕን በእጃችን ወስደን ተበቃይ እንዳንሆን ያስተምረናል።

ያነበብኩበት መጽሐፍ ባይታወሰኝም ፈታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ናቸው አንድ ቤተ ሰብ አንድ ነፍሰ ገዳይ አስይዘው ለዳኝነት ወደ እርሳቸው መጡ። ሰውየው ሟቹን የገደለው አውቆ አይደለም። ሟቹ እዛፍ ስር ተቀምጦ ሳለ ያኛው ከዛፉ ላይ በላዩ ወድቆበት ነው የሞተበት። እና ይገደልልን ብለው ነው ጥያቄ ያቀረቡት። ፊታውራሪው ሲመልሱ፥ ገዳዩ ሰው ሟቹ ተቀምጦ የነበረበት ቦታ ሄዶ ይቀመጥና የሟቹ ዘመድ የሆነ አንድ ሰው እዛፉ ላይ ወጥቶ አንድ ጊዜ ብቻ ይውደቅበትና ይግደለው ብለው ብያኔ ሰጡ። ፍትሕ ከሌለ በቀል ከመስመር ይወጣና ትውልድ ሊያልቅ ይችላል። ስለዚህ ዓይን ስለ ዓይን ማለት ስለ አንድ ዓይን አንድ ዓይን ብቻ ማለት መሆኑ እግዚአብሔርን በቀለኛ ከማስመሰል ፍትሕን የሚወድድ አምላክ መሆኑን ያሳየናል።

* * * * *

30. እግዚአብሔር ተጸጸተ ሲል ምን ማለት ነው? ይጸጸታል?

> መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ተጸጸተ እያለ ብዙ ይናገራል። ከተጸጸተ ተሳሳተ ማለት ነው? እግዚአብሔር እንደ ሰው ይጸጸታል? ምን ማለት ነው? (A. G.)

ሰላም A. G.፤ መጽሐፍ ቅዱስ ከ10 ጊዜያት በላይ እንደተጸጸተ ይናገራል። እነዚህን ጥቅሶች ስናነብብ ይህን እናገኛለን።

ዘፍ. 6፥6-7 እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ። እግዚአብሔርም፦ የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው <u>ተጸጽቼአለሁና</u> አለ።

1ሳሙ. 15፥10-11 እና 35 የእግዚአብሔርም ቃል፦ ሳኦል እኔን ከመከተል ተመልሶአልና፥ ትእዛዜንም አልፈጸመምና ስላነገሥሁት <u>ተጸጸትሁ</u> ብሎ ወደ ሳሙኤል

መጣ። ሳሙኤልም ተቈጣ፤ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። . . . ሳኦልም ወደ ቤቱ ወደ ጊብዓ ወጣ፡- ሳሙኤልም እስከ ሞተበት ቀን ድረስ ሳኦልን ለማየት ዳግመኛ አልሄደም፥ ሳሙኤልም ለሳኦል አለቀሰ፤ እግዚአብሔርም በእስራኤል ላይ ሳኦልን ስላነገሠ ተጸጸተ።

1ዜና 21፥15፤ እግዚአብሔርም ያጠፋት ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም መልአክን ሰደደ፤ ሊያጠፋትም በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር አይቶ ስለ ክፉው ነገር ተጸጸተ፥ የሚያጠፋውንም መልአክ፡- በቃህ አሁን እጅህን መልስ አለው። የእግዚአብሔርም መልአክ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር።

መዝ. 106፥45፤ ለእነርሱም ኪዳኑን አሰበ፥ እንደ ምሕረቱም ብዛት ተጸጸተ።

ኤር. 18፥8፥10፤ ይህ ስለ እርሱ የተናገርሁበት ሕዝብ ከክፋቱ ቢመለስ፥ እኔ አደርግበት ዘንድ ካሰብሁት ክፉ ነገር እጸጸታለሁ። በፊቴ ክፉን ነገር ቢያደርግ ቃሌንም ባይሰማ፥ እኔ አደርግለት ዘንድ ስለ ተናገርሁት መልካም ነገር እጸጸታለሁ።

ኤር. 42፥10፤ ስላደረግሁባችሁ ክፉ ነገር ተጸጽቻለሁና በዚህች ምድር ብትቀመጡ እሠራችኋለሁ እንጂ አላፈርሳችሁም፥ እተክላችኋለሁ እንጂ አልነቅላችሁም።

ኢዩ. 2፥13-14፤ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቍጣው የዘገየ፥ ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ። የሚመለስና የሚጸጸት እንደ ሆነ፥ ለአምላካችሁም ለእግዚአብሔር የእህልና የመጠጥ ቍርባን የሚሆነውን በረከት የሚያተርፍ እንደ ሆነ ማን ያውቃል?

አሞ. 7፥3፥6፤ እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤ ይህ አይሆንም፥ ይላል እግዚአብሔር። . . . እግዚአብሔርም ስለዚህ ነገር ተጸጸተ፤ ይህ ደግሞ አይሆንም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።

ዮና. 3:9-10፤ 4፥2፤ እኛ እንዳንጠፋ እግዚአብሔር ተመልሶ ይጸጸት እንደ ሆነ፥ ከጽኑ ቍጣውም ይመለስ እንደ ሆነ ማን ያውቃል? እግዚአብሔርም ከክፉ መንገዳቸው እንደተመለሱ ሥራቸውን አየ፤ እግዚአብሔርም ያደርግባቸው ዘንድ በተናገረው ክፉ ነገር ተጸጽቶ አላደረገውም። . . . ወደ እግዚአብሔርም ጸለየና፡- አቤቱ፥ እለምንሃለሁ፤ በአገሬ ሳለሁ የተናገርሁት ይህ አልነበረምን? አንተ ቸርና ይቅር ባይ፥ ታጋሽም፥ ምሕረትህም የበዛ፥ ከክፉው ነገርም የተነሣ የምትጸጸት አምላክ እንደ ሆንህ አውቄ ነበርና ስለዚህ ወደ ተርሴስ ለመኰብለል ፈጥኜ ነበር።

መጸጸት ለሰው ሲሆን ስሕተትን፥ መመለስን፥ መታረምን ያሳያል። እግዚአብሔር ተጸጸተ ሲባል እግዚአብሔር ተሳስቶ ነበር፥ እርማት አስፈልጎት ነበር ማለት ነው? ይህ ከሆነ እግዚአብሔር ይስታል ወይም ይሳሳታል ማለት ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ጥቅሶች እግዚአብሔር አይጸጸትም ይላሉ። ለምሳሌ፥ ዘኍ. 23፥19፤ 1ሳሙ. 15፥29፤ መዝ. 110፥4፤ 132፥11፤ ኤር. 4፥28፤ 20፥16፤ ሕዝ. 24፥14፤ ዘካ. 8፥14፤ ሮሜ 11፥29፤ ዕብ. 7፥20-21። እነዚህ ጥቅሶች በግልጽ እግዚአብሔር አይጸጸትም ይላሉ። ስለዚህ ቃሉ እርስ በርሱ ይጋጫል ማለት ነው? ወይስ እውነት እግዚአብሔር ይጸጸታል?

መጸጸት ማለት ለሰው ሲነገር መሳሳትን ማስተዋል፥ ትክክል እንዳልሆኑ ወይም እንዳላደረጉ ማወቅ፥ መቆጨት፥ ከስሕተት መመለስ ማለት ነው። መጸጸት ለእግዚአብሔር ከተነገረና በተመሳሳይ ትርጉም ካገናዘብነው እግዚአብሔርነቱን ያዋርዳል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ነው። ሁሉን አዋቂም ነው። ስለዚህም ሰው በሚሳሳትበት መንገድ ሊሳሳት ከቶም አይታሰብምና አይጸጸትም።

እግዚአብሔር ተጸጸተ ሲባል መታረሙን ወይም ራሱን ማረሙን ማሳየቱ ነው? አይደለም። እዚህ ጸጸት የተባለው ቃል נָחַם (ናኻም) የሚል ነው። ቃሉ እህህ! ማለት ማዘን፥ መራራት ማለት ነው። በብዙ ጥቅሶች መጽናናት እና ማጽናናት የተባለው ቃል ይህ ነው። ናሆም፥ ነህምያ፥ ኑሐሚን የሚባሉት ስሞች ምንጫቸው ይህ ቃል ነው። በበርካታ ጥቅሶች ውስጥም ቃሉ ማጽናናት ወይም መጽናናት እየተባለ ተጠቅሶአል፤ ለምሳሌ፥ ዘፍ. 37፥35፤ ሩት 2፥13፤ ኢሳ. 12፥1፤ 61፥2፤ ወዘተ። መጽናናት ወይም ማጽናናት እንደምናውቀው ከኀዘን ጋር የተቆራኘ ቃል ነው። ተጸጸተ የሚለው ቃል ከላይ እንዳየነው መሳሳት ሳይሆን ማዘን ወይም መራራት መሆኑን ለማየት ጥቂት በዚህ ትርጉም የተጠቀሱትን የዚህን ተመሳሳይ ቃል נָחַם (ናኻም) አጠቃቀሶች እንመልከት።

ዘጸ. 32፥12 እና 14፤ ግብፃውያንስ፦ በተራራ መካከል ሊገድላቸው፥ ከምድርም ፊት ሊያጠፋቸው ለክፋት አወጣቸው ብለው ስለ ምን ይናገራሉ? ከመዓትህ ተመለስ፥ ለሕዝብህም በክፉታቸው ላይ ራራ። እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ።

ኢሳ. 49፥13፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን አጽናንቶአልና፥ ለችግረኞቹም ራርቶአልና ሰማያት ሆይ፥ ዘምሩ፥ ምድር ሆይ፥ ደስ ይበልሽ ተራሮችም ሆይ፥ እልል በሉ።

በነዚህ ጥቅሶች መራራት የሚለው ቃል እና ቀደም ሲል ያየነው ተጸጸተ የሚለው አንድ ናቸው።

ዘዳ. 32፥36፤ ኃይላቸውም እንደ ደከመ፥ የተዘጋ የተለቀቀም እንደሌለ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳል፥ ስለ ባሪያዎቹም ያዝናል።

መሳ. 2፥18፤ እግዚአብሔርም መሳፍንትን ባስነሣላቸው ጊዜ እግዚአብሔር ከመስፍኑ ጋር ነበረ፤ እግዚአብሔርም ስለሚጋፉአቸውና ስለሚያስጨንቋቸው በጩኸታቸው ያዝን ነበርና በመስፍኑ ዘመን ሁሉ ከጠላቶቻቸው እጅ አዳናቸው።

2ሳሙ. 24፥16፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ኢየሩሳሌምን ያጠፋት ዘንድ እጁን በዘረጋ ጊዜ እግዚአብሔር ስለ ክፉው ነገር አዘነ፥ ሕዝቡንም የሚያጠፋውን መልአክ፦ እንግዲህ በቃህ እጅህን መልስ አለው። የእግዚአብሔርም መልአክ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠገብ ነበረ። ይኸው ታሪክ በተጻፈበት ሌላ ስፍራ፥ በ1ዜና 21፥15፤ እግዚአብሔርም ያጠፋት ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም መልአክን ሰደደ፤ ሊያጠፋትም በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር አይቶ ስለ ክፉው ነገር ተጸጸተ፥ የሚያጠፋውንም መልአክ፦ በቃህ አሁን እጅህን መልስ አለው። የእግዚአብሔርም መልአክ

በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር። በ2ሳሙ. 24፥16 አዘነ የተባለው ተመሳሳይ ቃል ነውና በ1ዜና 21፥15 ተጸጸተ ተብሎአል።

በእነዚህ ጥቅሶች ያለው ማዘን የሚለው ቃል እና ተጸጸተ የሚለው አንድ ናቸው።

ኤር. 15፥6፤ አንቺ እኔን ጥለሻል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ ወደ ኋላሽም ተመልሰሻል፤ ስለዚህ እጄን በአንቺ ላይ ዘርግቼ አጥፍቼሻለሁ፤ ከይቅርታ ደክሜአለሁ።

ይቅርታ የሚለው ቃል እና ተጸጸተ አንድ ናቸው።

ኤር. 26፥3፥13፤ 26፥19፤ ምናልባት ይሰሙ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ይመለሱ ይሆናል፤ እኔም ስለ ሥራቸው ክፋት ያሰብሁባቸውን ክፉ ነገር እተዋለሁ። . . . አሁንም መንገዳችሁንና ሥራችሁን አሳምሩ፥ የአምላካችሁንም የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ እግዚአብሔርም የተናገረባችሁን ክፉ ነገር ይተዋል። . . . በውኑ የይሁዳ ንጉሥ ሕዝቅያስና ሕዝቡ ሁሉ ገደሉትን? በውኑ እግዚአብሔርን አልፈሩምን? ወደ እግዚአብሔርስ አልተማለሉምን? እግዚአብሔርስ የተናገረባቸውን ክፉ ነገር አይተውምን? እኛም በነፍሳችን ላይ ታላቅ ክፋት እናደርጋለን።

እዚህ መተው የተባለው ከመጸጸት ጋር አንድ ቃል ነው።

ሲጠቃለል፥ መጸጸት ማለት ለሰው ሲነገር መሳሳትን ማስተዋል፥ ትክክል እንዳልሆኑ ወይም እንዳላደረጉ ማወቅ፥ ከስሕተት ለመምመለስ ብሎ መቆጨት ማለት ነው። መጸጸት ለእግዚአብሔር ከተነገረና በተመሳሳይ ትርጉም ካገናዘብነው እግዚአብሔርነቱን ያዋርዳል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም አይደለም ያሰኛል። እግዚአብሔር ግን ፍጹም አምላክ ነው። ሁሉን አዋቂም ነው። ስለዚህም ሰው በሚሳሳትበት መንገድ ሊሳሳት ከቶም አይታሰብምና አይጸጸትም። ነገር ግን ያዝናል፤ ይራራል፤ ይቅር ይላል፤ ይተዋል። ይህ ማዘን፥ መራራት፥ ይቅር ማለት፥ እና መተው ነው በአማርኛ መጸጸት የተባለው።

* * * * *

31. እግዚአብሔር ይፈትናል?

ሰላም ለአንተ ይሁን ፓስተር ጥያቀ መጠየቅ ፍልገ ነበር ስለ ከፍታ አጭር ፁሁፍ ፅፈህ ነበር ጥያቅዬ እ/ር ሰውን ይፈትናል? 1. ያዕቆብ አይፍትንም እርሱ እራሱ በማንም አይፈተንም ብሎናል እንዴት? 2. ሙሴ ደግሞ እ/ርም አብርሃምን ፈተነው ይለናል? 3. እ/ር የኤስራኤልን ልጆች ፈተነ ? 4. ከሐዋርያት አብዘኞች መጥምቁ ዮሐንስም ጭምር በፈተና ህይወታቸው አልፋአል ግን ለም? 5. በክፉ አይፍትንም ይላል ነብያትና ሐዋርያት ከክፋም የክፉ ክፉ ፈተና ነው የተፈተኑት እንደት ነው ልታረቅ የሚችላው? (ቤ. አ.)

ሰላም ቤ፤ ፈተና ሲባል ሁለት ዓይነት ፈተና መኖሩን በመጀመሪያ ማወቅ አለብን። አንዱ ፈተና ሆን ተብሎ እንድንሰናከል፥ እንድንፍገመገም፥ እንድንወድቅ የሚቀርብልን ፈተና ነው። ይህ በሌላ ቃል ማሳት፥ ማታለል ነው። ይህ በክፉ መፈተን የሚባለው ነው። እግዚአብሔር በባሕርይው ቅዱስ ነውና ይህን ማሳት አያስትም፤ ስለዚህ ይህን መሳይ ፈተናን አይፈትንም።

ሌላው የፈተና አሳብ ግን ማንነትን የሚገልጥ፤ ጥንካሬን የሚፈትሽ፤ እና ይበልጥ የሚያጠነክር፤ እምነትን የሚያጎለብት፤ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያጣብቅ ፈተና ነው። ይህ ጠቃሚውና አስፈላጊው ፈተና ነው። ጉልበትን ልምድን፥ አእምሮን፥ እምነትን፥ መንፈሳዊነትን፥ ያሳድጋል። ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተን በየሴሚስተሩና በየዓመቱ መጨረሻ የምንወስደው ፈተና ባይኖር ማወቃችንና ብቃታችን በምን ይለካል? ይህ ጤናማው ፈተና ነው። ይህንን መግቢያ አድርጌ ወደ ጥያቄዎችሽ ልለፍ። ጥያቄዎችሽ ብዙ አደረግሻቸው እንጂ ሁለት ብቻ ናቸው።

1. 1ኛውና 5ኛውን አንድ ላይ ልመልስ። ያዕቆብ እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንም አላለም። እርሱም ይፈትናል አላለም፤ ያዕ. 1፥13ን ልብ ብለሽ ተመልከቺው፤ ማንም ሲፈተን፡- በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም። ነው የሚለው። እዚህ እግዚአብሔር ፈታኝ ሳይሆን ተፈታኝ ነው። ደግሞም እዚህ ክፉ የተባለው ፈተናው ወይም ነገሩ ሳይሆን ፈታኙ ነው፤ ሰይጣን ነው ክፉው የተሰኘው። ሰይጣን ፈታኝ ነው፤ ከነስሙም በማቴ. 4፥3 እና 1ተሰ. 3፥5 ፈታኝ ተብሎአል። ሰይጣን ሰዎችን የሚፈትነው የበለጠ ነጥረው እንዲወጡ ሳይሆን ለማሰናከልና ለመጣል ነው።

2. የቀሩት (2-4) ተቀራራቢ ስለሆኑ አንድ ላይ ልመልሳቸው። እነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ያለው ፈተና የሰውን ፈቃድ ለእግዚአብሔር ከማስገዛት ጋር የተያያዘውን ፈተና የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር የፍተሻ ፈተናን ይፈትናል። እግዚአብሔር እንደሚፈትን እና ለምን እንደሚፈትን እነዚህን ጥቅሶች ማየቱ ይረዳል፤ ዘጸ. 15፥25፤ 16፥4፤ 20፥20፤ ዘዳ. 4፥34፤ 13፥3፤ ዮሐ. 6፥6።

በዔድን ገነት እነ አዳም አትብሉ የተባሉት ዛፍ መኖር እነ አዳምን ለመጣል ሳይሆን ታዝዘው፥ ፈቃዳቸውን አስገዝተው እንዲኖሩ ነው። አብርሃም መፈተኑ በግልጽ ተጽፎአል፤ ዘፍ፣ 22። እግዚአብሔር ሲፈትን ለመጣል አለመሆኑን የምናውቀው ለአብርሃም በተዘጋጀው የፈተናው ማለፊያ ነው፤ ሆኖም አብርሃም ማመኑን እንጂ የዚያ አስቸጋሪ ጥያቄ መልስ እዚያው መኖሩን አያውቅም ነበር። 1ቆሮ. 10፥13 ይህን እውነት በግልጽ ይነግረናል፤ ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል። በተጨማሪ 2ጴጥ. 2፥9-10 እና ራእ. 3፥10 ይህንኑ ያስተምሩናል። እንዲህ ያለው ፈተና እምነታችን ይበልጥ ከብሮ፥ ነጥሮ፥ ጠርቶ እንዲወጣ የሚያደርግ ፈተና ነው፤ 1ጴጥ. 1፥6-7። በእንዲህ ያለው ፈተና ሰዎች ከወደቁ ልባቸው ያለበትን ስፍራ፥ ዓመጸኛና የማይታዘዙ መሆናቸውን ነው የሚያሳየው።

ሌላው የፈተና አሳብ መከራ ነው። መከራ በራሱ ፈተና ነው ሊባል ይችላል። በእግዚአብሔር ላይ መታመናችንን ይፈትሻል። አቋራጭ ፈላጊዎች መሆንና አለመሆናችንን ይገልጣል። አፈግፋጊዎች መሆናችንንና አለመሆናችንን ይለያል። መከራ በዚህች በወደቀች ዓለም ስላለን በሰው ልጆች፥ በአዳም ልጆች ላይ የሚመጣ ክስተት ነው። ከእንደዚህ ያለው ፈተና ወይም መከራ የጸዳን አይደለንም፤ መሆንም አንችልም። በተለይ እኛ ክርስቲያኖች በዓለም ስንኖር መከራ እንዳለብን በግልጽ ተነግሮናል፤ ለምሳሌ፥ ዮሐ. 16፥33። ያዕቆብ ስለ ፈተና የተናገረው፥ ፈተና መኖሩንና ፈተናን በሕይወታችን የሚሠራው ሥራ ስላለ እንደ ደስታ መቁጠር እንዳለብን፥ ያዕ. 1፥1-3፤ በፈተና መጽናት ማስፈለጉን፥ ቁ. 12፤ እግዚአብሔር አለመፈትተኑን፥ ቁ. 13፤ ሰው በራሱ ምኞት የሚፈተን መሆኑን፥ ቁ. 14 ነው። ሰው በምኞቱ፥ በሥጋው፥ በሰይጣን፥ በዚህች ዓለም ውበት ይፈተናል። ይህን ወደ መሰለው ፈተና እንዳንገባ እንድንጸልይ ጌታ አስተምሮናል፤ ማቴ. 6፥13፤ 26፥41።

ሲጠቃለል ፈተና ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው ምንጩ ከሰይጣን የሆነው፥ ዓላማውና ግቡ ውድቀት የሆነው ፈተና ነው። ሌላው እምነታችን በእግዚአብሔር ላይ እንዲጸና፥ እንዲጠነክር፥ በእግዚአብሔር ላይ ያለን መታመን እንዲልቅ፥ ለሌሎችም እንዲገለጥ በሕይወታችን የሚመጣ ምንም ዓይነት ነገር ነው። መከራ ሊሆን ይችላል፤ ጥጋብም ሊሆን ይችላል። ከጸናን የተሻልን ክርስቲያኖች እንሆናለን። እግዚአብሔር እንድንወድቅ፥ እንድንሰናከል ሳይሆን አብርሃምን እንደፈተሸው፥ ኢዮብን እንደተመካበት ይፈትሸናል። በውጤቱም እርሱ ይከብራል። የኛም መታመን ወደ ላቀ ደረጃ ይሸጋገራል።

* * * * *

32. የአልኮል መጠጥ መጠጣት ፈጽሞ የተከለከለ ነው?

> ክርስቲያን መጠጥ መጠጣት አልተከለከለምና በምግብ ቤት ውስጥ መጠጥ ቢሸጥ ገበያውን እስከሳበ ድረስ ክፋት የለበትም የሚል ክርክር ነበረን። አንዷ እህታችን ለምን ጨርሶ መጠጥ መጠጣት ታሰበ? እኛ የማንጠጣውን ነገር ለምን መሸጥስ አስፈለገ? የሚል ጥያቄና ክርክር ይዘናል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ምንድነው?

ይህ ብዙዎች የሚጠይቁት፥ የማይጠይቁም የሚፈተኑበት ጉዳይ ስለሆነ ለጥያቄው ጥያቄነት ብቻ ሳይሆን ከዚያ ባለፈም በስፋት ልመልሰው።

ለክርስቲያን ወይን መጠጣትና ማጠጣት የተፈቀደ ነውን? በአንድ ጎራ አስካሪ መጠጥን የሚኮንኑ ከቶም ሊጠጣ ይቅርና ሊታሰብም የተገባ አይደለም የሚል አቋም የያዙ አሉ። በሌላው መጠጥ መጠጣት ይፈቀዳል ስካር ነው የሚከለከለው? የሚል አቋም ያላቸው አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙዎች የተመሰገኑና የተመሰከረላቸው ሰዎች

የወይን ጠጅ ጠጥተዋል፤ ጌታም የወይን ጠጅ ጠጥቶአል፤ ታዲያ ቢጠጣ ምን አለበት? የሚሉ ናቸው። 'በመጠጥ ደስታ ይገኛል ብላችሁ፤ መጠን አትለፉ ትቃጠላላችሁ' ነው ያለው ዘፋኙ የሚሉ ዓይነቶቹ ናቸው። ከነዚህ አንዳንዶቹ ራቅ ያለና እስከ መስከርስ ቢሆን? የሚል እርምጃ ይራመዳሉ።

በሁለቱም መሐል ያሉቱ ደግሞ ይህ የግለሰቡ ኅሊና ጉዳይ ነውና ለግሉ ውሳኔ መተው ነው እንጂ በዚህ ጉዳይ መነጋገር አስፈላጊ አይደለም የሚሉ መሐል ሰፋሪዎች ናቸው። የማይጠጣ ለጌታ ብሎ አይጠጣ፤ የሚጠጣም መንፈስ ከመሰከረለት ይኮምኩም ባዮች ናቸው። ስለዚህ አስካሪ መጠትም ሆነ ሌሎችም ሱስ የሚያስይዙም ሆኑ የማያስይዙ ነገሮች የግለሰቡ ኅሊና ውሳኔ ነው የሚል ኅሊናዊ አቋም ይይዛሉ።

ከነዚህ የማይርቁቱ ሌሎች ደግሞ መጠጣትም ሆነ አለመጠጣት ሰውነታችንን/ነፍሳችንን የማርከስ አቅም ስለሌለውና ደኅንነታችንን ከቶም ሙሉ ወይም ጎዶሎ ስለማያደርገው ይህ ጉዳይ እጥያቄ ውስጥም መግባት የለበትም የሚል ዳኝነት ይዳኛሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፈው አገባባቸው በመነሣት ወይንና የወይን ጠጅ እንዲሁም የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ የተለያዩ መሆናቸውን ማወቅ እንችላለን። ምክንያቱም እነዚህ ቃላት ተነባብረው የተቀመጡባቸው ስፍራዎች አሉና፤ ለምሳሌ፥ ዘሌ. 10፥9፤ ዘዳ. 29፥6፤ መሳ. 13፥4-14፤ 1ሳሙ. 1፥15፤ ኢሳ. 24፥9፤ ሉቃ. 1፥15። ከነዚህ አጠቃቀሶች በመንደርደር የወይን ጠጅ ሁሉ አስካሪ መጠጥ ነው ብለን እንዳንደመድም ሊያስገድደን የሚችል እውነት መኖሩን እናስተውላለን።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ጥቂት አሳቦችን በነጥብ አስቀምጣለሁ። ለእያንዳንዱ ነጥብም ጥቂት ናሙና ጥቅሶች አክላለሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው የወይን ጠጅ በዘመናችንም ያንኑ ቃል ይወክላል። አስካሪ መጠጥም ማናቸውንም አስካሪ መጠጥ ሊወክል ይችላል።

1. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወይን ልብን የሚያስደስት መሆኑ ተጽፎአል።

አንድ የኢትዮጵያ የወይን ጠጅ ፋብሪካ፥ አዋሽ የወይን ጠጅ ፋብሪካ ይመስለኛል፥ በመጠጥ ማከፋፈያ የጭነት መኪናዎቹ ላይ የመዝ. 104፥15ን በግዕዝ *ወይን ያስተፌስህ ልበ ሰብእ* ብለው ጽፈው ይዞሩ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በተወገዘበት የደርግ ዘመን እንኳ ሳይቀር ይህ ጥቅስ መነገኛ ሆኖ ነበር። እውን ወይን ያስተፌስህ? የወይን ጠጅ በእርግጥም ልብን ያስደስታል? ቃሉም እንደሚያስደስት ይናገራል፤

መሳ. 9፥13 ወይኑም፥ እግዚአብሔርንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ? አላቸው።

በተጨማሪ፥ ዘካ. 10፥7፤ መክ. 2፥3፤ መዝ. 104፥15።

2. ወይን ወይም የወይን ጠጅ በብሉይም ሆነ በአዲሱ ኪዳናት ዘመን በአይሁድ ዘንድ የተለመደ ባህላዊና ማኅበራዊ መጠጥ ነው።

ለመስተንግዶ፥ ለሠርግ፥ ለበዓላት፥ ለድግስ፥ ለነገሥትና ለመኳንንት፥ ለስጦታ፥ ለክፍያም ይውል ነበር። ንጉሦች ወይንና የወይን ጠጅ የሚያከማቹባቸው ማከማቻዎችና በተለይ ለዚህ የተሾሙ ሹሞችም ነበሩአቸው። ለምሳሌ፥

ዘፍ. 14፥15 የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ።

1ሳሙ. 16፥20 እሴይም እንጀራና የወይን ጠጅ አቁማዳ የተጫነ አህያ የፍየልም ጠቦት ወስዶ በልጁ በዳዊት እጅ ወደ ሳኦል ላከ።

በተጨማሪ፥ 1ሳሙ. 25፥11፤ 2ሳሙ. 16፥1-2፤ 1ዜና 27፥27፤ ነህ. 2፥1።

በዮሐ. 2፥3-10 ጌታ በመጀመሪያ ያደረገው ተአምሩ ውኃን ወደ ወይን መለወጡ ተጽፎአል።

ይህ ሠርግ ጌታ ተጋብዞ ወይም ታድሞ የሄደበት ሠርግ ነው። እናቱ ማርያም ውስጠኛና የቅርብ ሰው ሳትሆን አትቀርም። ባይሆን የጓዳውን ምስጢር፥ የወይን ጠጁን ማለቅ፥ ለጌታ አትናገርም ነበር። ይህ የወይን ጠጅ መጠጥ የሚጠጣበት ድግስ ስፍራ ነው፤ ወይን ጠጅ ደግሞ አለቀ። ጌታ በጉዳዩ ተሳታፊ ካልሆነ የሚያሳፍር ነገር ሊከሰት ነው። ጌታ ተአምራትን ያደርግ የነበረው ሁኔታዎችን ለመለወጥና ተአምራትን ማድረጉ አስፈላጊ ሲሆን ነው። ጌታ ተአምራትን እንዲያው እንደ በታኝ ዘሪ ሲበትን አይታይም። እዚህ አስፈልጎ ነበር። ደግሞም የመጀመሪያ ተአምሩ ነው። ጌታ በአካል በተገኘበት ሠርግ ጎዶሎነት አይኖርምና በመልካሙ ወይን ተአምር ሠርጉን ከጎዶሎነትና ከእፍረት ጠበቀ። ሠርጉን የታደገው ወይን ጠጁ ሳይሆን የጌታ መገኘት ነው። የጌታን የራሱን ምሳሌነት በሌላ ነጥብ እንመለከታለን።

ይህንን ተአምር አስካሪ መጠጥ የመጠጫ ዋነኛ መከራከሪያ የሚያደርጉ ጠጪዎች አሉ። ይህ ወይን ጠጅ የሚጠጣበት ባህላዊ ድግስ ነው። ሠርግ ነው። ወይን ጠጁም ከመናኛ ወይም ከቀጠነው እስከ መልካሙ ወይም ኃይለኛውና አስካሪው የሚለያይ ነው። ጌታ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠው ወደ መናኛው ሳይሆን ወደ መልካሙ ነው። ይህ በሰው እጅና ጊዜ የተጠመቀው ስላልሆነ ከመልካሙም የተሻለው መሆን አለበት።

3. ለመቅደስ አገልግሎትና ለመሥዋዕት ይቀርብ ነበር።

የወይን ጠጅ እንደ መጠጥ ቁርባን እና የሚፈስስ መስዋእት በመሆን ይቀርብ ነበር። የወይን ጠጅ እንደ አስራትም ሆኖ ለሌዋውያን ይሰጥ ነበር። ሕዝቡ በዓመታዊ በዓላቸውን ደስ እንዲላቸው ወይን ጠጅና ብርቱ መጠጥ ሊጠጡ ተፈቅዶላቸዋል።

ዘሌ. 23፥13 የእህልም ቍርባን ከመስፈሪያው ከአሥር እጅ ሁለት እጅ የሆነ በዘይት የተለወሰ መልካም ዱቄት ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን ለእሳት ቍርባን ይሁን የመጠጡም ቍርባን የወይን ጠጅ የኢን መስፈሪያ አራተኛ እጅ ይሁን።

በተጨማሪ፥ ዘኁ. 15፥4-7፤ ዘዳ. 12፥17፤ 14፥23 እና 26፤ 18፥4፤ ሆሴ. 2፥10-11።

4. በአገልግሎት ወቅት/ዘመን ግን እንዳይጠጡ ተደንግጎአል።

የወይን ጠጅ ለመስዋእትና ለስጦታ ይቅረብ እንጂ ሌዋውያን በአገልግሎታቸው ወቅት መጠጣት አልተፈቀደላቸውም።

ዘሌ. 10፥9 እንዳትሞቱ ወደ መገናኛው ድንኳን ስትገቡ አንተና ልጆችህ የወይን ጠጅና የሚያሰክርን ነገር ሁሉ አትጠጡ ይህም ለልጅ ልጃችሁ የዘላለም ሥርዓት ይሆናል

ሕዝ. 44፥21 ካህናቱም ሁሉ በውስጠኛው አደባባይ ሲገቡ የወይን ጠጅ አይጠጡ።

ለምን ተከለከሉ? አገልጋዮች ናቸው። አገልግሎታቸው አምልኮ ነው። በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡ ሰዎች ናቸውና አእምሮአቸው መበረዝ የለበትም። በአንቂም በአደንዛዥም ንጥረ ነገር መመረዝ የለባቸውም። ይህ በተለይ ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች ትልቅ ትምህርት ነው። የአዲስ ኪዳን አማኞች በሙሉ አገልጋዮች ናቸው፤ የንጉሥ ካህናት ናቸው፤ እግዚአብሔርም እንደብሉይ ዘመን ጊዜና የመቅደስ ቦታ የሚወሰንለት ሳይሆን በመንፈስና በእውነት ሁሌና የትም የሚመለክ አምላክ ነውና አምላኪዎቹና አገልጋዮቹ ሁሌም ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ እንደተባለው ሊሆኑ የተገባ ነው።

ናዝራውያን የዚህ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ናዝራውያን በናዝራዊነት ዘመናቸው ወይንና የወይን ጠጅ፥ የወይኑን ፍሬና ዘቢቡንም፥ ገፈፎውንም አይቀምሱም። ናዝራዊነታቸው ሲጠናቀቅ ብቻ መብላትም መጠጣትም ይችላሉ፤ ዘኁ. 6፥3-20፤

ሶምሶን ከመጸነሱ ጀምሮ ናዝራዊ ነበርና ሳይወለድ ጀምሮም እናቱ እንድትጠነቀቅ ተነገራት፤ መሳ. 13፥4-14

ሬካባውያን ሌላ ምሳሌዎች ናቸው፤ ታሪካቸው በኤር. 35፥1-9 ይገኛል።

እስራኤል በምድረ በዳው ጉዞአቸው ዘመንም ወይንና የሚያሰክር አልጠጡም። ያ ጉዞ የግንኙነትና የአምልኮ ጉዞ ነበረ፤ ገልበጥባጣና የማያምን ትውልድ ሆኑና በምድረ በዳ ቀሩ እንጂ የተጠሩትና የወጡትስ የካህናት መንግሥት ሆነው ሊያገለግሉትና ሊያመልኩት ነበረ። የተለየ ሕዝብ ሊሆኑለት ነበረ። ስለ ምድረ በዳው ጉዞ መልክ እንዲህ ተጽፎአል፤ ዘዳ. 29፥6 እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቁ ዘንድ እንጀራ አልበላችሁም፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክረውን መጠጥ አልጠጣችሁም።

የአዲስ ኪዳን አማኞች/አገልጋዮች ቅዱሳን ተብለዋል። ቅዱስ ማለት የተለየ ማለት ነው። እንደ ናዝራውያን መለየት የተለዩ ናቸው። መለየታቸው ግን እንደ ናዝራውያን ለጊዜው ሳይሆን ለሕይወት ዘመን ሁሉ ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎቱ ከወይን ጠጅና አስካሪ መጠጥ የጸዳ ነበረ። ሉቃ. 1፥15 በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤

ናዝራውያን በናዝራዊነታቸው ዘመን፥ ሌዋውያን በአገልግሎት ዘመናቸው፥ ሬካባውያን በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ፥ እስራኤል በነጻነት ጉዞአቸው ወቅት፥ መጥምቁ በዘመኑ ሁሉ መጠጥ አልጠጡም ነበር። ለእግዚአብሔር መለየት ማለት እግዚአብሔርን ማምለክና እርሱን ማገልገል ነው፤ ከእርሱ ጋር አብሮ የመሆንና የኅብረት ጊዜ ነውና አእምሮ በምንም ሌላ ገዢና ተቆጣጣሪ ስር መሆን የለበትም።

እነዚህ ያልጠጡቱ ወይም እንዳይጠጡ የተከለከሉቱ ለምን እንደተከለከሉ ስናጤን ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 14፥17 *የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና* ያለውን በውል መረዳት አይከብደንም።

5. ወይን ጠጅ አስከፊ መልክ አለው። በርካታ ምሳሌዎችም ተዘርዝረውልናል።

ጥንት ግሪካውያን አስተማሪዎች ለተማሪዎቻቸው የአስካሪ መጠጥን አስቀያሚነት ለማሳየት ወደ ማስተማሪያ ክፍላቸው ሰክሮ የጠነበዘ ሰው አምጥተው ያሳዩአቸው ነበር። ስካር በቀላሉ አታልሎ የሚወስድ ስለመሆኑ ደግሞ እንዲህ የሚል ምሳሌም ነበራቸው፤ በመጀመሪያ ለራስህ አንድ ዋንጫ ወይን ትጋብዛለህ፤ ቀጥሎ የጠጣኸው ወይን ሌላ ዋንጫ ይጋብዝሃል፤ ከዚያም የጠጣኻቸው ዋንጫዎች አንተን ይጠጡሃል።

መጽሐፍ ቅዱስ የወይን ጠጅን አስቀያሚ መልክም በግልጽ አስፍሮልናል። በበዓለ ኀምሳ ዕለት ደቀ መዛሙርት በሌሎች ቋንቋዎች ሲናገሩ ሲያደምጡአቸው፥ ሌሎች ግን እያፌዙባቸው፥ ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ። ሐዋ. 2፥13። እነዚህ ሰዎች ያልሰከሩ ቢሆኑም እንኳ እያፌዙባቸው የሚለው ቃል የወይን ጠጅ የጠገቡ ሰዎች የሚፌዝባቸው የፌዝ ጊጤዎች ናቸው ማለት ነው።

ዔሊም፥ ስካርሽ እስከ መቼ ነው? የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው አላት። 1ሳሙ. 1፥14። ሐና አልሰከረችም ሆኖም በመምሰሏ ይህም ቃል የወይን ጠጅን ውጉዝነት ያሳያል።

በተጨማሪ፥ ሆሴ. 4፥11፤ አሞ. 12፥2፤ ኢሳ. 28፥7።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች የወይን ጠጅ ሰለባ ሲሆኑ ይስታሉ፥ ያስታሉ፥ ያጠፋሉ፤ ይጠፋሉ። በአዲስ ኪዳን አገልጋይና ተገልጋይ የሚባል መደብ አለመኖሩን ማስተዋል

አለብን። ሁላችንም ካህናት፥ ሁላችንም ጸጋ የተቀበልን አገልጋዮች ነን። ስለዚህ ራሳችንን ከነዚያ የብሉይ ኪዳን ሁነኛ አገልጋዮች እንደ አንዱ ብናደርግ ትክክል ነን።

ጠጥተው የሳቱና ከመስመር የወጣ ነገር ያደረጉ ወይም የተደረገባቸው በርካታ ምሳሌዎች ተሰጥተውናል። ኖኅ ጠጣ፥ ሰከረ፥ እርቃኑ ታየ። አንድ የልጅ ልጁን ለእርግማን አሳልፎ ሰጠው።

ዘፍ. 9፥ 20-21 እና 24 ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ፥ ወይንም ተከለ። ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ በድንኳኑም ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ። ኖኅም ከሐዋ. 2፥13 ጠጁ ስካር ነቃ፥ ታናሹ ልጁ ያደረገበትንም አወቀ።

ሎጥ ሰከረ፤ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር ተኛ፤ ሲተኛና ሲነሣ ወይም በመካከል የሆነውን ነገር አላወቀም፤ ዘፍ. 19፥32-35።

አርጤክስስ ከመጠጡ በኋላ የሚስቱን ውበት ወደ አደባባይ ጠራ። ይህ ያልተለመደ ባህል ነበረ፤ አስ. 1፥10-11።

ብልጣሶር የወይን ጠጅ በቀመሰ ጊዜ የእግዚአብሔርን ንዋየ ቅድሳት ሊያረክስ ደፈረ፤ ዳን. 5፥ 1-23።

እነዚህን ሰዎች ስናይ በአስካሪ መጠጥ ግፊት ደፋሮች ሆነው ከመስመር የወጣ ነገር ሲያደርጉና ሲሆኑ እናገኛለን። መጠጥ ድፍረት ይሰጣል። ድፍረቱ ደግሞ ለመጥፎ ግብና ዓላማ ነው። በመጠጥ ዓይን አፋሩ ዓይን አውጣ ይሆናል። ጭምቱም ፎካሪ ይሆናል፤ ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል እንዲሉ።

6. የጠቢቡ ምክር

ጠቢቡ ንጉሥ ሰሎሞን ነው። ሰሎሞን ራሱ ወይንን የሚያውቅ፥ የወይን ጠጅን የቀመሰና ያጣጣመ፥ ሰውነቱን በወይን ጠጅ ያስደሰተ ሰው ነውና የመጽሐፉ ምክሮች የንድፈ ሐሳብ ብቻ ሳይሆኑ ከጠንካራ ተሞክሮ የተገኙ ናቸው። ተሞክሮውን ከመክ 2፥ 3 እናገኛለን። ምክሩን ደግሞ፥ ምሳ. 20፥1፤ 21፥17፤ 23፥20፤ ምሳ. 31፥4-6 እናገኛለን።

ምሳ. 23፥29-35 ዋይታ ለማን ነው? ኀዘን ለማን ነው? ጠብ ለማን ነው? ጩኸት ለማን ነው? ያለ ምክንያት መቍሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው? የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? የተደባለቀ የወይንን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚከተሉ አይደለምን? ወደ ወይን ጠጅ አትመልከት በቀላ ጊዜ፥ መልኩም በብርሌ ባንጸባረቀ ጊዜ፥ እየጣፈጠም በገባ ጊዜ። በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል፥ እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈስሳል። ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ፥ ልብህም ጠማማ ነገርን ይናገራል። በባሕር ውስጥ እንደ ተኛ ትሆናለህ፥ በደቀልም ላይ እንደ ተኛ። መቱኝ፥ ያውም አልተሰማኝም ጐሰሙኝ፥ አላወቅሁምም። መቼ እነሣለሁ? ደግሞ ጨምሬ እሻታለሁ ትላለህ።

እነማን መጠጣት እንዳለባቸውና እንደማን መጠጣት እንደሌለባቸው ምሳ. 31፥4-6 ይነግረናል።

መጽሐፍ ቅዱስ መስከርን መከልከሉ እውነት ነው። የወይን ጠጅ መጠጣትን አይከለክልም ብሎ ለመጠጣት ከመጋበዝ ይልቅ አለመምከሩንና አለማደፋፈሩን ማጉላቱ አግባብ አለው። ይህ ክፍል አለማደፋፈር ብቻ ሳይሆን አለመጠጣትም ብቻ ሳይሆን አለማየትንም ሲመክር ይታያል። አትጠጣ ብቻ ሳይሆን አትይ! ከሚጠጡ ጋርም አትቀመጥ። ስለዚህ 'ቃሉ አትስከር ነው የሚለው እንጂ አትጠጣ አይልም' ለሚሉት 'አትስከር ብቻ ሳይሆን አትመልከት፤ ከጠጪዎች ጋርም አትቀመጥም ይላል' ማለት ትክክለኛ መልስ አይሆንም?

የመጠጥን ውጤቶች ሲዘረዝር ዋይታ፥ ኀዘን፥ ጠብ፥ ጩኸት፥ መቁሰል፥ የዓይን ቅላት፣ ጋለሞታን ማየት፥ ጠማማ ነገርን መናገር፥ ፌዘኛ መሆን፥ ጠበኛ መሆን፥ ሕግን መርሳት፥ ፍርድን ማጉደል፥ ድኃ መሆን አሉበት። ይህ ከዚህ ክፍል ብቻ ነው።

አንዳንድ የመጠጥ ምርኩዞች አልኮል ለስርዓተ-ሰውነታችን ያስፈልገዋልና ስለዚህ መጠጣት ጥቅም አለው ይላሉ። የሕክምና ባለሙያዎችን ትንታኔ ከተከታተልን ግን ሰውነታችን ከምንወስደው ከማናቸውም መብልና መጠጥ የሚያስፈልገውን ሁሉ መቀመም የሚችል ተፈጥሮ እንዳለው ይነግሩናል። የሰውነትን አሠራር ለመርዳት አልኮልና አስካሪ መጠጥ በምንም መንገዱ መውሰድ ግን ጉዳቱ ብዙ መሆኑንም በግልጽ ያስረዱናል። የዘመናችን ጠቢባንም ከጠቢቡ ምክር ጋር ስምም ናቸው። ስለዚህ ከሰካራሞችና ከዶክተሮች ምክር የቱ ይመረጣል?

ለጥፋት የቀረበው ግን እንዲጠጣ መመከሩ ከጥፋት፥ ጥፋት የሚለው ቃል ይህንም የሚያሳይ ነውና ራሱን ከማጥፋት ወይም ከመግደል እንዲታቀብ ይመስላል።

7. የጌታ ምሳሌነት

ቀደም ሲል ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ መለወጡን አይተናል። ጌታ እየበላና እየጠጣ መምጣቱን ተናግሮአል። ይህ ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር ራሱን በማነጻጸር የዘመኑን አይሁድ ለመውቀስ የተናገረው ነው።

የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፥ እርሱም፦ እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ ይሉታል። ጥበብም በልጆችዋ ጸደቀች። ማቴ. 11፥ 19።

ሉቃ. 7፥33-34 ተመሳሳይ ቃል ይነግረናል። ትኩረቱ የእርሱ መብላትና መጠጣት ላይ ሳይሆን የሰዎቹ እርሱን አለመቀበል ነው። ይሁን እንጂ፥ እየበላና እየጠጣ መጥቶአል። የወይን ጠጅ ጠጭ ያሉት ግን እነርሱ እንጂ ጌታ ራሱን አይደለም። እየጠጣ የመጣው ወይን ይሁን ወይን ጠጅ አናውቅም። ዮሐንስ ምንም አልጠጣም ነበርና።

ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻ ራቱን በበላ ጊዜ ጽዋን አንስቶ አመስግኖ እንዲጠጡ ሰጣቸውና እንዲህ አላቸው፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር

ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም። ማቴ. 26፥29።

ይህ ወይን የወይን ጭማቂ ወይም የወይን ጠጅ እንደሆነ መገመት እንጂ እርግጥ ነው ብለን መናገር አንችልም። ጊዜው ወይን የሚለቀምበት ስላልሆነ ምናልባት የወይን ጠጅ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ። ከሆነም ለሥርዓት የወሰዱት እንጂ እስኪሰክሩ የጠጡት አለመሆኑ ግልጽ ነው። አስካሪ መጠጥ ከቶም ሊሆን አይችልም። ከዚህ በኋላ ጌታ ወደ ጌቴሴማኒ ሊሄድ ነውና፥ ይህን ራሱም ያውቀዋልና ይህን የመጨረሻ ገድል በተበረዘ አእምሮ ሊጋደል ነው ብንል በመስቀሉ ሥራ ላይ ሰይፍ መምዘዝ ይመስላል።

በመስቀል ላይ ሳለ በሐሞት እና/ወይም ከርቤ የተቀላቀለ ወይን ጠጅ ቀርቦለት ነበር፤ አልተቀበለም። በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም። ማቴ. 27፥34።

ማር. 15፥23ም ይኸው ተጽፎአል። ሊጠጣ አልወደደም። ለምን? ይህ አስካሪና አደንዛዥ መጠጥ ነው። የሚሰቀሉ ሰዎች ሕመማቸው እንዳይሰማቸው ሰውነታቸው እንዲደነዝዝ የሚቀርብላቸው መጠጥ ነው። ጌታ ይህን ወሰደ ብንል አበሳችንን በደነዘዘ አካሉ ተሸከመ ልንል ነው።

8. የጳውሎስ ትምህርት

ጠጪዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤጲስ ቆጶሳት መስፈርት ሲዘረዝር 'የማይሰክር' ማለቱ፥ 1ጢሞ. 3፥3 መጠጣት ይችላሉ መስከር ግን አይችሉም ማለት ነው ይላሉ። ይኸው አባባል የሚጠጣ ማለቱ ነው የሚባለውን ያህል የማይሰክር ሲል ጨርሶ የማይጠጣ ማለቱ ነው ሊባልም እንደሚችል ሊጤን የተገባ ነው።

ስለ ዲያቆናትም እንዲህ አለ፤ እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ በሁለት ቃል የማይናገሩ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ። 1ጢሞ. 3፥8።

አሁንም ጠጪዎች ብዙ የወይን ጠጅ ነው የተባለውና ብዙ አይሁን እንጂ ጥቂትስ ይፈቀዳል ማለት ነው ይላሉ። ብዙ ስንት ዋንጫ ነው? ጥቂትስ ስንት ጽዋ ወይም መለኪያ ነው? ብዙና ጥቂትን ለኪውና ወሳኙስ ማን ነው? ላንተ ሁለት ጽዋ ብዙ ከሆነ ለኔ አራት ዋንጫም ጥቂት ቢሆንስ? እኔ አራት ፋጋ ስጠጣ ያየ ሌላው ያንን ቁጥር መነሻው ቢያደርገውስ?

ለጢሞቴዎስ ስለሆዱ ሕመም የተነገረውስ? 1ጢሞ. 5፥23 ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ።

ይህ ለአንድ ጢሞቴዎስ ለዚያውም ለሆዱ ሕመም የተነገረ ነውና እንደ ደንብ ወይም የፈቃድ ወረቀት መታየት አይገባውም። ጳውሎስ ሐኪም አይደለም፤ ግን ሐኪም የሆነው ሉቃስ አብሮት ነበረና የእርሱ ምክር ወይም ትእዛዝ እንደሆነ መገመቱ ከትክክል የራቀ አይመስለኝም። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የሚሉት ውኃው የሆድ

ሕመም ፈጣሪ ተዋኃስያን ስለሚኖሩት ምናልባት በውኃው ውስጥ ወይም ያለ ውኃው ጥቂት የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ተነገረው። ደግሞስ የቱ ሐኪም ነው ያዘዘላቸው? ለውኃችን ክሎሪን ወይም ለሆድ ሕመማችን ሌላ መድኃኒት እንድንወስድ ይነግሩናል እንጂ የዘመናችን ሐኪሞች የወይን ጠጅን እንደ መድኃኒት ከቶም አያዝዙም።

ወይንን በተመለከተ የጳውሎስ ሁለት ዐበይት ምክሮች እኒህ ናቸው፤ አንደኛ፥ በወይን ጠጅ መስከር በወይን ጠጅ ቁጥጥር ስር መሆን በመንፈስ ቅዱስ መሞላትም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን ናቸው።

መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤ ኤፌ. 5፥18።

ቁጥጥር ቁጥጥር ነው። ትንሽ ከጠጣን በጥቂቱ ይቆጣጠረናል። በብዙው ከጠጣን በብዙው ይቆጣጠረናል። አሁንም የቁጥጥሩን መጠን ወሳኙ ማን ነው? የማይታወቅ የቁጥጥር ድንበር ከሚበጅ ጭራሽ ቢቀርስ? እውነትም በወይን ጠጅ መስከር ማባከን ነው። ገንዘብን፥ አእምሮን፥ ኅሊናን፥ ትዳርን፥ አካልን፥ ወዳጅነትን፥ ጓደኝነትን፥ ክብርን፥ ስምን፥ አገልግሎትን ማባከን ነው።

ሁለተኛ፥ የኛ መኖር ሌላውን ማነጽ እንጂ ማፍረስ መሆን የለበትም። መደገፍ እንጂ ማሰናከል የለበትም። ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው። ሮሜ. 14፥21። ላለማሰናከል ሥጋ ከቶ ስላለመብላት ከተነገረ ወይን ከቶውኑ ባይጠጣስ? ቢቀርስ? በመጽሐፈ ምሳሌ እንደተጻፈው አለመጠጣት ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ባይታይስ?

ሳጠቃልለው፥ የአዲስ ኪዳን አማኞች ከወይን ጠጅ የምንታቀበውና የምንርቀው "አትጠጡ፥ አትቅመሱ፥ አትንኩ" የሚል ትእዛዝ ተቀብለን ሳይሆን አልኮል ምንም ሁነኛ ጥቅም ስለሌለው ነው። የማንጠጣው፥ አስካሪ መጠጥ በአካልና በአካል ብልቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ጠንቅ ስለሚያስከትልና አካላችን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆነ ነው። አካላችን ከአስካሪ መጠጥ ብቻ ሳይሆን ከአደንዛዥም ከአነቃቂ እጾችና መድኃኒቶችም መጠበቅ አለበት።

የማንጠጣው መጠጥ ተቆጣጣሪ ኃይል ስላለው ነው። እኛ ለአርነት ተጠራን እንጂ በምንም ነገር ቁጥጥር ስር ወይም የምንም ሱስ ተገዥ መሆን የተገባን አይደለንም።

የማንጠጣው ሌላው በኅሊና ሊጎዳበት፥ በመንፈሳዊ ጉዞው ሊሰናከልበት ስለሚችል ነው። አስካሪ መጠጥን በመጠጣት ሌላ ሰው የሚፈርስበት እንጂ የሚታነጽበትን ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም።

አስካሪ መጠጥን በመጠጣት እግዚአብሔርን የሚያስከብር ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም።

* * * * *

33. የሰው ሁለንተና ምንድር ነው? ሰው ነፍስ ያለው በሥጋ ውስጥ የሚያድር መንፈስ ነው?

የሰው ሁለንተና ሲል ምን ማለት ነው? ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል ከሚለው ጋር ላስታርቀው አልቻልኩም? (I wanna know what Bible says about የሰው ሁለንተና... Can explain for me please... Neger gn Sew menfes new nefs alewu be siga wust yadral kemilewu gar mastarek alchalkum.... 1ተሰ 5:23 lay yalewun new miredawu። A. L.)

ሰላም A. L.)፤ በመጀመሪያ ራሱን ቃሉን፥ ሁለንተና የሚለውን እንፍታው። እየሠራሁት ካለሁት የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት የሁለንተናን ትርጉም እዚህ ላይ ልለጥፈው፤

ሁለንተና כָּלִיל ካሊይል፤ קָבַץ ቃባጽ፤ מָלֵא ማሌእ፤ ὅλος ሆሎስ፤ ὁλοτελής ሆሎቴሌስ፤ παντόθεν ፓንቶቴን፤ ሙሉ በሙሉ፤ ዙሪያ ሙሉ፤ ሙላት፤ ነገርን፥ ዕቃን፥ አካልን፥ በጠቅላላ ማለት ነው፤ የቁጥርን ሙላት፥ የማንነትን ተሰብስቦ አንድ ላይ መሆንን ወይም ያልጎደለ ማንነትንም ያመለክታል፤ ዘኁ. 4፥6፤ ሚክ. 2፥12፤ ናሆ. 3፥1፤ ዮሐ. 7፥23፤ 9፥34፤ 13፥10፤ 1ተሰ. 5፥23፤ ዕብ. 9፥4። በሉቃ. 19፥43 ያለው በየበኩሉ የሚለው ቃል ከዚህ አንድ ነው፤ በዙሪያ ሁሉ፥ በሁሉም አቅጣጫ ማለት ነው። (whole, complete, every whit, entire, all, all in all, wholly)

ይህ የሁለንተና ትርጉም ነው። ወደ ሰው ሁለንተና ስንመጣ ደግሞ የሰው ሁለንተና ጠቅላላ ማንነቱ ነው። ያም አካላዊ ማንነቱ ወይም ሥጋው እና መንፈሳዊው ወይም በዓይን የማይታይ ማንነቱ፥ ማለትም፥ ነፍሱና መንፈሱ፥ በአንድ ላይ ጠቅላላ ማንነቱ ነው። ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ያድራል የሚለው ትምህርት የWord-Faith ወይም Word of Faith የስሕተት ትምህርት ነው። ሰው ሰው ነው እንጂ መንፈስ አይደለም። በ1ተሰ. 5፥23 ያለው ቃል ὁλοτελής ሆሎቴሌስ ወይም ሙሉ በሙሉ ፍጹም ማለት ነው። ሙሉ ወይም በሙሉ እና ፍጹም በሚሉት ቃላት የተሠራ ነው። በዚያ ስፍራ ጳውሎስም ግልጽ አድርጎታል። ሁለንተናችሁን ሲል ሥጋን፥ ነፍስን፥ መንፈስን ብሎ አስቀምጦአል።

ሰው ሰው ሳይሆን በሥጋ ውስጥ የሚያድር ነፍስ ያለው መንፈስ ቢሆን ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ከማለት ምንም የሚያግደው ነገር የለም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በጠቅላላ ትምህርቱ ሰውን ሰው ይለዋል እንጂ መንፈስ አይለውም። ሰው መንፈስ ቢሆን ኖሮ ሰውን መንፈስ እያለ ለመጥራት ማንም የማይከለክለው ቃል ነው። ሰው ሲጀመርም ሲጨረስም ሰው እንጂ መንፈስ አይደለም። ሲጀመር ሰው መሆኑን ዘፍ. 2፥7 ይነግረናል። *እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም*

የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። ይላል። ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። ሕያው ነፍስ ያለው ምን? ሕያው ነፍስ ያለው ሰው። መንፈስ አይልም።

ሲጨረስም ሰው ሰው በመሆን እንደሚቀጥል ደግሞ ራእ. 21፥3 ይነግረናል። ለዘላለም የምንኖርበት አካላችንም መንፈስ አይባልም። ራእ. 21፥3 እንዲህ ይላል፤ *ታላቅም ድምፅ ከሰማይ:- እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል።* እግዚአብሔር በሰዎች መካከል ያድራል ይላል እንጂ በመንፈሶች መካከል ያድራል አይልም። በትንሣኤ የሚነሣው ሌላ ሳይሆን ይኸው አካል ነው። ግን የማይሞት፥ የማይበሰብስ አካል ሆኖ ነው የሚነሣው። መንፈሳዊ አካል እንጂ መንፈስ አይደለም። እንኳን አሁን ከትንሣኤ በኋላም ሰው መሆናችን ይቀጥላል እንጂ የእግዚአብሔር 'ክላስ' አንሆንም። ወይም ሞርመኖች እግዚአብሔር ጥንት እንደኛ ያለ ሰው ነበረ፤ እኛም ወደፊት እንደ እርሱ ያለ እግዚአብሔር እንሆናለን እንደሚሉት እግዚአብሔር አንሆንም። ባህርይ እና ማንነት ልዩነት አላቸውና ከመለኮታዊ ባህርይው ተካፋዮች መሆናችን መለኮት ወይም መለኮታውያን አያደርገንም።

ሰው መንፈስ ነው ብለው የሚያስተምሩት ሰዎች ጠማማና መርዛማ ትምህርት፥ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ ሰው በአምሳለ አምላክ ተፈጥሮአል፤ ስለዚህ ሰው መንፈስ ነው ወይም የእግዚአብሔር ምድብ (class) ነው የሚል መርዛማ ትምህርት ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በስፋት የጻፍኩት መጽሐፍ ስላለ፥ በአማርኛ ከ https://t.me/zelalemmengistu/463 እና በትግርኛም ስለተተረጎመ ትግርኛውን ከ https://t.me/zelalemmengistu/466 ማግኘት ይቻላል።

* * * * *

34. የእሳት ጥምቀት ምንድር ነው?

የእሳት ጥምቀት ምንድነው? ስለ እሳት ጥምቀት ምን ትላለህ? (ም. ኃ)

ሰላም ም. ኃ፥ የእሳት ጥምቀት የተጠቀሰው በመጥምቁ ዮሐንስ ነው፤ የተጠቀሰው በሁለት ወንጌሎች ቢሆንም (ማቴ. 3፥11 እና ሉቃ. 3፥16) የተነገረው ግን አንዴ ነው። አብሮ የተጠቀሰው ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በበዓለ ኀምሳ ቀን የጀመረውና አማኞች ሁሉ ጌታን ሲቀበሉ አካሉ የሚደረጉበት መንገድ ነው፤ 1ቆሮ. 12፥13።

የእሳት ጥምቀት ግን ሲፈጸም አልታየም። ይህንን ጥምቀት አንዳንዶች በሐዋ. 2 መንፈስ ቅዱስ በወረደ ጊዜ የታየው እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ነው ይላሉ፤ ይህኛው ነው እንዳንል አንደኛ ነገሩ ቀጣይ ሆኖ አልዘለቀም፤ የመንፈስ ቅዱስ

ጥምቀትና ሙላት በሆነባቸው ስፍራና ጊዜያት አልቀጠለም፤ ከቶም አልተደገመም። ሁለተኛ ቃሉ በሐዋ. 2፥3፥ *እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።* ነው የሚለው። የተቀመጡባቸው እና የታዩአቸው ልሳኖቹ ናቸው፤ ልሳኖቹም እንደ እሳት የተከፋፈሉ ወይም ምናልባት እንደ ነበልባል የመሰሉ ናቸው። ስለዚህ የወረደው እሳት የሚመስል ልሳን ወይም መላስ ነው። ልሳን ማለት በቀጥታ ልሳን ወይም መላስ ማለት ነው፤ ቋንቋ ማለትም ነው። ይህ አካላዊ እሳት ስላልሆነ የመጥምቁ ዮሐንስ ትንቢት በበዓለ ኀምሳ ቀን አልተፈጸመም።

ሌሎች ይህ የእሳት ጥምቀት ምሳሌያዊ ነው ይላሉ፤ ምሳሌነቱንም ከምድራዊውም፥ ከሰማያዊውም ጋር ያቆራኙታል። እንደ ፍርም ይመለከቱታል። ፍርዱም ሁለት መልክ ሊኖረው ይችላል፤ ገለባን መፍጀት እና በፍርድ ጊዜ ፈጽሞ መቃጠል። ገለባን መፍጀትም ፍርድም ዮሐንስ ከተናገረው ቃል ጋር ይቆራኛል፤ መጥምቁ ዮሐንስ የተናገረው ከፍርድ ጋር የተያያዘ ቃል ነውና (ማቴ. 3፥12 እና ሉቃ. 3፥17)። ምድራዊው ገለባን መፍጀት ምናልባት የመንፈስ ቅዱስ የመቀደስ ተግባር፥ አማኞችን የማንጻት፥ የማጥራት ሂደታዊ ሥራ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስንድን የሚጀምርና ከዚህ ሥጋ እስክንወጣ የሚቀጥል ነው። ክርስቶስን እንድንመስል የሚያደርገው ቀጣይ ሥራው ነው። በ1ተሰ. 5፥19 መንፈስን አታጥፉ ባለበት ስፍራ የተጻፈው ማጥፋት ልክ እሳትን፥ መብራትን፥ ነበልባልን ከማጥፋት ጋር ቃሉ አንድ ነው። በማቴ. 12፥20፤ 25፥8፤ ማር. 9፥44-48፤ ኤፌ. 6፥16፤ ዕብ. 11፥34 ማጥፋት የተባለው ቃል ከዚህ አንድ ነው። ይህ የማብራትን፥ የብርሃንነትን፥ የሙቀትንና የግለትን ሕይወት ያሳያል። ይህ ደግሞ በክርስትና ሕይወት ውስጥ በራስ ጉልበት የማያደርጉትና ሊያደርጉት ከቶም የማይችሉት ነገር ነው። ይሁን እንጂ ይህንን የእሳት ጥምቀት ከማሰኘት ይልቅ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወይም በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር መሆን ማለት ተገቢው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ነው።

ይህ የእሳት ጥምቀት ምድራዊውን ሳይሆን ዘላለማዊውን ፍርድ የመለከተ ነው የሚባለው መጥምቁ ዮሐንስ በማቴ. 3፥12 እና ሉቃ. 3፥17 የተናገረው ቃል ከፍርድ ቃል ጋር የተያያዘ በመሆኑና፥ “ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል” በማለት ስለማይጠፋ እሳት ስለሚናገር ስለ ፍርድ እና ስለ ጌታ ፈራጅነት የሚናገር ነው ይላሉ። ዐውዱን እና የጥምቀትን ቀጥተኛና ትክክለኛ ትርጉም (መድፈቅ፥ ማጥለቅ፥ መንከር) ስናጤን የእሳት ጥምቀት ይህንን የኋለኛውን ይመስላል። የኔም መረዳት ይህኛው የመጨረሻው ነው።

* * * * *

35. ደኅንነት ይጠፋል ወይ?

ሰላም ጋሽ ዘላለም እኔ በማመልከበት ወጣቶች ዘንድ ሰው አንድ ጊዜ ከዳነ በቃ ዳነ ነው በምንም ምክንያት ድህነቱ አይወሰድም የሚል ትምህርት ገባና እኔ አቋዋሜን ተጠየኩኝ ? የኔ እምነት ሰው እምነቱን በቃሉ ወይም በስራው ከካደ ደህንነቱን ሊያጣ ይችላል የሚል ነው ! ነገር ግን በእውቀት ላይ የተመሰረት መረዳት እንዲኖረኝ ፈለኩ ጊዜ ካለክ ብትረዳኝ ወይም ስለዚ ነገር የማነበው ነገር ካለ ብትጠቁመኝ ብዬ አሰብኩ ፣ ጌታ ይባርክክ ! ዮሴፍ ተፈራ።

ሰላም ጋሽ ዘላለም እኔ በማመልከበት ወጣቶች ዘንድ ሰው አንድ ጊዜ ከዳነ በቃ ዳነ ነው በምንም ምክንያት ድህነቱ አይወሰድም የሚል ትምህርት ገባና እኔ አቋዋሜን ተጠየኩኝ ? የኔ እምነት ሰው እምነቱን በቃሉ ወይም በስራው ከካደ ደህንነቱን ሊያጣ ይችላል የሚል ነው ! ነገር ግን በእውቀት ላይ የተመሰረት መረዳት እንዲኖረኝ ፈለኩ ጊዜ ካለክ ብትረዳኝ ወይም ስለዚ ነገር የማነበው ነገር ካለ ብትጠቁመኝ ብዬ አሰብኩ ፣ ጌታ ይባርክክ ! ዮሴፍ ተፈራ።

ሰላም ውድ ዮሴፍ፤ ሁለቱንም አመለካከት የያዙ ክርስቲያን ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ወድረው ይፋለማሉ፤ ወይም አምርረው መፋለም ይችላሉ። ሁለቱም ወገኖች ደርዘን ጥቅሶችንም ያቀርባሉ። እነ ዮሐ. 3፥15-18፤ 6፥37፤ 10፥28፤ 15፥4-6፤ ሮሜ. 8፥30-39፤ ፊል. 2፥12፤ ቲቶ 3፥5፤ ዕብ. 3፥12-14፤ 4፥15-16፤ 6፥4-6፤ ያዕ. 2፥18፤ ይሁ. 24፤ ወዘተ እየተጠቀሱ ሰፊ ቤተ ሰባዊ አተካራ ተነሥቶ አቧራ ሊንቧለል ይችላል። ጠሊቅ ስነ መለኮታዊና አስተምህሮአዊ ርእስም ነው። ጥያቄው የተነሣው በቤተ ክርስቲያን ከባቢህ ስለሆነ ተግባራዊነት አለው ብዬ አምናለሁና ለአዲስ አማኝም እንኳ በሚገባ ቃል ለመመለስ እሞክራለሁ። ደኅንነት የእኛ ተግባር ውጤት ሳይሆን የእግዚአብሔር መለኮታዊ ሥራ ነው። ኃጢአተኛነቱን ያወቀ ሰውን ከኃጢአቱ በክርስቶስ ደም የሚያነጻበት፥ ዳግም የሚወልድበት፥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በውስጡ የሚኖርበት አድራጎቱ ነው።

የኔ መረዳት አንድ ሰው መዳኑ በምን ይታወቃል? ከሚለው ይነሣል። አንድ ሰው መዳኑ የሚታወቀው በንስሐ ፍሬ ነው። አንድ ሰው ከዳነ እንዳልዳነ ሰው ሆኖ አይመላለስም። መመላለስም አይችልም። እንዳልዳነ ሰው ሆኖ ከተመላለሰ ቀድሞውኑም አልዳነም ለማለት ይቻላል። በማቴ. 13 ጌታ ሲያስተምር የዘሪውን ምሳሌ ተሰጥቶአል። በዚያ ምሳሌ ውስጥ አራት ዓይነት አፈሮች አራት ዓይነት ሰዎችን፤ አራት ዓይነት የልብ ሁኔታዎችን ወክለው ቀርበዋል።

የመጀመሪያው እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት። ተብሎአል። ሲተረጉመው፤ የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው። ብሎአል፤(ቁጥር 4 እና 19)። እንዲህ ያሉ ሰዎች አሉ፤ ቃሉን ይሰማሉ ዘሩ ጆሮአቸውን

ይመታዋል፤ ልባቸውን ያንኳኳል፤ ይሰማሉ አይቃወሙም፤ ግን እውስጣቸው አይገባም። ከውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጪም ድንጋያማ ልብ ያላቸው ናቸው።

ሁለተኛው፥ ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፤ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ተብሎአል። ሲተረጎምም፥ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም፥ በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል። ተብሎአል (ቁጥር 5-6 እና 20-21)። ጭንጫ መሬት ውኃ የሚቋጥር ለስላሳ አፈር ያለው፤ ነገር ግን ከጥቂት ሳንቲ ሜትሮች በታች ድንጋይ ነው። የተዘራው ቶሎ ይበቅላል፤ ግን እዚያ ላይ ያበቃል። እንዲህ ያት ሞቅ ያላቸው ስሜታውያን ሰዎች ናቸው። የብራ አየር ክርስቲያኖች ናቸው። አማኝ የሆኑ የሆኑ ይመስላቸዋል፤ አገልግሎትም ይጀምራሉ፤ በደስታም ያገለግላሉ። ሲጠየቁ ከች ይላሉ፤ ሁሉም ቦታ ቦታቸው ነው። አገር ምድሩን ይሞሉታል። ግን ፀሐይ እስኪወጣ፥ ስደት እስኪመጣ ነው። ጠወለገ፥ ደረቀ፥ ተሰናከለ ይለናል ቃሉ። ገና በቡቃያነት። ዋጋ የሚጠይቅ ጊዜ ሲመጣ ስፍራቸው ከጌታ ጋር አይደለም። ውጪያቸው በስሱ ለስላሳ ይመስላል ውስጣቸው ግን ድንጋያማ ነው።

ሦስተኛው ደግሞ፥ ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው። በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፥ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል። ተብሎአል፤ (ቁጥር 7 እና 22)። ይህ ፍሬ አድጓል አልጠወለገም፤ ብዙ ቆይቷል፤ እስከ መከር ድረስም ዘልቋል። ነገር ግን የታነቀ ተክል ነው። ይህ ሰው ቃሉን ይሰማል ክርስቲያን መስሎ ይመላለሳል። በእውነቱ ግን አሳቡ ከጌታ ይልቅ የዚህ ዓለም ነው። የባለጠግነት ጉዳይ ነው። እነዚህ ሰዎች ምድራዊና ዓለማዊ ነገርን ከጌታና ከመንፈሳዊ ነገር ይበልጥ የሚፈልጉ ናቸው።

አራተኛው፥ ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል። ተብሎአል፤ (ቁጥር 8 እና 23)።

አራተኛውን ፍሬ ከቀደሙት ከሦስቱ የተለያ ያደረገው ወይም የመጀመሪያዎቹን ሦስቱን ተመሳሳይ ያደረጋቸው ፍሬያምነት ወይም ፍሬቢስነት ነው። ደኅንነት የሚታወቀው በፍሬ ነው ስል ፍሬው የእኛ ፍሬ ሳይሆን የጌታ ፍሬ፥ የመንፈስ ፍሬ ነውና የእርሱ በእኛ ውስጥ መኖር ዋናው ምስክር ነው። ፍሬ ከሌለ እርሱ በእኛ ውስጥ የለም ማለት ነው። ወይም፥ እርሱ በእኛ ውስጥ ከኖረ ፍሬ እናፈራለን ማለት ነው። አንዱ ከሌላው ይበልጥ ወይም ያነሰ ያፈራ ይሆናል። ጉዳዩ ብዛቱ አይደለም፤ ማፍራቱ ነው። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ምንም ፍሬ አላፈሩም። ምንም። ለምን? ግድ የለሽነትና ፈቃደኛ አለመሆን አለ፤ መንፈሳዊነት ሳይሆን ስሜታዊነት የገነነበት ሁኔታ አለ፤ ዋጋ ለመክፈል አለመፈለግ አለ።

ስለዚህ ደኅንነት የመጥፋትና ያለመጥፋት ጉዳይ ሳይሆን በቅድስናና ጌታን በማክበር መመላለስና አለመመላለስ ላይ ነው። እምነትና ሥራ ደግሞ የተነጣጠሉ ነገሮች

አይደሉም። ባለፈው ስለ አሥራት ተጠይቄ ስመልስ አንዳንዶች አሥራት የአዲስ ኪዳን ሕግ አይደለም የሚሉት ከአሥራት የበለጠ ለመስጠት ካላቸው ልባዊ ጉጉት የተነሣ ሳይሆን ከዚያ አሳንሰው ለመስጠት ወይም ጭራሽ ላለመስጠት ፈልገው ነው ብዬ ነበር። እዚህም አንዳንዶች ደኅንነት አይጠፋም የሚሉት ኃጢአትን ለመለማመድ ሲፈልጉ ነው። በቅድስና የሚመላለሱ ሰዎች ዘንድ ይህ ጉዳይ ጥያቄም ሆኖ አይቀርብም።

አንዳንድ ሰዎች ከጌታ ቤት ጠፉ ሲባል የምጠይቀው የመጀመሪያ ጥያቄ፥ 'ሲጀመር ድነው ነበር ወይ? ዘሩስ ዘር ነው፤ ግን እነርሱ የትኛው አፈር ነበሩ?' የሚል ነው። ደኅንነት እውነተኛ ከሆነ አይጠፋም። እውነተኛ ደኅንነት ደግሞ መታወቂያ አለው። መታወቂያውም ፍሬ ነው። ሠላሳ፥ ስድሳ፥ መቶ።

. . . . .

ይህንን መልስ ጽፌ ከለጠፍኩ በኋላ ሰፋ ያሉ አስተያየቶችና ጥያቄና መልሶች ተለዋውጠናል። አንድ ወንድም ደኅንነት ይጠፋል ከሚል በመነሣት የኔን መልስ እንደ ስሕተት ትምህርትም ቆጥሮ ጽፎ ስለነበር እዚያው ለእርሱ የሰጠሁትን መልስም እዚህም ማያያዝ ትምህርታዊ ይመስለኛልና ከታጭ እጨምረዋለሁ።

> "ዘሉ! በቂ መልስ ሊሰጥበት ካልቻለበት ከዚህ ትምህርት ይማራል ብዬ ጠብቄ ነበር። እርሱ እንደሚለው ደህንነት የማይጠፋ ከሆነ፤ ለምንድነው ለዳኑ ሰዎች፤ ስለ መፅናት የምናስተምረው!? . . . ዘሉ ለዘመናት ሃሰተኛ ነቢያትን ሲቃወም እኔም ብዙዎቻችሁም ተባባሪው ነበርን። . . . አሁን ግን እርሱ ራሱ ሃሰተኛ አስተማሪ ሆኖ ሳገኘው እጅግ ተገረሙኩኝ። . . . ካልገባው አላስተዋልኩትም ወይም ይህን ትምህርት በሚገባ አላወኩም ማለት የተሻለ መልስ ነበር።"

ውድ ይ. ዳ.፤ ከጻፍካቸው ጥቂት ነጥቦችን ወስጄ በመጻፍ ልጀምር። ይህ ከላይ የጠቀስኩት ጥቂቱ ነው፤ ሌሎች ያላልኳቸውንና ያልጻፍኳቸውን ነገሮችም ጨምረህበታል። ካነሣሃቸው ነጥቦች ጥቂቱ ላይ ጥቂት ልበል፤ አስቀድሜ ግን አንድ ነገር ግልጽ ላድርግ፤ 'ክርስቲያን ፍጹም ነው፤ ከቶም በኃጢአት አይወድቅም፤ ሊወድቅም አይችልም' አላልኩም። ደግሞም፥ 'አንዴ ድኛለሁ፤ ለሁሌ ድኛለሁ ብለን ኃጢአት መሥራት እንችላለን' አላልኩም፤ አልወጣኝም።

በቅድሚያ ሌሎችም ሊመልሱልህ እንደሞከሩት የጠያቂውን አሳብም የኔን ማስረዳትም ችላ ብለህ አልፈኸዋል። ሁለቱንም እንደገና መመልከቱ አሳቡን እንድታገኘው ይረዳህ ይሆናል። ጥያቄው ወደ ካልቪኒዝም እና አርሚኒያን መከራከሪያ ነጥቦች በማለፉ እኔ ካልሚኒያን ነኝ ብዬ በጥቅሉ ጽፌአለሁ። ስለዚህ ጉዳይ ሁለቱም ወገኖች ክርስቲያኖች መሆናቸውን ሳንክድ በሰፊው መከራከር ይቻላል። ይህ የመረዳታችን እና የእርግጠኝነታችን መጠን እንጂ የስሕተት ትምህርት አይደለም። ይህንን መንደርደሪያ አድርገው በአንድ ወገን ወደ ሕገኝነት ጽንፍ የሚሄዱ ቢኖሩም ትምህርቱ ኃጢአትን ለመለማመድ ቀዳዳ የሚፈጥር አይደለም። ቀዳዳ ሽንቁረው ኃጢአትን የሚለማመዱ ከኖሩ እነዚያን በሌላ ቅይድ ውስጥ ማስቀመጥ አለብን። ይህንን ጉዳይ በግልጽ

ብዬዋለሁ፤ እዚህም እደግመዋለሁ። ዮሐንስ ካልቪንም ሆነ ያዕቆብ አርሚኒየስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስቲያኖች እና ስነ መለኮታውያን ነበሩ። ትምህርታቸውን የተከተሉትም ለኃጢአት እንዲህ የዘቀጠ አመለካከት የላቸውም፤ ኖሮአቸውም አያውቅም።

ምናልባት ወደፊት አስፈላጊ ከመሰለኝ ስለ ሁለቱም (ስለ አርሚኒየስ የቤልጂክ መግለጫ እና በዶርት ሲኖዶስ ለዚያ ምላሽ ስለተሰጠው አምስቱ የካልቪን ነጥቦች) እጽፍ ይሆናል። እኔ የምጽፈው በፌስቡክ ልደርሰው ለምፈልገው አካል ነው የምጽፈው፤ ስለዚህም፥ እዚያ ውስጥ አልገባሁም። በጥያቄዎች መልስ በኩል ግን ማንነቴን የገለጥሁ ይመስለኛል፤ ወይም የገለጥሁ እንደሆንኩ አምናለሁ። ‘ለመሆኑ ጠያቂው ይህን ጥያቄ ሲጠይቅ ምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንደሚጠይቅ ዘሉ መገመት ስለምን አቃተው?’ ብለሃል። ከጠያቂው ጋር በውስጥ ገጽ ተጻጽፈናልና መገመት አላስፈለገኝም። በግምትም አልመልስም። ሁሉንም ጥያቄዎች ከመጠየቁ በፊት ከጠያቂዎቹ ጋር ቢያንስ በጥቂቱ እጻጻፋለሁ። ጠያቂው ደግሞ መልሴ እንደጠቀመውና እንዳጠገበው ገልጦአል።

ሁለቱም ወገኖች (ካልቪኒስቶችም አርሚኒያኖችም) የሐሰት አስተማሪዎች ናቸው ያለ የለም፤ እኔም አልልም። አንተ ግን እኔን ከዚህ ለአንድ ወንድም ከመለስኩት መልስ ብቻ ተንደርድረህ፥ “እርሱ ራሱ ሃሰተኛ አስተማሪ ሆኖ ሳገኘው እጅግ ተገረሙኩኝ።” ብለሃል። እንዲህ ልትል ያስቻለህን ጉዳይ በግምት ብቻ ወስደህ ወደ ድምዳሜህ በመድረስህ በጣም አዝናለሁ። ድምዳሜህም የተንደረደረው ከስሕተት ግምት ነው። ግምቱም፥ ‘አንዴ የዳነ ሁሌም ድኖአልና ኃጢአት ቢሠራ ምንም ቅጣት አያገኘውም፤ ደኅንነቱም አይጠፋም ብሏል’ የሚል ነው። ይህንን አሳብ ነው ከየት እንዳገኘኸው ያላወቅኩት። ወይም ራስህ አመንጭተህ ከሆነም እዚህ በተደጋጋሚ የጻፍኩበት ጉዳይ ነው።

በጽሑፌ ያልኩትን መድገም አስፈላጊ አይደለም። ግን ይህንን መዳናችን ለኃጢአት የፈቃድ ወረቀት መቀበል ያለመሆኑን አሳብ በትክክል አስቀምጬዋለሁ። አንድ ሰው ድኛለሁ እያለ ኃጢአትን ካጣጣመና እየተደሰተበት እዚያ ሰፈር ከኖረ ቀድሞውኑም አልዳነም። ይህንን አሳብ ነው ያጎላሁት። እውነተኛ ደኅንነት አይጠፋም፤ እውነተኛ ደኅንነት ደግሞ ይታወቃል፤ መታወቂያውም ፍሬ ነው ብያለሁ። ስለዚህ ነው ማቴ. 13ን ወስጄ አራቱን አፈሮች የገለጥኩት። ኃጢአት እንዴት ሆኖ ነው የመዳን ፍሬ የሚሆነው? ሊሆን አይችልም። አሁንም ላስምርበት፤ አንድ ሰው ድኛለሁና መዳኔ ስለማይጠፋ በኃጢአት እየተደሰትኩ መኖር እችላለሁ ካለ ያ ሰው አልዳነም።

“ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ ሄደ ሲባልስ ከየት ወደ የት ነው የሄደው!? . . . እንደ ይሁዳ የሚጠለው ነገር ነው።” ብለሃል። ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ ከሄደ ቀድሞም ዓለማዊ ሰው ነበረ ማለት ነው። 1ዮሐ. 2፥15-16 ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለ ሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ፥ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ይላል። ዴማስ አገልጋይ ነበር፤ ይሁዳም ሐዋርያ ነበር። ከ12ቱ ጋር ተቆጥሮ ነበር፤ ለዚያ አገልግሎት ታድሎ ነበር፤ ሹመት ነበረው። ሳይድኑና ከጌታ ጋር

ሕያው ግንኙነት ሳይኖራቸው በቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ? አዎን ይችላሉ። ለእነዚህ ሰዎች ዓለምንና ጌታን ለምርጫ ብናቀርብላቸው ዓለምን ከመረጡ ጌታ መጠቀሚያቸው እንጂ ጌታቸው አይደለም ማለት ነው። ዴማስ በጳውሎስ ደብዳቤዎች 3ቴ ተጽፎአል፤ ሁለቴ ሰላምታ ሲያቀርብ እና አንዴ ወደ ዓለም ሲሄድ ነው የተጻፈው። ይህ ማለት ፍጻሜው ነው ማለት ነው? አናውቅም። የዴማስ ባዮግራፊ አልተጻፈልንም። እነዚህ ነገሮች ይህ ሰው ያደረጋቸው ነገሮች ናቸው። ተጸጽቶ ተመልሶ ይሆን? ዓለም ጥማው በዚያው ቀልጦ ቀርቶ ይሆን? አናውቅም። ወድቆ ተነሥቶ ሊሆን ይችላል። ዓለም ከጣመችው እና በእርሷ መደሰት ከክርስቶስ ከበለጠበት ክርስቶስን አልቀመሰም ማለት ነው። ለክርስቶስ እውነተኛ ተከታይ ዓለም ከክርስቶስ አትበልጥም። ጌታ ቸር መሆኑን የቀመሰ በቃሉ ወተት እንዲያድግ ቃሉ ያስተምራል። ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ፥ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ። 1ጴጥ. 2፥2-3።

"ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ተብሎስ የተፃፈው ስለምን ነበር?" ብለሃል። ይህ ቃል የተነገረው ለሐሰተኛ አስተማሪዎች መሆኑን መርሳት የለብንም። ይህ ጥቅስ ከተጻፈበት ጥቂት ቀደም ብሎ ቁ. 19 ላይ፥ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው፦ አርነት ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል፤ ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና። ይላል። አንድ ሰው ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ውሻ ወደ ተፋው ትፋት የሚመለስ ከሆነ የተፋውን ይፈልገዋል ማለት ነው። ባህርይው የውሻ ነው ማለት ነው። ቆሻሻ የሚወድና ወደ ቆሻሻ ሄዶ የሚንደባለል ከሆነ ባህርይው የእሪያ ነው ማለት ነው። ሰዎች በኃጢአት የሚደሰቱ ከሆኑ ትፋታቸውን እንደገና በመብላት የሚረኩ ከሆኑ፤ በመጨቅየትና በመቆሸሽ እሰይ የሚሉ ከሆኑ የቅድስና መንፈስ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናቸው ማለት እንደምን ይቻላል?

ከላይ ያልኩትን እንደገና ልድገመው፤ ክርስቲያን መሆን ወደ ፍጹምነት መጓዝ እንጂ ፍጹምነት አይደለም። ክርስቲያን በኃጢአት ሊወድቅ ይችላል፤ ግን በኃጢአት አይኖርም። ወዲያው ተጸጽቶ ይመለሳል። ጭቃውን፥ አመዱን፥ አፈሩን አራግፎ በጥፋቱ መጠን ተናዝዞ ይመለሳል። በኃጢአት እየተደሰተ አይኖርም። አንዴ ድኛለሁና ድነቴ አይጠፋም ስለዚህ እንዳሻኝ ልሁን፤ አትንኩኝ፤ አትናገሩኝ ካለ አስረግጬ እላለሁ፤ ያ ሰው ድነትን አላወቃትም። የዳነ ሰው የመዳኑን ዋጋ ያውቃል፤ በድነቱ አይዘብትም። ይኖርባታል፤ ያፈራልም። ከዚህ በፊት የፊልጵስዩስን መልእክት ሳስተምር መዳናችንን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ስለመፈጸም (ፊል. 2፥12) ያካፈልኩትን ይመለከቷል።

"እርሱ በቁጭትና በወንጌል ቅናት እነ ዳንሳን ሲተች መመዘኛው የጌታ ቃል አልነበረምን!!? . . . ስለ አለማፈግፈግና በሌላ ትምህርት ስለአለመወሰድስ ለምን እናስተምራለን!?" ብለሃል። አሁንም መመዘኛዬ እስፍራው ነው። ሚዛኑ ቃሉ ነው። ይህ ባይሆንማ ኖሮ ለምን ሐሰተኞችን እፋለም ነበር? በሐሰት ትምህርቶች ስላለመወሰድስ ለምን አስተምር ነበር? እነዚህ ሁለት ነገሮች እጅግ አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ዳንሳን እና እንደ እርሱ ያሉ ሐሰተኛ ነቢያትን ማሔሴና መግለጡ ይቀጥላል።

ይህን የማደርገው በመጽሐፍ ቅዱስ መዛኝነት ነው። ይህን የማደርገው ደግሞ በምክንያት ነው፤ ምክንያቱም አንድ ዘር ከተተከለ በኋላ በአንድ ወገን ውኃ ማጠጣትና መንከባከብ ተፈላጊ ነገር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ማረምና መኮትኮትም የዚያኑ ያህል አስፈላጊ ስለሆነ ነው። ተክልን በተመለከተ እነዚህን ሁለት ነገሮች የማድረግ አስፈላጊነትን የማውቀው በግብርና ቤተሰብ ስላደግሁም ጭምር ነው። እነዚህ ሁለት ነገሮች የሚደረጉት፥ ማለትም በአንድ ወገን ውኃ ማጠጣት፥ በሌላ ወገን አረምና አረማሞና አራሙቻ መንቀል የሚያስፈልጉት ተክሉ እንዲፋፋና ፍሬ እንዲሰጥ ነው። ምን እንዲሰጥ? ፍሬ። መልካሙን ትምህርት ማስተማር ውኃ እንደ ማጠጣት፥ ፍግ ወይም ማዳበሪያ እንደመስጠት ነው። ሐሰተኛ ትምህርቶችን መዋጋትና ሐሰተኛ አስተማሪዎችንና ነቢያትን መጋፈጥና መግለጥ ደግሞ አረምን እንደ መንቀል ነው። ለምን? ለፍሬ።

ስለ ፍሬ ጌታ በማቴ 13 ብቻ አይደለም ያስተማረው። በማቴ. 7፥15-20 ዛፍ በፍሬው እንደሚታወቅ አስተምሮአል። በሉቃ. 6፥43-44 ተመሳሳይ ነገር አስተምሮ፥ ‘ከእሾህ በለስ አይለቅሙም፥ ከአጣጥ ቍጥቋጦም ወይን አይቈርጡም’ ብሎአል። በሉቃ. 13፥ 6-9 ብዙ መልካም ስለተደረገላትና ስላላፈራች ለመቆረጥ ስለተዳረገች ዛፍ ተናግሮአል። በዮሐ. 15፥1-16 ፍሬ የማያፈራ ቅርንጫፍ እንደሚወገድ አስተምሮአል። ፍሬ የሚጠበቅ ነገር ብቻ ሳይሆን የእውነተኛ ሕይወት ምልክትም ነው። ሐዋርያቱ በመልእክቶቻቸው ስለ መንፈስ ፍሬ፥ ስለ ጽድቅ ፍሬ፥ የብርሃን ፍሬ፥ የበጎ ሥራ ፍሬ፥ የሰላም ፍሬ፥ የኑሮ ፍሬ፥ የከንፈሮች ፍሬ፥ ወዘተ፥ ተናግረዋል። ፍሬ የማይታይበት ሕይወት ውሸታም ሕይወት ነው።

ስለዚህ ውድ ይ. ዳ.፥ “ዘሉ ለዘመናት ሃሰተኛ ነቢያትን ሲቃወም እኔም ብዙዎቻችሁም ተባባሪው ነበርን። . . . አሁን ግን እርሱ ራሱ ሃሰተኛ አስተማሪ ሆኖ ሳገኘው እጅግ ተገረሙኩኝ።” ያልከው ከስሕተት መንደርደሪያ እና ካልተረዳኸው ነገር በመነሣት ነው። አንዴ ድኛለሁ ስለዚህ ለሁሌ ድኛለሁ፤ ድነቴ አይጠፋምና ኃጢአትን መለማመድ እችላለሁ የሚል ሰው ሲጀመርም አልዳነም። እውነተኛ ድነት አይጠፋም፤ እውነተኛ ድነት ደግሞ ይታወቃል፤ በምን? በፍሬው ይታወቃል።

* * * * *

36. ‘ወልድም ቢሆን አያውቅም’ ብሎአልና ጌታ የሚመጣባትን ቀኒቱን አያውቅም ነበር?

በማቴ 24: 36 ላይ ያለው ክፍል ስለ መጨረሻዋ ቀንና ሰአት ወልድም (ኢየሱስ ክርስቶስ) ቢሆን አያውቅም ማለቱ በእርግጥ ጌታ ኢየሱስ አያውቅም ማለት ነው? ስ. ሳ.

ብዙ ጊዜ ጠያቂዎችን፥ በተለይም አንባቢ የመሰሉኝን በጥያቄ ነው የምመልስላቸውና ይህንን ጠያቂ፥ 'ጌታ የኛን አቆጣጠር ቢከተልና ማክሰኞ ነሐሴ ፲፰ ቀን ፪ሺህ፲ እመጣለሁ ቢል ምን የሚሆን ይመስልሃል?' አልኩት። መልሱ፥ 'ቀኑን መናገሩ አግባብ እንዳልሆነ አምናለሁ። ነገር ግን እነሱ ማወቅ እንደሌለባቸው ለመናገር ከፈለገ ልክ በሐዋ 1:7 ላይ እንደተናገረው "ለእናንተ የማወቅ ስልጣን አልተሰጣችሁም" ማለት ይችላል። ማቴ ላይ ግን "ወልድም ቢሆን አያውቅም" ያለው ስለ ራሱ ነው። ለምን አላውቅም አለ?' የሚል ነው።

ሰላም ስ. ሳ.፤ ሐዋርያቱ በኋላ ለጠየቁት ተመሳሳይ ጥያቄ በሐዋ. 1፥7 እቅጩን ቀን እንዳልነገራቸው ሁሉ እዚያም አልነገራቸውም። ይህን ጥያቄ ከሁለት አቅጣጫ አየዋለሁ።

1. ጌታ የሚመጣበትን ቀኒቱንና ሰዓቲቱን ከላይ እንዳልኩት ቢናገር ኖሮ ይህ በሰዎች ላይ የሚፈጥረው እንድምታ (implication) አሉታዊ ይሆናል። ሰዎች ሊመጣ ጥቂት እስኪቀረው እንዳሻቸው ሊኖሩ ይጋበዛሉ። ይህ ከሆነ በመጨረሻም የሚገቡት ንስሐና እርሱን መቀበል የውሸት ይሆናል። የሚመጣበት ቀን መስሏቸው ገምተውም ደምረውና ቀንሰውም በዚህ ቀን ብለው ቀነ ቀጠሮ የሰጡ ጥቂት አይደሉም። ከመጀመሪያዎቹ አድቬንቲስቶች ወይም ሚለራውያን እስከ የይሖዋ ምስክር ነን ባዮቹ የዋችታወር ተከታዮች ድረስ በርካታ ቀኖች ተነግረው ሁሉም ከሽፈዋል። እስከ ሃቻምና ድረስም ቀጠሮ የሰጡ ነበሩ። ይህ የግምትና የስሌት ቀጠሮ ጌታ፥ 'ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።' ብሎ የተናገረውን በቀጥታ መናቅ ነው። ይህ ወደ ሁለተኛው ነጥብ ይወስደናል።

2. ኢየሱስ በሥጋ ሲመጣ ሰዋምላክ ነው የሆነው። አምላክነቱን አልተወም፤ ሥጋን ግን ጨምሮ ያዘ። እርሱ ፍጹም አምላክ መሆኑ ግልጽ ነው፤ ለምሳሌ. ዮሐ. 1፥1። አምላክ ከሆነ ሁሉን አዋቂ ነው። ሁሉን ማወቅ ከመለኮት ባህርያት አንዱ ነው። ሁሉን አዋቂነቱም ተደጋግሞ ተጽፎአል፤ ለምሳሌ፥ ዮሐ. 1፥49፤ 2፥24-25፤ 4፥17-18፤ 16፥30፤ ሉቃ. 18፥33፤ ወዘተ።

ሆኖም፥ በሥጋ በተመላለሰበት ዘመን እንደ ሰውነቱ (ስብእናው) ፈቃዱን ለአባቱ አስገዝቶ ነበርና መለኮታዊ ሥልጣኑንም ሆነ የተገባውን የራሱ የሆነውን 'መብቱን' (መብት ልበለው ለእኛ እንዲገባን) አልተጠቀመም፤ ወይም ሙሉ በሙሉም አልተለማመደም። ፈቃዱን ለአብ ፈቃድ በማስገዛቱ በሥጋ በተመላለሰባቸው ዓመታት በአንዳንድ ቦታዎች አንዳንድ ነገሮችን ያለ አብ ፈቃድ በራሱ ፈቃድ ብቻ እንዳያደርግ ወድዶ ገትቶአል። ይህ ከመለኮታዊ ባህርይ መጉደል ሳይሆን በፈቃድ ራስን መግታት እና መለኮታዊ ሥልጣንን አለመጠቀም ነው። ፈቃዱን ሳይሆን የአብን ፈቃድ ሊያደርግ መምጣቱን በብዙ ስፍራዎች ገልጦአል፤ ለምሳሌ፥ ማቴ. 26፥42፤ ዮሐ. 4፥34፤ 6፥38፤ ወዘተ። በጲላጦስ ፊት ሲከሰስ ዝም ማለቱ ወንጀለኛ ሆኖ አልነበረም። በዚያች ቅጽበት በመለኮታዊ ሥልጣኑ ቢገለጥ በእርሱ ላይ በፍርድ ወንበር የሚቀመጥ አይኖርም። ንጹሕነቱን ቢመሰክር ብቻም እንኳ መመስከርና ነጻ

መውጣት ይችል ነበር። መስቀል እና የኛ መዳን ግን አይኖርም ነበር። የመጣው ደግሞ ለዚህ ነው። እናም፥ በፈቃዱ ራሱን ሰጠ። ፊል. 2፥1-11 ይህንን ነው የሚነግረን።

ስለ ዳግም መምጣቱ ስንመለከትም ይህንን የአብን ፈቃድ መግለጡን ወይም ፈቃዱን ለአባቱ አስገዝቶ ነበርና መለኮታዊ ሥልጣኑንም ወይም 'መብቱን' አለመለማመዱን እናያለን። ማቴ. 24፥36 ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም። ሲል የፈቃድ አለማወቅ ወይም ፈቃድን የማስገዛት አለማወቅ ነው። ቀኒቱን አይናገር እንጂ ምልክቶቹን ግን ተናግሮአል። በደመና እንደሚመጣም ተናግሮአል፤ ማር. 13፥16፤ ሉቃ. 21፥27። ይህ በደመና መምጣት በዳንኤል መጽሐፍ የተጻፈው መሢሑ እርሱ የመሆኑ አመልካች ነው። በጥያቄህ እንዳመለከትከው ከትንሣኤውና ሰውነቱ መንፈሳዊ አካል ከሆነ በኋላ ግን ይህንን መለኮታዊ እውቀቱን መልሶ ቢቀዳጅም ተመሳሳይ ጥያቄ ተጠይቆ አሁም ቀኑን አልነገራቸውም፤ እርሱም፦ አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ሐዋ. 1፥7።

ስለዚህ ኢየሱስ በምድር እንደ ሰዋምላክ በተመላለሰበት ጊዜ ፈቃዱን ለአብ በማስገዛቱ ሙሉ መለኮታዊ ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ አለመለማመዱ ከመለኮት ያነሰ አስመስሎታል። ስለዚህም ነው፥ ለምሳሌ፥ እንደ ይሖዋ ምስክሮች ነን ባዮች ኢየሱስ ፍጡር አምላክ የሆነ ሚካኤል ነው የሚሉት። ነገር ግን የጎደለ አምላክ ሳይሆን በመለኮት ላይ ሥጋን የጨመረ ሰዋምላክ ነው። በዚያን ጊዜ ዳግም የሚመጣበትን ጊዜ አለመናገሩም ለአብ ፈቃዱን በማስገዛቱ ሁሉን አዋቂነትን ጨምሮ ሌሎችም መለኮታዊ ሥልጣኑን በውሱን ደረጃ አለመለማመዱ ነው።

* * * * *

37. ግለ ወሲብ ኃጢአት ነው?

ወንድም ዘላለም ሰላም ላንተ፤ . . . ጥያቄዬ ስለ ማስተርቤሽን (ግለ ወሲብ) ነው። የጥያቄዬ መነሻ የሆነው ከሁለት ዓመት በፊት የሆነ መጽሔት ላይ ያነበብኩት ነው፤ እንዲህ ይላል፤ ላላገቡ (unmarried) ወጣቶች ግለ ወሲብ ኃጢያት አይደለም ይልቅ እስኪያገቡ ማስተንፈሻ ነው በሚል እንዳስተማረ ነበር። አንዳንድ ወገኖች በዚህ ላይ ያላቸውን መረዳት ጠይቄያቸው ኃጢያት ነው ከማለት ውጪ ምንም አጥጋቢ መልስ አልሰጡኝም። እናም ጥያቄዬ . . . በዚ ነገር ላይ ያለህን መረዳት ሼር ብታረግልኝ። MHM

ሰላም MHM፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግለ-ወሲብ (masturbation) አይናገርም። ከዚህ የሚቀራረበው ጉዳይ ኦናኒዝም (የአውናን ድርጊት) የሚባለው ነው። ታሪኩ በዘፍ. 38፥8-10 ይገኛል። እዚህ በአካል መገናኘት ስላለበት መመሳሰሉ ዘሩን በምድር ከማፍሰሱ ጋር ብቻ ነው። አውናን ኃጢአት የሆነበት እና ያስቀሰፈው ለወንድሙ ዘር

ማቆም ሲገባው ይህን ባህላዊ ወግ (ኋላ ወደ ሕጉ ውስጥም የገባ ደንብ ነው) አለመፈጸሙ ነው። ሆኖም የአውናን ድርጊት ከሟች ወንድሙ ሚስት ጋር ይተኛ ነበርና ግለ ወሲብነት የለውም። ያስቀሰፈውም የዘሩ በምድር መፍሰስ ሳይሆን ዓመጹ ወይም እንቢተኛነቱ ወይም ቤተ ሰባዊ፥ ወንድማዊ ግዴታውን ለመወጣት አለመታዘዙ ነው። ስስቱ ነው፤ የእርሱ ዘር የወንድሙ ልጅ ተብሎ የወንድሙን ርስት እንዳይወርስ የሟች ወንድሙ ሚስት እንዳታረግዝ ሰውነቱን እያረካ፥ ዘሩን ግን በምድር በማፍሰስ ክፉ ማድረጉ ነው።

በሕልሙ ዘሩ የፈሰሰ ሰው ኃጢአት ሠራሁ፥ ወየሁ ጉዴ ብሎ መጠበብ የለበትም። ነገር ግን አንድ ሰው ግለ ወሲብ በሚያደርግበት ጊዜ ሥጋው ወይም አካሉ ብቻ አይደለም በዚያ ምናባዊ ወሲብ ውስጥ የሚጫወተው። አእምሮውም፥ አሳቡም፥ ስሜቱም፥ ልቡናውም ነው። ስለዚህ ያ ሰው ወንድ ከሆነ ግለ ወሲብ በሚያደርግበት ጊዜ በአሳቡ፥ በምናቡ የሚያያት ሴት ትኖራለች። ሴት ከሆነችም በምናቧ አብራ የምትሆነው ወንድ አለ። (እዚህ በወንድ ጾታ ብጽፍም ለሁለቱም ተደርጎ ይወሰድ።) ያ ደግሞ በማቴ 5፥28 እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል። ተብሎ ከተጻፈው ጋር ያልተራራቀ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ልባችንን አጥብቀን መጠበቅ እንዳለብን ያስተምረናል። የኃጢአት ምንጭም ልባችን መሆኑ ተገልጦአል። ጌታ በማቴ. 15፥19-20 ከልብ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መስረቅ፥ በውሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና። ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው . . . ብሎአል። የልባችንን ወይም አሳባችንን አጥር የፈረሰ ከሆነ ሌሎችም ብዙ የከፉ ነገሮች እንዲገቡበትና የማይረባ አእምሮ ተወራሲ ሊያደርገን ይችላል። ልባችን ወይም ውስጣዊ ማንነታችን ላይ ነው ጥንቃቄ መደረግ ያለበት። ጳውሎስ በ1ቆሮ. 7፥9 ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ። ያለው ምክር አግባብ ነው። የምኞት ትኩሳት ቀላል አይደለም። የወሲብ ትኩሳት ከባድ ንዳድ ነው። በተገቢው ስፍራና ሁኔታ መርገብ ያለበት ውጥረት ነው።

አንዳንዶች ይህ ጉዳይ በግልጽ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስላልተጻፈ ኃጢአት ነው ብሎ መፈረጅ ትክክል አይደለም ይላሉ። ንጹሕ ባልሆነ ምናብ ሊደረግ እንደሚችል ሁሉ ንጹህ በሆነ መንገድም (ለምሳሌ፥ አንድ ወንድ ከሚስቱ ርቆ ሲኖር እርሷን እያሰበ ቢፈጽመው) ሊደረግ ስለሚችል መፈረጅ ተገቢ አይደለም ይላሉ። ግለ ወሲብ በቆሸሸ አእምሮ እየታሰበ የሚደረገውን ያህል በተቀደሰ አሳብም ሊደረግ ይችላል ብለው ያስባሉ። ይህ ቀመር ሊወጣለት የሚችል ልምምድ አይደለም። ግብረ ወጥ ወሲብ ኃጢአት መሆኑ በቃሉ ተጽፎአል። የኃጢአት ሁሉ ምንጭ ደግሞ ልባችን ነው። የልብን ዝንባሌ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ የሚያውቀው ሰው ደግሞ ያ ሰው፥ ወይም ያቺ ሴት ናቸው።

በእኔ መረዳት የግለ ወሲብ ሌሎች ችግሮችም አሉት።

1) ግለ ወሲብ ሱስ ነው። ሱስ ደግሞ ፈተና ብቻ ሳይሆን ወጥመድ ነው። ገመዱ አጭር ወይም ረጅም ይሁን እንጂ መታሰር ነው። ባርነት ነው። ግን ሊላቀቁት የማይችሉት ቁራኛ አይደለም። ጌታ የነጻነት፥ የአርነት ጌታ ነው።

2) ሌላው የግለ ወሲብ ችግር ቀድሞ ከደረሱበት ምናባዊ ወሲብ 'ያለፈና የላቀ' ልምምድ ላይ ካልተደረሰ እርካታም ይጠፋል። ቀድሞ ካዩት የፖርኖግራፊ (ወሳባዊ ምስል) የሚያልፍ ምስል ካልታየ እንደ ከሽፈት ያህል ይሆናል።

3) ሌላው ችግር እርካታውን ተከትሎ የሚመጣው የወቀሳና የወንጀለኝነት ስሜት ነው። ክርስቲያን ግለ ወሲብ ፈጽሞ ግለ ወቀሳ የሚቀበለው በማቴ. 5፥28 የተጠቀሰው የልብ ምንዝርና አሳብ ተጠቂ ስለሚሆን ነው። ግለ ወሲብ ያልተቀደሰ፥ የረከሰ አሳብን የማስተናገድ ግዴታ ውስጥ ያስገባል።

4) የግለ ወሲብ ሌላው ችግር ለእውነተኛውና አካላዊው ወሲብ የሚፈጥረው ፍላጎት መቀነስና ለትዳርም የሚፈጥረው አመለካከት የወደቀ መሆኑ ነው። አንዳንዶች ይህን እንደ ዘላቂ የወሲባዊ ውጥረት ማርገቢያና ብሎም የጋብቻም አማራጭ ያደርጉታል። ደግሞም፥ በትዳር ውስጥ ባለ ወሲብ ደስታቸውን የሚለኩት ከምናባዊው ወሲባቸው ጋር ይሆንና በእጃቸው ያለው ወርቅ መዳብ ይሆንባቸዋል።

እግዚአብሔር ወሲብን ወይም ወሲባዊ ደስታን ሲፈጥር በፈጠረለት መንገድ ፍጡራት እንዲደሰቱበት ነው። ለወሲብ የፈጠረው የደስታ መንገድ ደግሞ ጋብቻ ነው። ከጋብቻ በፊት ባለው ጊዜ እንደ ክርስቲያን በተቀደሰ ጓደኝነት ቅጥር ውስጥ በመሆን፥ አሳብንም አካልንም ለመንፈስ ቅዱስ በማስገዛት፥ በጌታ ሥራ በመጠመድ፥ ግልጽ ሆኖ በዚህ ጉዳይ ላይ በመነጋገር፥ ለአንድ የቅርብ ወዳጅ በዚህ ጉዳይ ላይ በግልጽ ተጠያቂ በመሆን፥ ዕድሜ ለጋብቻ ሲደርስ ሳይዘገዩ በማግባት፥ አእምሮንና አካልን በሚይዙ መልካም ሥራዎችና ተግባራት በመጥመድ፥ ቴክኖሎጂን ለተመልካች ግልጽ በማድረግ፥ ቅድስናን በመፈለግ፥ ደካማነትን በመረዳት፥ ክርስቶስን በማሰብ፥ ለእርሱ በመገዛት፥ በመንፈስ ቅዱስ በመደገፍ መኖርና መመላለስ ከመፍትሔ አሳቦች መካከል የሚሆኑ ይመስለኛል። ሰዎች ስለ ጌታ አገልግሎት ብለው ራሳቸውን ከወሲባዊ ግንኙነት በማራቅ ጃንደረባ ሲሆኑ ወይም ላለማግባት ሲወስኑ አስበው እና አስልተው መሆን አለበት። ከሆነ ደግሞ ግለ ወሲብን በአማራጭ ይዘው አይደለም።

* * * * *

38. ክርስቲያን እራሱን ቢያጠፋ ምን ይሆናል?

> ዘላለም፥ ሰላም ለአንተ ይሁን። በቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው በጌታ አምኖ እራሱን ቢያጠፋ ይድናል ወይ? [በዚህ ጉዳይ] ለሁለት ተከፈልን አንዳንዶች ይድናል፤ አንዳንዶች አይድንም ሲሉ። . . . ውዝግብ ተፈጠረ፤ ምን ትለናለክ? ተ. ተ.

ሰላም ተ. ተ. በመጀመሪያ፥ እንዲህ ያለ ጥያቄ የሚፈጠረው ከአሳዛኝ ክስተት ተከትሎ በመሆኑ የሚነኩት ትኩስ ወይም ያመረቀዘ የስሜት ቁስል ሊኖር እንደሚችል የታወቀ ስለሆነ፥ ሌሎች አንባቢዎችም በተመሳሳይ መልክ የቅርብ ሰው ያጡበት መልክ ሊኖር

እንደሚችል ታሳቢ ሆኖ የጥያቄው መልስ የጥያቄ መልስ ብቻ ከመሆን እንደሚያልፍ የታመነ ነው።

ቀጥሎ፥ ይድናል ወይ? የሚለው ጥያቄ፥ አልዳነም ነበር ወይ ብሎ ያጠይቃል። ደግሞ ይህ ሰው፥ 'በጌታ አምኖ' ተብሎአልና በሌላው ወገን መዳን ጥያቄ ውስጥ አይገባም። (ይህን ጽሑፍ በተባዕት ጾታ ባደርገውም ለሁለቱም ተደርጎ ይነበብ።)

መዳን በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም። ድነት በሥራ እንዳልተገኘ ሁሉ በሥራም አይጠፋም። ድነት በሥራ አይጠፋም ማለት ክርስቲያን ከዳነ በኋላ ምንም ነገር እየሠራ ይኖራል ወይም ለኃጢአት የፈቃድ ወረቀት ያገኛል ማለት አይደለም። እውነተኛ ክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነውና ኃጢአትን የሚጠየፍ ባሕርይ ተካፋይ ነው። ድነት በሥራ አይጠፋም ማለት ሲጀመርም በስጦታ የተቀበልነው እንጂ ለፍተን ያገኘነው አይደለምና መዳን ዘላለማዊ ነው ማለት ነው። በኃጢአት እየተደሰተ፥ ኃጢአትን እየተለማመደ የሚኖር ክርስቲያን ሲጀመርም የዳነ ሰው ነው ማለት አይቻልም። ያልዳነ ሰው የዳነ መምሰል ብቻ ሳይሆን፥ የዳነ ሰው የሚያደርጋቸውን ነገሮችም ማድረግ ይችላል። ድነት የግንኙነት ጉዳይ ነው። ግንኙነት ሲባልም አንድ ቀን እጅ ወደ ላይ አንስቶ ጥቂት ቃላትን፥ ለምሳሌ፥ 'እኔ ዛሬ ጌታን እንደ አዳኜ አድርጌ ተቀብያለሁ፤ ወደ ልቤ ጋብዤዋለሁ፤ ዓለምንና ሰይጣንን ክጃለሁ፤ . . .' ማለት ሳይሆን መሆንና መኖር ነው።

እርግጥ ነው ጌታን መቀበል የሚለው አሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፤ ዮሐ. 1፥11-13። ቁም ነገሩ ግን ጌታን እንደተቀበሉት በእርሱ መመላለስ ነው፤ ቆላ. 2፥6። ክርስትና ዳግም ልደት፥ ደቀ መዝሙርነትና ፍሬያማነት ነው። ከላይ፥ ድነት በሥራ እንዳልተገኘ ሁሉ በሥራም አይጠፋም። ድነት የግንኙነት ጉዳይ ነው ብያለሁ። ግንኙነት አንድነት ነው፤ አብሮነት ነው፤ ከጌታ ጋር የመጎዳኘትና የመዳዝ ሕይወት ነው፤ ደቀ መዝሙርነት ነው። ደቀ መዝሙርነትም ጌታን በቅርበት መከተል ነው።

ከጌታ ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ሰው መጪውን ዘላለማዊ ፍስሐ በማሰብ በዚህ ምድር የሚኖርበትን ዘመን ለዚያ ግብ ማስቆጠሪያ አድርጎ ይኖራል። ለጌታው ክብር እና ለሌሎች ላልዳኑት የመዳን፥ ለዳኑት የበረከት ምክንያት መሆንን ይመኛል። ክርስቲያን ከመከራ የጸዳ ሕይወት ተስፋ አልተሰጠውም። ክርስቲያን መሆን መንፈሳዊ እንጂ መንፈስ መሆን አይደለም። አንድ ሰው ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት የነበረው ማንነት፥ የውስጡ ሰው አዲስ ፍጥረት ከመሆኑ በቀር ያው ነው። ይህ ሰው መንፈሳዊ ማንነቱ፥ ከአምላኩ ጋር ያለው ግንኙነት፥ እና ለኃጢአት ያለው አመለካከቱ ቢለወጥም በዚህ ምድር ማንም እንደሚኖረው ሁሉ ይኖራል። የግንኙነት፥ የኢኮኖሚ፥ የምድራዊ ቀውሶች፥ የጤንነት እና አካላዊ ችግሮች፥ ሌሎችንም ነገሮች መጋፈጡ ክርስቲያን ስለሆነ አይቀሩም።

የጤንነት እና አካላዊ ችግሮች የሚባሉት ውስጥ የአእምሮ መታወክም ሊኖር እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ክርስቲያን ክርስቲያን ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆና እንጂ የርኩስ መንፈስ ማደሪያ አይሆንም። አጋንንት አያድርበትም፤ ወይም ርኩስ መንፈስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ደባል ሆኖ በአንድ መኖሪያ ውስጥ

አይኖርም። ሆኖም ሰይጣን ሊፈትን፥ ሊረብሽ፥ ሊዞር፥ ሊያደናቅፍ፥ ሊገድል፥ ሊያርድ፥ ሊያጠፋ ይፈልጋል። ሰዎች ወደ ጌታ እንዳይመጡ፥ ከመጡም ቶሎ ቢጠፉለት ቢፈልግ አይገርምም፤ የቅዱሳን መኖር ለሥራው እንቅፋት ነው። የአእምሮ መታወክን በአጋንንት ከመያዝ ጋር ማቆራኘት የለብንም። ስነ ልቡናዊውን ወይም አእምሮአዊውንና መንፈሳዊውን ካልለየን እንቸገራለን።

ማንም ራሱን በራሱ ሊያጠፋ የሚፈልግ ሰው የአእምሮ ተቃውሶ ውስጥ የገባ ሰው ነው። ይህ ስነ ልቡናዊ ወይም አእምሮአዊ ጉዳይ ከመንፈሳዊ ይልቅ አካላዊ ነውና ክርስቲያን ከዚህ ችግር የጸዳ ይሆናል ማለት የዋሕነት ነው። ሰዎች ራሳቸውን እንዲያጠፉ የሚያስገድዷቸው ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፤ ክርስቲያኖችም ሰዎች ናቸው። ከላይ እንዳልኩት ክርስትና ጤናማ ግንኙነት ሆኖ እስከኖረ ድረስ ማንም እንዲህ ያለ አሳብን ሊያስተናግድ አይችልም። እንደ ኢዮብ ያለ መከራ የደረሰበት ሰው የለም፤ ኢዮብ ግን ራሱን አላጠፋም። *ሥጋዬን በጥርሴ እይዛለሁ፥ ሕይወቴንም በእጄ አኖራለሁ። እነሆ፥ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ፤ ነገር ግን መንገዴን በፊቱ አጸናለሁ።* ኢዮ. 13፥14-15። አኖራለሁ አለ እንጂ አጠፋለሁ አላለም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ራሳቸውን ያጠፉ ስድስት ሰዎች ይገኛሉ፤

ሶምሶን በፍልስጥኤማውያን መቅደስ ራሱንና ብዙ ፍልስጥኤማውያንን ገደለ፤ መሳ. 16፥29-30። ይህንን አንዳድንዶች እንደ ራስ መግደል ሳይሆን እንደ አርበኝነት ወይም ሰማዕትነትም ይጠቅሱታል፤ በዕብ. 11 መጠቀሱንም ምስክር አድርገው ይወስዳሉ።

ሳኦል በሰይፉ ላይ ወድቆ ሞተ፤ 1ሳሙ. 31፥4። በሰይፍ ላይ መውደቅ ማለት ራስን ወግቶ ለመሞት በገዛ ሰይፍ ሹለትና ስለት ላይ መውደቅ ነው።

ሳኦል ከሞተ በኋላ ጋሻ ጃግሬውም በሰይፉ ላይ ወድቆ ሞተ፤ 1ሳሙ. 31፥5።

አኪጦፌል ምክሩ ተቀባይነት ሲያጣ ወደ ቤቱ ሄዶ ታንቆ ሞተ፤ 2ሳሙ. 17፥23።

ዘምሪ የተባለው የእስራኤል ንጉሥ ከእርሱ በፊት የነበረውን ንጉሥ ገድሎ ለአጭር ጊዜ ነገሠና ሴራው ሲከሽፍ ወደ ንጉሡ ቤት ገብቶ ቤቱን በራሱ ላይ አቃጠለ። 1ነገ. 16፥18።

የአስቆሮቱ ይሁዳ ራሱን ሰቅሎአል፤ ማቴ. 27፥3-10።

የእነዚህን ሰዎች ራሳቸውን ማጥፋት ስንቃኝ አንዳንዶቹ ሃይማኖታዊ መልክ ይኑራቸው እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ቀርቶ ያልጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸውም የሚያሳይ አመልካች የለም። የሚያስጠብብ ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ ግን ይታያል። ያንን የሚያስጠብብ ሁኔታ መቀልበስ ባይችሉም እንኳን አመለካከታቸውን መለወጥ በሚችሉበት ሁኔታ ውስጥ አልነበሩም። በዚያች የታወከችና የተረበሸች ቅጽበት ውስጥ ወዳልተጠበቀ ውሳኔና እርምጃ ገብተዋል። ከከበባቸው ወስጥ መውጫው መንገድ ይህ ብቻ ይመስላቸዋል፤ እና ይወጡበታል።

ከላይ እንዳየናቸው ሰዎች የጊዜው ሁኔታቸውና እንደ ስነ አእምሮ ጠበብት ምርምር ከሄድን ራሳቸውን የሚያጠፉ ሰዎች ይህን በሚያደርጉበት ቅጽበት ሚዛኑን በሳተ

የአእምሮ ተቃውሶ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ናቸው። ይህ የአእምሮ ድብዛዜ ወይም መጨለም ነፍስ ማጥፋትንም ጨምሮ ወዳልተጠበቀ ውሳኔ ሊመራ ይችላል። ስለዚህ ነው ብዙ ጊዜ በነፍስ ማጥፋት (የሌላውን ነፍስ ማለቴ ነው) ወንጀል የተያዙ ፍርደኞች በጊዜያዊ ዕብደት ውስጥ (temporary insanity) ውስጥ ሆነው ወንጀሉን መፈጸማቸውን በማሳመን በጤነኛ ሳይሆን በዕብድ ላይ ብያኔ እንዲቀርብ የሚከራከሩት። ቀደም ሲል እንዳልኩት ክርስቲያኖችም ሰዎች ናቸውና፥ ከአእምሮ ተቃውሶ ሙሉ በሙሉ የጸዱ ናቸው ማለት አይቻልም።

በአንጻሩ፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የምናገኛቸው አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸውን የጠሉበት እና ባይኖሩ የወደዱበት ጊዜያት ኖረው ያውቃሉ፤ ርብቃ፥ 'በሕይወት መኖር ለምኔ ነው?' ብላ ነበር። ኤልያስ፥ 'ነፍሴን ውሰድ' ብሎ ነበር። ሰሎሞን፥ 'ሕይወትን ጠላሁ' ያለበት ጊዜ ነበረ። ዮናስ፥ 'ከሕይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ፥ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ' ብሎ ነበር። ሆኖም ማናቸውም ሕይወታቸውን አላጠፉም፤ ወይም የማጥፋት ሙከራ አላደረጉም።

የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ አትግደል ብሎ ያዝዛል። አትግደል ሲል ሌላ ሰውን አትግደል ማለቱ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ራስን ማጥፋትም መግደል ነው። ራስን መግደል ነው። መግደል ንጹሕ ሰውን፥ ያላሰበ፥ ያልጠበቀ ሰውን መግደል ነው። [በነገራችን ላይ ይህ ከፖሊስ እና ውትድርና ሙያ ወይም ከአገርና ጸጥታና ድንበር ጥበቃ ጋር የተያያዘ አይደለም።] አትግደል ሲል ከሕጉ አስቀድሞም ሰው የእግዚአብሔር አምሳል መሆኑን በመንገር የተሰጠ ማስጠንቀቂያ አለ፤ ዘፍ. 9፥6። መግደል አምሳሉን መፋቅ ነው።

ራስን ማጥፋት ይቅርታ የሌለው ወይም የማይሰረየው ኃጢአት መሆኑን የሚያስተምሩ ሰዎች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ይቅርታ የሌለውና ሕይወትን እንዳናይ የሚያደርገን ኃጢአት አንድ ብቻ መሆኑን፥ ያም የእግዚአብሔርን ልጅ አለመቀበል ብቻ መሆኑን ያስተምረናል፤ ዮሐ. 3፥36 ይህንን ይላል፤ *በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።* በሌላ ቦታመንፈስ ቅዱስን የሰደበ እንደማይሰረይለት የተጻፈ ስፍራም አለ፤ ማቴ. 12፥31 እና ሉቃ 12፥10። ይህ መንፈስ ቅዱስን መስደብም ከዮሐ. 3፥36 ጋር አንድ ነው፤ ስለ ኢየሱስ የመሰከረውን መንፈስ ቅዱስን አለመቀበል ኢየሱስን አለመቀበል ነው። ራስን ማጥፋት የማይሰረይ ኃጢአት መሆኑን የሚናገሩ ሰዎች የሚሉት፤ ከሞት በኋላ መናዘዝ ስለማይቻል የሚለው አሳብ ነው።

በዘመናዊው ሕክምና (በሰለጠነው ዓለም በሕግ የተፈቀደ ሆኖ) ስቃይ የሚበዛባቸው፥ ወይም ሩሃቸውን ስተው ብዙ የቆዩ (ኮማ ውስጥ የገቡ) ሰዎች በሐኪም እና የቅርብ ሰዎች ፈቃድና ስምምነት እንዲሞቱ (የርኅራኄ ሞት ወይም euthanasia ይሉታል) ይደረጋል። በአሜሪካ በአንዳንድ ግዛቶች ሕጋዊ ነው። አንዳንዴ ሕመምተኞቹ ራሳቸውም ይህንን ጥያቄ አቅርበው ፈቃድም ይሰጣሉ። ይህም ራስን ለማጥፋት ጋር ተያይዞ ይቀርባል። አንዳንዴ በተቃራኒው ሊሞቱ የሚችሉ ሩሃቸውን የሳቱ (clinically dead ወይም brain dead የሆኑ) ሰዎች ደግሞ በሰው ሠራሽ መሣሪያዎች ልባቸው እየመታና ሳንባቸው እየተነፈሰ እንዲቆይም ይደረጋሉ እንዲቆይ ይደረጋሉ።

የሁለቱም ጉዳዮች ትክክልነት በስነ መለኮታውያን እና በስነ ልቡናውያን ዘንድ መከራከሪያ ናቸው።

ይሁን እንጂ ሕይወትን የሰጠ እግዚአብሔር መሆኑና በሕይወት ላይም ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር መሆኑን እናምናለን። ዘመኖቻችን በእጁ መሆናቸውን መቀበል አለብን። ሕይወትን በራስ እጅ ማጥፋትም ይህን ስጦታ መጣልና ይህን ሥልጣንም መናቅ ነው። የእርሱን ሥልጣን በገዛ እጅ መውሰድ አግባብ አይደለም። የሰውን አስቀድሞውኑ መዳን የሚያውቀው እግዚአብሔር ሲሆን፥ ድነት በራስ የተገኘ ስላልሆነ በራስም የማይጠፋ ቢሆንም፥ የራሳቸውን ሕይወት የሚያጠፉ ሰዎች ከራሳቸው ስንበት ባሻገር በቀሩት ሰዎቻቸው ላይ የሚያደርሱት የስሜትና የስነ ልቡና ጉዳት ከፍተኛ ነው።

ቀደም ሲል፥ 'መዳን በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም። ድነት በሥራ እንዳልተገኘ ሁሉ በሥራም አይጠፋም።' እንዳልኩት ስንድን መዳናችን ዘላለማዊ ነው። ድነት የግንኙነት ጉዳይ ነው። በልጁ ስናምን የዘላለም ሕይወት እንደተቀዳጀን እናውቃለን፤ 1ዮሐ. 5፥13። ይህ የእውቀት ጉዳይ እምነትም ያለበት ነው። እምነት የግንኙነት ሕይወት ነው። በይቅርታና በእምነት ላይ የተመሠረተው ግንኙነት በቅጽበታዊ የአእምሮ ተቃውሶ፥ በተዛባና በደበዘዘ፥ በጨለመም አስተሳሰብ ወቅት ውስጥ በተደረገ ውሳኔ ላይ የተመሠረተ ነው ማለት በክርስቶስ ደም ማስተሰሪያነት የተመሠረተ ምሕረቱ ዘላለማዊ፥ ፍቅሩም ጽኑ የሆነ የእግዚአብሔርን ማዳን ወይም የሰውን ድነት ያዛባዋል። ስለዚህ፥ ይቅር የማይባል ኃጢአት ነው ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስረጅ የለንም።

ስንኖር ለእርሱ ክብር እና ለቅዱሳን በረከት ሆኖን እንድንኖር የጌታ ጸጋ ይብዛልን። ከጌታ ጋር ያለን ግንኙነታችን በሁኔታዎች ላይ የተመሠረተ አይሁን። ጸጋው እንደሚበቃን፥ ኃይሉም በድካማችን ብርቱ እንደሆነ አንርሳ። ያዳነን ጌታ ለጊዜው ሳይሆን ለዘላለሙ እንደሆነም አንርሳ።

* * * * *

39. መንፈስ ቅዱስን መስደብ ምንና እንዴት ነው?

> ሰላም ጋሼ፥ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ አይሰረይለትም ይላል ማር. 3 ውስጥ። መንፈስ ቅዱስን መስደብ ለመሆኑ ምንድነው? እንዴት ይሰደባል? ለምንድነው ስርየት የሌለው? ክርስቲያን ስርየት የሌለው ኃጢአት እና ንስሐ አይጋጩም? (ሳ. ኃ.)

በአዲስ ኪዳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሊያደርጉ የሚችሉአቸውን በርካታ ኃጢአቶችን እናገኛለን። እነዚህም መዋሸት፥ መፈተን ወይም መፈታተን፥ መቃወም፥ ማከፋፋት፥ መስደብ፥ ማሳዘን፥ እና ማጥፋት ናቸው። መስደብ ከነዚህ አንዱ ነው።

በመንፈስ ቅዱስ ላይ እነዚህ ነገሮች ተደረጉ ማለት መንፈስ ቅዱስ የሚደረግበት አካል ነው ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ ግዑዝ ኃይል ሳይሆን ሕያው አምላክ ነው። ከሥላሴ አካላት አንዱ ነው።

መንፈስ ቅዱስን መስደብ የእግዚአብሔር የሆነውን የእግዚአብሔር ሳይሆን የአጋንንት በማድረግ የእግዚአብሔርን እና እግዚአብሔርን ራሱንም አለመቀበል ነው። ዛሬ በተቃራኒው፥ የአጋንንት የሆነውን ነገርና ፎርጅድ ዕቃ ሁሉ የእግዚአብሔር አስመስሎና አድርጎ ማቅረብና መሸጥ በተለመደበት ጊዜ፥ 'ይህ የእግዚአብሔር ነው!' ብሎ በመከራከር ፈንታ፥ 'የለም፤ ይህ የሰይጣን ነው!' የሚያስብሉት እየበዙ መጥተዋል። ማለትም፥ የእግዚአብሔርን ለአጋንንት መስጠት ሳይሆን የአጋንንትን ለእግዚአብሔር መስጠት ነው በሐሰተኞቹ ዘንድ የሚታየውና ብዙዎች እየሳቱ እየተቀበሉት ያሉት። የመንፈስ ቅዱስ አሰዳቢዎች ናቸው። 'ጌታ ተናገረኝ፤ መንፈስ ቅዱስ ተናገረኝ፤ አሳየኝ፥ አመለከተኝ፥ ጠቆመኝ፤ . . .' የሚሉ ሰዎች እርሱ ያልተናገራቸውን ብቻ ሳይሆን ራሳቸው የፈጠሩትን፥ የሰሙትን ሳይሆን የተሰማቸውን፥ የስሜታቸውን የሚናገሩ ሰዎች፥ እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ አሰዳቢዎች ናቸው።

መንፈስ ቅዱስን መስደብ ምን መሆኑን እንይ። ጌታ ስለዚህ ጉዳይ የተናገረው በማር. 3፥20-30 ነው። የምንባቡ ክፍል እንደሚያስረዳን ጋኔን ያደረበትን ዕውርና ዲዳ ወደ ኢየሱስ ካመጡ በኋላ ሰውየው እስኪያይና እስኪናገር ተፈወሰ። አንዳንዶቹ ተገርመው መሢሁ እንደሆነ ጠየቁ፤ ሌሎች ግን በአጋንንት አለቃ አጋንንትን እንደሚያወጣ ተናገሩ።

እንዲህ ይላል፥ *እውነት እላችኋለሁ፥ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሁሉ የሚሳደቡትም ስድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም። ርኩስ መንፈስ አለበት ይሉ ነበርና።* ይላል። ከቁጥር 22 ጀምሮ መመልከት ትልቁን ምስል ያሳያል። ተመሳሳይ ታሪክ በማቴ. 12፥22-32ም እናገኛለን።

ጌታ ክርስቶስ ይህን የተናገረው፥ እርሱ በእግዚአብሔር ኃይል፥ በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን ሲያወጣ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ባሉት ጊዜ ነው። ማር. 3፥22 ላይ፥ *ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም፡- ብዔል ዜቡል አለበት፤ ደግሞ፡- በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው ተናገሩ።* ይላል። ብዔል ዜቡል አለበት፤ በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ማለታቸው በራሱ የከፋ ኃጢአት ሆኖ ሳለ፥ ከዚህ የከፋውና የማይሰረየው ኃጢአት እርሱን በማንነቱ አለመቀበላቸው ነው።

የኋላ ኋላ ውጤቱ፥ እርሱን በማንነቱ አለመቀበላቸው ነው። ኢየሱስን አጋንንት አለበት ማለታቸው ኢየሱስን እንደ ኢየሱስ፥ በሥጋ እንደመጣ አምላክ፥ እንደ ጌታ አለመቀበል ነው። እርሱን አለመቀበል ደግሞ የመዳን ብቸኛ መንገድ እርሱ ነውና፥ የመዳንን በር ጥርቅም አድርጎ መዝጋት ነው። እንድንበት ዘንድ የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ ምንም የለምና እርሱን አለመቀበል መዳንን አለመቀበል ነው። መዳንን

አለመቀበልና ሳይቀበሉ መሞት ደግሞ ስርየት የሌለው ኃጢአት ነው። ከሞት በኋላ ፍትህ የሞላበት ፍርድ እንጂ ፍትሐት የለም፤ ንስሐና ስርየትም የለም።

ክርስቲያን ሲድን የዳነው በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ነውና፥ የተጠመቀውና የአካሉ ብልት የሆነውም፥ ለቤዛ ቀን የታተመውና የእግዚአብሔር የሆነውም በመፈስ ቅዱስ አደራረግ ነውና መንፈስ ቅዱስን ሊሰድብ አይችልም። ላላመኑት ግን መንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ ሲያመለክታቸው ያንን አመልካች ባለመስማት ወደ እርሱ የተመለከተውንም ባለመቀበል በመጽናት መዳንን ላይቀበሉና ሊያጡ ይችላሉ።

የዳኑ ሰዎች የዳኑበትንና በውስጣቸው የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስን አይሰድቡም፤ ክርስቶስን ተቀብለውታልና። የማያምኑ ሰዎች ደግሞ መንፈስ ቅዱስን መስደባቸውንም አያውቁም፤ አይቀበሉትምም። አንድ ሰው ክርስቶስን ተቀብሎ የሚድነውና ዳግም የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ነውና መንፈስ ቅዱስን ከሰደበ ወይም ካልተቀበለ ደኅንነትን ሊያገኝ ከቶም አይችልም። ደኅንነትን ካላገኘ ደግሞ በኃጢአቱ ይሞታልና ለዘላለም ጠፊ ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስን መስደብ የሚባለው ኃጢአት እንግዲህ ክርስቲያኖችን ሳይሆን ያልዳኑትንና ክርስቶስን እንደ ክርስቶስነቱ፥ እንደ ጌትነቱ ሊቀበሉ የማይሹትን የሚመለከት ነው። ዳግም የተወለደ ክርስቲያን ዳግም እንዲወለድ ያደረገውን መንፈስ አይሰድብም።

የመንፈስ ቅዱስ ተቀዳሚ ተግባር ኢየሱስን ማጉላት እና ማክበር ነው፤ ዒላማው በሥጋ የተገለጠውን አምላክ ክርስቶስን ማሳየት ነው፤ ዮሐ. 16፥8-15። ዓለምን ስለ ኃጢአት ሲወቅስ በኢየሱስ ስለማያምኑ ነውና በኢየሱስ ሰዎች ያምኑ ዘንድ መውቀስና ማመልከት ተግባሩ ነው። ልብ እንበል፤ ጌታ፥ *በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም።* በማለት ይህንን የተናገረው ላመኑት ደቀ መዛሙርቱ ሳይሆን አጋንንት አለበት ላሉት ላልተቀበሉት፥ ሊቀበሉትም ላልወደዱት ሰዎች ነው። መንፈስ ቅዱስን መስደባቸው እነዚህ ሰዎች ክርስቶስን ያለመቀበላቸውና ባለመቀበልም መጽናታቸው ነው። ይቅር የማይባል ኃጢአት ደኅንነትን የመርገጥ ኃጢአት ነው። የክርስቶስን ማንነት፥ ማለትም አምላክነቱን የሚገልጠውን በመንፈስ ቅዱስ የተሠራ ሥራ ለሰይጣን በመስጠት፥ ወይም የሰይጣን በማድረግ በመጨረሻው ክርስቶስን ያለመቀበል ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስ ስለ እርሱ የመሰከረውን ምስክርነት ባለመስማት እርሱን ክርስቶስን አለመቀበል ስርየት የሌለው ኃጢአት ነው።

* * * * *

40. እውነተኛ ትንቢት እና እውነተኛ ነቢያት ዛሬ አሉ?

እውነተኛ ነቢያት ዛሬ አሉ?

ይህ ጥያቄ ከቀረቡልኝ ጥያቄዎች ሁሉ በላይ በጣም ተደጋግሞ የተጠየቅሁት ጥያቄ ነው። ይህንን ጥያቄ የተጠየቅሁበት ምክንያት ስለ ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት በስፋት ስለጻፍኩና ስላስተማርኩ ነው። ስለ ሐሰተኞቹ ብዙ ከመጻፌ ወይም ከማስተማሬ የተነሣ እውነተኛ ነቢያት በዚህ ዘመን መኖራቸውን እንደማላምን የሚገምቱ የጠየቁኝ ጥያቄ ነው።

ይህ ጥያቄ ጠንካራ ጥያቄ በመሆኑ ሰፋ አድርጌ በቪድዮ ምላሽ የሰጠሁበት ነው። የ50 ደቂቃ ትምህርት ስለሆነ እዚያ ያቀረብኩትን ሰፊ መልስ እዚህ በጽሑፍ ማቅረብ ስለሚያስቸግር እዚህ ጥቂት አሳቦችንና መደምደያውን ብቻ አካፍላለሁ።

ትንቢት ምንድር ነው? ትንቢት ሦስት ነገሮች ነው፤

<u>አንደኛ፥</u> ትንቢት ወደፊታዊ ንግግር ነው፤ ማለት፥ ወደፊት የሚሆነውን ገና ሳይሆን መናገር ማለት ነው። ለምሳሌ፥ ኢሳይያስ ድንግል እንደምትጸንስ የተናገረው ይህ ሳይሆን ከ700 ዓመታት በፊት ነው። መሢሑ መከራን የሚቀበል መሢሕ መሆኑንም ተናግሮአል፤ ኢሳ. 53። በኢሳ. 44 እና 45 ስለ ቂሮስ ይናገራል፤ ቂሮስ የሚባል ሰው ከመኖሩ ከ200 ዓመታት በፊት ነው ከነስሙ ተጠቅሶ የተነገረለት። ከአዲስ ኪዳን ለምሳሌ፥ አጋቦስ የተባለ ሰው በዓለም ሊመጣ ስላለው ራብ ተናገረ፤ ያ ራብ የተነገረም፥ የተፈጸመም መሆኑ በሐዋ. 11፥28 ተጽፎአል። በዚህ ጊዜ የአንጾኪያ ወገኖች ለኢየሩሳሌም ወገኖች እንደ ችሎታቸው አዋጥተው እርዳታ ላኩ። ትንቢቱንም ፍጻሜውም ተጠቅሶ ተጽፎአል።

<u>ሁለተኛ፥</u> ትንቢት ስለ አሁኑ፥ ስላለው ሁኔታ ያለውን እውነታ መናገር ነው። እያንዳንዱን የትንቢት ወይም የነቢያት መጻሕፍት ብንወስድ እንደዚህ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን። ጥቂት ስለወደፊቱ ቢናገሩም በአብዛኛው ስላለው ሁኔታ ነው የሚናገሩት። ኤርምያስን ወይም ሕዝቅኤልን፥ ዳንኤልን ወይም ዕንባቆምን ብንወስድ ይህንን ነው የምናየው። ዮናስን ብንወስድ የዮናስ መጽሐፍ የትንቢት ሳይሆን የታሪክ ነው የሚመስለው። ደግሞም ነው። ዮናስ እየተናገረ ያለው የሕዝቡ ኃጢአትና ንስሐ ካልገቡ ቅጣትን ነው። ይህ የነቢይ ሥራ ነው። የነቢይ ዋና ተግባር ሕዝቡ ያለበትን ሁኔታ መናገር። ዝቅጠቱን፥ ውድቀቱን፥ ከአምላክ ርቀቱን፥ በዚያ ከቀጠለ ቅጣትና ጥፋቱን መንገር ነው። ይህ ትንቢት ነው። ጥሩውን ማበረታታት፥ በስደትና በመከራ ሲያልፉ ማደፋፈር፥ እጃቸው እንዳይላላ ማጽናት ይህ ተግባራቸው ነው። ነቢያት በኃጢአት ውስጥ እስከ አፍንጫቸው ድረስ ለተዘፈቁ ሰዎች መሳካትንና መከናወንን አይሰብኩም። ይህን ያደረጉት የኤልዛቤል የበኣልና የማምለኪያ ዐጸድ ነቢያት ነበሩ።

እውነተኛ ነቢያት ያለውን እውነት የሚናገሩ ስለሆኑ ብዙም የማይወደዱ፥ የማይደነቁ፥ ጥላቻና ስደት በራሳቸው ላይ የሚጋብዙ አገልጋዮች ናቸው። ዓለማውያንም፥ ሥጋውያን ክርስቲያኖችም አይወዷቸውም። እውነተኛ ነቢያት ግንባረ ደረቅ የሆኑ ደፍረው የሚጋፈጡ ሰዎች ናቸው። እውነተኛ ነቢያት በዘመናችን ኀቢዩ፥ ሱጥር

ፕሮፌት፥ ሜጀር ፕሮፌት' የሚባል ሹመት ተጎናጽፈው እንደሚንጎራደዱት፥ ስምና አድራሻ ሳይሆን፥ ስልክ ቁጥር ሳይሆን፥ ገንዘብና ሎተሪ ሳይሆን፥ ጥርመሳና ሰበራ ሳይሆን ንስሐንና መመለስን፥ ቅድስናንና ዋጋ መክፈልን፥ መስቀልንና ደቀ መዝሙርነትን የሚሰብኩ ናቸው። የሚገስጹ ናቸው።

<u>ሦስተኛ፥</u> ሌላው፥ ትንቢት የሚነገረው ነገር ብቻ ሳይሆን የተጻፈው ቃሉ ነው። የተጻፈው ቃል፥ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ይባላል፤ ማቴ. 11፥13፤ 2ጴጥ. 1፥17-21፤ ራእ. 22፥7-19።

በአዲስ ኪዳን የቃሉ ትርጉም ነቢይ ማለት προφήτης (ፕሮፌቴስ) ቃሉን የሚናገር ማለት ነው። የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገር ማለት ነው። እግዚአብሔር ደግሞ አንድ ቃል ነው ያለው። ያም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ነቢይ ቃሉን፥ ማለትም፥ መጽሐፍ ቅዱስን የሚናገር ማለት ነው። προφήτης (ፕሮፌቴስ) የሚለው ቃል ከሁለት ቃላት የተሠራ ነው። πρό (ፕሮ) እና φημί (ፌሚ)። ፕሮ ወደ ፊት ማውጣት ማለት ሲሆን ፌሚ መናገር፥ መግለጥ ማለት ነው። አንድ ላይ ሲሆኑ ወደ ፊት አውጥቶ፥ ገልጦ መናገር ማለት ነው። ትንቢት ማለት ቃሉን መግለጥ፥ ቃሉን ወደ ፊት ማውጣት፥ ማምጣትና መናገር ማለት ነው። ቃሉ፥ የተጻፈው ቃል ነው። የተጻፈውን ቃል መጽሐፍ ቅዱስን ገልጦ ፈትቶ መናገር ትንቢት ነው። ስለዚህ ቃሉን፥ ቀድሞ የተነገረውንና የተጻፈውን ቃል መግለጥ፥ መፍታት፥ ማስረዳት፥ ማስገንዘብ ትንቢት መናገር ነው። ይህን የሚያደርጉም ነቢያት ሊባሉ ይችላሉ ማለት ነው።

ትንቢት ይህ ከሆነ ነቢይ ማለት ደግሞ እነዚህን ከላይ ያየናቸውን ነገሮች የሚያደርግ አገልጋይ ማለት ነው። ነቢያት በአካል ውስጥ ከዓይን እና አፍ ጋር የሚመሳሰሉ ሰዎች ናቸው። እውነተኛ ነቢያት ጉዳያቸው ከእውነት ጋር ነውና እውነት ስፍራውን ሲለቅቅ፥ ከመስመር ሲወጣ፥ ኡ! ኡ! የሚሉ፥ ሳይቆጥቡ የሚጮኹ ሰዎች ናቸው። ኃጢአትንና በደልን በጎሪጥ ያይደለ፥ አስተውለው የሚያዩና ኃጢአትን ኃጢአት ለማለት ከወዳጅም ከጠላትም የማይማከሩ ሰዎች ናቸው። አስመሳዩ ሐቀኛ መስሎ ሲመጣ ግንባራቸውን የማያጥፉ፥ ፊሽካ የሚነፉ ናቸው። አደጋን ሲያዩ የሚያስጠነቅቁ ስለሆኑ፥ ለመናገር ለስላሳ ቃላት እየፈለጉ አይቆዩም። መዝገበ ቃላት አገላብጠው፥ 'ከዚህ ይልቅ ይህንን ቃል ልጠቀም' የሚል ፖለቲካዊ ትክክለኝነት እና ሰውን የማያስቀይም ቋንቋ አያውቁም። አያመቻምቹም። የጭምብላሞችን ጭምብል ለማውለቅ ሁለት ጊዜ አያስቡም። ነቢያት ሰዎችን ሲጋፈጡና ፊት ለፊት ሲናገሩ የሚጎነጡ ሰዎች ናቸውና የማያሳምሙና የማይቆረቁሩ ቃላት ለመፈለግ አይሞክሩም። ስለዚህ፥ እውነተኛ ነቢያት አሳማሚ ስለሆኑ፥ ብዙም ተወዳጅና ታዋቂ፥ ተሞጋሽና ተደናቂ አይደሉም። እንዲያውም ብዙ ጊዜ ብቸኞች ናቸው። ይህ ደግሞ አያስጨንቃቸውም።

ትንቢትን ወይም ነቢያትን በተመለከተ ሦስት ትልልቅ ማስጠንቀቂያዎችን ማጤን አለብን።

ማስጠንቀቂያ 1. ነቢያት ወይም ትንቢት (ወይም ማናቸውም ስጦታ) ለመንፈስ ቅዱስ መሪነት ካልተገዛ አካልን መገንባት ሳይሆን ራስን መገንባት ሊሆን ይችላል። አካልን መገንባት ሳይሆን እንዲያውም በተቃራኒው ማፍረስ ሊከተለውም ይችላል።

ማስጠንቀቂያ 2. ትንቢትን መናቅ የለብንም። 1ተሰ. 5፥20 አትናቁ ሲል ምናልባት እንዲናቅ የሚያስደርጉ ሰዎች በተሰሎንቄ ሳይነሱ እንዳልቀሩ ይመስላል። የጸጋ ስጦታዎችን አንዳንድ ሰዎች አበላሹ ማለት ጸጋው ሊናቅና ሊንቋሸሽ ይገባል ማለት አይደለም።

ማስጠንቀቂያ 3. ሐሰተኞች ነቢያት መኖራቸው የማይካድ ነው። የውሸት ትንቢት የሚናገሩ ሐሰተኛ ነቢያት ነበሩ፤ አሁንም አሉ፤ ወደፊትም በዝተውና ተባዝተው ይኖራሉ።

የቪድዮው መደምደሚያ

. . . ይህን [ትምህርት] ስደመድም እውነተኛ ነቢያት የመኖራቸውንም እውነት ላስምርበት። እውነተኛ ነቢያት አሉ? አዎን፤ አሉ። እነዚህ እውነተኛ ነቢያት ያስፈልጉናል። በስሜታቸው ያልተነዱ፥ በሌላ መንፈስ ያልተመሩ፥ በገንዘብ ፍቅር ያልተጠመዱ፥ በዝና ፍቅር ያልሰከሩ፥ የሥልጣን ራብተኞች ያልሆኑ፥ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ያለንበትን ዝቅጠት ሳያመቻምቹ የሚነግሩን፤ ራሳቸውን ሳይሆን ክርስቶስን የሚያሳዩን፤ ሁሌ በረከትና ሰላም የማያውጁ፥ ብር የማያባዙ፥ መስቀሉን የማይደብቁ፥ ትንቢትና ነቢያት እንዲናቁ የማያደርጉ፥ ቤተ ክርስቲያንን እና የጌታን ስም የማያሰድቡ፥ ሥርዓትን የሚያውቁ፥ ቃሉን የሚገልጡ፥ ቃሉን ወደ ፊት አውጥተው የሚነግሩ ነቢያትን እግዚአብሔር ይስጠን። እነዚህ ያስፈልጉናል።

ይህ አጭር ምላሽ፥ 'እውነተኛ ነቢያት በዚህ ዘመን አሉ?' በሚል ርእስ በAugust 2017 ያካፈልኩትና በYouTube የሚገኝ ቪድዮ ሲሆን ቪድዮውን ከዚህ ማግኘት ይቻላል፤

https://www.youtube.com/watch?v=tmB2pq071EU

ክብር ለእግዚአብሔር።

ከዚህ በፊት የታተሙ

አዲስ ሕይወትን የማዳረስ ዘዴ፤ በወንጌል ስርጭት ለሰዎች አዲስ ሕይወትን ስለማብሰርና አዲስ ሕይወትን ያገኙ፥ ዳግም የተወለዱ ሰዎችን ደቀ መዛሙርት ስለማድረግ የተዘጋጀ የስምንት ሳምንታት፥ የአርባ ቀናት ትምህርቶች የያዘ የትመማ (TEE) ትምህርት መጽሐፍ ነው።

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ የስነ ጽሑፍ አገልግሎት ተዘጋጀ፤ በSIM Press አዲስ አበባ ታተመ፤ የመጀመሪያ ዕትም 1986 ዓ. ም.።



ደኅንነትና ዕድገት፤ ለአዳዲስ ክርስቲያኖች የተዘጋጀ የክትትል እና መሠረታዊ የክርስትና መጽሐፍ። ደኅንነት ምንድን ነው? የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ እንዴት ተገለጠ? መንፈሳዊ ዕድገት ምንድን ነው? የዳነ ሰው እንዴት ያድጋል? አማኝና ቤተ ክርስቲያንን፥ አማኝና አገልግሎትንም የተመለከተ ሥራ ነው።

መጀመሪያ በ1994 (እ ኤ አ) ተዘጋጀ፤ ቫንኩቨር፥ ካናዳ።

መንፈስ ቅዱስና ካሪዝማዊ ቀውሶች፤ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? የጸጋ ስጦታዎችስ ምን ምን ናቸው? የጸጋ ስጦታችንን እንዴት እናውቃለን? በክርስትና ታሪክ ካሪዝማዊ እንቅስቃሴ ኖሮ ያውቃል? መቼና የት? የጸጋ ስጦታዎችን ማበላሸት ወይም ካሪዝማዊ ቀውሶችስ ኖረው ያውቃሉ? ምን ምን ናቸው? እንዴት እንጠንቀቅ?

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ የስነ ጽሑፍ አገልግሎት ተዘጋጀ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ 1989 ዓ. ም. (1996)።

ኪቦርድ ለጀማሪዎች፤ የፔንታቶኒክ (አምስትዮሽ ድምጽ) አጨዋወትን መሠረት ያደረገ የኪ'ቦርድ ተጫዋቾችን ከጅምር፥ ከስያሜና ለቀማ፥ እስኬል፥ ኮርዶች፥ ቅኝቶች፥ እና ሌሎችም። በመጀመሪያ የማውቀውን ያህል ለጥቂት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለማስተማር ተብሎ የተሰናዳና ሌሎች ሁለት ወንድሞች (ነህምያ ሰሎሞን እና ምስጋና ግርማ) የጨመሩበት ሥራ ነው።

መጀመሪያ በ1999 (እ ኤ አ) ተዘጋጀ፤ ቫንኩቨር፥ ካናዳ።

መጽሐፍ ቅዱስና የአፈታት ስሕተቶች፤ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት ስልቶች ምን ምን መሆናቸውን፥ የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትን እንዴት መቅረብ እንዳለብን፥ የአፈታት ስሕተቶች እንዴት እንደሚስተዋሉ፥ የአፈታት ስሕተቶችና የሐሰት ትምህርቶች እንደምን እንደሚቆራኙና እነዚህን ስሕተቶች እንዴት ማስተዋልና መቋቋም እንደምንችል አመላካች መጽሐፍ ነው።

በመድረክ ዕዝራ አገልግሎት ተዘጋጀ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ 2000 ዓ. ም. (2007)።



መንፈሳዊው ሰው፤ በሉዊስ እስፔሪ ሼፈር (Lewis Sperry Chafer) የተጻፈው He That is Spiritual የተሰኘው መጽሐፍ ትርጉም ነው። ሦስት ዓይነት ሰዎች፥ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች፥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወይም እውነተኛ መንፈሳዊነት፥ መንፈስን ማሳዘን፥ ማጥፋትና በመንፈስ መመላለስ ምን ናቸው? እና ሌሎችም አሳቦች በስፋት ተጽፈውበታል።

በLapsley/Brooks Foundation፤ በSIM Press አዲስ አበባ ታተመ፤ 1989 ዓ. ም. (1996)።

ትንቢተ ዳንኤል፤ የትንቢተ ዳንኤል ቀላል ማብራሪያና የጥናት መርጃ መጽሐፍ።

በመድረክ ዕዝራ አገልግሎት ተዘጋጀ፤

መጀመሪያ በ1995 (2003)፤ ብሩክስ፥ ካናዳ።



መጽሐፈ ነህምያ፤ የመጽሐፈ ነህምያ ማጥኛና ቀላል ማብራሪያ መጽሐፍ።

በመድረክ ዕዝራ አገልግሎት ተዘጋጀ፤

መጀመሪያ በ2010 (2018)፤ ላስ ቬገስ፥ ኒቫዳ።



'ክርስቲያናዊ' ኢትዮጰኝነት፤ ኢትዮጰኝነት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከሌሎች ሁሉ ሕዝቦችና አገሮች የማላቅ የገነነ ስነ ልቡናና የበላይነት ስሜት ነው። 'ክርስቲያናዊ' ኢትዮጰኝነት ደግሞ ክርስትና ያስነሡትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያቆራኙት የተሳሳተ ፍልስፍና መሆኑን በስፋት የሚያትት መጽሐፍ ነው።

በመድረክ ዕዝራ አገልግሎት ተዘጋጀ፤ መጀመሪያ በ2011 (2018)፤ ላስ ቬገስ፥ ኒቫዳ።



እንዝፈን ወይስ እንዘምር? መዝሙሮቻችን እያሽቆለቆሉ ናቸው። ዘፈናምነትም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሰርጎ እየገባ ያለ ወረርሽኝ ነው። ዘፈን በክርስቲያኖች እንዲወደስ መጽሐፍ ተጽፎ ይደገስለታል። ቃሉም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታጥቦ እንዲወጣ እየተደረገ ነው። ለመሆኑ መዝሙር ምንድርን ነው? ዘፈንስ? ምንነታቸውን አውቀን በእውቀት እንመልስ፤ እንዝፈን ወይስ እንዘምር?

በመድረክ ዕዝራ አገልግሎት ተዘጋጀ፤ መጀመሪያ በ2011 (2018)፤ ላስ ቬገስ፥ ኒቫዳ።

የሐሰተኞች እሳተ ገሞራ ሐሰተኞች በሚበዙበት በመጨረሻው ዘመን እንገኛለን። በዓለማችንና በአህጉራችን፥ በአገራችንም ሐሰተኛ ነቢያት እና ሐሰተኛ ሐዋርያት በሐሰት ትምህርቶችና በሐሰተኛ ልምምዶች ቤተ ክርስቲያንን እያፈረሱ ይገኛሉ። ቃሉ ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል? ብዙ ይላል። ይህንን በስፋት የሚያትት መጽሐፍ ነው።

በፒዲኤፍ ተሰናድተው በማኅበራዊ ሚድያ የተሰራጩ፤ ክርስቲያን እና ኮሮና፤ ሰው ምንድር ነው? እና የቁር ኣኑ ዒሳ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ አይደለም።